# ጎንደር ስትረሳ እና ስታስታውስ

ጎንደር ቁስቋም በጥንታዊው ዕቃ ቤት ውስጥ
ዘመናዊ ሙዝየም ገንብታለች

አሁን የጎንደር ከተማ መነቃቃት ጀምራለች፡፡ መንገዶቿ አስፓልት እየለበሱ ነው፡፡ ሪል እስቴቶችም ብቅ ብቅ ብለዋል፡፡ ታላላቅ ሕንፃዎችም እየበቀሉ ናቸው፡፡ አብያተ ክርስቲያናትም ሙዝየሞችን በማሠራት ላይ ናቸው፡፡

ጥንታዊቷ የእቴጌ ምንትዋብ ቤተ ክርስቲያን ጎንደር ቁስቋም በጥንታዊው ዕቃ ቤት ውስጥ ዘመናዊ ሙዝየም ገንብታለች፡፡ የአስራ ስድስተኛውን እና የሥራ ሰባተኛውን ዘመን የሚያሳዩ ንዋያተ ቅድሳት፣ የወግ ዕቃዎች እና መጻሕፍት ለእይታ ቀርበዋል፡፡ ምንም እንኳን ቦታው ጠበብ ያለ ቢሆንም የአሥራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሕንፃ በመሆኑ ጉብኝቱን በታሪክ ላይ መሄድ ያደርገዋል፡፡

አስጎብኚው መሪጌታ ዳንኤልም መጻሕፍቱን ያነበቡ፣ታሪኩን የጠገቡ፣ አክበሮትን ከትኅትና ጋር የተላበሱ መሆናቸው በእቴጌ ምንትዋብ የግብር አዳራሽ የተጋበዛችሁ ያስመስላችኋል፡፡ ሕንፃው ሲሠራ መስኮት ስላልነበረው መብራት በማይኖር ጊዜ ጧፍ ይጠቀማሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ግን ቅርሶቹን ለእሳት አደጋ ሊያጋልጣቸው ይችላልና በተለ ይም በአሜሪካ እና በአውሮፓ የምትገኙ የቅርስ እና የታሪክ ወዳጆች በኤሌክትሪክ ቻርጅ ተደርጎ ለረዥም ሰዓት ሊያገለግል የሚችል ጠንካራ ባትሪ ብትልኩላቸው ስማችሁ ሁልጊዜ በጸሎት ይታሰብ ነበር፡፡

የእቴጌ ምንትዋብ አዳራሽ እና ቤተ መንግሥት በደርቡሽ ጊዜ ፈርሶ ትዝታን ብቻ እያሳየ ቆሟል፡፡ የዓባይን መነሻ አገኘሁ ያለው የ17ኛው መክዘ አሳሽ ጀምስ ብሩስ የኖረው እዚህ ቦታ ነው፡፡ እቴጌ ምንትዋብ ልዩ ክብካቤ ታደርግለት ነበር፡፡ የኢትዮጵያን ታሪክ ያጠናበት የነበረው ቤት ዛሬ ፍርስራሹ ይታያል፡፡

በአጣጣሚ ሚካኤልም ሙዝየም ተከፍቷል

እንደ ቁስቋም ሁሉ በአጣጣሚ ሚካኤልም ሙዝየም ተከፍቷል፡፡ በተለይም የጎንደር ፋሲል ቤተ መንግሥት ጎብኝዎች ከሚወጡበት በር አጠገብ መከፈቱ ለጎብኝዎቹ ምቹ እንዲሆን አድርገውታል፡፡

ጎንደር ላይ ሀገረ ስብከቱም ሙዝየም ከፍቷል፡፡ በተለይም የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ ሊቁ የሊቀ ሊቃውንት መሐሪ ትርፌ/ አቡነ ጴጥሮስ/ ቅርሶች ከአደጋ ተርፈው ለሙዝየም መብቃታቸው አስደናቂ ነው፡፡ ታሪኩን እና ቅርሱን ጠብቀው ለዚህ ወግ መዓርግ ያበቁትን አባ ሙሉንም ያስመሰግናቸዋል፡፡ በገንዘብ እንግዛዎት ተብለው እምቢ አሉ፡፡ በባለ ሥልጣናት ትእዛዝ ከደመወዝ እና ከሥራ ቢከለከሉም ቅርሱን ያለ ተረካቢ አልሰጥም አሉ፡፡ በመጨረሻ ግን ሕዝብ እና መንግሥት ባለበት ለትውልድ አስረከቡ፡፡ ምናለ እንደ አባ ሙሉ ያለ አሥር ቢሰጠን፡፡

የጎንደር አብያተ ክርስቲያናት እያንዳንዳቸው ሙዝየም ሊኖራቸው በተገባ ነበር፡፡ በውስጣቸው ገና ትውልድ ያላያቸው ብዙ ቅርሶች ይዘዋልና፡፡ መካነ ስብሐት ልደታ ለማርያም የተተከለችበትን ሦስት መቶኛ ዓመት በቅርቡ ልታከበር በዝግጅት ላይ ናት፡፡ ከዚህ በዓል በተያያዘም ሙዝየም ለመገንባት አስበዋል፡፡

ጎንደር ላይ ሁለት አሳዛኝ ቅርሶች አሉን፡፡

ከሸዋ መጥተው ጎንደር ወንበር ዘርግተው ያስተምሩ የነበሩ አለቃ ወልደ አብ የተባሉ መምህር ነበሩ፡፡ መቼም በጥንቱ ባህላችን ሰው ሞያው እንጂ ሀገሩ አይጠየቅም፡፡ እር ሳቸው ደግሞ ደረስጌ ሄዱና መምህር ወልደ ሚካኤል የተባሉትን አምጥተው በትምህርት አሳደጓቸው፡፡ አለቃ ወልደ አብ ሲያርፉ መምህር ወልደ ሚካኤልየ ግምጃ ቤት ማርያምን ትምህርት ቤት ተረክበው ማስተማር ቀጠሉ፡፡

መምህር ወልደ ሚካኤል እያስተማሩ እያሉ ደርቡሽ ጎንደርን ሊያቃጥል መጣ፡፡ ብዙዎቹ ሲሸሹ እርሳቸው ግን «መከራ ታዝዞብናልና እናንተ ሽሹ፤ እኔ ግን ጉባኤ አላጥፍም» ብለው እያስተማሩ እያሉ ከዘጠኝ ተማሪዎቻቸው ጋር በደርቡሽ ሰይፍ ተሰይፈው ዐረፉ፡፡

እነህ ለትውልድ አርአያ የሚሆኑ መምህር የተቀበሩት
እዚያው ግምጃ ቤት ማርያም ከግቢው በር በስተ ቀኝ በኩል ነው

እነህ ለትውልድ አርአያ የሚሆኑ መምህር የተቀበሩት እዚያው ግምጃ ቤት ማርያም ከግቢው በር በስተ ቀኝ በኩል ነው፡፡ የሚያሳዝነው ግን ምንም ዓይነት ምልክት የለውም፡፡ እንዲህ ዋኖቻችንን እየረሳን ነገ ሌላ «ዋና» ከየት እናገኛለን፡፡ የደብሩም ሰዎች ሆኑ ሌሎቻችን ቢያንስ መምህር ወልደ ሚካኤል ለሃይማኖታቸው እና ለጉባኤያቸው ሲሉ ተሰውተው እዚህ ቦታ ላይ መቀበራቸውን ምልክት ልናደርግላቸው ይገባል፡፡

እዚያው ግምጃ ቤት ማርያም በጀርባ በኩል ደግሞ እንደዚሁ በመረሳት ላይ ያለ ታሪክ አለ፡፡ የዐፄ ቴዎድሮስ አማካሪ የነበረው ፕላውዴን የተቀበረው ግምጃ ቤት ማርያም ነው፡፡ ፕላውዴን በምጥዋ የእንግሊዝ ቆንስል ሆኖ ነበር የተሾመው፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ ሲነግሡ ወደ ጎንደር መጣና ከንጉሡ ጋር ተገናኘ፡፡ ንጉሥ ቴዎድሮስም በመልካም ሁኔታ ተቀበሉት፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ከእርሳቸው አልተለየም ነበር፡፡

ፕላውዴን የተቀበረበት ቦታ
በብረት አጥር ታጥሮ ተቀምጧል፡፡
ነገር ግን የሰርዶ ዓይነት በቅሎበት
ሙጃው እንጂ መቃብሩ አይታይም

በመካከል ታመመና ለሕክምና ወደ ሀገሩ ሲሄድ የልጅ ጋረድ ሽፍቶች አገኙትና በደፈጣ ጦር ክፉኛ አቆሰሉት፡፡ ጥቂት ቀናትም ቆይቶ በጥር ወር 1853 ዓም ዐረፈ፡፡ ግምጃ ቤት ማርያምም ተቀበረ፡፡

ፕላውዴን የተቀበረበት ቦታ በብረት አጥር ታጥሮ ተቀምጧል፡፡ ነገር ግን የሰርዶ ዓይነት በቅሎበት ሙጃው እንጂ መቃብሩ አይታይም፡፡ በላዩ ላይ የነበረው ጽሑፍም ጠፍቷል፡፡ ይህ ቦታ የኢትዮጵያን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከሚያሳዩት ቦታዎች አንዱ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ለወዳጆቿ የምትሰጠውን ቦታም ያሳያል፡፡ ፕላውዴን እንግሊዛዊ ሆኖ እንደ ኢትዮጵያውያን የኖረ ነው፡፡ ታድያ ምነው ዝክረ ታሪኩን ዘነጋንበት?

ጎንደር ላይ እንቆይ፤ ሌላም እናያለን፡፡ ለመሆኑ በጎንደሩ ዐፄ ዮሐንስ ዘመን በዕንባ ስለ ተሳለችው ሥዕል ሰምተው ያውቃሉ?

# መልስ በሞባይል

እስኪ እዚያው ጎንደር ውስጥ አንድ ቀን እናሳልፍና ዐፄ ፋሲል ትምህርት ቤት ፊት ለፊት ቁጭ ብለን ከመምህራኑ ጋር እናውጋ፡፡

እኔ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ስማር በፈተና ሰዓት የሆነ አንድ ነገር ሁሌም ትዝ ይለኛል፡፡ በአንድ ክፍል ውስጥ አንድ ጎበዝ ተማሪ ነበር፡፡ ከእርሱ ቀድተው ለማለፍ የተዘጋጁ ደግሞ ብዙ ተማሪዎች፡፡ ታድያ ፈታኙ መምህር ጥብቅ ሆነና ዓይኑን እንደ ሰጎን ዓይን ተከለባቸው፡፡ ሊያነቃንቅ አልቻለም፡፡ የፈተና ማብቂያው ሰዓት ደግሞ እንደ ጎርፍ እየተንደረደረ ይነጉዳል፡፡

ከጎበዙ ተማሪ አጠገብ ያለው አንዱ ተማሪ አንዳች ነገር ዘየደ፡፡ መልሱን ከጎበዙ ተማሪ ቀዳና በአንድ ቁራጭ ወረቀት ላይ አሰፈረው፡፡ ከዚያም ከእርሱ ወንበር ባሻገር ያለው ተማሪ መምህሩን ለጥያቄ ጠራው፡፡ መምህሩ ጎንበስ ብሎ ያኛውን ተማሪ ሲያስረዳ ይኼኛው ተማሪ የመልሱን ወረቀት ከመምህሩ ጀርባ ላይ በፕላስተር ለጠፈው፡፡

ከዚያማ በየቦታው መምህሩን ለጥያቄ መጥራት ሆነ፡፡ እዚያ ሄዶ ጎንበስ ሲል አንዱ ይቀዳል፡፡ እዚህ መጥቶ ጎንበስ ሲል ሌላው ይቀዳል፡፡ እያጎነበሰ ሲያስቀዳ ዋለ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎቹ ከተሰጣቸው ጊዜ ቀድመው ጨረሱና የፈተናውን ወረቀት ይዞ ወደ ቢሮው ሄደ፡፡

የፈተናውን ወረቀት ቢሮው አስቀምጦ ወደ መምህራኑ ሻሂ ቤት ሲገባ ነበር መምህራኑ ሁሉ በሳቅ የፈነዱት፡፡ አጅሬ ተንቀሳቃሽ ሰሌዳ ሆኖ መልስ ሲያስገለብጥ ማርፈዱን አላወቀውም፡፡

ከዚህ የሚመሳሰል አንድ ወግ አንድ መምህር ቀጥሎ ያወጋናል፡፡

ተማሪዎችን ለዓመቱ የመዝጊያ ፈተና ፊዚክስ ሊፈትን ወደ አንድ ክፍል ይገባል፡፡ የፈተናውን ወረቀት አድሎ አንዱን ጥግ ይዞ ተፈታኞቹን ይመለከታል፡፡ ማንም ቀና የሚል የለም፡፡ ፈተናው ከብዷቸዋል መሰል ሁሉም አቀርቅረዋል፡፡ ለመኮራረጅ የሚሞክር ቀርቶ የሚያስብ የለም፡፡ እፎይ አለና ወንበር ስቦ ቁጭ አለ፡፡ አልፎ አልፎ በድንገት እየተነሣ ቢያያቸውም የመኮራረጅ ጠባይ አይታይም፡፡

ደነቀው፡፡ እዚህ የተመደበው በጣም በመኮራረጅ የታወቀ ክፍል ነው ተብሎ ነው፡፡ እርሱ ደግሞ የሚኮርጅን ተማሪ በመያዝ በት/ቤቱ ውስጥ የተዋጣለት ነው ይባላል፡፡ ዛሬ ግን ያለ ቦታው እንደተመደበ ገባው፡፡ አለያም ተማሪዎቹ የጠባይ ለውጥ አምጥተዋል፡፡

ብቻ የአንድ በሽተኛ ተማሪ የሳል ድምጽ ይሰማል፡፡ እየደጋገመ ይሰላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ አንዴ ስሎ ያቆማል፡፡ ሌላ ጊዜ ሁለት ሦስት ጊዜ ይስላል፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ ባለ ማቋረጥ ይስላል፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ ጉሮሮውን እንደ መጠራረግ ያደርጋል፡፡

ፈታኙ መምህር ይህንን ተማሪ ያውቀዋል፡፡ በት/ቤቱ ውስጥ አሉ ከሚባሉት ጎበዝ ተማሪዎች አንዱ ነው፡፡ አንጀቱ ተንሰፈሰፈ፡፡ በዚህ አስቸጋሪ ሰዓት መታመም አልነበረበትም አለ፡፡ ምን ያድርገው፡፡ እየሄደ ያጽናናዋል፡፡ «አይዞህ ጊዜ ካነሠህ እጨምርልሃለሁ» ይለዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ለመፈተን መምጣቱ አስደንቆታል፡፡

ልጁም እየሳለ፤ ተማሪዎቹም ጸጥ ብለው፤ መምህሩም በተማሪዎቹ ሥነ ምግባር እየተደነቀ የፈተናው ሰዓት አለቀ፡፡ የፈተናውን ወረቀት ሲሰበስብ በሁሉም ላይ የደስታ ስሜት ያነብብ ነበር፡፡ ያ በሽተኛ ተማሪ አንኳን ያንን ያህል ሰዓት የሳለ አይመስልም ነበር፡፡

እነሆ የፈተናው ጊዜ አበቃ፡፡ ከአንድ ሳምንት በኋላ ተማሪዎቹ ወረቀት ለመውሰድ መጡ፡፡

ጉድ ተባለ፡፡ የአንድ ክፍል ተማሪዎች ፊዚክስን ተጫወቱበት፡፡ ሁሉም ከ95 በላይ አመጡ፡፡ ፊዚክስ እንዲህ ተደፍሮ አያውቅም ተባለ፡፡ ፈታኙ መምህር ተጠየቀ፡፡ ፈጽሞ የመኮራረጅ ነገር አለማየቱን ምሎ ተገዝቶ ተናገረ፡፡ በመምህራኑ መካከል በድጋሚ መፈተን አለባቸው የለባቸውም የሚል ክርክር ተፈጠረ፡፡ ምንም ዓይነት የመኮራረጅ ነገር ሪፖርት ሳይደረግ እንዴት አድርገው ድጋሚ ይፈትኑ፡፡

የተማሪዎቹ ውጤት ጸደቀ፡፡

ከወራት በኋላ የፈተናው ምሥጢር ተገለጠ፡፡ ለካስ ያ በሽተኛ ተማሪ እያስኮረጀ ኑሯል፡፡ ተማሪዎቹ ቀድመው ተመካክረዋል፡፡ አንድ ጊዜ ሲስል «ኤ»፣ ሁለት ጊዜ ሲስል «ቢ»፣ ሦስት ጊዜ ሲስል «ሲ»፣ በረዥሙ ሲስል ደግሞ «ዲ» ማለቱ ነው፡፡ በተማሪዎቹ መካከል የውጤት ለውጥ የመጣው ይህንን ምሥጢራዊ ኮድ በመተርጎም እና ባለመተርጎም መካከል ነበር፡፡

እነዚህ ታሪኮች ዛሬ ጊዜ አልፎባቸዋል፡፡ መኮራረጅም ሃይ ቴክ ሆኗል፡፡ አሁን እነዚህን የሚያነሣ ፋራ ብቻ ነው፡፡

የሠለጠነውን የመኮራረጅ ታሪክ ልንገራችሁ፡፡

ለኀበዝ ተማሪ አስቀድሞ ይከፈለዋል፡፡ ሞባይሉም የሆለት መቶ ብር ካርድ ይሞላለታል፡፡ ከዚያም ሁሉም ሞባይሉን ከፍቶ መጠበቅ ነው፡፡ እርሱ ሠርቶ እንደጨረሰ በሞባይሉ መልሱን ቴክስት ያደርገዋል፡፡ ከዚያ እድሜ ለቴክኖሎጂ እያሉ መገልበጥ ነው፡፡

ይሄንን ነገር መምህራኑ ነቁ፡፡ ከዚያም ሞባይል እያስቀመጣችሁ ግቡ ተባለ፡፡ ሴቶቹ ደግሞ መሸፋፈን ሙብታችን ነው አሉ፡፡ ሞባይሉን ብብታቸው ውስጥ ከትተው ማዳመጫውን ደግሞ በመሸፋፈኛቸው ውስጥ ያስገቡታል፡፡ ያ መከረኛ ኀበዝ ተማሪ ቶሎ ቶሎ ይሠራና አንድ አሥራ አምስት ደቂቃ ሲቀር ሰጥቶ ይወጣል፡፡ ከዚያም ውጥ ሆኖ ስልክ ይደውላል፡፡

እቱም በመሸፋፈኛዋ ውስጥ በሰካችው ማዳመጫ መልሱን እየተቀበለች ትሞላና ፈገግ ብላ ትወጣለች፡፡ መምህራኑ እንዳጫወቱኝ ሞባይሉን በፓንታቸው ሥር ሸሽገው የሚገቡ ተማሪዎችም አሉ፡፡

አሁን መምህራኑን የሕግ አለመኖር እያስጨነቃቸው ነው፡፡ አንድን ተማሪ ሞባይል አትያዝ ለማለት የሚያስችል ሥልጣን አላቸው ወይ? ሞባይል የያዘን ተማሪስ ለመቅጣት የሚያስችል ምን ሕግ አለ፡፡ እስካሁን በሞባይል እያወሩ ስለማሽከርከር እንጂ ሞባይል ት/ቤት ውስጥ ይዞ ስለመግባት የወጣ መመርያም ሆነ ሕግ ያለ አይመስለኝም፡፡ ወደፊት ግን ሳያስፈልግ አይቀርም፡፡ «መልስ በሞባይል» የትምህርት ቤቶች አዲሱ ፈተና ሆኗልና፡፡

# ጀግና የናፈቀው ሕዝብ

ሰሞኑን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ሦስት ታሪካዊ ሊባሉ የሚችሉ ውሳኔዎችን አሳልፏል፡፡ ያለ አግባብ የቆመው የአቡነ ጳውሎስ ሐውልት እንዲፈርስ፣ በየቤተ ክርስቲያኑ የተሰቀለው ፖስተር እንዲነሣ እና በቤተ ክህነቱ ሥልጣን ሳይኖራቸው ባለ ሥልጣን የሆኑ መበለቶች እንዲገለሉ፡፡

ውሳኔው እንደ ተሰማ የሕዝቡ ደስታ ወሰን አልነበረውም፡፡ ስለ ጉዳዩ የዘገቡ ዌብ ሳይቶችን፣ ብሎጎችን፣ ፌስ ቡኮችን እና ሌሎችንም አጨናንቋቸው ነበር የዋለው፡፡ ለምን?

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጀግና ይወዳል፡፡ በጦር ሜዳውም፣ በግብርናውም፣ በሃይማኖቱም፣ በፖለቲካውም፣ በኪነ ጥበቡም ጀግና ይወዳል፡፡ ሌላው ቀርቶ ከባድ ኃጢአት ቢሠራ እንኳን ጀግናን ይቅር ይላል፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ ብዙ ሕዝብ በግፍ ገድለዋል፡፡ ብዙ የጭካኔ ሥራም ሠርተዋል፡፡ ነገር ግን ለእንግሊዝ እጄን አልሠጥም ብለው ለትውልድ ምሳሌ በሚሆን መንገድ ጀግንነት ፈጽመው ተሠው፡፡ ሕዝቡ የሠሩትን ክፉ ሥራ ሁሉ በፈጸሙት ገድል አስተሠረየው፡፡

በሃይማኖትም እንዲሁ፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በታሪኳ ከ100 በላይ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትን ቀብታለች፡፡ እንደ አቡነ ጴጥሮስ ስሙ የገነነ ጳጳስ ግን የለም፡፡ የኢትዮጵያውያንን የጀግና ጥም ያረኩ አባት ናቸውና፡፡

ባለፈው ሰሞን ሲኖዶሱ በአንድ ጳጳስ ቁጥጥር ሥር ከመዋል አልፎ ጉዳዩ በማይመለከታቸው እና ጉዳዩንም በማይመለከቱት ግለሰቦች ሥር ወድቆ ነበር፡፡ ሲኖዶሱ ምን ወሰነ መባሉ ቀርቶ የነማን በር ተሰበረ? እነማንን እነማን አስፈራሯቸው? እነማን ከነማን ጋር ተሰለፉ? ሆኖ ነበር ጨዋታው፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ፖለቲካዊ ካልሆኑ ተቋማት መካከል አንዱ እና ጠንካራዋ፣ ቀዳሚዋም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ የዚህች ቤተ ክርስቲያን የሉዓላዊነቷ መገለጫ ደግሞ ቅዱስ ሲኖዶሷ ነው፡፡ ይህ ጉባኤ ጳጳሳት መጀመርያውኑ ከሕዝብ ርቆ፣ ንጽሕ ጠብቆ መኖር ጀመረ፡፡ በኋላ ደግሞ ከቀኖናዊ አሠራር ወደ አምባ ገነናዊ አሠራር ተዛወረ፡፡ በመጨረሻም ከነ መኖሩ መዘንጋት ጀመረ፡፡

ይህ ሁኔታ ሕዝቡን ሲያስጨንቀው ነው የከረመው፡፡ ጭንቀቱ ለእምነቱ ተከታዮች ብቻ አልነበረም፡፡ የዚህችን ሀገር ብርታት፣ ጥንካሬ፣ ዕድገት፣ ዴሞክራሲያዊ ሂደት፣ መልካም ገጽታ እና በጎነት በሚመኙ አካላት ሁሉ ዘንድ ነበር፡፡ ትልቋ ቤተ ክርስቲያን እና ትልቁ ተቋም እንደዚህ ከሆነ የሌሎችስ ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይችላል? የሀገሪቱ ዕድገት ሁለገብ ዕድገት እንጂ የአንድ ወገን መመንደግ አይደለምና ከግማሽ በላይ የሚሆነውን ዜጋ የምትመራ ተቋም እንዲህ እየሆነች ዕድገት እንዴት ሙሉ ይሆናል? እያለ ያልተጨነቀ አልነበረም፡፡

በተለይ ደግሞ ለብዙዎች የሕይወታቸው መሪ ቤተ ክርስቲያን ለሌሎችም የሀገሪተ የሥነ ምግባር፣ የባህል፣ የርዕዮተ ዓለም፣ የትውፊት፣ የማንነት እና የወጥነት /ውርጂናሊቲ/ ምንጭ የሆነች ተቋም፣ ለሌሎችም የኢትዮጵያውያን ሲቪክ ሃይማኖት /civic religion/ ጠባቂ የሆነች ተቋም ከመንፈስ ልዕልና ይልቅ የምግባር እና የአሠራር ብልሹነቶች መገለጫ እየሆነች መምጣቷ አሳሳቢ ነበር፡፡

የቤተ ክርስቲያኒቱን ነባር አኩሪ ሥራ እና ታሪክ፣ የጠራ አስተምህሮ እና ሀገራዊ አስተዋጽዖ፣ የቅርስ ባለ ቤትነት እና የሕዝብ ባህል እና ሥነ ምግባር ባለአደራነት የሚሸፍኑ እና የሚያስረሱ ዜናዎች ከያቅጣጫው ይሰሙ ነበር፡፡ በተለይም ደግሞ የበላይ ሉዓላዊ አመራር የሆነው ሲኖዶስ ዐቅሙ እየደከመ፣ ክብሩ እየከሰመ፤ ድምጹ እየጠፋ፣ ዜናው እየከፋ መምጣቱ የቤተ ክርስቲያኒቱን ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱን ውድቀት አመላካች ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጀግና የፈለገው በዚህ ጊዜ ነበር፡፡ እንደ አቡነ ጴጥሮስ ለእምነቱ እና ለአቋሙ የጸና፤ የሚመጣበትን በጸጋ ለመቀበል የተዘጋጀ፣ ታሪክ ሠርቶ ታሪክ የሚያስ ቀምጥ፣ አሁንስ በቃ የሚል የጀግና አባት አባት ጥም የእምነት እና የዜግነት ጉሮሮውን ሰንጎ ይዞት፣ ዋልያ ወደ ውኃ ምንጮች እንደሚናፍቅ እርሱም ጀግና ይናፍቅ ነበር፡፡

ሀገሪቱ የዕድገት እና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አውጥታ ራሴን ከድህነት አወጣለሁ እያለች ላይ ከታች ትኳትናለች፡፡ በዚህ ሰዓት ሕዝቡ እንደ አጥቢያ ኮከብ ከሩቅ የምታበራለት አንዲት ሀገራዊ ተቋም ጉዳይ እያሳሰበው እንዴት ልቡን

ሰብስቦ ስለ ዕድገት ያስብ፡፡ የነበረውን እያጣ እንዴት አዲስ አገኛለሁ ብሎ ተስፋ ያድርግ፡፡ ይህንን የከፋ ወሬ ምርግ አፍርሶ ደግ ዜና የሚያመጣ ጀግና ነበር ሕዝቡ የፈለገው፡፡

ለዚህ ነበር ቅዱስ ሲኖዶስ እነዚያን ሦስት ታሪካዊ ውሳኔዎች ሲወስን አገር በእልልታ የቀለጠው፡፡ ጥቂትም ቢሆን የጀግንነት ጭላንጭል ለማየት ስለቻለ፡፡

በቤተ ክህነቱ ውስጥ ሥር የሰደዱ በአንድ ጉባኤ የማይፈቱ ችግሮች አሉ፡፡ እነዚህ ችግሮች ዝም ከተባሉ ከቤተ ክህነቱ አልፈው እንደ ወረርሽኝ ወደ ሌሎችም ተቋማት ሊጋቡ የሚችሉ ናቸው፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የአንድ ሰሞን ጉባኤ አይበቃቸውም፡፡ ወሳኙ ነገር ጀግንነት ነው፡፡ ጀግና ችግሮቹን ሁሉ ላይፈታ ይችላል፡፡ ለችግሮች ሁሉ ግን መፍትሔ እንዳለው ያመላክታል፡፡ ጀግና ያለፉትን ኃጢአቶች ሁሉ ላያስተ ሠርይ ይችላል፡፡ ዳግም ሌላ ኃጢአት እንዳይሠራ ግን በር ይዘጋል፡፡ ጀግና በወቅቱ ያለውን ችግር በፍጹምነት ላያስወግደው ይችላል፡፡ ነገር ግን ችግሮች መቼም ቢሆን ተቀባይነት እንደሌላቸው በመሥዋዕትነትም ቢሆን ያሳያል፡፡ ጀግና ጨለማውን ላይገፍፈው ይችላል፡፡ ነገር ግን ሕዝብ በጨለማ መካከል ጭላንጭል እንዲያይ ያደርጋል፡፡

አንዳንድ ሰዎች ትናንት ያጠፉትን፣ የተሳሳቱትን፣ ምናልባትም በማወቅም ሆነ ባለማ ወቅ ያጠፉትን እያሰቡ እንዲህ ባደርግ እንዲህ ያደርጉኛል፣ ብገልጣቸው ይገልጡኛል፣ ብነግራቸው ይነግሩኛል ብለው ይፈራሉ፡፡ ከጀግኖች ሜዳም ይሸሻሉ፡፡ ይህ ግን የኢት ዮጵያን ሕዝብ ጠባይ ካለማወቅ የሚመነጭ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጀግናን ኃጢአት ያስተሠርያል፡፡ ስለ ጀግኖቹ ክፉን ነገር ለመስማት በፍጹም አይፈልግም፡፡ የዚያን ሰው ርእዮተ ዓለም ባይቀበሉትም፡፡ ያ ጀግና እነርሱን ለመውጋት የተሰለፈም እንኳን ቢሆን፤ ጀግና ከሆነ ጀግንነቱን እንጂ ሌላውን አያይም፡፡

አባቶቻችንም እንዲህ እና እንዲያ እንጽፍባችኋለን እያሉ ከጀግንነቱ ሜዳ የሚያስቀሯችሁን አትቀበሏቸው፡፡ ባለፈው ሰሞን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ አቡነ ሳሙኤል ላይ ራሱን ቤተ ክህነትን የሚያሳፍር መጽሐፍ ተጻፈ፡፡ ግን ሕዝቡ ተቀበለው? አመነ? በብጹእ አባታችን ላይ ፊቱን አዞረ? ፈጽሞ፡፡ ሕዝቡ ጽሑፉን ሳይሆን ለምን እንደ ተጻፈ ነው ያነበበው፡፡ በጳፉት ላይ አዘነባቸው፤ ኀዘኑም ደርሶ ጸሐፊዎቹን እና አጻፊዎቹን እርስ በርስ አባላቸው እንጂ በእርሳቸው ላይ ምን ቀነሰባቸው፡፡ ከፊት ይልቅ ከበሩ፣ የማያውቃቸው ዐወቃቸው፡፡

ማስፈራሪያ እና ፈንጣጣ አንዴ ከወጣ በኋላ ዳግም አይመጣም፡፡ ጀግና መጀመርያ ማሸነፍ ያለበት ፍርሃትን ነው፡፡ ፍርሃትን ያላሸነፈ ሰው ሊጀግን አይችልም፡፡ እናም አባቶቻችን መጀመርያ ፍርሃትን አርቁት፡፡ እናንተም እንደምታስተምሩን መላእክት እንኳን ወደ ሰዎች ሲመጡ መጀመርያ የሚያርቁት ፍርሃትን ነው፡፡ «አትፍሪ፣ አትፍራ» ነው የሚሉት፡፡

ወሳኔዎቹ መወሰናቸው በራሱ አንድ ገድል ነው፡፡ ከሲኖዶስ የሚጠበቀው ትልቁ ነገር ጠንካራ ውሳኔ ነው፡፡ ቢያንስ የተሠሩት ስሕተቶች የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮ አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡ ነገ ታሪክ ለሚጽፉ ሰዎች በቂ ማስረጃም ይሆናል፡፡ ዛሬ ስሕተቱን ማረም ባይቻል እንኳን አርጌንስ ከሞተ በኋላ ተወግዞ ስሕተቱ እንደታረመው ሁሉ እንዲያ የሚደረግም ይኖራል፡፡

አባቶች አሁን የጀመሩትን ጀግንነት በሦስት ነገሮች ማጽናት አለባቸው፡፡ በአሠራር፣ በቀጣይነት እና እንዳይደገም በማድረግ፡፡ ስሕተቱ እንዲፈጸም በር የከፈቱትን አሠራሮች ረጋ ብለው መዝጋት እና ማስተካከል አለባቸው፡፡ ጀግንነቱ በአንድ ጉባኤ ታይቶ የሚጠፋ መሆንም የለበትም፡፡ በየጉባኤያቱ፣ በየሀገረ ስብከቱ፣ በየመምሪያው መቀጠልም አለባቸው፡፡ ችግር በሂደት እንጂ በክስተት አይፈታምና፡፡ የመጨረሻው ደግሞ ያለፈውን ለማጥራት እንዲቻል ሌሎች ስሕተቶች እንዳይደገሙ መደረግም አለባቸው፡፡ ለምሳሌ ስለ ቀጣዮቹ ጳጳሳት አሿሿም፣ ስለ መምሪያ ኃላፊዎች ሹመት እና አሿሿም ማሰብ እና መጨነቅ አለባቸው፡፡

ሦስት ነገሮችን ደግሞ ማሰብ አለባቸው፡፡ እግዚአብሔር ከጀግኖች ጋር ነው፡፡ የሰማዕታት ታሪክ ይህንን ይነግረናል፡፡ ሕዝብ ከጀግኖች ጋር ነው፡፡ አቡነ ቄርሎስን በግሪክ እና በጀርመን ለማሳከም ምእመናን ያደረጉት ርብርብ እና የሰሞኑ ዜና ሲነገር ሕዝብ የተሰማው ስሜት ይህንን ያሳየናል፡፡ መንግሥትም ከጀግኖች ጋር ነው፡፡ ሀገርን ማሳደግ፣ ሕዝብን ማሠልጠን፣ የሀገርን ገጽታ መገንባት፣ የሚሻ መንግሥት ጀግኖችን ይፈልጋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጀግና ናፍቆታል፡፡

# እንማር ወይስ እንማረር

ከሰሞኑ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤን በመላው ዓለም የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን እና የበጎ ነገር ወዳጆች ሁሉ ሲከታተሉት ነበረ፡፡ ጉባኤው በሦስት ነገሮች የተሻለ ገጽታ ነበበረው፡፡

**1**/ የብፁአን አባቶች አንድነት በተሻለ ጎልቶ የወጣበት በመሆኑ

**2**/ የቤተ ክርስቲያንን ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉ ውሳኔዎች የተላለፉበት በመሆኑ

**3**/ የሃሳብ ክርክር እንጂ የጡንቻ ክርክር ያልታየበት በመሆኑ ናቸው፡፡

ጉባኤው ይህንን የመሰለ መልክ እንዲኖረው ያደረጉ ምክንያቶችም ነበሩ፡፡ የመጀመርያው እግዚአብሔር ከቤተ ክርስቲያን ጋር መሆኑ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የተለያት ብትሆን ኖሮ መንፈሳችን በተስፋ መቁረጥ እንደተሞላ ይቀር ነበር፡፡ አንድ ስሙ ያልተገለጠ የኢየሩሳሌም ተሳላሚ ተናገረው ብሎ ጀምስ ብሩስ እንደገለጠው «ብንወድቅም እግዚአብሔር ግን ከወደቅነው ከኛ ጋር ነበር»፡፡ በሌላም በኩል ደግሞ እኛ የማናውቃቸው፣ እግዚአብሔር ግን የሚያውቃቸው ቅዱሳን የጸለዩት ጸሎት መልስም ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በተለያየ መልኩ በጉዳዩ ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ ያበረከቱ ምእመናን፣ ባለሞያዎች፣ ሽማግሌዎች ወዘተ ውጤትም ነው፡፡ እንደ ገናም አያሌ ሚዲያዎች ከወትሮው በተለየ መልኩ ችግሩን ሊፈታ በሚችል መልኩ መንቀሳቀሳቸው ያመጣው የቤተ ክርስቲያን ድል ነው፡፡

ይህ ሁሉ ተደርጎ በመጨረሻ የሰማነው ዓይነት ውጤት ተገኝቷል፡፡

አንዳንዶቻችን ፓትርያርኩ ሲወርዱ ወይንም ሥልጣናቸው ሲገደብ፣ ሐውልቱ ሲፈርስ፣ ሙስና ይፈጽማሉ የተባሉት አካላት በሕግ ሲጠየቁ፣ የተበላሸው አስተዳደር በሥር ነቀል ለውጥ ሲሻሻል ለማየት ባለመ ቻላችን ውጤቱን መጨበጥ ተስኖናል፡፡ በተለይም በስተ መጨረሻ ቃለ ጉባኤ በመፈረም እና ባለመፈረም፣ ጋዜጣዊ መግለጫ በመስጠት እና ባለመስጠት በተፈጠረ ውዝግብ የጉባኤው ድምቀት መደብዘዙ አንዳንዶቻችንን ተስፋ አስቆርጦናል፡፡

በርግጥ ቤተ ክህነት መሠረታዊ ለውጥ ከሚያስፈልገው ጊዜ እጅግ ዘግይቷል፡፡ የቤተ ክህነቱ አሠራርም expiry date አልፏል፡፡ በውስጡ ከሚሠሩት ሠራተኞች ጀምሮ የማይማረርበት የለም፡፡ የቤተ ክርስቲያኒቱን ዋና ተልዕኮ ለማስፈጸም ባለመቻል፣ በሠራተኛ አቀጣጠር፣ በመዋቅራዊ ተገቢነት፣ በፋይናንስ አያያዝ፣ በአምባገነናዊ አሠራር፣ በማስፈጸም ዐቅም ማነስ፣ ወዘተ የተወሳሰበ ችግር ላይ ይገኛል፡፡ ታድያ እነዚህን የተወሳሰቡ የዘመናት ችግሮች በአንድ የሲኖዶስ ጉባኤ መፍታት ይቻላልን? አሁን ያሉት ብጹአን አባቶችስ ብቻቸውን እነዚህን ችግሮች መፍታት ይችላሉ? እኛስ በጉባኤውና በሂደቱ መማገር ነው ወይስ መማረር ያለብን?

የአሁኑ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ውሳኔ ያላረካቸው፣ «ድሮም ብለን ነበር» ያሉ፣ «ምን ዋጋ አለው» ብለው ተስፋ የቆረጡ፣ «ከዛሬ ጀምሮ» ብለው የተማረሩ ወገኖቼ ንዴት እና ብስጭት የሚመነጨው ራሱን ቤተ ክህነቱን ካለማወቅ ጭምር ነው፡፡ ለመሆኑ አንዳንዶቻችን ወደ ቤተ ክህነት ግቢ ገብተን እናውቃለን? ከቤተ ክህነት ሰዎች ጋር ሠርተንስ እናውቃለን? የቤተ ክህነቱን የአሠራር መዋቅር አናው ቀውም፣ ሌሎቻችንም የቤተ ክህነት ሰዎችን የአሠራር ዐቅም እና ጠባያት አልተረዳንላቸውም፡፡ በዚህም የተነሣ ስለ ቤተ ክህነቱ የምናስበው የሆነውን ራሱን ሳይሆን እንዲሆን የምንፈልገውን ነው፡፡ ስለ ቤተ ክህነት መዋቅር እና አሠራር ስናስብም በትምህርት ቤት ከተማርናቸው አሠራሮች ወይንም በየመሥሪያ ቤቱ ከለመድናቸው አሠራሮች በመነሣት እንጂ ራሱን ቤተ ክህነቱን ከማወቅ አይደለም፡፡

የቤተ ክህነት አሠራርኮ በሀገሪቱ ብቸኛው አሠራር ነው፡፡ ገንዘብ ሚኒስቴር በሰባዎቹ በተዋቸው አሠራሮች ገንዘብ የሚሰበሰበው በቤተ ክህነት ነው፡፡ ያለ አካውንታንት ሂሳብ የሚሠራው በቤተ ክህነት ነው፡፡ የሰው ኃይል አስተዳደር ሥልጠና ያልወሰዱ ሰዎች የሰው ኃይል የሚያስተዳድሩት በቤተ ክህነት ነው፡፡ ላለፉት ሃምሳ ዓመታት ምንም ዓይነት የመዋቅር ማሻሻያ ያላደረጉ ሁለት ተቋማት በኢትዮጵያ አሉ፡፡ ዕድር እና ቤተ ክህነት፡፡ ከመላዋ ኢትዮጵያ የጠፉ ዋልያዎች በስሜን ተራራ እንደሚገኙ ሁሉ በመላ ኢትዮጵያ እየጠፉ ያሉት ታይፐ ራይተሮች የሚገኙት በቤተ ክህነት ነው፡፡

በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እያንቀሳቀሰ፣ ከ45 ሚሊዮን በላይ ምእመን እየመራ፣ ከ35 ሺ አብያተ ክርስቲያናት ከ1100 በላይ ገዳማት እየመራ፣ ዕቅድ የሌለው ብቸኛ የሀገሪቱ ተቋም ቤተ ክህነት ነው፡፡ ምን ያህል ሠራተኞች እንደሚያስፈልጉት ልኩ የማይታወቅ ብቸኛ መሥሪያ ቤት ቤተ ክህነት ነው፡፡

አብዛኞቹ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ዓለምን ባጨናነቁት ልዩ ልዩ ዓይነት ስብሰባዎች የመካፈል እና ልምድ የማግኘት ዕድል የላቸውም፡፡ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተው አያውቁም፡፡ በባለሞያዎች ከሚመሩ ኮሚቴዎች ጋር የመሥራት ልምድ አላገኙም፡፡ በየሀገረ ስብከቱ የመንበረ ጵጵስና የሰበካ አጠቃላይ ጉባኤያት አይደረጉም፡፡ በመንበረ ጵጵስና ደረጃ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች እየሠሩ አይደሉም፡፡

ዓለም በየጊዜው በአሠራር ለውጥ ላይ በመሆንዋ ለኃላፊዎች እና ለበታች ሠራተኞች ሥልጠና፣ ሴሚናር፣ ዐውደ ጥናት እና የሞያ ማሻሻያ ኮርሶችን ይሰጣል፡፡ በአንድ ወቅት ዋና ዋና የሀገራችን የፖለቲካ አመራሮች በተልዕኮ ትምህርት በከፍተኛ ዲግሪ መመረቃቸው ተዘግቦ ነበር፡፡ በቤተ ክህነት ለብፁአን አባቶችም ሆነ ለሌሎች ኃላፊዎች ሴሚናሮች፣ የሞያ ማሻሻያዎች፣ የአዳዲስ አሠራች ማስተዋወቂያዎች፣ ዐውደ ጥናቶች እና ሥልጠናዎች አይሰጡም፡፡ እንዲያውም አንዳንዴ እነዚህን ማድረግ ቀርቶ ማሰብ እንደ ድፍረት የተቆጠረበት ጊዜም አለ፡፡

በቤተ ክህነቱ ሁለት ዓይነት አገልግሎቶች እየተሰጡ ነው፡፡ መንፈሳዊ እና ዓለማዊ አገልግሎቶች፡፡ ዓለማዊ ሲባል በቀጥታ መንፈሳዊ ይዘት የሌላቸው ለማለት ነው፡፡ ቀደምት አባቶች በዘመኑ ለነበሩት ዓለማዊ አሠራሮች ምን ያህል ቅርብ እንደነበሩ የሚያሳየን የጻፏቸው እና የተረጎሟቸው ጽሑፎች ናቸው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከመንፈሳዊው ነገር በተጨማሪ የሕግ ለምሳሌ ፍትሕ ሥጋዊ፣ የታሪክ ለምሳሌ የዓለም ታሪክ፣ የሕንፃ አሠራር፣ የፍልስፍና ለምሳሌ አንጋረ ፈላስፋ፣ ጽፈው እና ተርጉመው አንበዋቸዋል፣ ተጠቅመውባቸዋልም፡፡

በየገዳማቱ ያለውን መንፈሳዊውን አሠራር ከዴሞክራሲያዊው አሠራር ጋር ያጣመረውን አሠራር ስናይ ብቃታቸውን እናደንቃለን፡፡ የገዳሙን መናንያን የገዳሙን ምርፋቆች/ ሥራ አስፈጻሚዎች ይመርጣሉ/፤ ምርፋቆቹ ደግሞ አበ ምኔቱን ይመርጣሉ፡፡ የገዳሙን አጠቃላይ ሁኔታዎች በተመለከተ እነዚህ ሥራ አሥፈጻሚዎች በጋራ እየተወያዩ ነበር የሚወስኑት፡፡

ቤተ ክርስቲያኒቱ ዘመናዊውን ቤተ ክህነት ስትጀምረው ግን ዘመናዊውን አሠራር ከመንፈሳዊ አሠራር ጋር በተጣጣመ መልኩ ከመከተል ይልቅ ፊውዳላዊውን አሠራር ወሰደች፡፡ ሀገሪቱ ከፊውዳሊዝም ወደ ካፒታሊዝም፣ ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም፣ ከሶሻሊዝም ተመልሳ ወደ ካፒታሊዝም ስትገለባበጥ ቤተ ክህነቱ ግን እስካሁን ያንኑ ፊውዳላዊ አሠራር እንደያዘ ነው፡፡

አሁንም «ከመስቀልዎ እግር ሥር ተንበርክኬ እለምናለሁ» እያሉ የሚለምኑ የሥራ ደብዳቤዎች አሉን፡፡ «ደጅ መጥናት» እንደ አንድ የሥራ መለኪያ ነው፡፡ አሠራሩ ወይንም ሕጉ ምን ይላል? ከማለት ይልቅ ኃላፊው ምን ይላሉ? የሚለው ዋናው የሥራ ማስኬጃ ነው፡፡ በአንድ ጉዳይ ላይ ከመነጋገር ይልቅ ሽንገላ እና ውዳሴ ማኹነድነድ ሞያ የሆነበት ቤት ነው፡፡ በጥንቱ የሀገራችን አሠራር ጉዳይ ለማስፈጸም ባልደረባ ይሰጥ እንደነበረው ሁሉ ጉዳይን በመሥመሩ ሳይሆን በሰው በኩል ማስፈጸም እንደ ዋና አሠራር የሚካሄድበት ቤት ነው፡፡

ንጉሡ ወይንም መሳፍንቱ የሁሉ ነገር ባለቤት እና ከላይ እስከ ታች አዛዥ ናዛዥ እንደሚሆኑት ሁሉ ፓትርያርኩ ከጥበቃ እስከ ጳጳሳት የሚመድቡበት ቤት ነው፡፡ በዐፄ ምኒሊክ ዘመን እንደነበረው ሁሉ «ጸሐፊ» /ጽሑፍ የሚጽፍ ወይንም executive secretary ማለት አይደለም/ የሚባል የኃላፊነት ቦታ ያለው በቤተ ክህነት ብቻ ነው፡፡ በርግጠኛነት በየስንት ጊዜው እንደሚታተም የማይታወቅ ጋዜጣ ያለው በቤተ ክህነት ነው፡፡

እንግዲህ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ነው በአንድ ጉባኤ እንዲፈቱ የምንፈልገው፡፡

አሁን ያለው ቤተ ክህነት ለቤተ ክርስቲያናችን የሚመጥናት አይደለም፡፡ ያንስባታል፡፡ ሥርዓትዋ፣ ትውፊቷ፣ ዶግማዋ፣ ጥርት ብሎ የሚታየውን ያህል የቤተ ክህነቱ አሠራር ገና አልጠራም፡፡ የመልክ መልካም ልጅን ገጽታ

የማይገባ አለባበስ እንደሚያጠፋው ሁሉ የቤተ ክርስቲያኒቱን መልካም ገጽታ የቤተ ክህነቱ ዝርክርክነት፣ ደረጃው አለመጠበቅ እና ብቁ አለመሆን ከልሎታል፡፡

ስለሆነም ካሁኑ ጉባኤ መማር እንጂ በጉባኤው ፍጹም ነገር በመጠበቅ መማረሩ ውጤት አያመጣልንም፡፡ ተጀመረ እንጂ አላበቃም፡፡ በመልካም ጎዳና ላይ ቆምን እንጂ መልካም ነገሮችን ሁሉ ሠርተን አልፈጸ ምንም፡፡ ድል ብቻ ሳይሆን ሂደትም ውጤት ነው፡፡ ሐዋርያት ዓለምን ሁሉ እንዲያስተምሩ ታዝዘው ነበር፡፡ ከመካከላቸው ግን ዓለምን ሙሉ የዞረ የለም፡፡ ነገር ግን ወንጌል በዓለም ዙርያ የሚሰበከበትን መንገድ ተልመው፣ ጀምረው እና ለዚያም መሥዋዕትነት ከፍለው አለፉ፡፡ ሂደቱ ነበር ውጤታቸው፡፡ እኛም ችግሩን ሁሉ በዘመናችን ላንፈታው እንችል ይሆናል፡፡ ግን በመንገዱ ላይ ነን ወይ? ነው ጥያቄው፡፡

አሁን ልናስብበት የሚገባን ዋናው ነገር ምን ልንማር ምንስ ልናደርግ እንችላለን? የሚለው ነው፡፡ እንደ እኔ ግምት የአሁኑ ጉባኤ አምስት ነገሮች ያስተምረናል፡፡

የመጀመርያው አባቶች ቤተ ክህነቱ አሁን ባለበት ችግር ላይ ከተስማሙ እና መፈታት እንዳለበት የጋራ ግንዛቤ ካላቸው ችግሮቹን መፍታት በአንድነት እንደሚቻል ትምህርት ያገኙበት ነው፡፡ ስለሆነም በየአካባቢው ቤተ ክህነቱ ያለበትን ደረጃ፣ ምን መሆን እንዳለበት? ምን አደጋ ከፊቱ እንደተጋረጠ? የተጠኑ ጥናቶች ለየብጹአን አበው በማቅረብ፣ በማወያየት፣ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በመጠቆም ብንሠራ በቀጣይ ጉባኤያት ከዚህ የተሻሉ ውጤቶች ይገኛሉ፡፡

እስካሁን ድረስ ችግሮቻችንን በማመልከት፣ ንዴታችንን በማሳየት እና ድጋፋችንን በመግለጥ ካልሆነ በቀር የተጠኑ፣ ችግሮችን በግልጥ የሚያሳዩ፣ ለጉባኤው ግብዐት የሚሆኑ እና የብጹአን አባቶችን ግንዛቤ ሊያሳድጉ የሚችሉ የጥናት ውጤቶችን አናቀርብላቸውም፡፡ በዚህም ምክንያት ችግሮቹን የተረዱ እና ለማስወገድ ቆራጥነት ያላቸው አባቶች እንኳን አማራጮችን ለማግኘት አልቻሉም፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ሁለገብ ጥረቶች ከተደረጉ መፍትሔዎቹ ቅርብ መሆናቸውን ማየት መቻላችን ነው፡፡ ከአሁኑ የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ በፊት እና በተጓዳኝ ግለሰቦች፣ አባቶች፣ ኮሚቴዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና ባለሞያዎች በማማከር፣ ሃሳብ በመስጠት፣ ግፊት በማድረግ እና አዎንታዊ ተጽዕኖ ያለማሳደር ባለማሰለስ ሠርተዋል፡፡ በየገዳማቱ እና በየአካባቢው የጸሎት ጸጋ የተሰጣቸው አባቶች እና እናቶችም በብርቱ ተጋድለዋል፡፡

እስከዛሬ ድረስ ብዙ አካላት ለቤተ ክርስቲያን ቅርብ ለቤተ ክህነቱ ግን ሩቅ ነበርን፡፡ አሁን የተከሰተው የቤተ ክህነት ፈተና ካመጣቸው በጎ ውጤቶች አንዱ ሕዝቡ ለቤተ ክህነቱ ጉዳዮች ቅርብ እንዲሆን ማድረጉ ነው፡፡ ጥንት ሲኖዶሱ ይሰብሰብ አይሰብሰብ፣ ጳጳሳት ይሾሙ አይሾሙ፣ ውሳኔ ይወሰን አይወሰን ከቤተ ክህነቱ ሠራተኞች ውጭ የሚያውቅ አልነበረም፡፡ ሌላው ቀርቶ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ማን እንደሆኑ ብዙ ምእመን አይለይም ነበር፡፡ አሁን ግን የቤተ ክህነት ጉዳይ ምእመናን እና ልዩ ልዩ አካላት እንደ ቆቅ ጆሯቸውን ሰትረው የሚከታተሉት ነገር ሆኗል፡፡

ይህ ሁኔታ ይበልጥ መቀጠል አለበት፡፡ የአዋሳ ምእመናን ችግሩን እህህ ብለው ከመጓዝ ይልቅ ሕግ እና ሕጋዊነትን ብቻ ተከትለው በመሄድ ችግሮችን ለመፍታት የተጓዙበት መንገድ ታላቅ አርአያነት ያለው ነው፡፡ በሌሎች ቦታዎችም

ምእመናን የቤተ ክርስቲያኒቱን ተልዕኮ የሚያደናቅፉ፣ የሀገርን ገጽታ የሚያበላሹ፣ ዕድገታችንን የሚያቀጭጩ፣ ዝርክርክ እና የተበላሸ አስተዳደርን የሚያበረታቱ አሠራሮችን መንፈሳዊ እና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ለማስተካከል መነሣት አለባቸው፡፡ በየአጥቢያው፣ በየወረዳው፣ በየሀገረ ስበከቱ ችግሮች እንዲስተካከሉ አዎንታዊ ግፊት ለማድረግ ወገባችንን አሥረን መነሣት ይገባናል፡፡

ሦስተኛው ትምህርት ብጹአን አባቶች በየግላቸው ያሳዩት ቆራጥነት ነው፡፡ ይህ ግላዊ ቆራጥነት ከጉባኤው ባሻገርም መቀጠል መቻል አለበት፡፡ ጀግንነት የሚጠቅመው ቀጣይነት ሲኖረው ነው፡፡ የእናንተን ጀግንነት የሚፈልጉ አህጉረ ስብከት፣ አጥቢያዎች እና ገዳማት አሉ፡፡ በአባ ወርቅነህ ቋንቋ ለመግለጥ ጋሪው ፈረሱን እየቀደመው ነው፡፡ ይህንን ሁኔታ በአዋሳው ሂደት አይተነዋል፡፡ እናም ብጹአን አባቶች በጠቅላይ ቤተ ክህነቱ እንዲኖሩ የሚፈልጓቸውን መልካም አሠራሮች በየሀገረ ስብከታቸው መጀመር አለባ ቸው፡፡ በጠቅላይ ቤተ ክህነቱ ደረጃ ለሚደረጉ ስሕተቶች ሌላውን ተጠያቂ እያደረግን አመካኘን፤ በየሀገረ ስብከታችንስ በማን ልናመካኝ ነው?

ምእመናን የሚያማርሩት አባት አይተን አንገታችንን እንደደፋነው ሁሉ እስኪ ምእመናኑ የሚሸልሙት አባትም እንይ፡፡ የምእመናን ክብካቤው፣ መንፈሳዊ ብስለቱ፣ አስተዳደሩ፣ የገንዘብ አያያዙ፣ የንብረት አጠባበቁ፣ በምእመናን ብቻ ሳይሆን በአካባቢው የመንግሥት አካላት፣ በሌሎች የእምነት ተቋማት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በሚዲያዎች የሚመሰገን ሀገረ ስብከት እስኪ ፍጠሩ፡፡

ጽዳት ከራስ፣ ምሕረት ከመቅደስ ይጀምራል እንዲሉ እስኪ መዋቅራዊውን ማሻሻያ ከራሳችሁ ጀምሩት፤ ጵጵስናውን አክብራችሁ አስከብሩት፣ የክህነት አሰጣጡን አስተካክሉ፣ የአድባራት አስተዳዳሪዎች መመዘኛ አውጡ፣ ለሀገረ ስብከታችሁ ዕቅድ ይኑራችሁ፣ የሂሳብ አሠራራችሁን ዘመናዊ አድርጉት፣ ምእመናን በሀገረ ስብከቱ አገልግሎት እንዲሳተፉ አድርጉ፣ ከባለሞያዎች ጋር ሥሩ፣ ከአካባቢው የመንግሥት ተቋማት፣ በጎ አድራጊ ድርጅቶች እና ባለሞያዎች ጋር በመነጋገር የሞያ ማሻሻያ ሥልጠናዎችን እና ሴሚናሮችን ጀምሩ፡፡ መዋቅሩን አስጠኑት፣ የሀገረ ስብከታችሁን ገንዘብ በውጭ ኦዲተርራችሁ አስመርምሩ፡፡ ሀገረ ስብከቱ የእናንተ ነው ማን ይከለክላችኋል፡፡ በጥቂቱ ያልታመነ በብዙ አይሾምም ብላችሁ ታስተምሩን የለ፡፡

አራተኛው የሚዲያዎች ሚና ነው፡፡ ዘመኑ የመረጃ ዘመን መሆኑን አይተናል፡፡ በተለይ ደግሞ ሚዲያዎች በአቋም፣ በዘገባ ትንታኔ፣ በመረጡት መዓዝን እና በሰጡን መረጃ ቢለያዩም አብዛኞቹ ከመሠረታዊ ችግሮች የጸዳ ቤተ ክህነትን ለማየት ሕልም እንዳላቸው ያሳዩ ነበር፡፡ መረጃዎችን ለሕዝቡም ለአባቶችም በማድረስ ታላቅ ሚና ተጫውተዋል፡፡ ሚዲያዎችን ለማግኘት ለማይችሉ አባቶች ኢንተርኔት ከፍተው በማስነበብ፣ አትመው በመስጠት፣ጋዜጦቹን እና መጽሔቶችን በነጻ በማደል፣ መረጃዎችን ጨምቀው በማቅረብ አያሌ ምእመናን ተግተው ሰንብተዋል፡፡ የአብዛኞቹ ሚዲያዎች ዘገባ እና ትንታኔ ከስሜታዊነት፣ ከጥላቻ፣ ከስድብ፣ ከግለሰባዊ መስተጻምር እና ከጩኸት ይልቅ በመረጃ እና በዕውቀት ላይ የተመሠረቱ መሆናቸው አስደናቂ ነበር፡፡

ይህ የሚዲያዎች ሚና እንዲቀጥል እና «ዕውቀት ተኮር፣ መረጃ ደገፍ፣ ሃሳብ ሰጭ፣ መንገድ አመልካች» እንዲሆኑ ባለቤቶቹ፣ ጋዜጠኞቹ፣ አንባቢዎቹ እና ጸሐፍቱ መጣር አለባቸው፡፡ በአሥራ ዘጠኝ ሰማንያዎቹ እናየው ከነበረው የሚዲያዎች ገጽታ በተሻለ መልኩ ሚዲያዎቹ ሰከን ብለው ውኃ ያዘለ መልእክት እና መረጃ ይዘው ተንቀሳቅሰዋል፡፡ ይህ ደግሞ ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ አድርጓቸዋል፡፡

አባቶች፣ የሃይማኖት ሊቃውንት፣ ባለሞያዎች እና ሃሳብ ያላቸው ሰዎች ትንታኔዎችን፣ አማራጮችን እና ሃሳቦችን የሚሰጡበት መንገድ መዘጋጀት አለበት፡፡ የቤተ ክህነቱን አደራ የበሉ ሰዎች እየሠሯቸው ያሉ ሙስና፣ የዝምድና አሠራር፣ብኩንነት እና ኢሞራላዊ ተግባራት ፀሐይ እንዲመታቸው መደረግ አለባቸው፡፡ እየተወሰዱ ያሉ መፍትሔዎች፣ እየተከናወኑ ያሉ በጎ ሥራዎች ደግሞ መበረታታት ይገባቸዋል፡፡

አምስተኛው ትምህርት መቀስቀስ እና መንቀሳቀስ ያለባቸው አካላት ገና እንደሚቀሩ መገንዘብ መቻል ነው፡፡ ዕድገት የሁሉንም ሱታፌ ይጠይቃል፡፡ የተኛውን መቀስቀስ፣ የደከመውን ማበርታት፣ የሳተውንም ማረም ይገባል፡፡ ሰሞኑን እንደታየው ዕድገት እንዲመጣ የሚፈልጉ ለዕድገቱ ግን ምንም አስተዋጽዖ የማያደርጉ አካላት ገና አሉ፡፡ አንዳንዶቹም ዕድገቱን ወይንም ለውጡን ከቤተ ክርስቲያኒቱ ጥቅም አንፃር ከመመዘን ይልቅ ለእነርሱ ከሚያመጣው ትርፍ እና ኪሳራ አንፃር ይመዝኑታል፡፡

በተለይም አንዳንድ የቤተ ክህነቱ ባለ ሥልጣናት እና ሊቃውንት እንደ እግር ኳስ ማን አሸነፈ? የሚለውን እንጂ ለቤተ ክርስቲያን ምን ተረፋት? የሚለውን ለመመዘን ፈቃደኞች አይደሉም፡፡ አሸናፊውን ለይተው ካሸናፊው ጋር በመቆም የጥቅም ተቋዳሽ መሆን እንጂ ቤተ ክርስቲያኒቱ እና ሀገሪቱ እንድታሸንፍ አይሠሩም፡፡ ብጹእ አቡነ ቀውስጦስ ለአዲስ አበባ ከተመደቡ ጀምሮ «እንኳን ደስ ያለዎ» ለማለት የሚጎርፈው ሰው «አትርሱኝ» እያለ መሆኑን ማንም ያውቀዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ዐቅሙ እና ዕድሉ እያላቸው ድምፃቸውን ለማሰማት ያልመረጡ ማኅበራትም ነበሩ፡፡ እነርሱ ራሳቸው ሲነኩ አገሩን የሚያናውጡት ማኅበራት ቤተ ክርስቲያኒቱ ስትነካ ግን ዝምታን መርጠው ሰንብተዋል፡፡ በታላላቅ የአዲስ አበባ አዳራሾች ኃይላቸውን ሲያሳዩን የከረሙት ማኅበራት ሰው በሚያስፈልግበት ሰዓት አድፍጠው ሰንብተዋል፡፡ አንዳንዶቹም የሚዲያዎቻቸውን ድምጽ አጥፍተው ከርመው «የበሬን ምስጋና ወሰደው ፈረሱ» እንደ ተባለው ነገሩ ካለቀ በኋላ «በኛ ጥረት ነው» ማለት ጀምረዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ካለፈው ትምህርት መውሰድ አለባቸው፡፡ አሁን ዘመኑ እነ «ወርቄ» መከፈልት የሚቆርሱበት ሳይሆን እነ «መንክር» ማኅሌት የሚቆሙበት ነውና፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ «የኋላዬን ትቼ በፊቴ ወዳለው እዘረጋለሁ» እንዳለው ያለፈውን ገምግመን እና ተምረን ከፊታችን ወዳለው የተከፈተ በር የምናመራበት ጊዜ ላይ እንገኛለን፡፡ ሀገራችንም ሆነች ቤተ ክርስቲያናችን እመርታ ማስመዝገብ ባለባቸው ዘመን ላይ ነው ያለነው፡፡ ማማረሩን እና ተስፋ መቁረጡን ትተን፣ ካፈውም ትምህርት ወስደን፣ ለበለጠ ሥራ እንነሣ፡፡ እርሱ የሰማይ አምላክ ያከናውነዋል፡፡

## ድንጋይ ስድብ ነው ወይ?

አንዳንድ ጊዜ በተለምዶ የተቀበልናቸው፤ እኛም ሳንመረምር ዝም ብለን የምናደርጋቸው እና የምንናገራቸው ነገሮች፣ የያዙት እውነታ ከሚታወቀው በተቃራኒ ሆኖ የሚገኝበት ጊዜ አለ፡፡ ትምህርት የማይገባውን፣ ሰነፉን እና ደደቡን፣ ሥራ ጠሉን እና ዘረጦውን ለመግለጥ «እገሌ ድንጋይ ነው» እንላለን፡፡ የሌላውን ሀገር አላውቅም እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን እንዲያ ብሎ መሳደብ እና ድንጋይን ለውጥ ለሌለው፣ ለሰነፍ እና ለሥራ ጠል አእምሮ ምሳሌ ማድረግ የምንችል አይመስለኝም፡፡

ስለ ኢትዮጵያ ፊደል አመጣጥ ሊጠየቅ የሚችለው መረጃ ድንጋይ ነው፡፡ ቀደምት ሳባውያን ታሪካቸውን እና የጉዞ ዘገባቸውን፣ ንግግራቸውን እና እምነታቸውን ጽፈው ያስቀመጡት በድንጋይ ላይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ዛሬ የምንጠቀምበት እና የምንኮራበት ፊደል እንዴት እና ከየት ተገኘ ብለን ብን መረምር የመረጃው ባለቤት ድንጋይ ነው፡፡

ፊደላችንን ብቻ ሳይሆን በወቅቱ የነበሩትን የጥበብ መሣርያዎቻችንን፣ የጦር መሣርያዎቻችንን፣ የእህል ዓይነቶቻችንን ፣ የምንጠቀምባቸውን ከብቶች፣ የዛፎቻችንን እና የማዕድናት ሀብቶቻችንን እንኳን የምናገኘው ከድንጋይ ላይ መረጃዎቻችን ነው፡፡

የኢትዮጵያ የጥንቱ ግዛት ከየት ተነሥቶ የት ይደርስ እንደ ነበር፣ ማን ማን የተባሉ ሕዝቦች በአኩስም መንግሥት ሥር ይተዳደሩ እንደ ነበር፣ የትኞቹ ቦታዎች በጦርነት ገብረው እንደ ነበር፣ የትኞቹ ቦታዎች ወርቅ፣ የትኞቹስ ቦታዎች አልማዝ፣ የትኞቹስ ቦታዎች ዕንቁ ይገብሩ እንደ ነበር የጥንቱን መረጃ የያዘው የድንጋይ ላይ ጽሑፍ ነው፡፡

ለመሆኑ የኢትዮጵያን የብዙ ሺ ዓመታት ታሪክ የድንጋይ ያህል አሟልቶ የሚያውቀው አለ? ለቅድመ ጽሑፍ ታሪካችን ምስክሩ የአኩስም እና የደቡብ ትክል ድንጋዮች ናቸው፤ ለአኩስም ዘመን ታሪካችን ምስክሩ በአኩስም አካባቢ እና ባሕር ተሻግሮ በየመን የተገኙት የድንጋይ ጽሑፎች ናቸው፡፡ በዘመኑ የተጻፈ የታሪክ መረጃ የለም ተብሎ በባለ ታሪኮች ዘንድ «የጨለማ ዘመን» እየተባለ ስሙ የጠፋው የዛግዌ ሥርወ መንግሥት ታሪካችን እንኳን ሕያው ምስክሩ የድንጋይ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፣ ከዛግዌ ሥርወ መንግሥት በኋላ ለመጣው የመካከለኛው ዘመን ታሪካችንም ከጦርነት የተረፉን መረጃዎቻችን በየዋሻዎቹ የምናገኛቸው መዛግብቶቻችን ናቸው፤ የጎንደር ዘመንም አሻራዎቹ ከድንጋይ የተሠሩት ግንቦቻችን ናቸው፡፡ ሐረር ለነበረው ሥልጣኔ እና ታሪክ ሕያው ምስክራችን ከድንጋይ የተሠራው የሐረር ግንብ ነው፡፡ እናም ሦስት ሺም እንበለው ሰባት ሺ የኛን ታሪክ ከድንጋይ በተሻለ ማን ያውቀዋል፡፡

በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረውን የክርስቲያን ሙስሊም ጦርነት በተመለከተ እንኳን በሁለቱም ወገን ከተጻፉት ታሪኮች ሌላ ምስክር የምናገኘው በድንጋይ ላይ ነው፡፡ የት የት ቦታዎች ጦርነቱ ተደረገ? በወቅቱ የድል በለስ እየቀናው የመጣው የኢብን ኢብራሂም አሕመድ አልጋዚ ወታደሮች እና ተከታዮች የት ቦታ ላይ ተቀበሩ? በመጨረሻም አሕመድ አልጋዚ የት ቦታ ድል ሆነ? እያልን ብንጠይቅ በወቅቱ የነበረውን ታሪክ የምናገኘው «የግራኝ» ድንጋይ በመባል ከሚታወቁት እና በወቅቱ ከተተከሉት ትክል ድንጋዮች ይመስለኛል፡፡

ሀገራችን በጦርነት ስትታመስ፤ ሕዝቦቿም ራሳቸውን እና ሀገራቸውን ሲከላከሉ የኖሩ ናቸው፡፡ አብዛኛው ታሪካችንም የጦርነት ታሪክ ነው ይባላል፡፡ በዚህም የተነሣ አያሌ ታሪካዊ መዛግብትን አጥተናል፡፡ መጻሕፍቱ፣ ሥዕላቱ፣ ድብዳቤዎቹ፣ ንዋያቱ እና የወግ ዕቃዎቹ እየተቃጠሉም፣ እየተዘረፉም፣ በአፈር እየተበሉም አልቀውብናል፡፡ የተረፉትም ቢሆኑ እድሜ ለድንጋይ በየዋሻዎቹ ተደብቀው፣ ከአፈር መበላት እና ከእሳት፣ ብሎም ከቀበኛ የተረፉልን ናቸው፡፡ እነዚህ የድንጋይ ምሶሶ እና የድንጋይ ወጋግራ ዘርግተው የተፈጠሩ የድንጋይ ዋሻዎች ባይኖሩ ኖሮ፣ አሁን የምንኮራባቸውን የብራና መጻሕፍት፣ ንዋያት እና የወግ እቃዎች አጥተን ተረት ብቻ ወርሰን በቀረን ነበር፡፡

እነዚያ የድንጋይ ዋሻዎች ንብረቶቻችንን ብቻ ሳይሆን በእነዚያ የጦርነት እና የመከራ ጊዜያት እናቶቻችንን እና አባቶቻችንንም አስጠልለው አትርፈዋል፡፡ በሰሜን ሸዋ ተራሮች ሥር የሚገኙት እና «ዋሻ እገሌ» እየተባሉ የሚጠሩት ለቁጥር የሚታክቱት ዋሻዎቻችን፣ የባሌው ሰብስቤ ዋሻ እና የጋሞጎፋው የቦረዳ ዋሻ ለዚህ ምስክሮ ቻችን ናቸው፡፡

ቀደምቶቻችን ሰማይ ሰማዩን ብቻ ሲያዩ አልኖሩም፡፡ ምድር ንም በሚገባ ዐውቀዋት ነበር፡፡ ከሰሜን እስከ ደቡብ የምናገኛቸውን የድንጋይ ጥበቦቻችን የተሠሩባቸው ዐለቶች ተመሳሳይ ጠባይ ያላቸው ናቸው፡፡ እነዚያ ጠቢባን

ድንጋዮቹን በሁለት መመዘኛ ነው ሲመርጧቸው የኖሩት፡፡ ቅርጽ ለማውጣት የሚያስችል እና ረዥም ዘመን ለመኖር ዐቅም ያለው፡፡ በሁለቱም ተሳክቶላቸዋል፡፡ የሚገርመው ግን እነዚህን መመዘኛዎች የሚያሟላውን ድንጋይ ለማወቅ የሚጠይቀውን የጂኦሎጂ ዕውቀት ከየት አገኙት? የሚለው ነው፡፡

አንድ ሊቅ «ኢትዮጵያውያን ማለት ድንጋይ ሲያናግሩ የኖሩ ሕዝቦች ናቸው» በማለት የተናገረው እውነቱን መሆን አለበት፡፡ መሬቱን ፈልገው፣ ድንጋዩን አጥንተው፣ መርጠው እና አለዝበው ዘመናትን የሚሻገር የሥልጣኔ አሻራ መተው የቻሉት ድንጋይ የማናገር ችሎታ ስለነበራቸው መሆን አለበት፡፡ እነዚያን ድንጋዮች ቤት ብቻ አይደለም የሠሩባቸው፡፡ መሠዊያቸውን፣ መስቀሎቻቸውን እና ደወሎቻቸውንም ሠርተውባቸዋል፡፡ በወሎ፣ በጎንደር እና በጣና ገዳማት የምናገኛቸው የድንጋይ ደውሎች ድምፃቸው ከመዳብ እና ከብረት ደውሎች ይበልጣል፡፡ ለዚህ የተስማማውን፣ ድምፅ ሊያወጣ የሚችለውን የድንጋይ ዓይነት በምን ዐወቁት? ወይስ ያን ጊዜ የጂኦሎጂ ትምህርት ነበረ እንዴ?

ምናልባትም ቀደምቶቻችን የተፈተነ ሕይወትን የሚወድዱ ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ በቀላሉ ከእንጨት፣ሣር እና ቅጠላ ቅጠል ሊሠሯቸው ይችሉ የነበሩትን ነገሮች ከባድ ከሆነው እና ልዩ ችሎታን እና ቴክኖሎጂ ከሚጠይቀው ከድንጋይ ለመሥራት የፈለጉት ተፈጥሮን ለመፈተን፣ ዕውቀትንም ለመገዳደር ይመስለኛል፡፡ የጀግንነታቸው አንዱ መገለጫም ጠላትን በመቋቋም ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮን ተፈታትነው በማስገበርም ጭምር እንዲሆን ሳያስቡ አልቀሩም፡፡ በዚህ መልኩ መከራን ተቋቁሞ ማለፍን አስቀድመው ከተፈጥሮ ጋር ባደረጉት ትግል ስለ ለመዱት ሳይሆን አይቀርም እነዚያን ክፉ ጊዜያት ታሪክ እና ቅርስን ጠብቀው ለማሳለፍ የቻሉት፡፡

ክርስቲያንም ሙስሊምም ያልነበሩት ቀደምት የዳአማት መንግሥታት ታሪካቸውን ያቆዩት በድንጋይ ነው፣ በክርስትናቸው የታወቁት የዛግዌ ነገሥታት እና ሕዝቦችም ታሪካቸውን ያቆዩት በድንጋይ ነው፡፡ ሙስሊም የተነበሩት ግዛቶቻችን እና ሕዝቦችም ታሪካቸውን ያቆዩት በድንጋይ ላይ ነው፡፡ በትግራይ፣ በላስታ እና በጎንደር ከ3000 በላይ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን እናገኛለን፡፡ በአርጎባ «ራሳ» አካባቢ ደግሞ አርጎባዎች «ቱሉል» ብለው የሚጠሯቸው ወደ 3000 የሚጠጉ በባለሞያ የተቀረጹ የድንጋይ ምስሎች እናገኛለን፡፡ እናም፣ ምንም በሃይማኖት ብንለያይም ሥልጣኔያችን ግን በድንጋይ ላይ ሠፍሮ አንድነታችንን ይመሰክርብናል፡፡

ከሰሜን እስከ ደቡብ ያለውን የኢትዮጵያውያንን አንድነትስ ቢሆን ከድንጋይ በተሻለ ማን ይመሰክረዋል፡፡ አንድ ሰው እንዳ ለው «እስክስታ እና ድንጋይን ያህል የኢትዮጵያን ሕዝቦች አንድነት የሚያሳይ ባሕላዊ ገጽታ የለም»፡፡ ትግራይ ላይ ከወደ አንገት እና ትከሻ የጀመረው እስክስታ፣ አገው እና አማራ ላይ ሲደርስ አንገትን ከትከሻ ያያይዝና፤ ኦሮሚያ ላይ አንገትን፣ ትከሻን እና ወገብን ከእጅ እንቅስቃሴ ጋር ያዛምዳል፡፡ ወላይታ እና ሐድያ ላይ ሲወርድ ደግሞ ወገብን ታክኮ ወደ ዳሌ ዝቅ ይላል፡፡ ከዚያም ደቡብ ጫፍ ሐመሮች ላይ ሲገባ እስክስታው በእግር ይጨርሳል፡፡ ያኔም ኢትዮጵያ አንድ ሰው ሆና ትታያለች ማለት ነው፡፡

ድንጋይም እንዲሁ ነው፡፡ ከሰሜን አኩስም እስከ ባሌ ተራሮች፣ ከምዕራብ ኦጋዴን እስከ አሶሳ፣ ኢትዮጵያ በታሪካዊ የድንጋይ ሐውልቶች የተሞላች ናት፡፡ በጣም የሚገርመው ደግሞ እነዚህ የድንጋይ ሐውልቶች ከመቃብር እና ከታሪካዊ ሁነቶች ጋር የተያያዙ መሆናቸው ነው፡፡

የአኩስም ሐውልት በታላላቅ የአኩስም ነገሥታት መቃብር ላይ መታሰቢያ ሆኖ ቆሟል፡፡ ከአዲስ አበባ ደቡብ 50 ኪሎ ሜትር ርቀት ጀምሮ በሲዳማ፣ ወላይታ፣ ሐድያ፣ ስልጤ፣ ከምባታ፣ በሰሜን በአዋሳ ሐይቅ፣ በምዕራብ ደግሞ በአባያ ሐይቅ ተከብቦ የሚገኘውና ከ150 በላይ ታሪካዊ ሥፍራዎችን የያዘው የድንጋይ ሐውልቶች ስብስብ፣ እንደ ሰሜኑ ሁሉ የመቃብር ሥፍራዎችን እና ታሪካዊ ሁነቶችን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በኦሮሚያ ክልል በተለይም በአርሲ እና ባሌ የምናገኛቸው ሐውልቶችም ይህንኑ የሰሜን እና ደቡብ እሴት ተጋርተው፣ አንድነታችንንም መስክረው ይሄው ዛሬም ይታያሉ፡፡

ድንጋይ ሥልጣኔያችንን ብቻ ሳይሆን ጀግንነታችንንም ሲመሰክር የኖረ ነው፡፡ መሣርያ እንደ ልብ ባልነበረበት በዚያ ዘመን ሉዓላዊነታችን ታፍሮ፣ ድንበራችን ተከብሮ፣ የኖረው በድንጋይ ጭምር ነው፡፡ ቆንጥር ለቆንጥር መወርወር፣ ተራራ ለተራራ መኖር የለመደው ሐበሻ በተራሮች ጫፍ መሽጎ ይለቅቀው በነበረው ናዳ ያለቀውን ጠላት ያህል ሌላው መሣርያችን መጨረሱን እጠራጠራለሁ፡፡ ከሜዳማ አካባቢዎች ይመጡ የነበሩት አብዛኞቹ የውጭ ጠላቶች ከመሣርያችን በላይ መቋቋም ያቃታቸው ለሀገሩ ልጅ ብቻ ይበገር የነበረውን መልክዐ ምድራችንን ነው፡፡

እናም ድንጋይ የታሪካችን፣ የፊደላችን፣ የሥልጣኔያችን፣ የእምነታችን፣ የቀጣይነታችን፣ የአንድነታችን፣ የኅብራችን መገለጫ ከሆነ «ድንጋይ» እንዴት ስድብ ይሆናል?

## ከአዞዞ እስከ ጃናሞራ

**ሼህ አብደላስጥ አባ ከርቤ**

ወደ ጎንደር ከተማ ልትገቡ ጥቂት ሲቀራችሁ አዞዞ የተባለውን ጥንታዊ ከተማ ታገኙ ታላችሁ፡፡ ጎንደር ከመቆረቆሯ በፊት የተከተመው ይህ አካባቢ ይበልጥ የሚታ ወቀው በአዞዞ ተክለ ሃይማኖት ነው፡፡ ከ300 ዓመታት በፊት የተተከለው ይህ ታላቅ ደብር ከደብረ ሊባኖስ ገዳም ጋር የቆየ ግንኙነት አለው፡፡ ታሪኩን በነገው ዕለት እተርከላቸኋለሁ፡፡ ለዛሬ ወደ ሼህ አብደላ ሰጥ አባ ከርቤ ልውሰዳችሁ፡፡

የአካባቢው አፈ ታሪክ እንደሚናገረው እኒህ ሰው በዐፄ ሱስንዮስ ዘመን የነበሩ ናቸው፡፡ በዚያ ዘመን አዞዞ ላይ የሱስንዮስን እምነት አልቀበል ያሉ 500 የአዞዞ እና የአካባቢው መነኮሳት ታርደዋል፡፡ እነርሱ የታረዱበት ቦታ ላይ ቀስተ ደመና ተተክሎ ነበር፡፡ እኒህ ሰው ከሩቅ ሀገር ወደ ጎንደር ሲመጡ በቦታው የተተከለው ቀስተ ደመና ይታያቸዋል፡፡ በነገሩ ተገርመው ወደ ቦታው ሲመጡ መነኮሳቱ ሃይማታችንን አንለውጥም ብለው እየታረዱ ነው፡፡ ሼህ አብደላም ይህ በረከት አያምልጠኝ ብለው ቀረቡ፡፡ አንገታቸውንም ለሰይፍ ሰጡ፡፡ ወዲያውም ከሰማዕታት ጋር ተቆጠሩ፡፡ የተቀበሩበት ቦታ ከአዞዞ ፊት ለፊት ተራራው ላይ ይታያል፡፡ መታሰቢያቸው በየዓመቱ ትንሣኤ በዋለ በሦስተኛው ቀን ይደረጋል፤ እስላሞቹም ክርስቲያኖቹም በቦታው ይገኛሉ፣ ብለው የአካባቢው ነዋሪዎች ነግረውኛል፡፡

አስደናቂው የሼህ አብደላስጥ አባ ከርቤ ታሪክ ይበልጥ ሊጠና የሚገባው ይመስለኛል፡፡

አዞዞ ተክለ ሃይማኖት

# እርሻውን ማን ያርመው ?

ከሀገራችን ገበሬ ከምንማራቸው ትምህርቶች አንዱ እርማት ነው፡፡ ገበሬው እንደ አካሉ የሚወደውን መሬት ገምሶ ከስክሶ፣ አርሶ አለስልሶ ይዘራዋል፡፡ ዘሩ ብቅ ሲል ከየት መጣ ያልተባለ አረምም አብሮ ብቅ ይላል፡፡ ታድያ ጀግናው ገበሬ፣ አርበኛው ገበሬ፣ ቆፍጣናው ገበሬ፣ አርሶ በሌው ገበሬ፣ ትእግሥተኛው ገበሬ አረሙን እንዳየ ለስሙ አይደለም የሚጨነቀው፡፡

የጀግናውን እርሻ እንዴት አረም ገባበት፣ የአርበኛውን ማሳ እንዴት አረም ደፈረው፣ የቆፍጣናውን መሬት እንዴት አረም ሄደበት እባላለሁ ብሎ አይጨነቅም፡፡ ሲዘራ ምርጡን ዘር እንደ ዘራ ያውቃል፤ አበጥሮ አንጠርጥሮ እንደዘራ ያውቃል፡፡ እርሱ አረሙን እንዳልዘራው ያውቃል፡፡ አረም ግን ይበቅላል፡፡

ገበሬው ለእርሻው እንጂ ለስሙ አይጨነቅም፤ ለፍሬው እንጂ ለስሙ አይንገበገብም፣ ለምርቱ እንጂ ለስሙ ጊዜ አያባክንም፡፡ አረም የለም፤ አረምም አልበቀለም፤ የኔ እርሻ ምርጥ ዘር ተዘርቶ ምርጥ ዘር ብቻ ነው ያበቀለው፤ ዓይኔን ግንባር ልቤን ደረት ያርገው ብሎ ድርቅ አይልም፡፡ የገበሬው እምነት አንድ ነው፡፡ አረም ሊበቅል ይችላል፤ ግን ሊታረምም ይችላል፡፡ ከተቻለ አረም እንዳይበቅል ይደረጋል፡፡ ከበቀለ ግን አረም ነው ተብሎ በግልጽ ይታረማል፡፡ የስንዴን ስም ላለማጥፋት ሲባል አረም ስንዴ ነው ተብሎ አይታወጅም፡፡

የገበሬው የመጀመርያ ሥራ አረሙን ከምርቱ መለየት ነው፡፡ የተለያየ ጠባይ፣በልዩ ልዩ መንገድ የሚመጡ አረሞች አሉ፡፡ ወፍ የሚዘራቸው፤ ከመሬቱ ውስጥ የነበሩ፣ ምናልባት ከዘር ጋር ሳይታዩ የተቀላቀሉ፣ ጠላት ለተንኮል የዘራቸው፣ ነፋስ ያመጣቸው፣ ሌሎችም ሌሎችም፡፡ ታድያ ኀበዙ ገበሬ ያውቃቸዋል፤ በግብር ብቻ ሳይሆን በስምም ይለያቸዋል፡፡

ገበሬው የአረሙን ዓይነት እና መጠን ያይና ከቻለ ራሱ ብቻውን ያርመዋል፣ካልቻለ ቤተሰቡን ሰብስቦ ያርማል፤ ከዚያም በላይ ከሆነበት ቀየውን ደቦ እና ወንፈል ይጠራል፡፡ «እንዲህ ባለ ቀን አረም ስለማርም እርዱኝ» ብሎ በይፋ ሲናገር አያፍርም፡፡ እንዲያውም ማሳውን ለአረም ባለማስገበሩ ይኮራል፡፡ «አይ ቆምጫናው እጁን አይሰጥምኮ» ተብሎ ይመሰገንበታል፡፡

የቀየው ወዳጆቹም እንዴት በርሱ እርሻ አረም ተገኘበት ብለው አያሙትም፤ አያሳማማ፡፡ እንዲያውም ማልደው ወገባቸውን አሥረው ለአረም ይሠማሩለታል፡፡ ድምፀ መልካሞቹም

*የወይኖ ጌታ የሰመ ጥሩ*

*የጫሎ ጌታ የሰመ ጥሩ*

*ማዕበል የመታው ይመስላል ፈሩ*

*የወይኖ ጌታ የቆዩ በሬ*

*የጫሎ ጌታ የግራ በሬ*

*እርፉ እስኪናጋ ኮልኳይ ገበሬ*

*አስተራረሱን አገር ያወቀው*

*ጎተራው በጤፍ የተጨነቀው፡፡*

*ከወይኖ ጌታ የገባች አረም*

*ከጫሎ ጌታ የገባች አረም*

*ዘሯ አይገኝም እስከ ዝንታለም፡፡*

እያሉ ያቀነቅኑለታል፡፡ ያወድሱታል፡፡ እውነታቸውን ነው ገበሬው እርሻዬ ሊታረም ይገባዋል ካላለ፤ አረም እና ዘር ካልለየ፣ አረሙንም በጊዜ ካላረመ ምኑን ጀግና ገበሬ ሆነው፡፡ የጀግና ገበሬ አንዱ መለኪያኮ አረሙን መለየት እና በጊዜ ማረም ነው፡፡

ያለበለዚያማ አረሙ ዘሩን ይውጠውና የእህል እርሻ መሆኑ ቀርቶ የአረም እርሻ ይሆናል፡፡ መሬቱም ይበላሻል፤ ገበሬውም ይራባል፤ አገርም ትጎዳለች፡፡ ያውም አገር በሁለት ነገር ነው የምትጎዳው፡፡ በአንድ በኩል ገበሬው ከራሱ ተርፎ ለሌሎች ሊያወጣው የነበረው እህል ይቀራል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የገበሬውን እርሻ የወረሰ አረም መጀመርያ መንደሩን፣ ከዚያም ወረዳውን በመጨረሻም አገሩን ሁሉ ያዳርሰዋል፡፡

ለዚህም ነው ባህላዊው ገጣሚ፥

*ጉልጓሎውን ትቶ መሸታ ቤት ከርሞ፣*

*አረሙንም ትቶ መሸታ ቤት ከርሞ፣*

*ዳዋውን አልብሶ ማነኝ ይላል ደግሞ፡፡*

ብሎ የገጠመው፡፡

ገበሬ ሆይ ምናለ ይህችን ሞያህን ለኛም ብታስተምረን፡፡ እንዳንተ እርሻችንን በሚገባ ማወቅ አልቻልንምኮ፡፡ እንዳንተም አረሙን ለይቶ መንቀል አልቻልንምኮ፡፡ አንተ ከኔ የተሻለ የራሴን እርሻ የሚያውቀው የለም፡፡ ከኔ የተሻለ አረሙንም ለመለየትና ለማረም የተሻለ አይገኝም ብለህ አንተው ታርመዋለህ፡፡

የኛ ችግራችን ምን እንደሆነ ታውቃለህ? መጀመርያውኑ አረም ሊኖርብን ፈጽሞ አይችልም ብለን እንከራከራለን፡፡ ያ ክርክራችን ደግሞ ጭፍን ክርክር ነው፡፡ አረም ሊኖር የማይችለው እንዲህ እና እንዲያ ስላደረግኩ፣ እንዲህ እና እንዲያ ዓይነት ቴክኖሎጂ ስለተጠቀምኩ ነው ብለን አይደለም የምንከራከረው፡፡ እንዴት የኔ እርሻ ሆኖ አረም ይኖረዋል? እንዴት እገሌ እና እገሌ እያሉበት አረም አለው ይባላል ነው ክርክራችን፡፡ እንዴት ነው አረም በስም እና በታላቅነት ይጠፋል እንዴ?

አረሙን እንኳን እያየነው ለስማችን፣ ለዝናችን፣ ለክብራችን ስንል ስንዴ ነው አረም አይደለም ማለትን እንመርጣለን፡፡ «የኛ ስም ከሚጠፋ አረም ዘር ቢሆን ይቀላል» የሚለውን ብሂል አንተ ታውቀዋለህ?

አንተ ኀበዝ ነህ ወዳጄ እርሻዬ አረም ይዟል ብለህ ራስህ ታርመዋለህ፡፡ ምናለ አንተን የማኅበር ሰብሳቢ እና ዋና ጸሐፊ፣ የፓርቲ ሊቀ መንበር፣ የዕድር ዳኛ፣ የሃይማኖት መሪ፣ የድርጅት መሪ፣ የመሥሪያ ቤት አለቃ፣ ብናደርግህ፡፡ ይኼው ስንቱ አረም በየቦታው ዘር መስሎ ተቀምጦ የለም እንዴ፡፡ አንዳንዱ ከመኖር ብዛት በቅሎ፣ አንዳንዱ በሰው በኩል ገብቶ፣ አንዳንዱን ራሳቸው መሪዎቹ ዘርተውት፣ አንዳንዱን ጠላት ዘርቶት፣ ሌላውንም ከዘር ጋር ተቀላቅሎ ተዘርቶ እያየነው ነው፡፡

ዋናው ችግር አረም መኖሩ አልነበረም፡፡ ባይኖር የተሻ ነበር፡፡ ግን አለ፡፡ ታድያ እንዳንተ ማን ይመን፡፡ ሁሉ አረም የለብንም፤ እኛ ንጹሕ ነን ባይ ሆነ፡፡ አረሙ ደግሞ በቅሎ በቅሎ ይኼው በግልጽ እየታየ ነው፡፡ ሲሆን ሲሆን አረሙ ዘሩን ከመዋጡ በፊት እንዳንተ አረም አለብኝና ላርመው ብሎ መነሣት የአባት ነበር፡፡ ካልሆነ ደግሞ ዘመድ፣ ጎረቤት፣ ጎደኛ፣ ባልንጀራ፣ ባለሞያ፣ ጋዜጠኛ፣ውስጥ ዐዋቂ፣ አላፊ አግዳሚ፣ ታዛቢ፣ ተመልካች «ኧረ ይኼንን እርሻ አረም እየዋጠው ነው፣ አንድ ነገር ይደረግ» ብሎ ሲናገር ተቀብሎ ማረም ይገባ ነበረ፡፡

ጀግናው ገበሬ ያንተን ልብ ሀገሯ የት ነው? ያንተንስ ቆራጥነት ማደርያዋ ወዴት ነው? በቀይ ዕንቁስ የገዛት ማን ነው? ሁሉም ለምን ተነከቼ ባይ ሆነ፡፡ ዐቅም ከቻለ ራስን በራስ ማረም፣ ዐቅም ካልቻለም እንዳንተ እባካችሁ እርሻዬን

ለማረም ርዱኝ ብሎ በጠየቅ አሁን ምኑ ያስነውራል? ራሱ አረሙ ሳያስነውር ስለ አረሙ ማውራት ያስነውራል? የአረሙ መኖር ሳያሳፍር ለምን አረም አለ ተባለ የሚለው ለምን ያሳፍራል?

ወዳጄ አንተ ልክ ነህ፡፡ ራስህ አረሙን ቀድመህ ለየኸው፤ ራስህም ማረሙን ጀመርክ፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ ያሉትን ሰምተሃል አይደል፡፡ አንድ ቀን እልፍኛቸው ውስጥ እያሉ በማታ ከእቴጌ ጋር ይጋጫሉ፡፡ እቴጌም አንጀታቸው አርሮ ዐፄ ቴዎድሮስን ልክ ልካቸውን ይነግሯቸዋል፡፡ ከእልፍኙ ውጭ ሆኖ የሚጠብቀው የቴዎድሮስ ጋሻ ጃግሬ የእቴጌን ንግግር እየሰማ አንጀቱ ያርራል፡፡ ያ የቤተ መንግሥት ጠላ እና ጠጅ የለመደ ግብረ በላ ጠባቂ እንዴት ጌታዬን ይናገሩታል ብሎ ወዲያ ወዲህ ይንቆራጠጥ ጀመር፡፡

በመጨረሻም ጠባቂው ንዴቱ ከዐቅሙ በላይ ሆነና በሩን ከውጭ በርግዶ ወደ እልፍኙ ዘው አለ፡፡ ንጉሡ እና እቴጌይቱ በሁኔታው ደነገጡ፡፡ «ምንድን ነው?» አሉ ንጉሥ ቴዎድሮስ፡፡ «እንዴት ጌታዬን እመቤቲቱ እንዲህ ይናገሯቸዋል ብዬ ነው» አለ ጠባቂው እሳት እንደ ላሰ፡፡ ቴዎድሮስ ፈገግ አሉ፡፡ «አየህ» አሉት ጠባቂያቸውን «አንተ የምታውቀኝ ለብሼ፣ ተሸልሜ ነው፤ እርሷ ግን የምታውቀኝ ራቁቴን ነው፤ ልዩነታችሁ እዚህ ላይ ነው፤ በል አሁን ውጣ» አሉት ይባላል፡፡

እውነታቸውን ነው፡፡ ያ አንጋች ቴዎድሮስን የሚያውቃቸው አርድ አንቀጥቅጥ ለብሰው ጎምለል ብለው ሲወጡ ነው፡፡ እቴጌ ግን ሰው የማያውቀውን ያውቁታል፣ ድካማቸውን እና ብርታታቸውን ያውቁታል፤ ጠባሳቸውን እና ቁስላቸውን ያውቁታል፡፡ ጋሻ ጃግሬው ሲነቁ ነው የሚያውቃቸው፤ እቴጌ ግን ሲተኙም ያውቋቸዋል፡፡ ጋሻ ጃግሬው ሲስቁ ነው የሚያውቃቸው፤ እቴጌ ግን ሲያለቅሱም ያውቋቸዋል፡፡ ጋሻ ጃግሬው ሲበረቱ ነው የሚያውቃቸው፤ እቴጌ ግን ሲደክሙም ያውቋቸዋል፡፡ ራቁቴን ታውቀኛለች ያሉት ይህንን ነው፡፡

አንተም ገበሬው፣ እርሻህን ራቁቱን የምታውቀው አንተው ባለቤቱ ነህ፡፡ የውጮቹማ እንደ ለበሰ ነው የሚያውቁት፡፡ ለውጮቹ አምሮ ደምቆ የሚታየውን አንተ ነህ እንከኑን ነቅሰህ የምታየው፡፡ እናም አንተው ራስህ ብታርመው ያምርብሃል፡፡ «ከጠላት ምስጋና የወዳጅ ተግሣጽ ይበልጣል» እንዳለ ጠቢቡ፡፡ መጣፉምኮ «ጴጥሮስን የገሠፀው ጳውሎስ ነው» ነው የሚለው /ገላ 2፣11/፡፡ እውነት ነው፤ የጳውሎስ ያህል ጴጥሮስን ማን ያውቀዋል፡፡ ሌሎች እንደ ለበሰ ነው የሚያውቁት፣ እርሱ ግን ራቁቱን ነው የሚያውቀው፡፡

ራሳቸው ዐፄ ቴዎድሮስስ ባልዋን እና አባቷን የገደሉባት ምንትዋብ የተባለች ሴት

*አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ*

*ሊቃጥሎ ለብልቦ አንድዶ ፈጃችሁ*

*ይህንን ሲሰማ ያጎራል ላመሉ*

*ማናትም ቢሏችሁ ምንትዋብ ናት በሉ*

ብላ ትገጥምላቸዋለች፡፡ እንሾማለን እንሸለማለን ያሉ፤ ለሥራ ያልደረሱ ለሙብል ያላነሡ ነገር ለቃሚዎች ከነፋስ ፈጥነው ለቴዎድሮስ ያደርሱላቸዋል፡፡ «ታድያ ባልዋን እና አባቷን ገድዬባት ልታመሰግነኝ ኑሯል እንዴ፤ በሉ ቀለብ ሥፈሩላት፤ ባይሆን እርሷ እውነቱን ትንገረኝ እንጂ» ብለው ያዝዛሉ፡፡ እንዳሉትም እስኪሞቱ ድረስ እውነቱን ስትነግራቸው ኖረች፡፡ መቅደላ ላይ ሲሠው «ገደልንም እንዳይሉ ሞተው አገኟቸው» ብላ የገጠመች እርሷ ናት ይባላል፡፡

ባይሆን አንዳንዶቻችሁ እንኳን እውነት ተናገሩ እንጂ፡፡

## ተማኅፅኖ /Asylum/ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሰ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ዓላማዋ ከሆነው ስብከተ ወንጌልን የማስፋፋት ተልዕኮዋ በተጨማሪ ለሕዝቡ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባሕላዊና ኤኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ ሚና ተጫውታለች፡፡ የተጠናከሩ ማኅበራዊ ተቋማት ባልነበሩበት ጊዜ የኅብረተሰቡን ማኅበራዊ ዋስትና ሊያስጠብቁ የሚችሉ ተግባራትን ፈጽማለች፡፡ ከነዚህ ተግባራት መካከል ዕድር፣ ዕቁብ፣ ሰንበቴ፣ የማስታረቅ አገልግሎት፣ የጋብቻ አገልግሎት፣ የትምህርት አገልግሎት ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡

ከማኅበራዊ አገልግሎቶቿ መካከል አንዱ ፍትሕ እንዳይዛባ፣ በስሜታዊነት ሕግ እንዳይጣስ፣ ደካሞች በኃይለኞች እንዳይጠቁ ለማድረግ ትሰጠው የነበረው የመማፀኛነት /Asylum/ አገልግሎት ነው፡፡

**ተማኅፅኖ /Asylum/**

***መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜ-*** በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ተማኅፅኖ /Asylum/ ከባላጋራው ሸሽቶ ለመጣ ሰው ፍትሕ ርትዕ እስከ ሚያገኝ ድረስ መጠለያ መሸሸጊያ ወይም የደኅንነት ጥበቃ መስጠት ነው፡፡ ይህ ተግባር ከዘመነ ኦሪት ጀምሮ የነበረ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጥልናል፡፡

*እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ተናገረው- «ለእሥራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው፡፡ ወደ ከነዓን ምድር ዮርዳኖስን በተሻገራችሁ ጊዜ በስሕተት ነፍስ የገደለ ወደዚያ ይሸሽ ዘንድ የመማፀኛ ከተሞች እንዲሆኑላቸው ከተሞችን ለእናንተ ለዩ፡፡ ነፍሰ ገዳዩ በማኅበሩ ፊት ለፍርድ እስኪቆም ድረስ እንዳይሞት ከተሞቹ ከደም ተበቃይ የመማፀኛ ከተሞች ይሁንላችሁ፡፡... እነዚህ ከተሞች በመመካከላቸው ለሚቀመጡ እንግዶችና መጻተኞች መማፀኛ ይሆናሉ» /ዘኁ.35÷9-15/፡፡*

እነዚህ ስድስት ከተሞች ኬብሮን፣ ሴኬም፣ ቃዴስ፣ ቦስር፣ ራሞት፣ ጎላን ይባላሉ /ኢያ.20÷7-9/፡፡ በነዚህ ከተሞች መሠዊያዎች ነበሩ፡፡ ተማፃኙ ሰው የመሠዊያውን ቀንድ ይይዛል 1ነገሥት 1÷30/፡፡

በዘመነ ብሉይ በእነዚህ የመማፀኛ ከተሞች በመጠቀም ብዙዎች ከደም ተበቃዮቻቸው ተርፈዋል፡፡ ለምሳሌም ያህል ንጉሥ ዳዊት መንግሥቱን ለልጁ ለጠቢቡ ሰሎሞን ባስረከበ ጊዜ ዳዊት ሳያውቅ በራሱ ጊዜ የነገሠው አዶንያስ ፈርቶ የመሠዊያውን ቀንድ ያዘ፡፡ መልእክተኛም ልኮ ንጉሡ ሰሎሞን በሠራው ጥፋት ተበቅሎ እንዳይቀጣው ምሕረትን ለመነ፡፡ ሰሎሞንም «እርሱ አካኼÄ#ን ካሣመረ ከእርሱ አንዲት ጠጉር እንኳን በምድር ላይ አትወድቅም» ብሎ ቃል ስለ ገባለት /1ነገሥት 1÷32/ ከቅጣቱ ሊተርፍ ችሏል፡፡

በሌላም በኩል የመሠዊያውን ቀንድ ይዞ የተማፀነው ኢዮአብ እንደ አዶንያስ ሳይተርፍ በሰሎሞን ትእዛዝ ተገድሏል /1ነገሥት 2÷28-35/፡፡

***ተማኅፅኖ በኢትዮጵያ***

- ኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳንን ተቀብላ የኖረች ሀገር እንደ መሆንዋ ይህ ሥርዓት ወደ ሀገሪቱ ገብቶ የሥርዓቷና የባሕሏ አካል ሆኖ የቀጠለ ይመስላል፡፡ በስድስተኛው መ.ክ.ዘ የዓረቢያ ቆሪሾች የነቢዩ መሐመድን ተከታዮች ባሳደዷቸው ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ጥገኝነት /Asylum/ ጠየቁ፡፡ በወቅቱ ንጉሥ የነበሩት ንጉሥ አርማሕ የሳዑዲ ዐረቢያ ገዥዎች ስደተኞቹን አሳልፈው እንዲሰጧቸው ቢጠይቋቸውም በሀገሪቱ ነባር ሥርዓት መሠረት ተማፃኝን ለባላጋራ መስጠት ክልክል በመሆኑ አሳልፈው አልሰጧቸውም፡፡ ይህም ቤተ ክርስቲያኒቱ ለሀገሪቱ ሥርዓተ መንግሥት ካበረከተቻቸው ደንቦች አንዱ በመሆኑ ነው፡፡

በሌላም በኩል ይህን የኢትዮጵያን ሥርዓት ያወቁ ብዙ ክርስቲያኖች በሀገራቸው የሃይማኖት ስደት በተነሣ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እንደ ሀገሪቱ ዜጎች ለመኖር ችለዋል፡፡ በኬልቄዶን ጉባኤ ምክንያት በተዋሕዶዎች ላይ በአውሮፓ፣ በታናሽ እስያና በመካከለኛው ምሥራቅ የተነሣውን ስደት ሸሽተው የመጡት ተሰዓቱ ቅዱሳን ታሪክ ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

በየጊዜውም ግብፆች፣ የመናውያን፣ አርመኖች፣ ሕንዶች ወዘተ. ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በዚህ ሥርዓት ኖረዋል፡፡ ለምሳሌ በአጼ ዳዊት ዘመነ መንግሥት የነበረውና ለበልበሊት ኢየሱስ ገዳም መመሥረት አስተዋጽዖ ያደረገው የመናዊው ነጋዴ ፊቅጦር፣ በ10ኛው መክዝ ኢትዮጵያ ውስጥ በጥገኝነት የነበረውና በኋላም ጵጵስና ለእኔ ይገባል እያለ ያስቸግር የነበረው አብዱን የተባለው ግብፃዊ፣ በ10ኛወ መክዘ በቱርኮች ወረራ በተነሣው ስደት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በየገዳማቱ የገቡት አርመኖች፣ በአጼ ምኒሊክ ዘመን የመጡትና በባለሟልነት ደረጃ ባለ ርስት ለመሆን የበቁት ሐጂ ቀዋስ [ ***ሐጂ ቀዋስ ከሕንድ የመጡ አርክቴክት ናቸው፡፡ ከአጼ ምኒሊክ ጋር የተገናኙት አንኮበር ነው፡፡ እዚያ ብዙ ሕንፃ ገንብተዋል፡፡ ሚስታቸው ሞታባቸው ከሰንዳፋ ሐሊማ የተባለችውን አገቡና ልጅ ወለዱ፡፡ ነገር ግን ሚስታቸውና ልጃቸው በ1910/11 በእንፍሉዌንዛ ሞቱባቸው፡፡ አማርኛ አጣርተው የሚናገሩት ሐጂ ቀዋስ ከምኒልክ ጋር ከመግባባታቸው የተነሣ እንደ ባለሟል ይታዩ ነበር፡፡ ብዙ መሬትም ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከሕንድና ከየመን ዕቃ እያስመጡ የሚሸጡበት ትልቅ ሱቅ አዲስ አበባ ውስጥ ነበራቸው፡፡ መጀመርያ ባሻ ወልዴ ሠፈር በኋላም ደጃች ነሲቡ ሠፈር ይኖሩ ነበር ፡፡ከአዲስ አበባ አዲስ ዓለም የሚያመላልስ በበሬ የሚጎተተት ጋሪ ሠርተው ነበር፡፡ በ1905 ዓም አርፈው ጉለሌ ተቀበሩ፡፡***] የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

***የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና የተማኅፅኖ አገልግሎት***

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለሕዝቡ ትሰጣቸው ከነበሩት አገልግሎቶች አንዱ የመማፀኛ ቦታ በመሆን ማገልገል ነው፡፡ በተለይም ገዳማትና አድባራት በሚደበሩበትና በሚገደሙበት ጊዜ ንጉሡ በአካል ተገኝቶ ወይም ደግሞ እንደ ራሴውን ልኮ

*«ይህ ቦታ ዳሩ እሳት መሐሉ ገነት ይሁን፤ ከዛሬ በኋላ ማንኛውም የሀገር ገዥ የዚህን ደብር ክብር እንዳይሸር፡፡ አበሉንም በጉልበት እንዳይቀማ፡፡ በጳጳሳቱ አንደበት የተወገዘ ይሁን፡፡ በስሕተት ለገደለም መማፀኛ ይሁን» በማለት ያውጃል፡፡ ጳጳሱም ዐዋጁን በግዝት ያጸኑታል፡፡ ወዲያውም ጸሐፊ ተመርጦ ቃሉን በደብሩ ወንጌል ዳር ያሠፍረዋል፡፡ ንጉሡም ማኅተሙን ያትምበታል፡፡*

ከዚህ በኋላ የደብሩ ክልል ተብሎ የተከለለው አካባቢ ሁሉ የመማፀኛ ቦታ ይሆናል፡፡

**የተማኅፅኖ አጠያየቅና አፈጻጸም**

1. ወደ ደብሩ/ገዳሙ ክልል የገባው ተማፃኝ ደወል ይመታል፣

2. ጉዳዩን ለካህናቱ ያስረዳል፡፡

3. ካህናቱ/መነኰሳቱም ምግብና መጠለያ ሰጥተው ከጥቃት ያስጠብቁታል፣

4. ጉዳዩን በእርቅ ለመፍታት ከተቻለ ከባለጋራው ያስታርቁታል ካልተቻለ ግን ፍርድ ሊያገኝ ወደሚቻልበት ቦታ ያደርሱታል፡፡ ከዚያ ውጭ ባላጋራው ወይም ደመኛው እጁን ስጡኝ ብሎ ቢጠይቅ ካህናቱ /መነኰሳቱ አሳልፍው ላለመስጠት ዐቅማቸው የፈቀደውን ያህል ተጋድሎ ያደርጋሉ፡፡ ከዐቅማቸው በላይ በሆነ ኃይል ካልተሸነፉ በቀር አሳልፈው አይሰጡም፡፡

**የተማኅፅኖ አፈጻጸም በሦስት አድባራት/ገዳማት**

**ጨለቆት ሥላሴ / ትግራይ/**

ጨለቆት ሥላሴን ያስተከሉት ራስ ወልደ ሥላሴ ሐምሌ አራት ቀን 1785 ዓ.ም የደብሩ ቅዳሴ ቤት ሲከበር «እንበለ ቀዳሲ ኢይባእ ነጋሢ» በማለት ዐውጀው ነበር፡፡ በዚህ ዐዋጅ ላይ «በቦታው ገብቶ የደወል ወንጀለኛ ይማራል» የሚል ሥልጣን ለደብሩ ሰጥተዋል፡፡ በዚህም የተነሣ ዐዋጁ በተነገረበት ሰሞን ነፍስ ገድሎ ሸፍቶ የነበረ ሸፍታ

መጥቶ ደወል መታ፡፡ በአካባቢው የነበሩት ራስ ወልደ ሥላሴም ለባለደሞቹ ካሣ ከፍለው አስታርቀውታል፡፡ ለብዙ ዘመናትም የአካባቢው መማፀኛ በመሆን አገልግሏል፡፡

**ማኅደረ ማርያም /ደቡብ ጎንደር/**

በተለይም የደቡብ ጐንደርዋ ማኅደረ ማርያም በዘመነ መሳፍንት ከፍተኛ የመማፀኛነት አገልግሎት ትሰጥ ነበር፡፡ ዐፄ ሠርፀ ድንግልና እቴጌ ማርያም ሥና በ1589 ዓ.ም ሲደብሯት አቡነ ማቴዎስና እጨጌ ዮሐንስ በተገኙበት «መሐሏ ገነት ዳሯ እሳት ይሁን፣ የመማፀኛ ቦታ ትሁን፡፡ ማንም በኃይል አይድፈራት፤ የወደቀ አይነሣባት የተተከለ አይቆረጥባት» ተብሎ ታውጆ ነበር፡፡

በዚህም የተነሣ ብዙ መኳንንትና መሳፍንት በደብርዋ ክልል ቤት ሠርተው አስቀምጠው ነበር፡፡ በመከራ ጊዜ ለመጠለል፡፡ ለምሳሌም ያህል ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስና ራስ ጉግሣ ወሌ በደብሯ የመማፀኛ ቤቶች ነበሯቸው፡፡

በዚህች ደብር ተማኅፅኖ ያቀረቡት የመጀመርያው ባለ ሥልጣን አቤቶ ኃይሉ ናቸው፡፡ አቤቶ ኃይሉ ከንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ ጋር ተጋጠተው ጐጃም ቡሬ ታስረው ይኖሩ ነበር፡፡ አቤቶ ኃይሉ ከቡሬ አምልጠው ማኅደረ ማርያም ገብተው ተማፀኑ፡፡ ካህናቱ በደብሩ ካስጠለሏቸው በኋላ ወደ ላስታ ዘመዶቻቸው ዘንድ እንዲሄዱ አደረጉ፡፡ ይሁን እንጂ በዚያም ሊመቻቸው ባለመቻሉ ተመልሰው ወደ ማኅደረ ማርያም መጥተው ለአራት ዓመታት በጥገኝነት ተቀምጠዋል፡፡

ራስ ዓሊ አሊጋዝ ከበጌምድሩ ገዥ ራስ ወልደ ገብርኤል ጋር ተጣልተው ማኅደረ ማርያም ሲገቡ ራስ ወልደ ገብርኤል መጥተው ለመውሰድ ጠየቁ፡፡ የማኅደረ ማርያም ካህናት ግን ፈጽመው ተቃወሙ፡፡ ራስ ወልደ ገብርኤል የደብሩን መብት ተጋፍተው በመግባት ራስ ዓሊን አሥረው በወታደር አስጠበቋቸው፡፡ ራስ ወልደ ገብርኤል መርሐ ቤቴ ዘምተው ከባላምባራስ አሥራት ጋር ባደረጉት ጦርነት ድል ሆኑ፡፡ በዚህ ጊዜ ካህናቱ ራስ ዓሊን ፈትተው ነጻ አወጧቸው፡፡

የትግሬና የሰሜን ገዥ ደጃች ውቤና የጐጃሙ ገዥ ደጃች ጐሹ በራስ ዓሊ ላይ በተነሡ ጊዜ የራስ ዓሊ ባለቤት ወ/ሮ ጎኑት የራስ ውቤ ልጅ በመሆናቸው ፈርተው ማኅደረ ማርያም ገቡ፡፡ ራስ ዓሊ ድል ሲሆኑ ደጃች ውቤ መጥተው ወ/ሮ ጎኑትን ለመውሰድ ጠየቁ፡፡ የማኅደረ ማርያም ካህናት ግን ድርጊቱን ተቃወሙት፡፡ በኋላ ላይ ግን በኃይል ገብተው ወ/ሮ ጎኑትን ወሰዷቸው፡፡

በአይሻል ጦርነት ሰኔ 22 ቀን 1846 ዓ.ም ዐፄ ቴዎድሮስ ራስ ዓሊን ድል ሲያደርጉ ራስ ዓሊ ማኅደረ ማርያም ገብተው ተማፀኑ፡፡ በዚያም ለጥቂት ጊዜ ቆይተው ወደ የጁ ዘመዶቻቸው ዘንድ ሄደዋል፡፡ የማኅደረ ማርያም ካህናት ራስ ዓሊን ከኃይ ለኛው ከዐፄ ቴዎድሮስ በመደበቃቸውና አሳልፈው ባለመስጠታቸው ምክንያት ንጉሡ ካህናቱንና ሊቃውንቱን አርደዋል፡፡

**ዋልድባ /ሰሜን ጎንደር/**

በመማፀኛ ቦታነት የታወቀው ሌላ ቦታ ደግሞ የዋልድባ ገዳም ነው፡፡ የነገሥታቱ ዘመን አልፎ ዘመነ መሳፍንት ሲተካ ፈጻሜ መንግሥት ተክለ ጊዮርጊስ የተጠለሉት በዋልድባ ስቋር ገዳም ነበር፡፡ በኋላም የገዳሙ መናኒ ሆነው በዚያው ቀሪ ሕይወታቸውን አሳልፈዋል፡፡ መናኔ መንግሥት ተብለው የሚጠሩት ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስም ከዘመነ መሳፍንት የመኳንንቱ መገዳደል የተረፉት በዋልድባ ስቋር ተማፀነው ነው፤ በኋላም በ1769 ዓ.ም መንኩሰው በዚያው ዐርፈዋል፡፡

**ማጠቃለያ**

ቤተ ክርስቲያን ትሰጣቸው ከነበሩ ፈርጀ ብዙ ማኅበራዊ አገልግሎቶች አንዱ የሆነው የመማፀኛነት አገልግሎት በአሁኑ ጊዜ እምብዛም ሲተገበር አይታይም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ከ1966 ዓ.ም በኋላ የቀረ ይመስላል የሚል አመለካከት አላቸው፡፡

ይህ አገልግሎት ፍትሕ ርትዕ እንዳይጓደልና መበቃቀል በፍርድ ምትክ ቦታውን እንዳይዝ ያደርጋል፡፡ በግርግርና በፀጥታ መታወክ ጊዜ የሰው ሕይወት በቀላሉ እንዳይጠፋ ከፉውን ዘመን ለማለፍ ያገለግላል፡፡ በመሆኑም ኅብረተሰቡ ይህንን በመረሳት ላይ ያለ አገልግሎት እንዲያስታውሰውና እንዲጠቀምበት ቢደረግ መልካም ነው፡፡ ይኸም፡

በተለይ በገጠር የሚገኘውን በመበቃቀል መገዳደል በመቀነስ ሰዎች በሕጋዊና በሕጋዊ ፍርድ ብቻ ሙብታቸውን እንዲያጡ ያደርጋል፤

በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለመቀነስ የተበደሉ ሴቶች ወይም በደል ሊደረስባቸው የታሰቡ ሴቶች ተማጽነው ፍትሕ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

በሀገሪቱ ሰላም በሚናጋበት ጊዜ በባለሥልጣናት እና ሕዝቡ መካከል መገዳደል እንዳይኖርና ሰላም ነግሦ ፍትሕ እስኪሰፍን ድረስ ፖለቲካዊ ጥላቻ እንዳይባባስ ያደርጋል፡፡

**ዋቤ መጻሕፍት**

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ***የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ***፡ 1953፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

ልሳነ ወርቅ ገብረ ጊዮርጊስ /መሪጌታ/፣ ***ጥንታዊ ሥርዓተ ማኅሌት ዘአቡነ ያሬድ፣***

መቕሌ ንዑስ ማዕከል፣ ***ዝከረ ጽዮን/መጽሔት/***፣ 1994 ዓ.ም

***«መጽሐፈ ታሪክ ዘማኅደረ ማርያም»*** በደብሩ የሚገኝ

በሪሁን ከበደ፣ ***የዋሏድባ ገዳም ታሪክ፣*** 1983 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

Tareqegn Yibabe, ***The History of Mahidere Maryam.*** CA. 1596-1939. AAU. May 1988 (BA Thesis)

H.Welde. Bludeu. ***Royal Chronicle of Abyssinia 1769-1840*** (Cambridge, 1922)

Allen C.Myers. ***EErdmans Bible Dictionary.*** (Grand Rapids, Michigan 1987)

# ማኅሌት እና መከፈልት

አንድ የቆሎ ተማሪ ነበረ አሉ፡፡ ትምህርት አይወድም፡፡ ትምህርት ያደክማል የሚል ፍልስፍና ነበረው፡፡ «ትምህርት ይቀትል፣ ወምላስ የሐዩ» የሚለው አባባሉ ተይዞለታል፡፡ እግረ ተማሪ የሚሉት ዓይነት ነው፡፡ በየትምህርት ቤቱ ይዞራል እንጂ ቀለም አይዝም፡፡ እርሱ እቴ የሚፈልገው «ከየኔታ እገሌም ይህን ተምሬያለሁ፣ ከየኔታ እገሌም ይህን ቀጽያለሁ» እያለ ማውራት ነው፡፡

ታድያ የመንደሩን ወይዛዝርት እና መኳንንት ለመቅረብ እና ጠባያቸውን ለማወቅ ማንም አይቀድመውም፡፡ እያንዳንዱ ቤት ድግስ የሚደግስበትን ዝክር የሚያዘክርበትን ቀን ከባለቤቶቹ በላይ እርሱ ያውቀዋል፡፡ ክብረ በዓል ሲሆን አምሞ ጠምጥሞ ዋዜማ ይቆማል፡፡ ነገር ግን አንዲት ቀለም ከአፉ አትወጣውም፡፡ ብቻ ወይዛዝርቱ እንዲያዩት ከፊት ከኋላ እያገረገደ ያሟሙቃል፡፡ አይመራ፣ አይመራ፣ አያዜም፣ አይቀኝ፣ መቋሚያውን ይዞ አንገቱን እንደ በግ እንደደፋ ያመሻል፣ያድራል፡፡

ጠዋት ታድያ የዓመት በዓሉ ድግስ ቤተ ምርፋቅ ሲገባ ከሊቃውንቱ እና ከካህናቱ ቀድሞ የከበሬታውን ሥፍራ የሚይዘው እርሱ ነው፡፡ ሴት ወይዛዝርቱ እና ወንድ መኳንንቱ ሌሊት ሲያገረግድ ስላዩት ሊቅ የሚመስላቸው እርሱ ነው፡፡ አንዳንዶቹማ እርሱ ባይኖር ማኅሌቱ አይደምቅም ነበር እያሉ የመሪጌታውን ቦታ ይሰጡታል፡፡

«ለእገሌ ጣሉለት ለእገሌ ንሡት» እያለ አጋፋሪ ሆኖ ድግሱን ያሳምረዋል፡፡ ያ ሌሊቱን ጨዋ ሆኖ ተለጉሞ ያደረ አንደበት አሁን ጉሮኖ እንደ ሰበረ የፍየል መንጋ ይለቀቃል፡፡ «ፈቀደ እግዚእ» እንኳን ለማለት የተሣሣረ ምላስ ቤተ ምርፋቁን የዋሸራ ባለቅኔ የገባበት ቅኔ ማኅሌት ያስመስለዋል፡፡ በየዋሕነት አንገታቸውን እየነቀነቁ ለሚሰሙት ምእመናን የባጡን እና የቆጡን ብቻ ሳይሆን የመደቡንም ሳይቀር ይለፈልፍላቸዋል፡፡

ታድያ ይህ ጠባዩ ሊቃውንቱን እና ተማሪውን እያናደደ ቢኖርም አብዛኞቹ ዳዊቱ እንደሚለው «በልባቸው ይረግሙት» ነበር እንጂ ገሥፀውት አያውቁም ነበር፡፡ ምእመናኑም ለደብሩ እጅግ አስፈላጊ ሰው ስለመሰላቸው «መሪጌታ» እያሉ እፍታ እፍታውን የሚጥሉት እርሱ ገበታ ላይ ነው፡፡ ስለ ድግሳቸውም የሚያማክሩት እርሱን ነው፡፡

አንድ ቀን አንድ ኃይለኛ ተማሪ ገጠመው፡፡ ያሙቱ ማርያም ዋዜማ ተቁሞ እያለ የሊቁን ቅኔ በዜማ ተመራ አለው፡፡ አጅሬ ዐቅሙን ያውቃልና በብልጠት ትኅትና አንገቱን ደፋ፡፡ ከበሮ ያዝ አለው፤ «ሲይዙት ያደናግር» የሚሉት ይደርስብኛል ብሎ አይሆንም አለ፡፡ «መልክአ ማርያም አድል» አለው፡፡ «ከኔ የሚበልጡ አሉ» እያለ ሸሸ፡፡ እንዲህ ሲያመልጥ ሲያመልጥ ቅዳሴው ደረሰ፡፡

ሠርሖተ ሕዝብ ሆኖ ካህን እና ሕዝብ ወደ ድግስ ሲወርዱ ቀድሞ መደላድሉን ይዞ ያሣምረው ጀመር፡፡ ያወቀ እየሳቀ፣ ያላወቀ እያደነቀ ድግሱን ተቀላቀለ፡፡ እየበሉ እየጠጡ ዝም የጋን ወንድም ይባላል፡፡

*ዝ ጠላ ከመ ወይን ጣዕሙ*

*እስኩ ድግሙ ድግሙ*

*እስኩ ድግሙ*

እያለ በዜማ እያወረደለት የደረቀ ጉሮሮውን ቋሚው ሁሉ አራራሰው፡፡ ሆድ ሲደላደል፣ ጉሮሮ ሲረጥብ ምግቡ ተግ ይልና ጨዋታው ይደራል፡፡ የአጅሬም ሊቅነት አሁን ይጀምራል፡፡ እንደ አራቱ አፍላጋት የርሱ ወሬ አራቱን መዓዝን ያዳርሰዋል፡፡

አንዱ ተናደደ፡፡ አጽፉን አጣፋና ዘሎ ተነሣ፡፡ ወደ አጅሬ እያየም እንዲህ አለ፡፡

*ሀገርከ ቆላ ወስምከ ወርቄ*

*በጊዜ ማኅሌት በግዕ ወበጊዜ መከፈልት አንቄ፡፡*

ሊቁ ሁሉ አወካ፡፡ ከዳር እዳር አስገመገመ፡፡ «ወገብረ ሙብረቀ በጊዜ ዝናም» በዝናም ጊዜ ሙብረቅን አደረገ ማለት ይኼ ነው አሉ፡፡ አጅሬ ውርጭ እንደ መታው የሞላሌ በግ ነጭ ሆነ፡፡ «ሀገርህ ቆላ ነው ስምህም ወርቄ ነው፤ በማኅሌት ጊዜ እንደ በግ ዝም ትላለህ፣ መከፈልት ሲመጣ ግን እንደ ጭልፊት ትሞጨልፋለህ» ነበር ያለው፡፡

እነሆ ይህ ታሪክ በቆሎ ትምህርት ቤት ምሳሌ እየሆነ ሲነገር ይኖራል፡፡

ወርቄ ብቻውን አይደለም፡፡ ከእርሱም በፊት ሆነ ከእርሱ በኋላ ብዙ ሰዎችን አፍርቷል፡፡ በትግሉ፣ በሥራው፣ በልፋቱ፣ በድካሙ፣ ከውጣ ውረዱ የሉበትም፡፡ በግ ናቸው፡፡ ከድግሱ፣ ከሹመቱ፣ ከሽልማቱ፣ ከመድረኩ፣ ከአደባባዩ፣ ከሙገሳው፣ ከምርቃቱ እንደ ጭልፊት ማንም አይቀድማቸውም፡፡

የአፍ ቅልጥፍና ከአእምሮ ቅልጥፍና፣ የምላስ ርዝመት ከልቡና ስፋት፣ የከንፈር ፍሬ ከሥራ ፍሬ፣ ሥራ ከመቻል ውዳሴ መቻል ይበልጥ በሚወደድበት ማኅበረሰብ ውስጥ ወርቄ ትልቅ ቦታ አለው፡፡

ወርቄ ምን ተሠራ? ለሚለው አይጨነቅም እንዴት ይቀርባል? የሚለው ነው የሚያስጨንቀው፡፡ ወርቄ አሳማኝ ነገር አለ ወይስ የለም? የሚለው አይደለም የሚያስጨንቀው፤ እንዴት ማሳመን ይቻላል የሚለው ነው፡፡ ወርቄ ምን ውጤት መጣ? አያሳስበውም፡፡ ምን ይታይ? የሚለው ግን እንቅልፍ ይነሣዋል፡፡ የወርቄ መመርያ «ሰው የሚጠቅመውን ሳይሆን የሚያየውን ይመርጣል» የሚለው ነው፡፡ ከሰው ልብ ከመግባት ከሰው ዓይን መግባት ይሻላል ይላል ወርቄ፡፡

ሲሠራ አይታይም፤ ሲሸለም ግን ይታያል፤ ሲደክም አይታይም፣ ሲመሰገን ግን ይገኛል፤ ሲለፋ አይታይም፤ ሲደነቅ ግን ይታያል፤ በስብሰባው ሰዓት የለም፤ መግለጫ ግን ይሰጣል፤ ከምርምሩ የለበትም፤ ምርምሩ ሲታተም ግን ስሙ ይጠቀሳል፡፡ የመስክ ሥራው ላይ የለም፤ ሪፖርቱ ውስጥ ግን ይገባል፡፡ የመሥሪያ ቤቱን ሥራ አያውቀውም፣ ስለ መሥሪያ ቤቱ ግን የሚጠየቀው እርሱ ነው፡፡

ወርቄ ብዙ ዕውቀት አያውቅም፤ ብዙ ሰው ግን ያውቀዋል፡፡ ወርቄ ሞያ የለውም፣ ብዙ ባለሞያ ግን ያስተዳድራል፡፡ ወርቄ ስለ ጉዳዩ ባያወቅም፣ ያንኑ የማያውቀውን ጉዳይ እንዲመራ ግን ይመረጣል፡፡ ወርቄ ልብስ አያሰፋም፤ ሌሎች ያሰፉትን ግን አሣምሮ ይለብሰዋል፡፡ ወርቄ መዓድ አይሠራም፡፡ ሌሎች የደገሱትን ግን በሚገባ ያስተናግዳል፡፡ ወርቄ አያበላም፡፡ በሰው ግብዣ ግን ብሉልኝ ጠጡልኝ ይላል፡፡

ጓደኞቹ የማኅሌቱን ቀለም ለማጥናት ሁለት ሦስት ዓመት ይወስድባቸዋል፡፡ ወርቄ ግን በጆሮ ጠገብ ስለ ማኅሌት የሚያውቀውን አሠማምሮ መከፈልቱን ለማግኘት ደቂቃ አይወስድበትም፡፡ ከማኅሌታውያኑ በላይ ማኅሌታዊ ሆኖ ብቅ ይላል፡፡ እንዲያውም ስለማኅሌታውያኑ ሞያ የሚያስተዋውቃቸው እርሱ ይሆናል፡፡

በሹመት አደባባይ፣ በከበሬታ ሥፍራ፣ በመኳንንት ደጅ፣ በወይዛዝርት ሳሎን፣ በድግስ አዳራሽ፣ ወርቄዎች ሞልተዋል፡፡ ወርቄ ለጋዜጠኞች ቅርብ ነው፡፡ ለቴሌቭዥን መስኮትም ይስማማል፡፡

ብዙ ማኅሌታውያን ወርቄን ይፈሩታልም፣ ይፈልጉታልም፡፡ ዕውቀት የማይከፍታቸው፣ ችሎታ የማይሰብራቸው፣ ሞያ የማይደፍራቸው፣ ብቃት የማይሻገራቸው፣ ሊቅነት የማይደርስባቸው፣ ትኅትና የማያልፍ ባቸው፣ አያሌ በሮች አሉ፡፡ እነዚህን በሮች ለማለፍ እንደ ወርቄ ያሉ ያስፈልጋሉ፡፡ የምሁራኑን፣ የሊቃ ውንቱን፣ የባለሞያዎችን ጸሎት ወደ ጽርሐ አርያም ለማሳረግ ያለነ ወርቄ አማላጅነት አይሆንም፡፡ እነ ወርቄ ቅጣልን ብለው ያስቀጣሉ፤ ማርልን ብለው ያስምራሉ፡፡

እንደዚያ የነደደ የቆሎ ተማሪ እነ ወርቄን ደፍሮ የሚናገራቸው የለም፡፡ የሌላቸውን አለን፣ ያላደረጉትን አድርገናል፣ ያልሆኑትን ሆነናል፣ ያልደረሱበትን ደርሰናል ሲሉ ዝም ይባላሉ፡፡ ደግሞ በዚህ ሀገር ትርጉም ዝምታ ቁጥሩ ከመስማማት ነው፡፡ የሰው ድካም ወስደው የራሳቸው አድርገው ሲያቀርቡ፣ ባልተዋጉበት ግዳይ ሲጥሉ፣ ያለ ቃላት ድርሰት፣ ያለተዋናይ ድራማ ሲሠሩ፤ ያለ ዜማ ሙዚቃ፣ ያለ ካሜራ ፊልም ሲሠሩ፤ የሚናገራቸው የለም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ነገሩን ማን ሠራው? የሚለው ይቀርና ማን የኔ ነው አለ? የሚለው ዋና ጉዳይ ይሆናል፡፡

ተማሪው ጎጃም የሚገኙትን የመምህሩን ቅኔ ይዞ ይሄድና አያውቁብኝም ብሎ ትግራይ ውስጥ ቅኔ ማኅሌት ገብቶ ይዘርፈዋል፡፡ የራሱ እንዲመስል ንፋስ እንደ ነካው የወፍ መንጋ ከግራ ወደ ቀኝ ከቀኝ ወደ ግራ እየተመላለሰ ያወርደው ጀመር፡፡ በግራ በቀኝ የነበረው ተመልካች ሰም እና ወርቁን ፈትቶ ምሥጢሩን ባይረዳውም ድምፁን እና እንጉርድጃውን አይቷልና ይበል ይበል ብሎ አጨበጨበለት፤ እልልታውም ደመቀለት፡፡

ስሜቱ በርዶ፣ ፊቱም እንደ ሕፃን ልጅ ተፍለቅልቆ ወደ ማኅሌታውያኑ ሲመለስ አንዱ ሊቅ ዞር አሉና «የኔታ እገሌ ቅኔስ ደረሰን፤ ለመሆኑ የኔታ ደኅና ናቸው» ብለው ጠየቁት፡፡ እንደ ዳታን እና አቤሮን መሬት ተከፍታ የዋጠችው ነው የመሰለው፡፡

ዛሬ ማን እንደዚህ ይላል፡፡ በየምርምር ቦታዎች እነ ወርቄ የሰው ጥናት ሲዘርፉ፣ በየሥነ ጽሑፍ መስኩ እነ ወርቄ የሰው ድርሰት ሲነጥቁ፣ በየሥነ ጥበብ ሜዳው እነ ወርቄ የሰው ዜማ ሲሞጨልፉ፣ ከፈጠራ ጓዳ ገብተው የሰው ሃሳብ እና የፈጠራ ውጤት በስማቸው ሲያወጡ፤ ሳይደክሙ ሲሾሙ፣ ሳይጾሙ ሲፈስኩ፤ ሳይማሩ ሲያስተምሩ፣ ሳይሠሩ ሲከበሩ ማን ይናገራቸዋል፡፡

የሚነግዱት ሌሎች፣ የሚያተርፉት እነ ወርቄ፤ የሚዘሩት ሌሎች፣ የሚያፍሱት እነ ወርቄ፤ የሚያጠኑት ሌሎች፣ ፈተና የሚያልፉት እነ ወርቄ፤ የሚወዳደሩት ሌሎች፣ የሚያሸንፉት እነ ወርቄ፤ የሚጽፉት ሌሎች፣ የሚታተመው በነ ወርቄ ስም፤ የሚያጩት ሌሎች፣ የሚያገቡት እነ ወርቄ፤ የሚሮጡት ሌሎች፣ ሜዳልያ የሚወስዱት እነ ወርቄ፤ ማኅሌታውያኑ እና መከፈልተኞቹ ተላያዩኮ፡፡

***የበሬን ምስጋና ወሰደው ፈረሱ***

***ከኋላ ተነሥቶ ከፊት በመድረሱ***

ይባል የለ፡፡ በሬው ከጠዋት እስከ ማታ አርሶ አርሶ ደክሞት ቀስ ብሎ እያዘገመ ሲሄድ፣ ሲግጥ ያረፈደ ፈረስ ገሥግሦ ይደርስና ስለ እርሻው፣ ስለ ማሳው፣ ስንት ትልም እንደታረሰ፣ ምን እንደተዘራ፣ ምን እንደ ቀረ የሚያውቀውንም የማያውቀውንም እየጨማመረ፣ እያሣመረ፣ በል ሲለውምም አሂሂሂሂሂ በሚለው የፈረስ ሳቅ እያጀበ ዜናውን አዳርሶት ይጠብቀዋል፡፡

የዋሑ በሬ እያዘገመ ሲደርስ ፈረሱ ተመስግኖ፣ ወሬውም ቀዝቅዞ ይደርሳል፡፡ ከዚያ በኋላ ለርሱ ትኩረትም የሚሰጠው የለም፡፡ ከዚያ በኋላ የበሬው ድርሻ በረት ተኝቶ ራሱን እየነቀነቀ ማዘን ብቻ ይሆናል፡፡ ለዚህ ነው በሬ ሌሊት በተኛበት ቀንዱን ከግራ ቀኝ እያወዛወዘ አንገቱን ሲነቀንቅ የምናየው ይባላል፡፡ ምስጋናው ተወስዶበት፡፡ አይ በሬ፤ ስንት እንዳንተ ምስጋናው ተወስዶበት አንገቱን ሲነቀንቅ የሚያድር ሰው አለ መሰለህ፡፡

# ከቺሊ ሰማይ ሥር

ይህንን ጽሑፍ ስጽፍ የመጨረሻው የማዕድን አውጭ ከጉድጓዱ ውስጥ ወጥቶ ነበር፡፡ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ሆኗል፡፡ ለ69 ቀናት የጠበቅናቸው እነዚህ ሰዎች ተአምራዊ በሆነ መንገድ ከ622 ሜትር ጉድጓድ ውስጥ ወጡ፡፡ የቺሊ ፕሬዚዳንት ሴባስቲያን ፔኔራ «እግዚአብሔር ከምንወጣው በላይ የሆነ ፈተና አይሰጠንም» እንዳሉት እውነትም የሚወጡት ፈተና ሰጥቷቸዋል፡፡ የሀገሬ ሰውስ «ማከኪያውን ላይሰጥ እከኩን አይሰጥም» ይል የለ፡፡

ቺሊ ውስጥ ሳን ሆዜ በተባለ የማዕድን ማውጫ ቦታ ይሠሩ የነበሩ 33 ሠራተኞች የመውጫ መንገዳቸው ተዘግቶ ዋሻ ውስጥ መቅረታቸው የተሰማው የዛሬ 69 ቀን ነበር፡፡ ቺሊያውያን እና መላው ዓለም ደነገጠ፡፡ አዘነ፡፡ ምን ሊሆን ይችላል? እያለም ፈራ፡፡ ረዥሙን ቱቦ ሠርቶ፣ ቴክኖሎጂውንም ተጠቅሞ እነዚያን ሰዎች ለማውጣት ቢያንስ አራት ወር ይፈጃል፡፡ እንዲያውም ከገና በፊት የማይታሰብ ነው ተባለ፡፡

ፀሐይን ሳያዩ፣ በቂ ምግብ ሳያገኙ፣ አስፈላጊው ሕክምና ሳይደርሳቸው፣ ነገ ምን እንደሚሆን ሳያውቁ፣ ከቤተ ሰቦቻቸው ተለይተው እንዴት ይከርማሉ? ሙቀቱን እና ቅዝቃዜውን እንዴት ይችሉታል? ያልተነሣ የጥያቄ ዓይነት አልነበረም፡፡

የቺሊ መንግሥት በተለይም ፕሬዚዳንቱ ሴባስቲያን ፔኔራ አስፈላጊው ሁሉ እንደሚደረግ አስታወቁ፡፡ ራሳቸው ፕሬዚዳንቱ እና የማዕድን ሚኒስትሩ ጉዳዮችን ሁሉ በቅርብ ይከታተሉ ነበር፡፡ አሜሪካ እና ጀርመን የቴክኖሎጂ ድጋፍ ለማድረግ ቃል ገቡ፡፡ የቺሊ ሊቀ ጳጳስ ጸሎት ዐወጁ፡፡ ሕዝቡ በየቤተ ክርስቲያኑ ከተተ፡፡ ባለ መሰልቶች እና ባለማቋረጥ በመላ ቺሊ ጸሎት ይደረግ ነበር፡፡ በመጨረሻም ከ22 ሰዓታት በላይ በፈጀ የማውጣት ርብርብ ሁሉም የማዕድን ሠራተኞች ከ622 ሜትር ጉድጓድ በተአምር ወጡ ፡፡

ይህንን ዓለም እንደ ልብ ሰቃይ ፊልም በንቃት የተከታተለውን የ33 የማዕድን ሠራተኞች ታሪክ፤ ይህንን የቺሊያውያን አንድነት፣ አርበኛነት እና የሃይማኖት ጽናት የታየበትን ታሪክ፤ ይህንን ከ300 የሚዲያ ተቋማት የመጡ 2000 ጋዜጠኞች የተከታተሉትን ልብ አንጠልጣይ የሰው ልጅ ታሪክ ስመለከት ብዙ ነገሮች በኅሊናየ ይመጡ ነበር፡፡

H#ለት መቶኛ የነጻነት በዓሏን በቅርቡ ያከበረችውን ቺሊን ለመጀመርያ ጊዜ ያወቅኳት በአሥራ አንደኛ ክፍል የታሪክ መጽሐፍ ስለ ቺሊ አብዮት ስንማር ነው፡፡ በዓለም ላይ አሥቸጋሪ የሆነ ሶሻሊስታዊ ሥርዓት ተዘርግቶባቸው ከነበሩ ሀገሮች አንዷ ነበረች ቺሊ፡፡ ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የገባቸው በቅርቡ ነው፡፡

መጀመርያ ነገር የሚደነቀው የቺሊ መንግሥት እውነታውን ተገንዝቦ የወሰደው ርምጃ ነው፡፡ ችግሩን ከመሸፋፈን እና አልተደረገም ብሎ ከመካድ ይልቅ የሆነውን ነገር ተገንዝቦ ለቺሊ ሕዝብ እና ለዓለም ገልጾ፣ የሚቻለው ነገር ሁሉ እንደሚደረግ ቃል ገባ፡፡ ከምድር ወለል 622 ሜትር ርቀው ለነበሩት የማዕድን ሠራተኞች ፕሬዚዳንቱ ቀርበው የሆነውን ነገሯቸው፤ ቃላቸውን ሰሟቸው፤ አጽናኗቸው፤ ጥቂት ጊዜ ይፈጃልና አይዟችሁ አሏቸው፡፡

መንግሥት የፕሬስ ማዕከል በአካባቢው አቋቁሞ በየሰዓቱ እየሆነ ያለውን በግልጽ ይናገር ነበር፡፡ ምን እንደተደረገ፣ ምን እንደታሰበ፣ ከጉድጓዱ ውስጥ ያሉት ሠራተኞች ምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንዳሉ የቺሊ ሕዝብ እና ዓለም በየጊዜው በቂ መረጃ ያገኝ ነበር፡፡ ተደብቆ የሚፈለግ፣ ተሸሽጎ የሚጋለጥ፣ ባለ ሥልጣን ብቻ የሚያውቀው፣ ሕዝብ የሚያጉረመርምበት መረጃ አልነበረም፡፡ እንዲያውም የቺሊ መንግሥት ምናልባት 30 ጋዜጠኞችን ነበር የጠበቀው፡፡ ነገር ግን ከ2000 በላይ ጋዜጠኞች አካባቢውን በመሣርያ ዎቻቸው አጥረውት ነበር የከረሙት፡፡

ሰውን ከመርዝ በላይ የሚገድለው ተስፋ መቁረጥ ነው፡፡ ከምድር ወለል ርቀው የነበሩት እነዚያ የማዕድን ሠራተኞች ስንቃቸው ተስፋ ነበረ፡፡ በየጊዜው በሚላክላቸው መልእክት አማካኝነት ተስፋቸው ይለመልም ነበር፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በጸሎት እና በቃለ እግዚአብሔር አማካኝነት ትልቅ መጽናናትን እንዳገኙ ተናግረዋል፡፡ የሲ ኤን ኤን ጋዜጠኛ እንዳለው «ምናልባት አስቸኳይ የሕክምና ርዳታ የሚፈልግ ሰው ቢኖር ኖሮስ፣ የልብ ድካምን የመሰለ ችግር ቢከሰት ኖሮስ፣ ቀዶ ጥገና የሚያስፈልገው ነገር ተከስቶስ ቢሆን» መልሱ አንድ ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰምቷል፡፡

የዋሻ መደርመሱ ከመድረሱ በፊት የፈረቃ መሪ የነበረው ሉዊስ ኡርዝዋ ያከናወነውን ነገር አስቡት፡፡ እያንዳንዱን የማዕድን ሠራተኛ በሦስት ፈረቃ ከፍሎ በማስተባበር፣ ሥራ በመስጠት፣ አመጋገባቸውን እና የጤና አጠባበቃቸውን በመምራት፣ ተስፋቸው እንዲለመልም በማድረግ፣ በውጭ ከነበሩት የነፍስ አድን ሠራተኞች ጋር በየጊዜው እየተገናኘ በመሥራት፣ ያከናወነው የመሪነት ተግባር፡፡

መሪ ማለት ይህ ነው፡፡ ሕዝቡን ከመከራ የሚያወጣ፡፡ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሳይጨነቅ፣ ተስፋ ሳይቆርጥ፣ አእምሮውን ሳያጣ፣ ሳይረበሽ እና ሳይርበተበት መፍትሔ የሚያስብ፡፡ ከደረሰው ችግር ይልቅ ሊመጣ የሚገባውን መፍትሔ የሚያስብ፡፡ ተረጋግቶ የሚያረጋጋ፤ ወስኖ የሚያስወስን፤ ጸንቶ የሚያጸና፡፡ ብርሃን አይቶ የሚያሳይ፡፡

ሉዊስ ኡርዝዋ ከሁሉም በመጨረሻ ነው የወጣው፡፡ መሪ ማለት ይኼ ነው፡፡ ራሱን ለሚመራቸው ሰዎች የሚሠዋ፤ ለመከራ ራሱን ለጥቅም ሌሎችን የሚያስቀድም፡፡ መሪ እረኛ ነው፤ መሪ አባት ነው፤ መሪ ሩኅሩኅ ነው፡፡ ሕዝቡን ስለ ራሱ ሳይሆን ራሱን ስለ ሕዝቡ የሚሠዋ፡፡ እኔ አለቃችሁ ነኝ፤ ብዙ ነገር የሠራሁ ነኝ፣ ብዙ የደከምኩ ነኝ ስለዚህ ቅድሚያ ይገባኛል አላለም፡፡ ሁሉም ወዳጆቹ ወጥተው ካልተጠናቀቁ ዕረፍት እንደማ ይኖረው አስቧል፡፡ እናም

መጨረሻ ወጣ፡፡ ፕሬዜዳንቱ «ሉዊስ ዛሬ የሺፍት መሪነትህ ሥራ ተጠናቀቀ፤ መርተሃል፣ አስተባብረሃል፣ መሥዋዕትነት ከፍለሃል፤ አሁን ጨርሰሃል፤ መሪ ማለት አንተ ነህ» ነበር ያሉት፡፡

ይህ አጋጣሚ ቺሊያውያን እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው የታዩበት ነው፡፡ ወታደሮች፣ ጋዜጠኞች፣ ካህናት፣ ሐኪሞች፣ መሐንዲሶች፣ መሪዎች፣ ሁሉም ለአንዲት ሀገር የሚጠበቅባቸውን አደረጉ፡፡ ለቺሊ «የበረከት መከራ» ነው የሆነላት፡፡ መሪዎቿ ይህንን መጥፎ አጋጣሚ የሕዝቡን አንድነት፣ ጽናት፣ ሀገራዊ ስሜት፣ መተሳሰብ እና መቀራረብ ለማምጣት ተጠቅመውበታል፡፡ ከሕዝባቸው ጋር በመሥራት ፍቅራቸውን እና ክብራቸውን አሳይተዋል፡፡

ሠላሳ ሦስት የማዕድን ሠራተኞች ብቻ ሳይሆኑ ቺሊያውያን በጠቅላላው ከመሬት መንቀጥቀጡ በኋላ ከነበሩበት የመከራ ጉድጓድ ወጥተዋል፡፡ ፕሬዚዳንት ፔኔራ «ቺሊ ከ69 ቀናት በፊት በነበረችበት ሁኔታ ላይ አይደለችም፤ ሌላ ሀገር ሆናለች» እንዳሉት፡፡

የሚገርሙ ፕሬዚዳንት ናቸው፡፡ የማውጣቱን ዕቅድ መርተዋል፤ ተከታትለዋል፤ በመጨረሻም ከመጀመርያው ሰዓት ጀምረው በቦታው ተገኝተው ጸልየዋል፣ አልቅሰዋል፣ ተደስተዋል፤ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ እንደ አባት ሁሉን አቀፉ፡፡ እንደ መሪ ተከታተሉ፣ እንደ ዜጋ ዘመሩ፣ እንደ መንፈሳዊ ጸለዩ፣ እንደ ሰው አነቡ፡፡ ሁኔታውን በስልክ ወይንም በሪፖርት አይደለም የተከታተሉት፤ ስብሰባ ላይ ወይንም በዓል ላይ አልነበሩም፤ እንደ ሠራተኞቹ ልብሳቸውን ለብሰው በቦታው ነበሩ፡፡ ለ22 ሰዓታት ያህል በቦታው ቆመው እያንዳንዱ የማዕድን ሠራተኛ ሲወጣ ጨብጠውታል፣ አቅፈውታል፣ ስመውታል፣ አበረታተውታል፡፡

ከሠራተኞቹ ጋር ሲያወሩ፣ ከቤተሰቦች ጋር ሲመካከሩ፣ ሲስቁ እና ሲጫወቱ ላየ ፕሬዚዳንት አይመስሉም ነበር፡፡ እኔ ፍርሃት ሳይሆን አክብሮት፣ በሕዝብ እና በመሪ መካከል ርቀት ሳይሆን ፍቅር ነበር ያየሁት፡፡

የተቀበሩትን የማዕድን ሠራተኞች የማውጣቱ ሂደት የተጀመረው በስብሰባ አይደለም፡፡ በጸሎት ነው፡፡ ሕዝቡ ሁሉ ልቡናውን አቅንቶ ጸልዮአል፡፡ መሪዎች እና ሕዝብ እንደ ነነዌ ሰዎች አንድ ሆነው የእግዚአብሔርን ረድኤት ጠይቀዋል፡፡ የለመኑትን የማይነሣ፣ የነገሩትን የማይረሳ አምላክም ረድቷቸዋል፡፡ ለዚህም ነበር ፕሬዚዳንት ፔኔራ «እግዚአብሔር ባይረዳን ኖሮ» ያሉት፡፡

ሕዝብ እግዚአብሔርን ሲያስቀድም፤ መሪዎች ከእግዚአብሔር ረድኤት ሲጠይቁ፤ ቅድሚያውን ለፈቃደ እግዚአብሔር ሲሰጡ፡፡ ስሙን በክብር ሲጠሩ እና ሲያመሰግኑ መስማት ያስቀናል፡፡ በእውነቱ የቺሊያውያንን ጸሎት የሰማ እኛንም ይስማን፡፡

ለቤተሰቦቻቸው የተሰጠው ቦታ የሚገርም ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች እዚያ ዋሻ ውስጥ የቀሩት ሀገራቸውን ሲያገለግሉ ነው፡፡ የተከበሩ ዜጎች ናቸው፡፡ እነርሱን ያፈሩ፣ የተንከባከቡ እና የነፍሳቸው ቁራጭ የሆኑ ቤተሰቦቻቸው ክቡራን ናቸው፡፡ ቦታ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ከመጀመርያው ጀምሮ መረጃ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ የማውጣቱ ሥራ ሲጀመር በቦታው ተገኝተው አይተዋል፡፡ ወዳጆቻቸው ከጉድጓዱ ሲወጡ በእንባ ተቀብለዋቸዋል፡፡ የሀገር መሠረቱ ቤተሰብ ነውና ተገቢውን ቦታ አግኝተዋል፡፡

«ቺሊያውያን በመሆናችን ኩራን» ነበር የሚሉት ቺሊዎች በየጎዳናው፡፡ ለምን አይኮሩ፡፡ አገር አንድ ሆኖ ሥራ ሲሠሩ አዩ፡፡ የሠላሳ ሦስት ሰዎች ጉዳይ ጉዳያችን አይደለም የሚለውን ከመሪዎቻቸው አልሰሙም፡፡ ታሪክን በአይናቸው እንጂ በሪፖርት አልሰሙም፡፡ ክፉ እና ደጉን ከመሪዎቻቸው ጋር ተካፈሉ፤ በመሬት መንቀጥቀጥ የተጎዳው ልባቸው በታሪካዊው ሥራቸው ተጠገነ፡፡ ከተለመደው ዓለም ርቃ በላቲን አሜሪካ ደቡብ ጥግ ያለችው ቺሊ በዓለም ሕዝቦች ልብ ውስጥ ገባች፡፡

ከተቻለ ችግር አይምጣ፤ ከመጣም በሚጠቅመን እና በሚያፋቅረን መንገድ እንወጣው፤ ደግሞም እንማርበት፡፡ ፕሬዚዳንት ፔኔራ «ካለፈው ትምህርት ወስደናል፤ በቀጣይ የማዕድን አወጣጥ መንገዳችንን እንፈትሻለን፤ እናስተካክክላለን» ነበር ያሉት፡፡ የ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያዊው ፈላስፋ ዘርዐ ያዕቆብ «ስሕተት ባይኖር ኖሮ ሰው እንዴ ይሻሻል ነበር» እንዳለው ለተማረበት ስሕተት የዕድገት እና የለውጥ መነሻ ይሆናል፡፡ ሲሸፋፍነው የሚኖር ግን ጠባዩ እስኪመስል ድረስ ይደጋግመዋል፡፡

ሌሎችን ወደ ላይ ለማውጣት ስድስት ባለሞያዎች ወደ ታች ወረዱ፡፡ ከፍ ለማድረግ ዝቅ አሉ፡፡ ሠላሳ ሦስቱን የማዕድን አውጭዎች አውጥተው ሲጨርሱ እነርሱ ጉድጓዱ ውስጥ ነበሩ፡፡ የተላኩበትን ተግባር ሲፈጽሙ mission Cumplida አሉ፡፡ እኛስ? አላሉም፡፡ እነርሱ ሌሎችን እንደረዱ ሁሉ ያመኑት እግዚአብሔር እነርሱን አይረዳም እንዴ፡፡

# [አንድነት ይቅርብን]

ብዙ ጊዜ ለኢትዮጵያውያን ችግራችን አንድ ያለመሆን ነው፤ ልዩነቶቻችንን ትተን አንድ እንሁን፤ አንድነት ኃይል ነው ወዘተ እያልን ጩኸናል፤ አስተምረናል፤ ጽፈናል፤ አንብበናል፤ አዚመናል፤ ሰብከናል፡፡ አሁን አሁን ግን ሳስበው እንዲያውም ችግራችን አንድ ከመሆን የመጣ ነው የሚመስለኝ፡፡ እንዲያውም ሀገራችንን አሁን ለደረሰችበት ውድቀት የዳረጋት አንድ መሆናችን ነው፡፡ ደግሞ መች ተለያይተን እናውቃለን? መች ልዩነት አለ በመካከላችን? ሁላችንም እንደ አህያ ጆሮ እንደ ጦር ጉሮሮ አንድ አይደለን እንዴ፡፡

ለመሆኑ እኛ ኢትዮጵያውያን የተለያየነው በምን በምንድን ነው? በዘር? በሃይማኖት? በፖለቲካ? በአመለካከት? በምንም፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ከጥንት ጀምሮ የሚሠራው ፊልም አንድ ዓይነት ነው፡፡ ተዋንያኑ ግን በየጊዜው ይለያያሉ፡፡ ፊልሙ የሚሠራበት ቦታ እና ቋንቋ ግን ይለያያል፡፡ አንዳንዶቹ ያንኑ ፊልም በሚገባ ይሠሩታል፤ ይዋጣላቸዋል፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ፊልሙን በበቂ ሁኔታ አይተውኑትም፡፡ በዚያም ተባለ በዚህ ግን በፊልሙ አንድ ነን፡፡ በፊልሙ ውስጥ መገዳደል፤ መጨራረስ፣ አምባገነንነት፣ እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን፣ጠባብነት፣ ጎጠኛነት ወዘተ አሉበት፡፡

ፊልሙ በአማርኛም ተሠራ በኦሮምኛ፤ በትግርኛም ተሠራ በሶማልኛ፤ በአፋርኛም ተሠራ በወላይትኛ፣ በሐረሪኛም ተሠራ በሲዳምኛ የፊልሙ ስክሪፕት ያው ነው፡፡ የማጀቢያ ዜማውም «ኧረ ጎራው ኧረ ደኑ፤ ግደል ግደል አለኝ፤ የሚቃወምህን አጥፋው አጥፋው አለኝ፤ ካንተ ሌላ ሃሳብ አትስማ አትስማ አለኝ´፤ የሚለው የጥንቱ ዘፈን ነው፡፡

ታድያ ኢትዮጵያውያን አንድ ዓይነት ፊልም እየሠሩ እንዴት ነው የሚለያዩት? ኧረ አንድ ናቸው፡፡

ለመሆኑ የዘር ልዩነት አለን እንዴ? ሁላችንም ከምናውቃት ቋንቋ በላይ መስማት አንፈልግም፤ ስለሌላው ዘር የሚያንቋሽሹ ቃላት በሁላችንም መዝገበ ቃላት ውስጥ አሉ፤ የተናቁ እና የተዋረዱ ማኅበረሰቦች በየዘራችን አሉ፤ ገድለን ጀግና የምንሆንባቸው ማኅበረሰቦች በየጎሳችን አሉ፤ ሁላችንም ጎሳዎቻችንን ብቻ የሚወክሉ ፓርቲዎች አሉን፤ ሁላችንም ጎሳዎቻችንን ነጻ ለማውጣት እንታገላለን፤ ሁላችንም ተጨቁነናል፤ ታድያ አሁን እኛ በዘር ተለያይተናል? ምኑ ላይ ነው ልዩነታችን? አንድ ዘር እኮ ነን፡፡

አሁን እኛ በፖለቲካ ተለያይተናል? ለመሆኑ ምንድን ነው የለየን? ሁላችንም «ሌላ ድምፅ አልሰማም ከንግዲህ በኋላ´ አይደል እንዴ የምንለው፡፡ የገዥ ፓርቲ መሪዎችም አይለወጡም፤ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችም አይቀየሩም፤ ፖሊት ቢሮ፤ ማዕከላዊ ኮሚቴ፤ ጠቅላላ ጉባኤ፤ በሁሉም ዘንድ አሉ፤ ለምሳሌ በቅርቡ በአምስተርዳም የአቶ መለስ ዜናዊ ምስል ያለበትን ቲሸርት የለበሰ ሰው በኢትዮጵያውያን መደብ ደቡ እንደ ትልቅ የድል ዜና ሲነገር ነበር፡፡ ታድያ ገዥው ፓርቲ እኛን ከዚህ እና ከዚያ ከለከለን ብሎ መናገር እንዴት ይቻላል? ልዩነታችንስ ከምኑ ላይ ነው? እኔ ልሙት አንድ ነን፡፡

እዚያ ኢሳት ተከለከለ ብለን ሰልፍ እንወጣለን፤ እዚህ የእነ እገሌን ሬዲዮ አትስማ፤ ቴሌቭዥናቸውን አትይ፣ እንጀራቸውን አትግዛ እንላለን፤ እዚያ 99 በመቶ የሚያሸንፍ አለ፤ እዚህም 99 በመቶ የሚያሸንፍ አለ፡፡ ሁሉም ተቃራኒ ሳይሆን ጠላት አለው፡፡ ሁሉም ጠላቱን ለማውደም ተነሥቷል፡፡ አሁንም «እገሌ ያሸንፋል´ ብለን እንፎክራለን፡፡ ታድያ በምንድን ነው ልዩነታችን? ኧረ አንድ ነን፡፡

ማነው ለመሆኑ ይኼ ኢትዮጵያውያን ተለያይተዋል እያለ የሚያሟርትብን፡፡ ባያውቀን ነው እንጂ እኛስ ተለያይተን አናውቅም፡፡ አሁን እኛ ተለያይተናል? ስንት ሰው አለ እባካችሁ ያላየውን የሚያወራ፡፡

በውጭ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ገለልተኛ፣ ስደተኛ፣ የሀገር ቤት እያሉ ተለያይተዋል ብሎ የሚያማን ሰው ምን የተረገመ ነው፡፡ አሁን በኛ መካከል እንዲህ ያለ ልዩነት አለ? ሁሉም ጳጳስ ይፈልጋሉ፤ ሁሉም ግን በጳጳስ መታዘዝ አይፈልጉም፡፡ ሁሉም በስም የተለያዩ መስለው ለመንግሥት ባስገቡት ደንብ ግን አንድ ናቸው፡፡ ሁሉም የተለያየ ስም ነገር ግን አንድ ዓይነት ግብር ያለው ቦርድ አላቸው፡፡ ሁሉም ዋናው ገቢው ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ሁሉም ጋ የሚፈልጡ የሚቆርጡ ወይዛዝርት፤ የሚያዝዙ የሚናዝዙ መኳንንት፤ የሚከታተሉ የሚቆጣጠሩ ፖለቲከኞች፤ የሚፈሩ፣ ለሥጋ የሚያድሩ አገልጋዮች፤ አሉ፡፡ ታድያ በምን ተለያይተን ነው ተለያዩ እያሉ የሚያሟርቱብን፡፡

ለእነዚህ ገብርኤል የጎንደር ነው፤ ለእነዚያ አቡነ አረጋዊ የትግሬ ናቸው፤ ለእነዚህ ማርያም የሸዋ ናት፤ ለእነዚያ ደግሞ ሥላሴ የጎጃም ናቸው፤ ለወዲህኞቹ ሚካኤል የደቡብ ነው፤ ታቦቶቻችን ሁሉ ዘር እና ጎጥ አላቸው፡፡ ታድያ በዚህ ሁሉ አንድ ሆነን ሳለን እንዴት ተለያይተዋል እንባላለን፡፡ ይህንን የሚሉን የኛን ክፉ የሚመኙ ብቻ ናቸው፡፡

ፕሮቴስታንቶቹስ ቢሆኑ እዚህ ጌታ የወለጋ ነው፤ እዚያ የአማራ ነው፤ ወዲያ የትግራይ ነው፤ እልፍ ሲል የወላይታ ነው፤ ሲመለስ የሲዳማ ነው፤ ታድያ ሁላችንም ቢሆን ጌታን እንደ የብሔረሰባችን ተቀብለነዋል፤ ደግሞም ሁላችንም በብሔረሰባችን ቋንቋ ብቻ በመዘመር እና በመስበክ እናምናለን፤ ሁላችንም ጌታ ከኛ ቋንቋ ውጭ አይሰማም ብለን እናምናለን፤ ሁላችንም ፓስተሮቻችን ሲጣሉ ለሁለት ተከፍሎ የየራሳቸው ቸርች በመመሥረት እናምናለን፤ ሁላችንም ሌላውን ወንጌል ያልገባው መሆኑን አጥብቀን እንመሰክራለን፤ ታድያ ይህንን የመሰለ አንድነት እያለን እንዴት ተለያይተዋል እንባላለን፡፡

ሙስሊሞችና ክርስቲያኖችስ ቢሆኑ መች ተለያዩ፡፡ ይኼ የጠላት ወሬ ነው፡፡ እነዚያ ሀገሪቱን በመስጊድ በማጥለቅለቅ፤ እነዚህም በቤተ ክርስቲያን በማጥለቅለቅ ያምናሉ፡፡ እነዚያም በኃይለኛ ማይክራፎን አዛኑን በመልቀቅ፣ እነዚህም ቅዳሴውን በኃይለኛ ማይክራፎን በማስማት ያምናሉ፡፡ ሁለቱም ከመወያየት ይልቅ መፋጠጥን፣ መልስ መሰጣጣትን ይመርጣሉ፡፡ ሁለቱም ከጥራት ይልቅ ለቁጥር ይጨነቃሉ፡፡ ሁለቱም ለአምላካቸው በመታየት ሳይሆን ለሕዝብ በመታየት ይስማማሉ፡፡ ታድያ ይህንን የመሰለ አንድነት እያለ ምኑን ተለያየነው፡፡

ምሁሮቻችን ያላቸው አንድነት የሚገርም ነው፡፡ ሕዝብ በሚያውቀው ቋንቋ ባለመጻፍ፤ በውጭ ሀገር እንጂ በሀገር ውስጥ የጥናት ወረቀት ባለማሳተም፤ በአካዳሚያዊ ክበቡ ውስጥ እንጂ በሕዝቡ ዘንድ ባለመታወቅ፤ በወረቀት እንጂ በሥራ ባለማመን፤ ከአባትነት ይልቅ በገዥነት መንፈስ በመመራት፤ ከመመሰጋገን ይልቅ በመተቻቸት በማመን፤ ምሁራዊ ዘረኛነትን በማስፋፋት፤ ምሁሮቻችን አንድ አይደሉ እንዴ፡፡ ማን ነው በመካከላቸው መለያየት አለ እያለ ያላየውን የሚያወራ፡፡ ወሬኛ፡፡

አንድነት ሰለቸን፡፡ እስኪ ደግሞ እንለያይ፡፡ የተለያየ አመለካከት፣ የዕውቀት ደረጃ፤ የአሠራር መንገድ፤ የችግር አፈታት መንገድ፤ የዕድገት መንገድ፤ የመረጃ መንገድ እስኪ ይኑረን፡፡ በቋንቋ፣ በባህል፣ በአመጋገብ ብቻ ሳይሆን በሌላውም እስኪ እንለያይ፡፡ የተለያየ የፊልም ስክሪፕት፣ የተለያዩ ተዋንያን፣ የተለየ የፊልም ጭብጥ፣ የተለየ እመርታ ያለው ፊልም እስኪ ይኑረን፡፡ አንድ ዓይነት ፊልም ሰለቸን፡፡

እስኪ የተለየ ልቦለድ እንጻፍ፡፡ መቼት፣ ትረካ፣ ግጭት፣ ዐጽመ ታሪክ፣ አላባውያን፣ ገጸ ባሕርያት ከሚለው የተለየ የለም እንዴ? እስኪ እንለያይ እነዚህ የሌሉት ወይንም ደግሞ ሌሎች ነገሮች ያሉት ልቦለድ መጻፍ አይቻልም እንዴ?

አንድነት አልጠቀመንም፡፡ ዓለም የተጠቀመው ተለያይቶ ነው፡፡ ፓርላማው ይለያይ፤ ካቢኔው ይለያይ፤ሲኖዶሶ ይለያይ፤ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤቱ ይለያይ፤ የወጣት፣ የሴት ማኅበራቱ ይለያዩ፡፡ የሞያ ማኅበራቱ ይለያዩ፡፡ በውስጣቸው ያሉ አባላቱ የተለያየ ሃሳብ፣ አመለካከት፣ አቅጣጫ፣ የዕውቀት ስብጥር፣ ዳራ፣ ይኑራቸው፡፡ይፋጩ፡፡ ተፋጭተው ተፋጭተው እንደ ብረት ተስለው የሰላ ሃሳብ ያውጡ፡፡ ምሁራኑም ይለያዩ ስለ አንድ ጉዳይ ከተለያየ አቅጣጫ ይናገሩ፣ ይጻፉ፣ ይተቹ፣ ያበጥሩ፣ ያንጠርጥሩ፡፡ አዳዲስ አካሄድ ያሳዩ፡፡ አይስማሙ፤ መስማማት የግድ አይጠበቅባቸውም፡፡ እንዲያውም ይለያዩ፡፡ የተለያየ መረጃ፣ የተለያየ ዘዴ፣ የተለያየ ግኝት ነው የምንፈልገው፡፡

የእምነት ተቋማቱም ይለያዩ፡፡ በአሠራር፣ በችግር አፈታት፣ በማስተማርያ መንገድ፣ በምእመናን አያያዝ፣ ለሀገር በሚያበረክቱት አስተዋጽዖ፤ በአሠራር ማሻሻያ፣ በመሪዎች አመራረጥ፣ ሙስናን እና ብኩንነትን በመዋጊያ መንገድ፣ በግልጽነት እና ተጠያቂነት ማስፈኛ መንገዶች ይለያዩ፡፡ ይበላለጡ፤ ይቀዳደሙ፡፡ ያን ጊዜ አንዱ ከሌላው ሃይማኖት ባይማርም አሠራር ይማራል፤ ጥበብ ይማራል፡፡ እንደ ኮካ ኮላ ጠርሙስ አንድ ከመሆን አምላክ ይታደጋቸው፡፡

እስካሁን አንድ ሆነን አይተነዋል፡፡ እስኪ ደግሞ ተለያይተን እንሞክረው፡፡ አንድነት ኃይል ነው የሚለው ይቀየርና ልዩነት ኃይል ነው ብለን እንነሣ፡፡

***ሎስ አንጀለስ፣ ዩ ኤስ ኤ***

## መስቀሉ የት ነው ያለው?

በእምነት ታሪክ ውስጥ የታሪክ፣ የአርኬዎሎጂ እና የቅርስ ጥናት ሰዎችን ያስጨነቁ ሁለት ጥያቄዎች አሉ፡፡ ታቦተ ጽዮን እና ጌታ የተሰቀለበት መስቀል የት ነው ያሉት? የሚሉት ጥያቄዎች፡፡ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ አሰሳዎች፣ ቁፋሮዎች፣ መዛግብትን የማመሳከር ሥራዎች፣ አሉ የተባሉ የይዞታ ጥያቄዎችን የመመርመር ፍተሻዎች በመካሄድ ላይ ናቸው፡፡ በጣም የሚገርመው ነገር ግን የዓለም ቅርሶች መናኸርያ የሆነችው ኢትዮጵያ ሁለቱንም በተመለከተ ለዓለም የምትገልጣቸው ነገሮች አሏት፡፡

ሰሞኑን በሀገራችን ኢትዮጵያ የመስቀል በዓል በመከበር ላይ በመሆኑ «ለመሆኑ ጌታ የተሰቀለበት መስቀል የት ነው ያለው?» የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ያሉ መረጃዎችን እንቃኝ፡፡

**የመስቀሉ መጥፋት**

በአብያተ ክርስቲያናት ከሚነገረው ትውፊት በስተቀር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሎት የነበረው መስቀል እንዴት ሊጠፋ እንደቻለ የተመዘገበ ታሪክ እኔ አላገኘሁም፡፡ አብዛኞቹ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ግን አይሁድ በመስቀሉ ላይ ይደረግ የነበረውን ተአምራት በመቃወም ከክርስቲያኖች ነጥቀው እንደ ቀበሩት ይተርካሉ፡፡ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊው አውሳብዮስ የቆስጠንጢኖስ የሕይወት ታሪክ /Life of Constantine/ በተሰኘው መጽሐፉ ላይ በክርስቲያኖች ዘንድ ታላቅ ሥፍራ የነበረው የጌታ መቃብር ተደፍኖ በላዩ ላይ የቬነስ ቤተ ጣዖት ተሠርቶ እንደ ነበር ይናገራል፡፡ አውሳብዮስ በዝርዝር አይግለጠው እንጂ ይህ የቬነስን ቤተ መቅደስ በጎልጎታ ላይ የመሥራቱ ጉዳይ የሮሙ ንጉሥ ሐድርያን በ135 ዓም ኢየሩሳሌምን Aelia Capitolina አድርጎ እንደ ገና ለመገንባት የነበረው ዕቅድ አካል ነው፡፡

አይሁድ በሮማውያን ላይ እስከ ዐመጹበት እና ኢየሩሳሌም ከክርስትና በኋላ ለመጀመርያ ጊዜ እስከ ጠፋችበት እስከ 70 ዓም ድረስ መስቀሉ በክርስቲያኖች እጅ እንደ ነበር ይታመናል፡፡ በኋላ ግን ክርስቲያኖቹ የሮማውያንን እና የአይሁድን ጦርነት በመሸሽ ከኢየሩሳሌም ወጥተው ወደ ሌሎች ሀገሮች ሲሰደዱ፤ በኋላም በባር ኮባ ዐመፅ ጊዜ /132-135 ዓም/ ኢየሩሳሌም ፈጽማ በሮማውያን ስትደመሰስ የመስቀሉ እና የሌሎችም ክርስቲያናዊ ንዋያት እና ቅርሶች ነገር በዚያው ተረስቶ ቀረ፡፡ ንጉሥ ሐድርያንም የኢየሩሳሌም ከተማን ነባር መልክ በሚለውጥ ሁኔታ እንደ

ገና ሠራት፡፡ ያን ጊዜ ነው እንግዲህ የቬነስ ቤተ መቅደስ በጌታችን መቃብር ላይ የተገነባው፡፡ ቆስጠንጢኖስ ለኢየሩሳሌሙ ኤጲስ ቆጶስ ለአቡነ መቃርዮስ በጻፈው እና ሶቅራጥስ እና አውሳብዮስ መዘግበው ባቆዩን ደብዳቤ ላይ ይህ ታሪክ ተገልጧል፡፡

ቀጣዮቹ 300 ዓመታት ለክርስቲያኖች የመከራ ጊዜያት ነበሩ፡፡ የሮም ቄሳሮች ክርስትናን እና ክርስቲያኖችን የሚያሳድዱባቸው ዓመታት በመሆናቸው መስቀሉን የመፈለግ ጉዳይ በልቡና እንጂ በተግባር ሊታሰብ አይችልም፡፡ ዓመታት እያለፉ ሲሄዱም ኢየሩሳሌም እየተዘበራረቀች እና የጥንት መልኳ እየተቀየረ በመሄዱ በጌታ መቃብር ላይም የሮማ አማልክትን ለማክበር ቤተ መቅደስ በመሠራቱ ነገሩ ሁሉ አስቸጋሪ እየሆነ ሄደ፡፡

**የመስቀሉ እንደገና መገኘት**

ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች መስቀሉን እንደገና ያገኘችው ንግሥት ዕሌኒ መሆንዋን ይናገራሉ፡፡ በ380 ዓም አካባቢ የተወለደው ታሪክ ጸሐፊው ሶቅራጥስ Ecclesiastical History በተሰኘው መጽሐፉ ላይ በምእራፍ 17 መስቀሉ እንዴት እንደ ተገኘ ዝርዝር መረጃ ይሰጠናል፡፡ ንግሥት ዕሌኒ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዛ በጎልጎታ የጌታ መቃብር ላይ የተሠራውን የቬነስ ቤተ መቅደስ አፈረሰችው፤ ቦታውንም በሚገባ አስጠረገችው፡፡ በዚያን ጊዜም የጌታችን እና የሁለቱ ሽፍቶች መስቀሎች ተገኙ፡፡ ከመስቀ ሎቹም ጋር ጲላጦስ የጻፈው የራስጌው መግለጫ አብሮ ተገኘ፡፡

ሶቅራጥስ ከሦስቱ መስቀሎች አንዱ የክርስቶስ መሆኑን እንዴት ሊታወቅ እንደቻለ ሲገልጥ እንዲህ ይላል «አቡነ መቃርዮስ በማይድን በሽታ ተይዛ ልትሞት የደረሰችን አንዲት የተከበረች ሴት አመጡ፡፡ ሁለቱን መስቀሎችንም አስነኳት፤ ነገር ግን ልትድን አልቻለችም፤ በመጨረሻ ሦስተኛውን መስቀል ስትነካ ድና እና በርትታ ተነሣች፡፡ በዚህም የጌታ መስቀል የትኛው እንደሆነ ታወቀ» ይላል፡፡ ከዚያም ንግሥት ዕሌኒ በጌታ መቃብር ላይ ቤተ ክርስቲያን አሠራች፡፡ ከመስቀሉ የተወሰነውን ክፍል ከፍላ ከችንካሮቹ ጋር ወደ ቁስጥንጥንያ ስትወስደው ዋናውን ክፍል በጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ተወችው፡፡

ይህንን ታሪክ ሄርምያስ ሶዞሜን የተባለው እና በ450 ዓም አካባቢ ያረፈው ታሪክ ጸሐፊም Ecclesiastical History, በተሰኘው ጥንታዊ መጽሐፉ በክፍል ሁለት ምእራፍ አንድ ላይ ይተርከዋል፡፡ ዞሲማን እንደሚለው በ325 ዓም የተደረገው ጉባኤ ኒቂያ ሲጠናቀቅ የቆስጠንጢኖስ ትኩረት ወደ ኢየሩሳሌም ዞረ፡፡

ምንም እንኳን ሶዞሜን ባይቀበለውም መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ያመለከተው ከከተማዋ በስተ ምሥራቅ ይኖር የነበረ አንድ አይሁዳዊ መሆኑን እና እርሱም ይህንን መረጃ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ከነበረ መዝገብ ማግኘቱን እንደ ሰማ ጽፏል፡፡ ንግሥት ዕሌኒ ባደረገችው አስቸጋሪ ቁፋሮ መጀመርያ ጌታ የተቀበረበት ዋሻ፤ ቀጥሎም ከእርሱ እልፍ ብሎ ሦስቱ መስቀሎች መገኘታቸውን ሶዞሜን ይተርካል፡፡ ከመስቀሎቹም ጋር የጲላጦስ ጽሑፍ አብሮ መገኘቱን እና የጌታ መስቀል ከሌሎች የተለየበትን ሁኔታ ከሶቅራጥስ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ይተርከዋል፡፡

ንግሥት ዕሌኒ በጎልጎታ፣ በቤተልሔም፣ በደብረ ዘይት፣ አብያተ ክርስቲያናትን አሠርታ በሰማንያ ዓመቷ እንዳረፈች ሶዞሜን ይተርካል፡፡ ብዙ የታክ ጸሐፊዎች ዕረፍቷን በ328 ዓም አካባቢ መስቀሉ የተገኘ በትንም በ326 ዓም ያደርጉታል፡፡

በ457 ዓም አካባቢ ያረፈው ቴዎዶሮት የተባለው ታሪክ ጸሐፊም የመስቀሉን የመገኘት ታሪክ ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ያቀርበዋል፡፡

**መስቀሉ በኢየሩሳሌም**

ንግሥት ዕሌኒ ለበረከት ያህል የተወሰነ ክፍል ወደ ቁስጥንጥንያ ከመውሰዷ በቀር አብዛኛውን የመስቀሉን ክፍል በብር በተሠራ መሸፈኛ አድርጋ በጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን እንዲቀመጥ ለአቡነ መቃርዮስ ሰጥታቸዋለች፡፡ ይህ መስቀል በየተወሰነ ጊዜ እየወጣ ለምእመናኑ ይታይ እንደ ነበር አንዳንድ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በ380 ዓም ኤገርያ የተባለች ተሳላሚ መነኩሲት ቅዱስ መስቀሉ ወጥቶ በተከበረበት በዓል ላይ ተገኝታ ያየችውን ለመጣችበት ገዳም ጽፋ ነበር፡፡ /M.L. McClure and C. L. Feltoe, ed. and trans. The Pilgrimage of Etheria, Society for Promoting Christian Knowledge, London, (1919)/

አንዳንድ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የመስቀሉ ክፍልፋዮች ወደ ተለያዩ ሀገሮች መወሰድ የጀመሩት በዚህ ጊዜ ነው፡፡ በሞሪታንያ ቲክስተር በተባለ ቦታ የተገኘውና በ359 ዓም አካባቢ የተጻፈው መረጃ የመስቀሉ ክፍልፋዮች ቀደም ብለው ወደ ሌሎች ሀገሮች መግባት እንደ ጀመሩ ያሳያል፡፡ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም መስቀሉ ከተገኘ ከሃያ አምስት ዓመታት በኋላ በ348 ዓም በጻፈው አንድ ጽሑፍ ላይ «ዓለሙ በሙሉ በጌታችን መስቀል ክፍልፋዮች ተሞልቷል» በማለት ገልጦ ነበር፡፡ ከዚህም ጋር «ዕጸ መስቀሉ እየመሰከረ ነው፡፡ እስከ ዘመናችንም ድረስ ይኼው እየታየ ነው፡፡ ከዚህ ተነሥቶም በመላው ዓለም እየተሠራጨ ነው፡፡ በእምነት ክፍልፋዮቹን እየያዙ በሚሄዱ ሰዎች አማካኝነት» ብሏል፡፡/On the Ten Points of Doctrine, Colossians II. 8./

ዮሐንስ አፈ ወርቅም የመስቀሉን ቅንጣቶች ሰዎች በወርቅ በተሠራ መስቀል ውስጥ በማድረግ ምእመናን በአንገታቸው ላይ ያሥሩት እንደ ነበር ጽፏል፡፡ በዛሬዋ አልጄርያ በቁፋሮ የተገኙ ሁለት ጽሑፎች የመስቀሉ ክፍልፋዮች በ4ኛው መክዘ የነበራቸውን ክብር ይናገራሉ፡፡ /Duval, Yvette, Loca sanctorum Africae, Rome 1982, p.331-337 and 351-353/፡፡ በ455 ዓም በኢየሩሳሌም የነበረው ፓትርያርክ ለሮሙ ፖፕ ለልዮን የመስቀሉን ቁራጭ እንደ ላከለት ተመዝግቧል፡፡

በአውሮፓ ምድር የተዳረሰው አብዛኛው የመስቀሉ ክፍልፋይ የተገኘው ከባዛንታይን ነው፡፡ በ1204 ዓም በአራተኛው የመስቀል ጦርነት ጊዜ የዘመቻው ተካፋዮች በዓረቦች ጦር ድል ሲመቱ ፊታቸውን ወደ ቁስጥንጥንያ አዙረው ከተማዋን፣ አድባራቱን እና ገዳማቱን ዘረፏቸው፡፡ በዚያ ጊዜ ተዘርፈው ከሄዱት ሀብቶች አንዱ ዕሌኒ ከኢየሩሳሌም ያመጣችው የመስቀሉ ግማድ ነበር፡፡ ይህንን ግማድ እንደ ገና በመከፋፈል አብዛኞቹ የአውሮፓ አብያተ ክርስቲያናት ሊዳረሱት ችለዋል፡፡ የወቅቱን ታሪክ ከመዘገቡት አንዱ ሮበርት ዲ ክላሪ «በቤተ መቅደሱ ውስጥ አያሌ ውድ ንዋያት ይገኙ ነበር፡፡ ከእነዚህም መካከል ከጌታ መስቀል የተቆረጡ ሁለት ግማዶች ነበሩ፡፡ ውፍረታቸው የሰው እግር ያህላል፤ ቁመታቸውም ስድስት ጫማ ይህል ነበር» ብሏል፡፡ /Robert of Clari's account of the Fourth Crusade, chapter 82: OF THE MARVELS OF CONSTANTINOPLE/

**የመስቀሉ ለሁለተኛ ጊዜ መጥፋት**

እስከ ስድስተኛው መከዘ ድረስ በኢየሩሳሌም ኅልጎታ የነበረው መስቀል በ614 ዓም በፋርሱ ንጉሥ ክሮስረስ 2ኛ /Chrosroes II/ ተወሰደ፡፡ የፋርሱ ንጉስ ኢየሩሳሌምን በወረረ መስቀሉን እና ፓትርያርክ ዘካርያስን ማርኮ ወደ ፋርስ ወሰዳቸው፡፡ እንደ ገና ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሰው ሕርቃል በ627 ዓም ባደረገው ጦርነት ክሮስረስ ድል ሲሆን ነው፡፡ ሕርቃል በመጀመርያ ወደ ቁስጥንጥንያ ካመጣው በኋላ እንደ ገና ወደ ኢየሩሳሌም ወስዶ በቀድሞ ቦታው በጎልጎታ አስቀምጦት ነበር፡፡

እስከ አሥረኛው መከዘ ድረስ በኢየሩሳሌም በቀድሞ ክብሩ ቢቆይም ዐረቦች አካባቢውን እየተቆጣጠሩ ሲመጡ በኢየሩሳሌም የሚኖሩት ክርስቲያኖች መስቀሉን በ1009 ዓም አካባቢ ሠወሩት፡፡ ለ90 ዓመታት ያህል ያለበት ቦታ ተሠውሮ ከኖረ በኋላ በመጀመርያው የመስቀል ጦርነት ጊዜ በ1099 ዓም ከተሠወረበት ወጥቶ እንደ ቀድሞው መታየት ጀመረ፡፡

**ለሦስተኛ ጊዜ መጥፋት**

በ1187 ዓም በሐቲን ዐውደ ውጊያ ሳላሕዲን የተባለው የዓረቦች የጦር መሪ የመስቀል ጦረኞችን ድል አድርጎ ኢየሩሳሌምን ሲቆጣጠር በዚያ የነበረውን መስቀል መውሰዱን አንዳንድ የታሪክ መዛግብት ይገልጣሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ግን መስቀሉ የት እንዳለ እስካሁን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በወቅቱ የነበሩት የሮም ነገሥታት መስቀሉን ለማግኘት ከሳላሕዲን ጋር ብዙ ድርድር አድርገው ሳይሳካላቸው ቀርቷል፡፡

በአብዛኞቹ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የመስቀሉ ክፍልፋይ እንዳለ ሁሉም ይናገራሉ፡፡ አንዳንዶቹ አለ የሚባለው ክፍልፋይ ከመብዛቱ የተነሣ የሚያነሡት ትችት አለ፡፡ ጆን ካልቪን «ሁሉም ክፍልፋዮች ከመስቀሉ የወጡ ከሆነ፤ እነዚህን ሁሉ ብናሰባስባቸው አንድ መርከብ የግድ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ወንጌል ግን ይህንን መስቀል አንድ ሰው እንደ ተሸከመው ይነግረናል» ብሎ ነበር፡፡

ይህንን የካልቪንን ሂስ በተመለከተ መልስ የሰጠው ራውል ዲ ፈሌውሪ /Rohault de Fleury,/ በ1870 ዓም በዓለም ላይ አሉ በሚባሉት የመስቀል ክፍልፋዮች ላይ ጥናት አድርጎ ነበር፡፡ ራውል መጀመርያ የት ምን ያህል መጠን እንዳለ ካታሎግ አዘጋጀ፤ ከዚያም መጠናቸውን አንድ ላይ ደመረ፡፡ በታሪክ እንደሚነገረው የመስቀሉ ክብደት 75 ኪሎ፣ ጠቅላላ መጠኑም 178 ኪዩቢክ ሜትር ነው፡፡ ራውል ያገኛቸውና አሉ የተባሉት ክፍልፋዮች አንድ ላይ ቢደመሩ .004 ኪዩቢክ ሜትር /3.,942,000 ኪዩቢክ ሚሊ ሜትር/ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ቀሪው 174 ኪዩቢክ የሚያህለው ሜትር የመስቀሉ ክፍል ጠፍቷል ማለት ነው ብሏል፡፡ /Mémoire sur les instruments de la Passion, 1870/

**ግማደ መስቀሉ በኢትዮጵያ**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መዛግብት እንደሚሉት ግማደ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ14ኛው መከዘ በዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ነው፡፡ በግሼን አምባ የተቀመጠው ደግሞ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን ወደ ኢየሩሳሌም ያደርጉ የነበረውን ጉዞ፣ የኢትዮጵያ ነገሥታት የነበራቸውን ታዋቂነት እና ወደ ሀገረ ናግራን ተጉዘው የሠሩትን ሥራ ስንመለከት ኢትዮጵያ እስከዚያ ዘመን ድረስ ግማደ መስቀሉን ለማግኘት ትዘገያለች

ብሎ ለማሰብ ይከብዳል፡፡ በኢየሩሳሌም የሚገኘው የኢትዮጵያ ገዳም መስቀሉ ለወጣበት ቦታ እና ለጎልጎታ ያለውን ቅርበት፤ ዐፄ ካሌብም ከናግራን ዘመቻ በኋላ ዘውዳቸውን ለጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን መላካቸውን ስናይ ይህንን የመሰለ ቅዱስ ንዋይ ኢትዮጵያውያን እስከ 13ኛው መክዘ ድረስ አንዱን ክፋይ ሳያገኙት ቆዩ ለማለት ያስቸግራል፡፡ ኤርትራ ውስጥ ግማደ መስቀሉ አለበት የሚባል አንድ ገዳም መኖሩን ሰምቻለሁ፡፡

ክርስትና ብሔራዊ ሃይማኖት ከሆነ በኋላ ነገሥታቱ በሳንቲሞቻቸው ላይ የመስቀል ምልክት ማድረጋቸው፣ እንደ ንጉሥ አርማሕ ያሉትም በበትረ መንግሥታቸው ላይ መስቀል ማድረጋቸው፤ ከቀደምት ክርስቲያን ነገሥታት አንዱ የሆነው ንጉሥ ዐፄ ገብረ መስቀል ተብሎ መሰየሙን ስናይ የመስቀሉ ነገር በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረውን ቀደ ምት ታሪክ ያመለክተናል፡፡

በዛግዌ ሥርወ መንግሥትም ዐፄ ላሊበላ ስመ መንግሥቱ ገብረ መስቀል መባሉን፣ ሚስቱም ንግሥት መስቀል ክብራ መባሏን፣ ከሠራቸው አስደናቂ ውቅር አብያተ ክርስቲያ ናት አንዱ ***ቤተ ጊዮርጊስ*** በመስቀል ቅርጽ መሠራቱን ስናይ ኢትዮጵያውያን ከመስቀሉ ጋር ቀድመው መተዋወቃቸውን ያስገምተናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ መዛግብትን የማገላበጥ እና የመመርመር ሥራ የሚቀረን ይመስላል፡፡

በዐፄ ዳዊት ዘመን መጥቶ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ አማካኝነት በግሼን አምባ የተቀመጠው ግማደ መስቀል በይፋ የታወቀውና በነገሥታቱ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት የመጣው ዋናው እንጂ የመጀመርያው ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡

ተክለ ጻድቅ መኩርያ ግብጻዊው ጸሐፊ ማክሪዝ Historia Rerum Isi amiticarumin Abissinia በሚለው መጽሐፉ የገለጠውን መሠረት በማድረግ «የኢትዮጵያ ታሪክ ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል» በሚለው መጽሐፋቸው ላይ እንደሚተርኩት አስቀድሞ በሰይፈ አርእድ ዘመን በግብጹ ሡልጣን እና በኢትዮጵያዊው ንጉሥ መካከል የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት የልዑካን ቡድን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ነበር፡፡ የልዑካን ቡድኑ መሪ የኢየሩሳሌሙ ፓትርያርክ አባ ዮሐንስ ነበሩ፡፡

ልዑካኑ ወደ ኢትዮጵያ ሲደርሱ ያገኟቸው ዐፄ ዳዊትን ነበር፡፡ በሁለቱ ሀገሮች መካከል የነበረውን ችግር በውይይት እና በስምምነት ፈትተው አስማሟቸው፡፡ ዐፄ ዳዊትም ግማደ መስቀሉን እንዲልኩለት የኢየሩሳሌሙን ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስን አደራ አላቸው፡፡ እርሳቸውም ከግማደ መስቀሉ ጋር ሌሎች ንዋያትንም ጨምረው ላኩለት፡፡ በግብጹ ሡልጣን እና በንጉሥ ዳዊት መካከል የተፈጸመው ስምምነት ለኢትዮጵያውያን ተሳላሚዎች እና ነጋዴዎች ጥበቃ ማድረግን የሚያካትት ስለ ነበር ግማደ መስቀሉን የያዙት የዐፄ ዳዊት መልእክተኞች ያለ ችግር ኢትዮጵያ ገቡ፡፡

አንዳንድ የታሪክ መዛግብት ዐፄ ዳዊት ጥቅምት ዘጠኝ ቀን 1404 ዓም በድንገት ሲያርፉ ግማደ መስቀሉ በሱዳን ስናር ነበር ይላሉ፡፡ ከስናር ያነሡት ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ መሆናቸውንም ይተርካሉ፡፡ ተክለ ጻደቅ መኩርያ ግን ዐፄ ዳዊት ወደ ኢትዮጵያ አስገብተውት በተጉለት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ሠርተውለት እንደ ነበር ይናገራሉ፡፡ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ የነገሡት በ1434 ዓም ነው፡፡ በእነዚህ ሠላሳ ዓመታትም አያሌ ነገሥታት ተፈራርቀዋል፡፡ እነዚህ ነገሥታት ግማደ መስቀሉን ለመውሰድ ያልቻሉበትን ምክንያት ማወቅ አይቻልም፡፡ ምናልባት ግን በነበረው የርስ በርስ ሽኩቻ ተጠምደው ይሆናል፡፡ ሌሎች መዛግብት እንጂ በኋላ ዘመን /ምናልባትም በዐፄ ልብነ ድንግል/ የተጻፈው የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል የግማደ መስቀሉን ነገር አይነግረንም፡፡

ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ግሼን አምባ ላይ ግማደ መስቀሉን ያስቀመጠበት ሁለት ምክንያቶች ይኖራሉ፡፡ የመጀመርያው የአምባው የመስቀለኛ ምልክት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አምባው በዘመኑ በልዩ የንጉሡ ነገሥቱ ኃይል ይጠበቅ ስለ ነበር ነው፡፡ በግራኝ አሕመድ ወረራ ጊዜም ቢሆን ሌሎች ሀብቶች ከአምባው ላይ መዘረፋቸውን እንጂ የተቀበረውን ለማውጣት ሙከራ መደረጉን የግራኝን ታሪክ የጻፈው ዐረብ ፋቂህ አያነሣም፡፡

ግማደ መስቀሉን የማውጣት ጥረት ተደረገ የሚባለው በ1851 ዓም ዐፄ ቴዎድሮስ በጣም የሚወዷቸው ባለቤታቸው እቴጌ ምንትዋብ ከሞቱ ከአንድ ዓመት በኋላ ነው፡፡ ንጉሥ ቴዎድሮስ እቴጌ ምንትዋብን እጅግ ይወዷቸው ስለነበር በመስቀሉ አማካኝነት ከሞት ለማስነሣት አስበው ነበር፡፡ ይህንንም በወታደሮች ኃይል በማስቆፈር አስጀምረውት ነበር፡፡ በመካከል ግን ከጉድጓዱ ኃይለኛ ሽታ እና ጢስ ወጥቶ ከቆፋሪዎቹ የተወሰኑትን በመግደሉ ሃሳባቸውን ሠርዘው ባለቤታቸውን በግሼን አምባ ቀብረው ተመልሰዋል፡፡

## መስቀሉ የት ነው ያለው? ክፍል ሁለት

ባለፈው ጽሑፍ ላይ የጌታችንን መስቀል በተመለከተ ጥንታውያን መዛግብት ምን እንደሚሉ በመጠኑ ለማየት ሞክረን ነበር፡፡ ለዛሬ ደግሞ እነዚህን መዛግብት ከሀገራችን መዛግብት ጋር እናስተያያቸዋለን፡፡

መስቀሉ እንዴት ጠፋ?

የሀገራችን ሊቃውንት እና መዛግብት መስቀሉ እንዴት እንደ ጠፋ የሚተርኩት ታሪክ የጥንታውያኑን መዛግብት የተከተለ ነው፡፡ በመስከረም 16 እና 17 የሚነበበው ስንክሳራችን የጌታችን መስቀል በጎልጎታ በጌታችን መቃብር እንደነበረ ይተርክልናል፡፡ አይሁድ በመስቀሉ እና በመቃብሩ የሚደረገውን ተአምር አይተው በምቀኝነት መነሣሣታቸውንም ያትታል፡፡ እስከ 64 ዓም አይሁድ በኢየሩሳሌም እና በአካባቢው ኃይል አልነበራቸውም፡፡ በ64 ዓም አካባቢ ግን አይሁድ ራሳቸውን ከሮማውያን አገዛዝ ነጻ ለማውጣት ዐመጽ ጀመሩ፡፡ ኢየሩሳሌምም በአይሁድ ቁጥጥር ሥር ዋለች፡፡

አይሁድ መስቀሉን፣ ሌሎች ንዋያተ ቅድሳትን እና የጌታችንን መቃብር የተቆጣጠሩት እና ክርስቲያኖች እንዳይገቡ ያገዱት በዚህ ጊዜ ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ጎልጎታ የከተማዋ ጥራጊ እንዲደፋበት አዘዙ፡፡ ምክንያቱም በዚያ ጊዜ በኢየሩሳሌም እና በአካባቢዋ አብያተ ክርስቲያናት አልነበሩም፡፡ ክርስቲያኖች ግን በጌታችን መቃብር አካባቢ ዋሻዎችን ፈልፍለው ይገለገሉባቸው ነበር፡፡

ዛሬ በአሮጌዋ ኢየሩሳሌም ክልል የሚገኘው ጎልጎታ በዚያ ዘመን ከከተማዋ ውጭ ነበር፡፡ ጌታንም የሰቀሉት ከከተማ አውጥተው ነው፡፡ አይሁድ የከተማ ጥራጊ መድፊያ እንዲሆን የፈለጉትም ቦታው ከከተማ የወጣ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ጭምር ነው፡፡

ይህ ታሪክ በስንክሳራችን ከተጻፈው ታሪክ ጋር አንድ ዓይነት ነው፡፡

**መስቀሉ የት ተቀበረ?**

አንዳንድ አካላት የሚተርኩት ታሪክ በስንክሳራችንም ሆነ በጥንታውያን መዛግብት ከተገለጠው የተለየ ነው፡፡ በመስከረም 17 እና በመጋቢት 10 የሚነበበው ስንክሳራችን መስቀሉ የተቀበረው በዚያው በጎልጎታ እንደሆነ ይተርካል፡፡ «የጎልጎታን ኮረብታ ባስጠረገች ጊዜ የከበረ መስቀልን አገኘችው» ይላል፡፡ አንዳንድ አካላት ግን መስቀሉን አይሁድ በሌላ ቦታ ጉድጓድ ቆፍረው እንደቀበሩት ይገልጣሉ፡፡

በስንክሳራችን የተገለጠው እና መስቀሉ የተቀበረው በጎልጎታ ነው የሚለው ታሪክ በሦስተኛው እና በ4ኛው መክዘ ከነበሩት የታሪክ ጸሐፊዎች ገለጻ ጋር አንድ ነው፡፡ በ380 ዓም አካባቢ የተወለደው ታሪክ ጸሐፊው ሶዜማን መስቀሉ የተገኘው ከጎልጎታ መሆኑን መዝግቦ አቆይቶናል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ መስቀሉ በጎልጎታ ተቀብሮ ነበር የሚለው የስንክሳራችን ትረካ ከግብጽ፣ ከሶርያ እና ከሌሎች ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ስንክሳር ትረካ ጋር አንድ ዓይነት ነው፡፡

በሦስተኛ ደረጃም እሌኒ ንግሥት መስቀሉን ቆፍራ ያወጣችበት እና በኋላም የመስቀሉን ቤተ ክርስቲያን የሠራችበት ቦታ የሚገኘው በዚያው በጎልጎታ፣ ያውም ከኢትዮጵያ የዴር ሡልጣን ገዳም ሥር ነው፡፡

በመሆኑም መስቀሉን አይሁድ በሌላ ቦታ ቀበሩት የሚለው ሃሳብ የሚያስኬድ አይመስልም፡፡

**መስቀሉ እንዴት ተገኘ?**

መስቀሉ እንዴት እንደ ተገኘ በቤተ ክርስቲያናችን የሚገለጠው ታሪክ ከሌሎች ጥንታውያን መዛግብት ታሪክ ጋር አንድ ዓይነት ነው፡፡ መስቀሉን ያወጣችው የቆስጠንጢኖስ እናት ንግሥት እሌኒ መሆንዋን ሁሉም ይስማሙበታል፡፡

እሌኒ ንግሥት ወደ ኢየሩሳሌም ስትገባ መስቀሉ የተቀበረበት ቦታ በቀላሉ የሚገኝ አልነበረም፡፡ ለዚህም ሦስት ምክንያቶች ነበሩ፡፡ የመጀመርያው በኢየሩሳሌም ከ132 እስከ 135 በተደረገው እና ከተማዋ ፈጽማ በጠፋችበት ጦርነት ምክንያት ክርስቲያኖች ከከተማዋ ርቀው መኖራቸው ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ አይሁድ መስቀሉን በጎልጎታ ከቀበሩ በኋላ መጀመርያ ጥራጊ መድፋታቸው ሲሆን ሦስተኛው ንጉሥ ሐድርያን በ135 ዓም የኢየሩሳሌምን ገጽታ የቀየረውን አዲስ ፕላን በማውጣት ከተማዋን እንደገና መሥራቱ፤ በጎልጎታም ላይ የቬነስን መቅደስ መገንባቱ ነው፡፡ የቬነስ መቅደስ መገንባት ክርስቲያኖች ወደ አካባቢው ፍጹም እንዳይቀርቡ አስከላከላቸው፡፡

ንግሥት እሌኒ ወደ ኢየሩሳሌም ገብታ ያደረገችውን ስንክሳራችውን እንዲህ ይተርከዋል «እርሷ በመጣች ጊዜ የጌታችን የክርስቶስን መቃብር እስካሳዩዋት ድረስ አይሁድን ይዛ አሰቃየቻቸው፤ ያንን ኮረብታም እስከ ጠረጉ ድረስ አስገደደቻቸው፤ የከበረ መስቀሉም ከተቀበረበት ተገልጦ ወጣ» ይላል፡፡ በሌላም በኩል የመጋቢት 10 ቀኑ ስንክሳር ታሪኩን ያውቃል የተባለውን አንድን አይሁዳዊ አሥራ በማስጨነቅ ምሥጢሩን እንዳውጣጣችው ይገልጣል፡፡ ይህ አገላለጥ ከጥንታውያን መዛግብት አገላለጥ ጋር የተስማማ ነው፡፡ ዞሴማን አልተቀበልኩትም ቢልም አንድ አይሁዳዊ ሽማግሌ ለንግሥት እሌኒ መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ እንዳሳያት የሚተርከው ታሪክ በቤተ ክርስቲያናችን ኪርያኮስ

የተባለ አረጋዊ ነገራት እየተባለ ከሚተረከው ጋር ተመሳይ ነው፡፡ በወቅቱ ይህ አይሁዳዊ ስለ ዕጣንም ሆነ ጸሎት ሊናገር የሚችል አይመስልም፡፡ ይህ ሃሳብ ምናልባት በወቅቱ የኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ የነበሩት የአቡነ መቃርዮስ ይሆናል፡፡

እስካሁን እኔ በሌሎች መዛግብትም ሆነ በስንክሳራችን ላይ ያላገኘሁት «ደመራ ተደምሮ ጢሱ አመለከተ» የሚለውን ታሪክ ነው፡፡ ቅዱስ ያሬድ በድጓው ጢሱ ለመስቀሉ መስገዱን ይገልጣል፡፡ እሌኒ ንግሥት ክርስቲያናዊት እናት እንደ መሆንዋ መጠን አይሁድ የሰጧትን መረጃ ብቻ ተቀብላ ቁፋሮ አታስጀምርም፡፡ በአይሁድ የተነገረው በጸሎት እንዲረጋገጥ አድርጋለች፡፡ ያን ጊዜ ጸሎት ተደርጎ ዕጣን ሲታጠን ጢሱ ወደ ጎልጎታ አመለከተ፡፡ ይህንን በተመለከተ መዛግብትን ማገላበጥ ይቀረናል፡፡

**በዓለ መስቀል እንዴት ተወሰነ?**

በኢትዮጵያም ሆነ በግብጽ ያሉ ስንክሳሮች ላይ መስቀሉ የተገኘው መስከረም 17 ቀን መሆኑን ይገልጣሉ፡፡ ቁፋሮው መቼ እንደተጀመረ በትግጠኛነት የሚገልጥ መረጃ አላገኘሁም፡፡ የኛ ሊቃውንት ቁፋሮው መስከረም 17 ተጀምሮ መጋቢት 10 ቀን መጠናቀቁን ይገልጣሉ፡፡ በወቅቱ ከነበረው ቴክኖሎጂ አንፃር ሊወስድ ይችላል፡፡ መጋቢት 10 ቀን ግን ራሱን የቻለ ታሪክ አለው፡፡ መስቀሉ በፋርሶች ከተማረከበት በንጉሥ ሕርቃል ተመልሶ ወደ ጎልጎታ የገበባበት ቀን ነው፡፡

የቀድሞ አባቶች ታከን ከታሪክ ማገናኘት ልማዳቸው ነውና መስቀሉ መጋቢት 10 ቀን ወደ ጎልጎታ እንዲገባ ያደረጉት ቀድሞ ከተገኘባት ቀን ጋር ለማስተሣሠር ሊሆን ይችላል፡፡ በስንክሳራችን መስከረም 16 ቀን በኢየሩሳሌም እና በአካባቢው በንግሥት እሌኒ የተሠሩ አብያተ ክርስቲያናት በመስቀሉ የተባረኩበት ቀን መሆኑን ይነግረናል፡፡ መስከረም 17 ቀን ደግሞ ቅድስት እሌኒ መስቀሉ በተገኘበት በጎልጎታ ያሠራችው የመስቀሉ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቤት ነው፡፡

ነገር ግን በዐቢይ ጾም በዓል ስለማይከበር የመስቀሉ በዓል ቅዳሴ ቤቱ በተከበረበት ቀን በመስከረም 17 እንዲከበር ሊቃውንት ሥርዓት መሥራታቸውን ስንክሳሩ ይነግረናል፡፡

**እንዴት ወደ ኢትዮጵያ ገባ?**

ግማደ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደገባ ሁለት ዓይነት ታሪኮች አሉ፡፡ አንዱ ከግብጽ ሁለተኛው ከኢየሩሳሌም፡፡ ለመስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ምክንያት የሆነው በዐፄ ሠይፈ አርእድ ተፈጥሮ የነበረ ችግር ነው፡፡ በዚህ ዘመን የግብጽ ሡልጣኖች በግብር እያመካኙ የግብጽ ክርስቲያኖችን ባሰቃዩዋቸው ጊዜ ንጉሥ ሠይፈ አርእድ እስከ ደቡብ ግብጽ እየዘመተ ወግቷቸዋል፡፡ ከዚህም በላይ የንግድ መሥመሩን ከለከለባቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ከኢትዮጵያ እና ከኑቢያ የሚሄደው ዕቃ ተቋረጠ፡፡

ሁኔታው ከሥጋት ላይ የጣላቸው የግብጽ ሡልጣኖች በግብጽ ክርስቲያኖች ላይ የጣሉትን ቀንበር አላሉ፡፡ የግብጹ ጳጳስ እና ሡልጣኑ ተስማምተው ወደ ኢትዮጵያ መልከተኛ ላኩ፡፡ በጉዳዩም በኢየሩሳሌም የነበሩት ፓትርያርክ ዮሐንስ ገቡበት፡፡ አቡነ ዮሐንስ የመልክተኞቹ መሪ ሆነው መጡ፡፡

በጊዜው በዙፋኑ ላይ የነበረው ዐፄ ዳዊት ስለነበረ እርሱም ንግዱን ላይዘጋ ሡልጣናቱም ክርስቲያኖቹን ላያጉላሉ ተስማሙ፡፡ ለስምምነቱ ማሠርያ ይሆን ዘንድም ከጌታ ግማደ መስቀል እንዲመጣለት ንጉሥ ዳዊት ጠየቀ፡፡ ሡልጣኑም ተስማማ፡፡

በ1387 ዓም ግማደ መስቀሉን የሚያመጡ ሊቃውንት ወደ ካይሮ ተላኩ፡፡ መልክተኞቹ ለሡልጣኑ የሚሰጥ በ20 ግመል የተጫነ ስጦታ ይዘው ነበር፡፡ ዐፄ ዳዊት አስቀድሞ ሃሳቡን ለኢየሩሳሌሙ ሊቀ ጳጳስ ለአቡነ ዮሐንስ ነግሯቸው ስለነበር እርሳቸው ሉቃስ የሳላትን ሥዕል፣ ኩርአተ ርእሱ የተባለውን የጌታ ሥዕል እና ግማደ መስቀሉን ላኩለት፡፡ ግማደ መስቀሉ መስከረም 16 ቀን ተጉለት ገብቶ ንጉሡ ባሳነፁት ቤተ ክርስቲያን የቀመጠ፡፡ /***ተክለ ጻድቅ መኩርያ፣ ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል፣ ገጽ 116-118***/

በሌላ በኩል ደግሞ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ በመጣ ጊዜ ለመቀበል ዐፄ ዳዊት ወደ ስናር ወርደው ነበር፡፡ በዚያም ባዝራ ፈረስ ጥላ ስለረገጠቻቸው ሞቱ፡፡ ግማደ መስቀሉም በስናር ቆየ የሚል ታሪክም አለ፡፡ ይህንን ታሪክ ለመቀበል የሚከብደው በወቅቱ ሱዳን በዐረቦች መወረሯን፤ስናርም ለግዛታቸው ቅርብ የነበረ መሆኑን ስናስበው ነው፡፡ ከዚህም በላይ ከዐፄ ዳዊት እስከ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ሠላሳ ዓመታት በዚያ ተቀመጣ ለማለት ይከብዳል፡፡ ምናልባትም የተክለ ጻድቅ መኩርያ ትረካ የተሻለ ይመስለኛል፡፡

በሌላም በኩል ግማደ መስቀሉ ከኢየሩሳሌም መጣ የሚለው ታሪክ በወቅቱ ኢየሩሳሌም ከነበረችበት ሁኔታ አንፃር ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም በ1187 ዓም ሳላሕ ዲን ኢየሩሳሌምን ከያዛት በኋላ መስቀሉ ከአካባቢው ተሠውሯል፡፡ የሮም ነገሥታትም እርሱን ለማግኘት ተደራድረው አልተሳካላቸውም፡፡ የመስቀል ጦረኞችም ቢሆኑ ወደ ኢየሩሳሌም ገብተው ሌሎችን ንዋያት አመጡ እንጂ መስቀሉን አላገኙትም፡፡

እንደ እኔ ግምት ግማደ መስቀሉን ያገኘነው ከእስክንድርያ መሆን አለበት፡፡ ንግሥት እሌኒ የኢየሩሳሌም አብያተ ክርስቲያናትን ሥርታ ስታጠናቅቅ የቁስጥንጥንያ፣ የአንፆኪያ እና የእስክንድርያ አባቶች ካህናትን ልከዋል፡፡ ግማደ መስቀሉ ወደ እስክንድርያ የገባው በዚያ ዘመን ሳይሆን አይቀርም፡፡ በኋላም ዐፄ ዳዊት ግማደ መስቀሉን ሲጠይቅ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ላደረገው ውለታ ልከውለት ይሆናል፡፡ በሌላም መልኩ ሡልጣኑም ግፊት ማድረጉ አይቀርም፡፡

አያሌው ተሰማ የተባሉ ምሁር «ታሪክ ነው ገበያ፣ የሁሉ መዋያ» በተሰኘ መጽሐፋቸው ላይ ዐፄ ዳዊት ግማደ መስቀሉን ያገኘው ዓባይን ገድቦ ግብፆችን በማስጨነቅ ነው ይላሉ፡፡ ሁኔታው ያሰጋቸው የግብጽ ባለ ሥልጣናት ለላኳቸው መልክተኞች ግማደ መስቀሉን እንዲሰጧቸው በመጠየቃቸው ሡልጣናቱ ግብፃውያኑን አባቶች ተጭነው እንዳሰጧቸው ይተርካሉ፡፡

***ደመራ***

የደመራ በዓል መላዋን ኢትዮጵያ ከሚያስተሣሥሩት በዓላት አንዱ ነው፡፡ አንዳንድ ሊቃውንት የደመራ በዓል መነሻ ንግሥት እሌኒ ናት ይላሉ፡፡ ነገር ግን ስለ ንግሥት እሌኒ በተጻፉት ጥንታውያን መዛግብት ሁሉ ይህንን የሚደግፍ

ነገር አላገኘሁም፡፡ ነገር ግን የኢየሩሳሌም አብያተ ክርስቲያናት ቅዳሴ ቤት ሲከበር አበው ሊቃነ ጳጳሳት መስቀሉን ይዘው ችቦ አብርተው እየዞሩ መባረካቸውን የሚገልጡ መዛግብት አሉ፡፡

ኢትዮጵያውያንም ይህንን በመያዝ የመስቀልን በዓል በደመራ በዓል ማክበር ጀምረዋል፡፡ ደመራ የአባቶቻችን የመንፈሳዊ ብቃት መገለጫ እንጂ ከውጭ አልመጣም፡፡ የጌታችንን ጥምቀት በዓል ታቦቱን በበዓለ ከተራ ይዞ በመውረድ እና በበዓሉ እንዲመለስ ሥርዓት እንደሠሩት ማለት ነው፡፡

የደመራ ሥርዓት ከሰሜን እስከ ደቡብ ጫፍ በተመሳሳይ ሰሞን እና ሥርዓት ይከበራል፡፡ የደቡብ ኢትዮጵያ ወርቃማው የክርስትና ዘመን የሚባለው ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘመን እስከ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ያለው ዘመን ነው፡፡ የመስቀል ደመራ ሥርዓት በደቡብ ውስጥ የሠረፀው እና መከበር የጀመረው በዚህ ዘመን ወይንም ቀደም ብሎ መሆን አለበት፡፡ አንድን ሥርዓት ባህል ለማድረግ ብዙ መቶ ዓመታት ያስፈልጋልና፡፡

በደቡብ ግራኝ ሊያጠፋቸው ካልቻሉ ክርስቲያናዊ ሥርዓቶች አንዱ መስቀል ነው፡፡ በወላይታ፣ በጋሞ፣ በጎፋ፣ በጉራጌ፣ በከፋ ሸካ ከነ ክብሩ እና ሞገሡ አሁንም ይከበራል፡፡ አንዳንድ ሕዝቦች ትምህሩ ጠፍቶባቸው እንኳን ሥርዓቱን አልረሱትም፡፡

ይህ ነገር የደመራ በዓል ከግማደ መስቀሉ መምጣት በፊት በሀገራችን ሊኖር እንደሚችል ያመለክታል፡፡ በዚህ ጉዳይ ዜና መዋዕሎችን እና መዛግብትን ማገላበጥ ገና ይቀረናል፡፡

በሌላም በኩል የደብረ ታቦርን እና የአዲስ ዓመት መለወጫን በዓል በደመራ እና በችቦ የማክበሩ ባህላችን ደመራ ከመስቀል በዓል ጋር ብቻ የተያያዘ አለመሆኑን ፍንጭ ይሰጠናል፡፡

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ይህንን ችቦ የማብራት ሥርዓት ከጥንት ሀገራዊ ባህል እና ከኢየሩሳሌም መብራት የማውጣት ሥርዓት የቀመሩት ይመስላል፡፡ በኢየሩሳሌም ከጌታ መቃብር በየዓመቱ ለበዓለ ትንሣኤ መብራት የማውጣት ሠርዓት ነበር፡፡ ይህ ሥርዓት ልዩ ልዩ የፈትል እና ዘይት መብራቶችን በአንድነት አስተሣሥሮ ይዞ መውጣት ነው፡፡ ይህንን ሥርዓት በኢትዮጵያዊው ችቦ በመወከል በበዓል ቀን እንዲበራ ሥርዓት የሠሩልን አባቶች በረከታቸው ይደርብን፡፡

**ግሼን እና ግማደ መስቀሉ**

ግማደ መስቀሉ የተቀመጠው በግሼን ማርያም መሆኑን በገዳሙ የሚገኘው መጽሐፈ ጤፉት ይናገራል፡፡ ለዚህ ዋናው ምክንያት መስቀሉን በመስቀልኛ ቦታ አስቀምጥ የሚል ራእይ ለዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በመገለጡ ነው፡፡ አምባ ግሼን ከንጉሥ ይኩኖ አምላክ ጀምሮ የነገሥታቱ ልጆች የሚቀመጡባት ቦታ ነበረች፡፡ ከመካከላቸው አንዱ ይነግሥና ሌሎቹ በግሼን በምባ ይቀመጣሉ፡፡ በዚያ ቦታ ለነገሥታቱ ልጆች የተሠራ ቤተ ክርስቲያን፣ ቤተ መንግሥት እና የወግ

ዕቃ ቤት ነበሩ፡፡ በዚህም ምክንያት የግእዝ መጻሕፍት ቦታዋን በልዩ ልዩ ስም ይጠሯታል፡፡ «ደብረ ነገሥት» የነገሥታት ቦታ፣«አምባ ግሼን»፣ ደብረ ከርቤ፡፡

ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ግሼንን የሚያውቃት እንደ ሌሎቹ የነገሥታት ልጆች ተይዞ በአምባው ታሥሮ በነበረ ጊዜ ነው፡፡ ዐፄ ዳዊት ያመጣውን ግማደ መስቀል ለማክበር ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ያሰበበት ምክንያት ነበረው፡፡ በመጀመርያ እንደ ታሪክ ነገሥቱ ከሆነ መስቀሉ የነበረበት ቦታ እና ዘርዐ ያዕቆብ የነገሠበት ቦታ ተመሳሳይ ነው፡፡ ሁለቱም ተጉለት ውስጥ ነው የነበሩት፡፡ በሌላም በኩል ዘርዐ ያዕቆብ ለመስቀል ልዩ ፍቅር ስለነበረው መስቀሉን ለጊዜው ከተሠራለት ቦታ በዘላቂነት ተጠብቆ ወደሚቆይበት ቦታ ለማዛወር ፈለገ፡፡ በዚህ ጊዜ ነው ያንን ራእይ ያየው፡፡

እስካሁን የሚገርመው ነገር መስቀሉ በግሼን አምባ ከተቀመጠ በኋላ ምእመናኑ እንዴት ይሳለሙት እንደነበረ ነው፡፡ ምክንያቱም አምባው በወታደሮች የሚጠበቅ እና የነገሥታቱ ልጆች ብቻ ይገቡበት የነበረ ቦታ ነበርና ነው፡፡ ግራኝ አምባውን ለመስበር ሁለት ጊዜ አለመቻሉን ስንረዳ አምባው ምን ያህል ጠንካራ እንደነበር ያሳያል፡፡ ምናልባት ምእመናን እንደልባቸው ወደ አምባው መግባት የቻሉት ከግራኝ በኋላ አምባው የነገሥታት ልጆች ወኅኒ መሆኑ ሲቀር ነው፡፡ በጎንደር ዘመን ደግሞ ወኅኒው ወደ ወኅኒ አምባ በመዛወሩ ምእመናኑ እንደ ልብ መግባት ችለዋል፡፡

የግራኝ ሠራዊት ወደ አምባው በወጣ ጊዜ የካቲት 22 ቀን 1532 ዓም የነገሥታቱን የወግ እቃ መዝረፋቸውን እንጂ ግማደ መስቀሉን ለማውጣት መሞከራቸውን አይገልጥልንም፡፡

አሁን ያለውን የእግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን ያሠሩት ዐፄ ምኒሊክ ሲሆኑ የእመቤታችንን ቤተ ክርስቲያን ያሠሩት ደግሞ እቴጌ መነን ናቸው፡፡ /***ልዑል ራስ እምሩ ኃ/ሥላሴ፣ ካየሁት ከማስታውሰው፣ ገጽ 168፣169/***

እስካሁን ትክክለኛ ምክንያቱን ያላገኘሁት ግሼን የግማደ መስቀል መንበር ሆና እያለ በዓለ ንግሡ በመስከረም 21 ለምን እንደ ሆነ ነው?

**ግማደ መስቀሉን በተመለከተ ሊጠኑ የሚገባቸው ነገሮች**

1. ኢትዮጵያ ጥንተ ክርስቲያን ሀገር ሆና፣ በጎልጎታ ጥንታዊ ገዳም የነበራት ሀገር በመሆንዋ፣ ገዳምዋም ከመስቀሉ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በመሆኑ ግማደ መስቀሉን እንዴት ሳታገኘው ቀረች?

2. ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም በ348 ዓም በጻፈው ጽሑፍ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሳለም የሚመጡ ሁሉ ከመስቀሉ ቁራጭ ይወስዱ እንደ ነበር ገልጧል፡፡ ታድያ ኢትዮጵያውያን ሳያመጡ ቀሩን? ተጨማሪ ጥናት በተለይ በጣና ገዳማት፣ በትግራይ እና በኤርትራ ገዳማት ይቀረናል፡፡

3. ስለ ግማደ መስቀሉ አመጣጥ ግብጻውያን መዛግብት ምን ይላሉ?

4. ግማደ መስቀሉ በየት በኩል መጣ? ከስናር ወደ ግሼን ወይስ ከስናር — ተጉለት— ግሼን፡፡ በተለይም በተጉለት አካባቢ ተጨማሪ መረጃዎች የማፈላለግ ሥራ ይቀረናል፡፡

5. ስለ መስቀል በዓል አከባበር በዜና መዋዕሎቻቸን እና በገድሎቻችን የሚገኙ ተጨማሪ መረጃዎች ካሉ? እስኪ የምትችሉ በርቱ፡፡

## የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት የሚጀምረው ስንት ሰዓት ላይ ነው?

ዓርብ ለቅዳሜ ምሽት፣ ጳጉሜን አምስት 2002 ዓም ማታ በኢትየጵያ ቴሌቭዥን ይተላለፍ የነበረውን የአዲስ ዓመት ዋዜማ እያየሁ ነበር፡፡ ከአሜሪካ የገባሁት በዚያው ቀን ነበርና ዕንቅልፌ ሊስተካከልልኝ ስላልቻለ በደንብ ነበር የተከታተልኩት፡፡ እኩለ ሌሊት ሊደርስ ሲል ግን አንድ አሳዛኝ ነገር ተከሰተ፡፡

የማከብራቸው አርቲስቶች ወደ መድረኩ ተሰባስበው ወጡና በዚያች ታሪካዊት ቀን ታሪካዊ ቀን ታሪካዊውን ስሕተት ሠሩት፡፡ እኩለ ሌሊት ስድስት ሰዓት ሊሆን ሽርፍራፊ ሰኮንዶች ሲቀሩ «አዲሱ ዓመት ሊገባ ስለሆነ እንቁጠር» አሉና ወደ ኋላ አሥር፣ዘጠኝ፣ ስምንት፣ እያሉ እስከ ዜሮ ቆጠሩ፡፡ ከዚያም ከምሽቱ ስድስት ሰዓት ላይ አዲሱ ዓመት ገባ ብለው ዐወጁ፡፡

«ሊቃውንቱ ስሕተት እድሜ ሲያገኝ ሕግ ይሆናል» ይላሉ፡፡ በጥንት ጊዜ አውስትራልያ የገባ አውሮፓዊ አይቷት የማያውቅ አዲስ ፍጡር ያይና የሀገሬውን ነዋሪ «ይህቺ እንስሳ ማን ትባላለች?» ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ ያም የሀገሩ ነዋሪ «ካንጋሮ» ብሎ መለሰለት፡፡ ያም ሰው «ካንጋሮ» የምትባል እንስሳ አገኘሁ ብሎ ለዓለም ተናገረ፡፡ በሀገሬው ቋንቋ ግን «ካንጋሮ» ማለት «አላውቅም» ማለት ነበር፡፡ አንድ ሞኝ የተከለውን አምሳ ሊቃውንት አይነቅሉትም እንዲሉ ይሄው ስሟ ሆኖ ቀረ፡፡

ይህ የአዲስ ዓመት መግቢያ ሰዓትም በየሚዲያው እና በየአዳራሹ ብቅ ጥልቅ እያለ ሰነበተና ስሕተት «ሕግ» ሆኖ በአደባባይ ታወጀ፡፡ ለመሆኑ ግን የስሕተቱ መነሻው ምንድን ነው?

የመጀመርያው ቁርጥ ያለ ሕግ ካለመኖሩ የተነሣ ይመስለኛል፡፡ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 51/20 ላይ አንድ ወጥ ካላንደርን ማወጅ የፌዴራል መንግሥቱ ሥልጣን መሆኑን ይገልጻል፡፡ ሳላውቀው ታውጆ ካልሆነ በቀር እስካሁን የተወካዮች ምክር ቤት ካላንደርን በተመለከተ ያወጣው ሕግ የለም፡፡ ስለዚህም እንደ ዘመነ መሳፍንት «ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ጀመር»፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የሚመለከታቸውን ባለሞያዎች በሚመለከታቸው ቦታ ያለማሳተፍ ልማዳችን የፈጠረው ሊሆንም ይችላል፡፡ አንድ ሰው እድሉን እና መድረኩን ካገኘ፤ ታውቃለህ ከተባለ፤ አጋጣሚውም ከተፈጠረለት ሁሉንም ይሆናል፡፡ ደራሲም፣ አዘጋጅም፣ ዳይሬክተርም፣ ተዋናይም፣ ይሆናል፡፡ ዘፋኝም፣ ኮምፖዘርም፣ ደራሲም፣ የድምፅ ባለሞያም ይሆናል፡፡ ይኼ ልማዳችን የዘመን አቆጣጠራችንን በተመለከተም በሞያው የደከሙ፣ ከልክ በላይ የሠለጠኑ፤ ነገሩን ከነምክንያቱ ሊያስረዱ የሚችሉ ሊቃውንት እያሉ ሞያውን የማያውቁት እና ለሞያውም ትኩረት የማይሰጡ አካላት ገቡበትና ሁሉም የየራሱን መንገድ ፈጠረ፡፡

እንደገናም ደግሞ ፈረንጅ ያደረገው ሁሉ ትክክል ነው የሚለው ክፉ ልማዳችንም ለዚህ ሳያጋልጠን አልቀረም፡፡ ፈረንጆቹ አዲሱን ዘመናቸውን የሚቀይሩት በእኩለ ሌሊት ነው፡፡ ያም እንኳ ቢሆን ትክክል ሆኖ አይደለም፡፡ የዘመን መለወጫ በሽርፍራፊ ሴኮንዶቹ የተነሣ በየጊዜው ይለዋወጣልና፡፡ ነገር ግን በልማድ ሕግ /customary law/ መሠረት በእኩለ ሌሊት ሰዓታቸውን በመጀመራቸው ከሰዓታቸው ጋር እንዲገጥም አድርገው ተጠቀሙበትና

በዚያው ጸና፡፡ ታድያ እኛም ለመሠልጠን እንደ እነርሱ በእኩለ ሌሊት አዲሱን ዓመት መቀበል አለብን ተብሎ ሳይታሰብ አልቀረም፡፡

ፈረንጆቹ በእኩለ ሌሊት አዲስ ዓመታቸውን ቢቀበሉ እውነታቸውን ነው፡፡ ምክንያቱም የእነርሱ የቀን አቆጣጠር ከእኩለ ሌሊት አንድ ሰዓት አልፎ ይጀምርና በእኩለ ሌሊት ያልቃል፡፡ አዲሱ ዓመታቸውም 00 ብሎ የሚጀምረው በእኩለ ሌሊት ነው፡፡ ኮፒ በሚጠቅም መንገድ ከተደረገ አንዳንድ ጊዜ መልካም ነው፡፡ ነገር ግን ኮፒ ሲደረግ ለገልባጩ እንዲያመቸው አድርጎ ካልሆነ ከመኮረጅ የባሰ ስሕተት ይሠራል፡፡

ትምህርት ቤት እያለን የሚቀለድ አንድ ቀልድ ነበረ፡፡ አንድ ሰነፍ ተማሪ ነበረ ይባላል፡፡ ይኼ ተማሪ አራተኛ ክፍል ይደርስና እንዴት እንደሚያደርግ ግራ ይገባዋል፡፡ በመጨረሻም በፈተና ሰዓት አነጣጥሮ ተኳሽ መሆን እንደሚያዋጣው ራሱን አሳምኖ ፈተና ክፍል ይገባል፡፡ ከዚያም እያነጣጠረ ከጎበዙ ተማሪ መኮረጅ ይጀምራል፡፡ አንዲትም ጥያቄ ሳታመልጠው ይኮርጃል፡፡ በመጨረሻም ፈተና በሚመለስበት ቀን ግቢው ሁሉ በሳቅ አወካ፡፡

ለካስ ያ ሰነፍ ተማሪ ከጎበዙ ተማሪ ሲኮርጅ ከነ ስሙ እና ከነ ቁጥሩ ኑሯል የኮረጀው፡፡

የኛም አኮራረጅ የዚህን ሰነፍ ተማሪ ዓይነት ሆነ፡፡ ቢያንስ ቢያንስ የአዲስ ዓመት በዓል አከባበራቸውን ወስደን የኛ አዲስ ዓመት በሚከበርበት ሰዓት ብናደርገው ከሰነፉ ተማሪ አኮራረጅ የተሻለ በኮረጅን ነበር፡፡

ምናልባትም ደግሞ ነገሮችን በአራቱም አቅጣጫ ካለማየት የመጣም ይሆናል፡፡ ዕውቀት ማለት ነገሮችን ከአራት አቅጣጫ ማየት መቻል ነው፡፡ ማንበብ፣ መጠየቅ፣ መመራመር፣ ማነፃፀር፣ ማወዳደር፣ መተንተን የሚባሉት ነገሮች የሚመጡት ነገሮችን ከአራቱም አቅጣጫዎች ለማየት ሲሞከር ነው፡፡

በእኩለ ሌሊት ተነሥተው አዲስ ዓመት ገብቷል ብለው የሚያውጁ አካላት ሌላው ቀርቶ የእጅ ሰዓታቸውን እንኳን ቢያዩት በታረሙ ነበር፡፡ «ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት» ነበር የሚለው፡፡ በዚያ ሰዓት ስድስት ሰዓት ካለ ደግሞ ሌሎች አምስት ሰዓታት ከፊቱ ሄደዋል፤ ወይንም ደግሞ ሌሎች ስድስት ሰዓታት ከኋላው ይቀሩታል ማለት ነው፡፡ በዚያ ሰዓት ስድስት ሰዓት ከተባለ ደግሞ ያ ሰዓት ያለፈው ቀን ቅጣይ እንጂ የአዲስ ቀን መጀመርያ አለመሆኑን መረዳት ይገባ ነበር፡፡

አንዳንዶች ይህንን የአዲስ ዓመት ጉዳይ ከገና እና ፋሲካ በዓላት ጋርም ያያይዙታል፡፡ በገና እና ፋሲካ በዓላት ጊዜ በዓሉ የሚበሰረው በእኩለ ሌሊት ነው፡፡ ከዚህ አያይዘውም አዲስ ዓመትም በእኩለ ሌሊት ይበሠራል ይላሉ፡፡ ገና እና ፋሲካ በእኩለ ሌሊት የሚበሠሩት በበዓላቱ ታሪካዊ ምክንያት የተነሣ እንጂ የበዓሉ ቀን በእኩለ ሌሊት ስለ ገባ አይደለም፡፡ ክርስቶስ የተወለደውም ሆነ ከሙታን የተነሣው በእኩለ ሌሊት ነው ተብሎ በቤተ ክርስቲያን ስለሚታመን በዓሉ በእኩለ ሌሊት ተከበረ እንጂ ዕለታቱ በስድስት ሰዓት ስለሚገቡ አይደለም፡፡

በቤተ ክርስቲያን ሁለት ዓይነት አቆጣጠሮች አሉ፡፡ የፀሐይ አቆጣጠር እና የጨረቃ አቆጣጠር፡፡ የፀሐይ አቆጣጠር ከጠዋቱ አሥራ ሁለት በኋላ ጀምሮ እስከ ሌሊቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ይደርሳል፡፡ አብዛኛውን የሕዝቡ በዓላት እና አቆጣጠር /civil calendar/ የተመሠረተው በዚህ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የጨረቃ አቆጣጠር ነው፡፡ ይህም በምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ጀምሮ በማለዳው አሥራ ሁለት ሰዓት ያልቃል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቱ በዓላት፣ በተለይም ዐበይት በዓላት የሚወጡት ይህንን አቆጣጠር ከፀሐይ አቆጣጠር ጋር በማጣመር ስለሆነ /Liturgical calendar/ ተብሎ ይጠራል፡፡ በሥርዓተ ጸሎት ምሽት ሲገባ የቀጣዩን ቀን ጸሎት የምናደርሰው የጸሎት አቆጣጠራችን የጨረቃን አቆጣጠር ጭምር ስለሚከተል ነው፡፡

በተለይም የነነዌ ጾም፣ የዐቢይ ጾም መጀመርያ፣ ደብረ ዘይት፣ ስቅለት፣ ትንሣኤ፣ ዕርገት እና ጰራቅሊጦስ በዚህ መሠረት የሚወጡ ናቸው፡፡ መሠረቱ ደግሞ የትንሣኤ በዓል ነው፡፡ የትንሣኤ በዓል ሦስት ነገሮችን መሠረት አድርጎ መውጣት አለበት፡፡ ከእሑድ መልቀቅ የለበትም፤ ከአይሁድ ፋሲካ በኋላ መሆን አለበት፣ ከእርሱ ጋር የተያያዙ በዓላትን ጥንት ማስለቀቅ የለበትም፡፡ እነዚህም ደብረ ዘይት እሑድ፣ስቅለት ዓርብ፣ ዕርገት ኀሙስ፣ ጰራቅሊጦስ እሑድ እንዲውሉ ማድረግ ነው፡፡

የትንሣኤ በዓል የሚወጣው በጨረቃ/ፀሐይ አቆጣጠር ነው፡፡ ምክንያቱም አይሁድ በዓለ ፋሲካቸውን የሚያወጡት በጨረቃ አቆጣጠር በመሆኑ ነው፡፡ አይሁድ በጨረቃ አቆጣጠር ተጠቅመው ያወጡትን የአይሁድ ፋሲካ በዓል አልፎ አማናዊውን ትንሣኤ ለማክበር በጨረቃ/ፀሐይ ቆጥሮ ማውጣትን ይጠይቃል፡፡ የሚገርመው ግን በዚሁ በጨረቃ ብንቆጥረው እንኳን አዲሱ ዓመት የሚገባው ከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት እንጂ ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ሊሆን አይችልም፡፡

ቤተ ክርስቲያን ሁለቱንም አቆጣጠሮች እንደየ አስፈላጊነታቸው ትጠቀምባቸዋለች፡፡

አንዳንድ መፍቀርያነ በዓል ደግሞ በዓሉ የሚያምረው እና የሚደምቀው በእኩለ ሌሊት ሲሆን ነውና በእኩለ ሌሊት ብናከብረው ምናለ ይላሉ፡፡ በዓሉን በእኩለ ሌሊት ማክበርና አዲሱ ዓመት በእኩለ ሌሊት ገባ ብሎ ማወጅ ይለያያሉ፡፡ የበዓሉን ዋዜማ ከእኩለ ሌሊት ጀምሮ እስከ ንጋት ድረስ ማክበር ይቻላል፡፡ የሺ ዘመናትን ሥርዓት እና አቆጣጠር በአንድ ሌሊት በማወቅ እና ባለማወቅ መናድ ግን በታሪክ እና በትውልድ የሚያስጠይቅ ነው፡፡

ሠለጠን የምንል ሰዎች ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነን በጎርጎርዮሳዊው ቀመር ሰዓታችንን እንሞላዋለን፡፡ በኛ የሰዓት አቆጣጠርም ዕለቱ የሚጀምረው በኛ ከሌሊቱ ስድስት በእናንተ ደግሞ ከሌሊቱ 00 ሰዓት ነው፡፡ የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር እያከበሩ በአውሮፓ ሰዓት መጠቀም ግን በዶሮ ወጥ ላይ ማርማላታ እንደ መጨመር ነው፡፡ ሁለቱንም አያይዞ ማጥፋት፡፡

**ታድያ የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት የሚብተው ስንት ሰዓት ነው?**

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ እንችል ዘንድ አራት ነገሮችን እናንሣ፡፡ የመጀመርያው በኛ አቆጣጠር ዕለት የሚባለው ምንድን ነው? የሚለው ነው፡፡ ዕለት ሁለት ነገሮችን ይይዛል፡፡ ቀን እና ሌሊት፡፡ በፈረንጆቹ አቆጣጠር ዕለት የሚባለው ከመንፈቀ ሌሊት እስከ ማለዳ ያለውን ግማሽ ሌሊት፣ ከዚያም ከማለዳ እስከ ማታ ያለውን ቀን እና ከማታ እስከ እከየለ ሌሊት ያለውን ግማሽ ሌሊት የያዘው ክፍል ነው፡፡ በኛ ግን አንድ ቀን እና አንድ ሌሊትን ብቻ የያዘ አቆጣጠር ነው፡፡

ስንክሳሩ መስከረም አንድን ሲጀምር «ይህ የመስከረም ወር የተባረከ ነው፤ እሱውም የግብጽ እና የኢትዮጵያ ዓመቶች መጀመርያ ነው፡፡ የዚህ ወር ቀኑ እና ሌሊቱ እኩል 12 ሰዓት ነው» ይላል፡፡ ይህ የሚያመለክተን በመስከረም አንድ ቀኑ እና ሌሊቱ እኩል የሆነ አንድ ቀን እንጂ በግማሽ ሌሊት እና በሙሉ ቀን የሚቆጠር አይደለም ማለት ነው፡፡

ምንም እንኳን በየወራቱ የቀኑ እና የሌሊቱ ርዝመት ልዩነት ቢኖረውም ሰዓቱ ግን እኩል አሥራ ሁለት ሰዓት ቀን እና ሌሊት ነው፡፡ ለምሳሌ አሜሪካውያን በዓመት ሁለት ጊዜ የሰዓት ማስተካከያ ወደፊት እና ወደ ኋላ ያደርጋሉ፡፡ አውሮፓውያን፣ በተለይም ሰሜኖቹ ደግሞ ከአንድ ሰዓት ሌሊት እስከ ሁለት ሰዓት ቀን የሚደርሱበት ጊዜ አለ፡፡ በኛ ግን የቀኑ እና የሌሊቱ ርዝመት ብዙም ልዩነት የለውም፡፡

<u>ቀኑ</u> <u>ሌሊቱ</u>

መስከረም 12 ሰዐት 12

ጥቅምት 11 13

ኅዳር 10 14

ታኅሣሥ 9 15

ጥር 10 14

የካቲት 11 13

መጋቢት 12 12

ሚያዝያ 13 11

ግንቦት 14 10

ሰኔ 15 9

ሐምሌ 14 10

ነሐሴ 13 11

ይሆናሉ፡፡ ይህም የሚያሳየን ቀኑም ሆነ ሌሊቱ ከአሥራ አምስት እንደማይረዝም፤ ከዘጠኝ እንደማያንስ ነው፡፡

እንግዲህ አዲስ ዓመት በመስከረም ወር እንዲብት የተደረገበት አንዱ ምክንያት ቀኑ እና ሌሊቱ እኩል የሚሆንበት ጊዜ ስለሆነም ነው፡፡

ሁለተኛው ነገር ደግሞ የዓመቱን ወራት የምናወጣው በምን አቆጣጠር ነው የሚለው ነው፡፡ ቀደም ብለን እንዳየነው የዓመቱን ወራት የምንቆጥረው በፀሐይ አቆጣጠር ነው፡፡ በፀሐይ አቆጣጠር ደግሞ መዓልቱ ሌሊቱ ይስበዋል፡፡

ምክንያቱም ፀሐይ የሚሠለጥነው በቀን ነውና /ዘፍ 1፤14፣16/፡፡ ያ ከሆነ ደግሞ በአቆጣጠራችን ቀኑ ቀድሞ ይጀምራል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የኛ አንድ ሰዓት ማለዳ ላይ እንጂ እኩለ ሌሊት ላይ ሊጀምር አይችልም፡፡

ሦስተኛው ደግሞ የሰዓት አቆጣጠራችን ነው፡፡ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር አንድ ብሎ የሚጀምረው መቼ ነው? አዲሱን ዓመት በእኩለ ሌሊት የሚያውጁት ሚዲያዎች እንኳን መልሰው ጠዋት ይነሡና «መስከረም አንድ ቀን ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ነው» ይሉናል፡፡ የፈረንጆቹ ሰዓት ግን በዚያ ሰዓት 7 ሰዓት ነው የሚለው፡፡ ምክንያቱም እኩለ ሌሊት ላይ አንድ ብሎ ጀምሯልና፡፡ አንድ ሰዓት ደግሞ ስድሳ ደቂቃዎች እና 3600 ሰኮንዶች ነው፡፡ ስለዚህም አንድ ሰዓት ለማለት እነዚህ ተቆጥረው ማለቅ አለባቸው፡፡ እነዚህ መቆጠር የሚጀምሩት ደግሞ ከጠዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ነው፡፡ አሥራ ሁለት ሰዓት የሌሊቱ ማጠናቀቂያ ነውና፡፡

በአራቱ ወንጌላውያን ምግብና እናከብር ካልን ደግሞ በየአራት ዓመቱ አዲሱ ዓመት የሚገባ እና የሚወጣበት ይለያያል ማለት ነው፡፡ ማቴዎስ ምግብናውን ማታ በሠርክ 12 ሰዓት ጀምሮ በመንፈቀ ሌሊት በስድስት ይፈጽማል፤ ማርቆስ ምግብናውን በመንፈቀ ሌሊት ይጀምራል፣ በነግህ 12 ሰዓት ይፈጽማል፤ ሉቃስ ምግብናውን በነግህ 12 ሰዓት ይጀምራል፣ በእኩለ ቀን 6 ሰዓት ይፈጽማል፤ ዮሐንስ ምግብናውን በቀትር 6 ሰዓት ይጀምራል፣ በሠርክ 12 ሰዓት ያልቃል፡፡ እናም በምግብናቸው መሠረት ከሄድን ደግሞ በየዓመቱ የአዲሱ ዓመት መግቢያ ይለያያል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለሕዝቡ መምታታትን ይፈጥራል፡፡

አውሮፓውያንም ቢሆኑ ይህ በየዓመቱ ያለውን የወንጌላውያን መለያየት ያውቁታል፡፡ ነገር ግን የአዲስ ዓመት መግቢያቸውን በእኩለ ሌሊት ያደረጉት አንድ ወጥ ለማድረግ ነው፡፡ እኛም በዚያው በእኩለ ሌሊቱ ብንቀጥለው ምናለ? የሚሉ ሃሳብ አቅራቢዎች አሉ፡፡ ቀደም ብለን እንዳየነው የእነርሱ የዘመን መለወጫቸው ከሰዓት አቆጣጠራቸው ጋር አብሮ ይሄዳል፡፡ የኛ ግን ዘመን ለወጥን ብለን መልሰን ሰባት፣ ስምንት እያልን መቁጠሩ መምታታት ነው፡፡

እንግዲህ እነዚህን ነጥቦች ስናያቸው የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት በእኩለ ሌሊት ሊጅምር የሚችለው የወንጌላውያንን መግቦት ከተከተልን በዘመነ ማርቆስ ብቻ ነው፡፡ ያም ቢሆን ከሰዓት አቆጣጠራችን ጋር ይጋጫል፡፡ ከሰዓት አቆጣጠራችንም ሆነ ከባህላችን ጋር፣ ብሎም ከመስከረም የቀን እና ሌሊት እኩል መሆን ጋር የሚገጥመው አዲሱን ዓመት በማለዳ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ መቀበሉ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ጋዜጠኞች እና አርቲስቶች ጳጉሜ አምስት እና ስድስት ሌሊት ተነሥተው መከራ ከሚያሳዩን ሰነድ ማገላበጥ እና ምሁራኑን መጠየቅ አለባቸው፡፡ ሊቃውንቱም ቢሆኑ ደፍረው ወጥተው ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የውይይት መድረክ የሚያዘጋጁ አካላትም አንዱ የመወያያ ጉዳይ አድርገው ፈር እንድንይዝ ቢያደርጉ ይመሰገኑበታል፡፡

ይበልጥ ደግሞ ያለ ምርምር በዘፈቀደ እየተፈጸመ ያለው ስሕተት ሕግ ሆኖ እንዳይቀጥል በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 51/20 መሠረት ፓርላማው አንዳች ነገር ማድረግ አለበት፡፡ በሀገሪቱ ወጥ የሆነ የዘመን አቆጣጠር የመወሰን ሥልጣን የተሰጠው የፌዴራሉ መንግሥት ሊቃውንቱን፣ ባለሞያዎችን እና ሕዝቡን አማክሮ፤ ሰነድ አገላብጦ እና ታሪክ መርምሮ ይህንን ዝብርቅርቁ የወጣውን የአዲስ ዓመት የመባቻ ሰዓት ጉዳይ አንዳች እልባት የሚሰጥ ዐዋጅ ማወጅ ይጠበቅበታል፡፡

***መልካም ዘመን***

*ናይሮቢ፣ ኬንያ*

# [ምን ዓይነት ሲኖዶስ ያስፈልገናል?]

ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያን የመጨረሻው ላዕላይ አካል፣ የትምህርተ ሃይማኖቷ፣ የሥርዓቷ እና የትውፊቷ ጠባቂ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱን የመወከል የመጨረሻው ሥልጣን ያለው፣ መናፍቃንን እና ከሀድያንን ለማውገዝ፣ የተመለሱትንም ይቅርታ ለማድረግ ሥልጣን ያለው የቤተ ክርስቲያን አካል ነው፡፡

ከላይ ከተገለጡት ሃይማኖታዊ ተግባራት በተጨማሪ የፋይናንስ፣ የሠራተኛ አስተዳደር፣ የንብረት፣ የይዞታ፣ የማኅበራዊ ጉዳዮች፣ የቅርስ እና የቤተ ክርስቲያኒቱን ግንኙነት በተመለከተ ፖሊሲ እና መመርያ የሚያወጣ፣ አቅጣጫ የሚወስን እና የመጨረሻውን ውሳኔ የሚሰጥ አካልም ነው፡፡ ቅዱስ ሲኖዶስ ሃይማኖታዊ፣ ሀገራዊ፣ ማኅበራዊ፣ ዓለም ዐቀፋዊ እና ሰብአዊ ኃላፊነቶች ያሉበት የቤተ ክርስቲያን ሉዓላዊ አካል ነው፡፡

እነዚህን ከባድ ኃላፊነቶቹን መወጣት ይችል ዘንድ ሃይማኖታዊ፣ ኍባሬያዊ እና አስተዳደራዊ ጥንካሬዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡

***ሃይማኖታዊ***

የአንድ ሲኖዶስ ሃይማኖታዊ ጥንካሬ ሲባል አባላቱ በሐግ እና በሥርዓት የተሾሙ፣ እምነታቸውን ጠብቀው የሚያስጠብቁ፣ ለእምነታቸው ታማኝነት ያላቸው፣ ላመኑበት ነገር እስከ መጨረሻው ለመቆም ጥብአት እና ጥንካሬ ያላቸው ማለት ነው፡፡

በቤተ ክርስቲያናችን የቅዱስ ሲኖዶስ ኣባት የሚሆኑት ብጹአን ሊቃነ ጳጳሳት ናቸው፡፡ ስለዚህም የሲኖዶሱ ጥንካሬ በብጹአን ጳጳሳት ጥንካሬ ላይ የተመሠረተ ነው ማለት ነው፡፡ ይህም ጥንካሬ በሚከተሉት ሁኔታዎች ይገለጣል፡፡

***የሃይማኖት ትምህርት ብቃት***

የቅዱስ ሲኖዶስ አንዱ ተግባር የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት መጠበቅ እና መመስከር ነው፡፡ ይህንን ለመወጣት ደግሞ አባላቱ የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት በሚገባ ያወቁ፣ዐውቀውም ለመመስከር የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ አንድ ሲኖዶስ ይህንን የመሰሉ አባቶች ካሉት ሊቃነ ጳጳሳቱ ነገረ ሃይማኖትን ሲያስተምሩ፣

ሲያብራሩ እና ሲተነትኑ ይታያሉ፡፡ ምእመናን ሃይማኖታቸውን እንዲጠብቁም መጻሕፍትን ይጽፋሉ፤ ለመናፍቃን ጥያቄ በየጊዜው መልስ ይሰጣሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሚያከራክሩ፣ የሃሳብ ልዩነት የተፈጠረባቸው እና ምእመናንን የሚያደናግሩ ጉዳዮች ላይ እየተወያዩ አንድ ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡

**የቤተ ክርስቲያን ሀብታት ዕውቀት**

የአንድ ጠንካራ ሲኖዶስ አባላት የቤተ ክርስቲያኒቱን ሥሪት በሚገባ ያውቁታል፡፡ ገዳማዊ ሥርዓቷን፣ የቅዳሴ ሕይወቷን፣ የጸሎት ጉዞዋን፣ የቅርስ ሀብቷን፣የንብረት ይዞታዋን፣ ታሪኳን እና ባህልዋን፣ ችግርዋን እና ፈተናዋን በሚገባ ይረዳሉ፡፡ በዚህ ረገድ ለሚጠየቁት ጥያቄ በቂ መልስ ይሰጣሉ፡፡ ችግሮች ተባብሰው አደጋ ከማድረሳቸው በፊትም መፍትሔ ይሰጣሉ፡፡

**መንፈሳዊ ብቃት**

የአንድ ጠንካራ ሲኖዶስ አባላት በምእመናኑ፣ በሚያገለግሉበት ድርሻ እና በራሱ በሲኖዶሱ የተመሰከረለት ሕይወት ያላቸው ናቸው፡፡ ምእመናንን የሚያሰናክል፣ በፍርድ ቤቶች አደባባይ የሚያውል፣ እነርሱንም በቆራጥነት ከመጋደል የሚያግድ ነውር ነቀፋ አይኖርባቸውም፡፡ ምእመናን አፋቸውን ሞልተው ይመሰክሩላቸዋል፡፡ በሕግ ከሚያስጠይቅ ወንጀልም ነጻ ናቸው፡፡

የጸሎት፣ የስግደት፣ የትምህርት፣ የቅዳሴ፣ የተባሕትዎ፣ የተጋድሎ ሕይወታቸው ለሌሎች አርአያ የሚሆን ነው፡፡ ከምቾት እና ቅንጦት ይልቅ ቀላል እና ጽዱ የሆነ አኗኗርን ይመርጣሉ፡፡ ከሀብት ክምችት ይልቅ የጸጋ ስጦታን በብርቱ ይፈልጋሉ፡፡ ከዘመዶ ቻቸው ይልቅ የመንፈስ ልጆቻቸውን ያሰባስባሉ፡፡ ከምድራዊ ወንዝ ይልቅ ሰማያዊውን የሕይወት ወንዝ ይሻሉ፡፡

በገዳማዊ ሕይወታቸው የተመሰከረላቸው፤ በየጊዜው በገዳማቱ ሱባኤ የሚይዙ፤ ከሥጋዊ መፍትሔ ይልቅ መንፈሳዊ መፍትሔ የሚመርጡ ይሆናሉ፡፡ በከተሞች ከመቀመጥ ይልቅ በገዳማቱ ማሳለፍን፤ የገጠር ምእመናንን መጎብኘትን፣ የሕዝቡን ችግር መፍታትን ይመርጣሉ፡፡ ሕመሙማንን ለመጠየቅ በሐኪም ቤቶች፣ ርሃብተኞችን ለመጎብኘት በረሃብ ቦታዎች፣ ገበሬዎችን ለማበረታታት በገጠሮች፣ ሠራኞችን ለማጽናት በፋብሪካዎች ይገኛሉ፡፡ የሕዝብ አባትም ይሆናሉ፡፡

መኪና ከየት እገዛለሁ፣ ቤትስ መቼ እሠራለሁ ብለው አይጨነቁም፡፡ አገልግሎታቸውን ያዩ ምእመናን መኪናውን ያዘጋጃሉ፤ በመንበረ ጵጵስናቸውንም ይሠሩላቸዋል፡፡ አይናገሩም፤ ነገር ግን በፍቅር ያስደርጋሉ፤ አይለምኑም፣ ነገር ግን በሃይማኖት ያስፈጽማሉ፡፡

ሲሆን ሲሆን እግዚአብሔር ትምህርታቸውን በተአምራት ያጸናላቸዋል፡፡ የማስተማር፣ አጥምቆ የመፈወስ፣ ጽፎ የማስረዳት፣ ጸልዮ ግዳጅ የመፈጸም፤ ተክሎ የማፍራት፣ገዳም ተክሎ የማጽናት፣ ጸጋን ያድላቸዋል፡፡ ምእመናኑ እንደ አለቃ ሳይሆን እንደ አባት፣ እንደ ባለ ሥልጣን ሳይሆን እንደ መምህር ያዩዋቸዋል፡፡ እነርሱ እረኞች ናቸው እንጂ ምንደኞች አይደሉምና፡፡

**አስተዳደራዊ**

አስተዳደራዊ ብቃት ስንል የየአንዳንዱ የሲኖዶስ አባል እና የምልዐተ ጉባኤው አስተዳደራዊ ብቃት ማለታችን ነው፡፡

**ግላዊ**

እያንዳንዱ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት አስተዳደራዊ ብቃት ከሌላቸው የሁሉም ውሑድ የሆነው ምልዐተ ጉባኤ ብቃት አይኖረውም፡፡ ይህንን ብቃት ለማግኘት ደግሞ አመራረጥ፣ ልምድ እና ሥልጠና ወሳኞች ናቸው፡፡

**አመራረጥ**

የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የሚሆኑ ጳጳሳት ሲመረጡ ከሃይማኖታዊ ብቃት እና ዕውቀት በተጨማሪ አስተዳደራዊ ዕውቀት እና ብቃት ወሳኞች ናቸው፡፡ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ለምሳሌ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ለኤጲስ ቆጶስነት የምትመርጣቸውን አባቶች አስቀድማ በመምረጥ በልዩ ልዩ የኃላፊነት ቦታዎች ትመድባቸዋለች፣ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ታደርጋለች፣ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ቦታዎች ገብተው ያያሉ፣ ይፈተናሉ፡፡ ድክመታቸውን ያሻሽላሉ፣ ብርታታቸውን ያጠነክራሉ፡፡

በመካከሉ ነውር ነቀፋ ከተገኘባቸው፤ ሕዝብ የሚያማርራቸው፣ ሀብት እና ገንዘብ የሚያባክኑ፣ አስተዳደራቸው የማይሻሻል እና ለሙስና የተጋለጠ ከሆነ ወደ ቀጣዩ የክህነት መዓርግ አይሸጋገሩም፡፡ ነገር ግን በበጎ ሥራቸው የተመሰከረላቸው፣ አብረዋቸው የሠሩት አካላት ያመሰገኗቸው እና የሥራ ፍሬያቸው የሚታይ ከሆነ ቤተ ክርስቲያኒቱ ትሾማቸዋለች፡፡

ቤተ ክርስቲያን ብጹዐን ጳጳሳትን ከሾመች በኋላ ልታስብበት የሚገባ አንዱ ጉዳይ የሚያስፈልጋቸውን መሣርያ ስለማሟላት ነው፡፡ መጀመርያ ደረጃ ታውጣ፡፡ ተመሳይ ደረጃ ያላቸው መንበረ ጵጵስናዎች፣ የቤት ዕቃዎች፣ አልባሳት፣ ተመሳይ ደረጃ ያላቸው መኪኖች፣ የአገልግሎት መሣርያዎች እንዲኖሯቸው ሕግ ታውጣ፡፡ ግዥው በአንድ መምሪያ ሥር፣ ከአንድ የበጀት ቋት ይሁን፡፡ ሽላሚ ያገኘ ባለሚሊዮን መኪና ያላገኘ ባለ በቅሎ መሆን የለበትም፡፡ ጋምቤላም፣ አሶሳም፣ ጂግጂጋም፣ አዲስ አበባም ተመሳሳይ ደረጃ ይኑራቸው፡፡ አባ እገሌ በዚህን ያህል ብር መኪና ገዙ የሚለው ዜና እንዲቆም ቤተ ክርስቲያኒቱ በዕቅድ ታሟላላቸው፡፡ መኪና ለአባቶቻችን ምናቸው

ነው፡፡ እንዲያውም ለአሶሳ፣ ለጋምቤላ፣ ለውጋዴን፣ ለሐረር፣ ለአፋር አህጉረ ስብከት ጳጳሳት ከአገልግሎታቸው አንፃር ሄሊኮፕተርም ያስፈልጋቸዋል፡፡ የሀገሪቱ ሕግ ከፈቀደ፡፡ ነገር ግን ይህ ሁሉ በሲኖዶሱ ተፈቅዶ በዕቅድ ይገዛ እንጂ በሽልማት እና በስጦታ ስም መሆን የለበትም፡፡ አንዱ ተደሳች ሌላው ተመልካች መደረገም አይገባውም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ እንደ ግብጽ እና አርመን ቤተ ክርስቲያን አባቶች የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በበጀት እንጂ በደመወዝ መተዳደር የለባቸውም፡፡ የሚያስፈልጋቸውን ቤተ ክርስቲያን ታሟላ፡፡ ከዚያ ውጭ ለጳጳሳት ደመወዝ መክፈል እረኞችን ቅጥረኞች ማድረግ ነው፡፡ ጳጳሳትም ለዕለት ከሚጠቀሙበት በቀር ቋሚ ሀብት ማፍራት፣ ቤት መሥራት ዘር መዝራት አያስፈልጋቸውም፡፡ ቤተ ክርስቲያን የማን ሆና ነው እነርሱ በየመንደሩ ቤት የሚሠሩት፡፡

በምእመናኑ ድጋፍ እና ፍቅር የተሾሙ፣ ቤተ ክርስቲያን የምትመሰክርላቸው አባቶች ከተሾሙ ነገ ዐረፍተ ዘመናቸው ሲደርስ መቀበር ያለባቸው በሀገረ ስብከታቸው ነው፡፡ ቫቲካንን ያየ ሰው ከሚቀናባቸው ነገሮች አንዱ ለፖፖቹ የተዘጋጀው የቀብር ሥርዓት ነው፡፡ እኛም በየሀገረ ስብከቱ የታወቀ የቀብር ቦታ፣በተለይም በገዳማት መዘጋጀት አለበት፡፡ ይህም ቦታ ምእመናን የሚጸልዩበት፣ሻማ የሚያበሩበት እና የአባቶች ንዋየ ቅድሳት እና አልባሳት የሚቀመጡበት መሆን ይገባዋል፡፡ አንድ ሊቀ ጳጳስ መቀበር ያለበት ባገለገለበት ሀገረ ስብከት እንጂ ዘመዶቹ ባሉበት ቦታ መሆን የለበትም፡፡ ሲያርፍም ንብረቱ ለአገለገለበት ሀገረ ስብከት መሰጠት አለበት፡፡ ያም ሀገረ ስብከት ለምእመናን በቅርስነት መታየት ያለባቸውን በመቃብራቸው አካባቢ ሊታዩ በሚችሉበት ቦታ ማስቀመጥ፣ሌሎቹን ደግሞ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ማድረግ ይገባዋል፡፡

### ሥልጠና

አስተዳደራዊ ክሂሎት በአንድ ጀምበር አይመጣም፣ በአንድ ኮርስም አይገነባም፡፡ ነገር ግን ልዩ ልዩ ዘዴዎችን፣ወቅታዊ አሠራሮችን እና የተለዋወጡ ሕጎችን ለማወቅ እንዲቻል የሥራ ላይ ሥልጠናዎች ወሳኞች ናቸው፡፡ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ለጽድስና መብቃት ማለት በሁሉም ነገር መመረቅ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህ ግን ፈጽሞ ስሕተት ነው፡፡ ሰው ምሉዕ በኩልሄ ሊሆን አይችልም፡፡ ነገር ግን ሁሉን አቀፍ መሆን ይችላል፡፡ በተለይም ዓለማዊ አሠራሮች፣ ሕጎች፣ መዋቅሮች እና ስልቶች በየጊዜው ስለሚለዋወጡ እነርሱን ተከታትሎ ለማወቅ ወቅታዊ ሥልጠናዎች ያስፈልጋሉ፡፡ ይህ ደግሞ ብጹአን አባቶችንም ይመለከታል፡፡

ለምሳሌ በኛ ቤተ ክርስቲያን ለጳጳሳት ሥልጠና ማዘጋጀት እና መስጠት እንደ ድፍረት ይቆጠራል፡፡ ይህ ግን ፈጽሞ ስሕተት ነው፡፡ መሠለጥን ማለት አላዋቂነትን መግለጥ ማለት አይደለም፡፡ ዐዋነትን ማጽናት እንጂ፡፡ ወቅቱን እንድንቀድመው፣ ከምእመናንም የተሻለ እንድናውቅ የሚያደርገን ነው፡፡

ዛሬ ዛሬ በየሀገረ ስብከቱ ጳጳሳት ፋይናንስ ያንቀሳቅሳሉ፣ሀብት ያስተዳድራሉ፣የቦታ ይዞታ ጉዳይን ያያሉ፣ የሠራተኛ አስተዳደር ይመለከታቸዋል፣ የሕግ ክርክሮችን ያያሉ፣ የቤተሰብ ጉዳዮችን ይዳኛሉ፣ በጤና ጉባኤያት ይሳተፋሉ፡፡ እነዚህ ትምህርቶች ደግሞ በአብነት ት/ቤቶቻችን ውስጥ የሉም፡፡ ብጹአን አባቶች እነዚህን ጉዳዮች በሚገባ ተገንዝበው ለመምራት እና ለመወሰን እንዲችሉ ወቅታዊ ሥልጠናዎች ያስፈልጓቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በመላው ዓለም በተበተኑበት በአሁኑ ዘመን አባቶች በመገናኛ ብዙኃን ተደራሽ መሆን አለባቸው፡፡ ሲሆን ሲሆን እያንዳንዱ ሀገረ ስብከት የየራሱ ዌብ ሳይት ያስፈልገዋል፣ አባቶችም ፌስ ቡክን በመሳሰሉ መሣርያዎች ማስ ተማር አለባቸው፡፡ ትምህርቶቻቸውን በቪሲዲዎች እና በዲቪዲዎች ልናገኛቸው ይገባል፡፡ ለዚህ ለዚህ ደግሞ ዘመኑን የዋጀ ሥልጠና ወሳኝ ነው፡፡ ግብፆች ከ1400 በላይ ዌብ ሳይት ሲኖራቸው የኛ አባቶች እና ቤተ ክህነት አንድም ጠንካራ የመረጃ መረብ የለንም፡፡

በሀገር ዐቀፍ እና በዓለም ዐቀፍ መድረኮች ቤተ ክርስቲያንን ወክለው ጥናታዊ ጽሑፎችን ማቅረብ፣ የቀረቡትን ሰምቶ ሃሳብ መስጠት፣የቤተ ክርስቲያኒቱን ዐቋም ማንፀባረቅ፣ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተገኝተው ማብራርያ መስጠት፣ መንግሥት ሕግ ሲያወጣ ተገኝተው የቤተ ክርስቲያንን መብት ማስከበር ዘመኑ ይጠይ ቃቸዋል፡፡

እስካሁን ድረስ በጥናታዊ መጽሔቶች ውስጥ ጥናታዊ ጥሑፋቸው የታተመላቸው የቤተ ክርስቲያናችን ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ብቻ ናቸው፡፡

**ልምድ**

የመንግሥትን ልዩ ልዩ ኃላፊዎች እና የፓርላማ አባላት ብንመለከት በየጊዜው ወደ ልዩ ልዩ ሀገሮች እየተጓዙ ልምድ ይቀስማሉ፡፡ ይህ ነገር ለብጹአን አባቶችም ያስፈልጋል፡፡ በተለይም በሃይማኖት ከሚመስሉን አኃት አብያተ ክርስቲያናት ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ ዕውቀት ያስገበያል፡፡ ከእነርሱ ድክመት እና ጥንካሬም እንድንማር ያደርጋል፡፡ ስለ ችግሮች አፈታት፣ስለ ምእመናን አያያዝ፣ ስለ ሀብት እና ንብረት አስተዳደር፣ ስለ ገዳማት አሠራር፣ ስለ ስብከተ ወንጌል ሥርጭት ልምድ መቅሰም ያስፈልጋል፡፡

በሌላም በኩል በሀገር ውስጥ ከሚገኙ መሥሪያ ቤቶች፣ ተቋማት፣ ድርጅቶች፣ የትምህርት ማዕከላት እና ከመሳሰሉት ልምድ መቅሰሙ፣የሞያ እና የልምድ እገዛ መጠየቁ፣ ብሎም ተባብሮ መሥራቱ የብጹአን አባቶችን አገልግሎት ውጤታማ ያደርገዋል፡፡

**ጉባሬያዊ**

ቅዱስ ሲኖዶስ እንደ አንድ ተቋም አስተዳደራዊ ብቃት እና ጥንካሬ ያስፈልገዋል፡፡ አሁን ባለው አሠራር የቤተ ክርስቲያናችን ሲኖዶስ ከጊዜያዊ ኮሚቴ ባለፈ መካሪም አማካሪም የለውም፡፡ ራሱ ያረቅቃል፣ ራሱ፣ ይፈትሻል፣ ራሱ ያጸድቃል፡፡ ሌሎች የቤተ ክርስቲያን አካላት እና ምእመናን የሚሳተፉበት ምንም ዓይነት መንገድ የለውም፡፡

ከአኃት አብያ ክርስቲያናት ግብጽን፣ ከሌሎቹ ደግሞ የሮም ካቶሊክን ብንመለከት ግን ይህ ዓይነት አሠራር የላቸውም፡፡ ሲኖዶሳቸው በሥሩ ቋሚ ኮሚቴዎች አሉት፡፡ እነዚህ ቋሚ ኮሚቴዎች በሊቃነ ጳጳሳት፣ በሊቃውንት

ቤተ ክርስቲያን፣በባለሞያዎች እና በጽ/ ቤት ሠራተኞች የተደራጁ ናቸው፡፡ አስቀድመው ጉዳዮች የሚታዩት፣ የሚረቅቁት፣ የሚስተካከሉት እና ለውሳኔ የሚቀርቡት በእነዚህ ቋሚ ኮሚቴዎች አማካኝነት ነው፡፡

ሲኖዶሱም አንድን አጀንዳ ተነጋግሮበት ለዝርዝር እይታ ወደ እነዚህ ኮሚቴዎች ነው የሚመራው፡፡ ዕቅድ የሚዘጋጀው፣ የፖሊሲ ረቂቅ የሚቀርበው፣ የጳጳሳት ምርጫ ዕጩ የሚቀርበው፣ የኃላፊዎች ሹመት ዕጩ የሚቀርበው በእነዚህ ኮሚቴዎች ነው፡፡ ይህ አሠራር ነገሮች ጊዜ ተወስዶባቸው በዝርዝር እንዲታዩ ከመርዳቱም በላይ ከስሕተትም ይጠብቃል፡፡ የሚመለከታቸው አካላትም ሃሳብ እንዲሰጡ ዕድል ይሰጣል፡፡

ለምሳሌ አንድ የሕግ ረቂቅ ሲዘጋጅ የሕግ ኮሚቴው ከቅዱስ ሲኖዶስ በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት ያረቅቃል፤ የሚመለከታቸውን አካላት እና ግለሰቦች ጠርቶ ያወያያል፤ ሃሳብ ያሰባስባል፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ ጨምቆ እና የሕግ መልክ አስይዞ ለሲኖዶሱ ያቀርባል፡፡ ቅዱስ ሲኖዶስም የቀረበለትን መርምሮ ያጸድቃል፡፡ በዚህ ሂደት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ ምእመናን፣ ባለሞያዎች እና ሌሎች መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ስለተሳተፉበት የሲኖዶሱ ውሳኔ ተጠቃሽ፣ አግባቢ እና ሁሉም የሚቀበለው ይሆናል ማለት ነው፡፡

**ለምሳሌ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ የሚከተሉት ቋሚ ኮሚቴዎች አሉት፡፡**

1. የዶግማ እና መንፈሳዊ ትምህርት

2. የሕግ

3. የአህጉረ ስብከት ጉዳዮች

4. የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እና ትውፊት ጉዳዮች

5. መንፈሳዊ ግንኙነት

6. የሕዝብ ግንኙነት

7. የክህነት ጉዳዮች

8. የዕቅድ

እንዲሁም በጽ/ቤቱ ሥር ቃለ ጉባ የሚይዙ እና ውሳኔዎችን የሚከታተሉ ባለሞ ያዎች አሏቸው፡፡

**የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስም**

በብፁአን አበው የሚመሩ፤ ሦስት ጳጳሳት፣ሦስት ሊቃውንት፣ ሦስት ባለሞያ ምእመናን የሚሳተፉባቸው፣ በየራሳቸው የተሟሉ የጽ/ቤት መሣርያዎች፣ በጀት እና ድጋፍ ሰጭ የሰው ኃይል ያላቸው ቋሚ ኮሚቴዎች ቢኖሩት መልካም ነው፡፡ እነርሱም፡

1. **የዶግማ እና የቀኖና ጉዳዮች፡** የቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት እና ሥርዓት የሚያብራራ፣ ለሚነሡ ጥያቄዎች በሲኖዶሱ መወሰን ያለባቸውን የዶግማ እና የሥርዓት ጉዳዮች አርቅቆ የሚያቀርብ፣ ለሚነሡ ክርክሮች ዝርዝር ምላሽ የሚያዘጋጅ፤ ሥርዓት ሊሠራባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በመለየት ረቂቅ የሚያቀርብ፣ በቅዱስ ሲኖዶስ የሚታዩ የሃይማኖት መጻሕፍትን የሚመረምር፣ ከልዩ ልዩ አካላት ለሚቀርቡ የቤተ ክርስቲያንን ሃይማኖታዊ አስተያየት ለሚጠይቁ ጉዳዮች መልስ የሚያዘጋጅ፡፡

2. **የካህናት እና የክህነት ጉዳዮች፡** የካህናትን አሿሿም፣ ሥርዓት፣ አለባበስ፣ አቀጣጠር፣ የሥነ ምግባር ሁኔታ፣ ብዛት፣የሚመለከት፤ ክህነትን ለሚመለከቱ ቅሬታዎች እና ጥያቄዎች ዝርዝር መልስ የሚያዘጋጅ፤ በካህናት መካከል ለሚነሡና የሲኖዶሱን ውሳኔ ለሚፈልጉ ጉዳዮች ረቂቅ ውሳኔ የሚያዘጋጅ፡፡ ክህነትን እና ካህናትን በተመለከተ መጽደቅ ያለባቸውን ረቂቅ የሕግ ሃሳቦች የሚያመነጭ፤ ከልዩ ልዩ አካላት ካህናትን በተመለከተ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስ የሚያዘጋጅ፡፡ ስለሚሾሙ ኤጲስ ቆጶሳት መረጃ የሚያሰባስብ፣ሥልጠና የሚያዘጋጅ፣ እጩ የሚያቀርብ፡፡

3. **የገዳማት ጉዳዮች፡** የገዳማትን ይዞታ፣ሥሪት፣ የገዳማውያንን አገባብ፣ አኗኗር፣ የገዳማትን ሀብት እና ንብረት፣ የገዳማትን አስተዳደር፣ የምንኩስናን አሰጣጥ፣ የመነኮሳትን አመዘጋገብ፣ በተመለከተ የሚያይ፣ረቂቅ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ፣ሕግ የሚያዘጋጅ፡፡

4. **የቤተሰብ እና ማኅበራዊ ጉዳዮች፡** ክርስቲያናዊ ቤተሰብን በተመለከተ መውጣት ያለባቸውን ፖሊሲዎች እና መመርያዎች የሚያረቅቅ፣ ማኅበራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ሃሳብ የሚያቀርብ ነው፡፡ የቤተሰብ ምጣኔ፣የወሊድ መቆጣጠርያ፣ ኤች አይቪ/ኤድስ፣ የቤተሰብ ሕግ፣የሕፃናት አስተዳደግ፣ የአረጋውያን ሁኔታ፣ ጤና ጉዳዮች፣ የሴቶች መብት ጉዳዮች፣ ወሊድ እና ከወሊድ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች፣ የዚህ ኮሚቴ ጉዳዮች ናቸው፡፡

5. **የቅድስና እና ቅዱሳት መጻሕፍት ጉዳዮች፡** የቤተ ክርስቲያኒቱ ቅዱሳን እነማን እንደሆኑ፣ ታካቸው፣ ገዳማቸው፣ክብረ በዓላቸው ተጠንቶ በሲኖዶሱ እንዲጸድቅ፡፡ የቤተ ክርስቲያኒቱን መጻሕፍት የመለየት፣ በቀኖና ዕውቅና የመስጠት፣ በቅዱስ ሲኖዶስ መዓርገ ቅድስና ሊሰጣቸው የሚገቡ ቅዱሳንን ማጥናት እና ማቅረብ፤ የዚህ

ኮሚቴ ተግባራት ናቸው፡፡

6. **የፋይናንስ፣ የበጀት እና ኢኮኖሚ ጉዳዮች፡** የቤተ ክርስቲያኒቱን የገቢ ምንጮች ሃሳብ ማቅረብ፣ የፋይናንስ ሕጎችን ማርቀቅ፣ የፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማርቀቅ፣ የአብያተ ክርስቲያናትን የፋይናንስ አያያዝ በተመለከተ ሃሳብ ማቅረብ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ በኢኮኖሚ ራስዋን የምትችልበትን ሃሳብ ማቅረብ፡፡ በሀገሪቱ የፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ጉዳዮች የቤተ ክርስቲያኒቱ ድምፅ የሚሰማበትን መንገድ መተለም፤ ከልዩ ልዩ ክፍሎች የሚቀርቡትን የቤተ ክርስቲያኒቱን የበጀት ጉዳዮች ተመልክቶ ለቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ፡፡

7. **የንብረት፣ የአስተዳደር እና መረጃ ጉዳዮች፡** የቤተ ክርስቲያኒቱን ሠራተኞች ሁኔታ፣ የደመወዝ ደረጃ፣ የአስተዳደር ስልት እና መንገድ፣ አዳዲስ የአሠራር መንገዶችን፣ የመረጃ እና የመረጃ ቋትን በተመለከተ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን የመረጃ ግንኙነት በተመለከተ፣የዶከመንት እና አርካይቭን ጉዳይ በተመለከተ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን የንብረት እና ቅርስ አያያዝ በተመለከተ፣ የይዞታ እና ርስት ጉዳዮችን በተመለከተ የሚመለከትና ሀሳብ የሚያቀርብ፣ የፖሊሲ እና የመመርያ ረቂቅ የሚያቀርብ፡፡

8. **የውጭ ግንኙነት ጉዳዮች፡** የቤተ ክርስቲያኒቱን ኢኩሜኒካል ግንኙነት፣ ከአኃት አብያተ ክርስቲያናት፣ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት፣ ከዓለም ዐቀፍ ድርጅቶች፣ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ስለሚኖራት ግንኙነት የሚያጠና፣ የፖሊሲ እና የሕግ ረቂቅ የሚያቀርብ፣በሚወሰኑ ውሳኔዎች ላይ ሃሳብ የሚያቀርብ፡፡

9. **የሕዝብ ግንኙነት እና ሚዲያ ጉዳዮች፡** ስለ ቅዱስ ሲኖዶስ መረጃ የሚሰጥ፣ ጋዜጣዊ መግለጫ የሚያዘጋጅ፣ መታወቅ ያለባቸውን የቅዱስ ሲኖዶስን ውሳኔዎች ለሕዝብ የሚገለጡበትን መንገድ የሚያመቻች፤ የቅዱስ ሲኖዶስን እንቅስቃሴ የሚገልጡ የመረጃ መረቦችን የሚያደራጅ እና የሚከታተል፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ የሬዲዮ፣ የቴሌቭዥን፣ እና የኅትመት ሚዲያ እንዲኖሯት፣ ያሏትም እንዲበለጽጉ ለቅዱስ ሲኖዶስ ሃሳብ የሚያቀርብ፣ የፖሊሲ ረቂቅ የሚያዘጋጅ፣ የሚያማክር እና ሃሳብ የሚያመነጭ፡፡

10. **የወጣቶች እና ትምህርት ጉዳዮች፡** የሰንበት ት/ቤቶችን፣ የማኅበራትን እና ከወጣቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚያጠና፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ነባር እና ዘመናዊ ት/ቤቶችን በተመለከተ የትምህርት ፖሊሲ የሚያረቅቅ፣ ስለ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ኮሌጆች እና ማሠልጠኛዎች ሃሳብ የሚያቀርብ፣ የሚያማክር፤ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የትምህርት ተቋማት የፕሬዚዳንቶችን እና ዲኖችን ሹመት የሚያቀርብ፣

11. **የሕግ ጉዳዮች፤** በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጡ ሕጎችን አስቀድሞ የሚያይ፣ ከሌሎች ኮሚቴዎች ጋር በመሆን ሕጎች የቤተ ክርስቲያኒቱን አሠራር፣ የሕግን ቅርጽ እና የሀገሪቱን የሕግ አግባብ የጠበቁ መሆናቸውን የሚከታተል፣ ለሲኖዶሱ የሕግ ምክር የሚሰጥ፣የሚሻሻሉ ሕጎችን ለይቶ የሚያቀርብ፣ የአዳዲስ ሕጎች ሃሳብ የሚያመነጭ፡፡

እነዚህ ቋሚ ኮሚቴዎች ከላይ ከተጠቀሱት ተግባሮቻቸው በተጨማሪ ከሥራቸው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የጠቅላይ ቤተ ክህነት የሥራ ክፍሎች ይከታተላሉ፡፡ ሪፖርቶቻቸውን ይመረምራሉ፤ ዕቅዶቻቸውን ተመልክተው ለቅዱስ ሲኖዶስ ያቀርባሉ፤ በየጊዜው እየጠሩ በጉዳዮች ላይ ማብራርያ ይጠይቃሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ቅዱስ ሲኖዶስ ለመምሪያዎች፣ለኮሚሽኖች፣ለድርጅቶች እና ለልዩ ልዩ ተቋማት የሚሾሟቸውን ኃላፊዎች የሚመለከታቸው ኮሚቴዎች አጥንተው፣ መረጃ አዘጋጅተው ያቀርቡለታል፡፡ ይህ አሠራር ሲኖዶሱን ከሐሜት የሚያወጣ እና በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ እንዲሰጥ የሚያደርግ ነው፡፡

በሌላ በኩል በቤተ ክርስቲያናችን ሁሉም ጳጳሳት ተመሳሳይ ስም፣ መዓርግ እና አገልግሎት ነው ያላቸው፡፡ በአኃት አብያተ ክርስቲያናት ግን እንደዚህ አይደለም፡፡ ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚሾሙ ጳጳሳት ስማቸውም ድርሻቸውም የተለያየ ነው፡፡ ለምሳሌ ግብፃውያን የሚከተሉት ዓይነት ጳጳሳት አሏቸው፡፡

**ፓትርያርክ፡** የሲኖዶሱ ሰብሳቢ

**ሜጥሮጶሊጣን**፡ በታላላቅ ከተሞች እና በኢየሩሳሌም የሚሾሙ ጳጳሳት

**ሊቃነ ጳጳሳት፡** በሥራቸው ኮሬ ኤጲስ ቆጶሳትን እና ኤጲስ ቆጶሳትን የሚያስተዳድሩ እና ታላላቅ ሀገረ ስብከቶችን የሚመሩ፡፡ ለምሳሌ የአፍሪካ ሊቀ ጳጳስ

**አበ ምኔቶች፡** monastic Bishops ገዳማትን የሚያስተዳድሩ

**ኮሬ ኤጲስ ቆጶሳት፡** ለገጠሪቱ ቤተ ክርስቲያን የሚሾሙ፣ በሌላም በኩል በአንድ ሊቀ ጳጳስ ሥር ሆነው ሰፊ ሀገረ ስብከቱን ተካፍለው የሚያስተዳድሩ፡፡

**አጠቃላይ ጳጳሳት፡** General Bishops በሀገረ ስብከት ደረጃ ሳይሆን ለልዩ ልዩ ጉዳዮች የሚሾሙ፣ ለምሳሌ ለመምሪያዎች፡፡

**ጳጳሳት፡** Diocesan Bishops ሀገረ ስብከት ተሰጥቷቸው የሚሾሙ፡፡

**ረዳት ጳጳሳት**፡ ፓትርያርኩን በልዩ ልዩ ጉዳዮች የሚያማክሩ ጳጳሳት

**ሊቀ ካህናት**፡ በትዳር የሚኖሩ ካህናትን በመወከል በቅዱስ ሲኖዶስ የሚሰበሰብ ካህን፡፡ እነርሱ wakil-al batrakiya ይሉታል፡፡ የካህናትን ጉዳይ በሲኖዶሱ የሚያቀርብ ነው፡፡

***የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ሁሉንም ሊቃነ ጳጳሳት ከምታደርግ፡***

• ***ለታላላቅ ገዳማት አበምኔቶቻቸውን ጳጳሳት ቢያደርግ መልካም ነው፡፡*** ገዳማውያን ክህነት ለመቀበል እና ለቡራኬ ከተማ ከሚመጡ፣ የሥርዓት ጉዳዮችን ለማስወሰን ወደ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤቶች ከሚወጡ እዚያው ቢጨርሱ፡፡ በሌላም በኩል ገዳማት የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና ነገሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም የቅዱስ ሲኖዶስ የቅርብ ክትትል ያስፈልጋቸዋል፡፡

• **የቤተ ክርስቲያኒቱን ዋና ዋና ጉዳዮች የሚመሩ አጠቃላይ ጳጳሳት ቢኖሯት፡፡** ስብከተ ወንጌል መምሪያ፣ገዳማት መምሪያ፣ የወጣቶች ጉዳይ መምሪያ፣ የካህናት ጉዳይ መምሪያ፣ ወዘተ በጳጳሳት ቢመሩ፡፡ ሌሎች ድጋፍ ሰጭዎች፣ ማለትም የፋይናንስ፣ የአስተዳደር፣ የበጀት፣ የልማት፣ አስተዳደር እና ጠቅላላ አገልግሎት፣ ወዘተ በባለሞያ ምእመናን ወይንም ካህናት ቢመሩ፡፡

• ***እንደ አዲስ አበባ ላሉ ታላላቅ ከተሞች ሜጥሮጶሊጣን ቢመደቡ፡፡***

• ***ለታላላቅ ሀገረ ስብከቶች ሊቃነ ጳጳሳት ተመድበው በሥራቸው ኤጲስ ቆጶሳት ቢኖሩ፡፡*** ለምሳሌ ለአፍሪካ፣ ለአሜሪካ፣ ለአውሮፓ፣ እና በሀገራችንም ብዙ አድባራት እና ገዳማት ላሉባቸው አህጉረ ስብከት በሥራቸው ኤጲስ ቆጶሳት ተመድበው ሊቃነ ጳጳሳት ቢያስተዳድሯቸው፡፡ ይህ አሠራር አዳዲስ ኤጲስ ቆጶሳት ከነባሮቹ ልምድ እንዲያገኙ፤ አረጋውያን አባቶችም በኤጲስ ቆጶሳት ታግዘው አገልግሎታቸውን እንዲፈጽሙ ያደርጋቸዋል፡፡

• ***ኤጲስ ቆጶሳት፡*** በሊቃነ ጳጳሳት ሥር ከሚመደቡት በተጨማሪ ለታላላቅ እና ታሪካዊ አድባራት ኤጲስ ቆጶሳት ቢመደቡ መልካም ነው፡፡ ለምሳሌ አኩስም ጽዮን፣ ላሊበላ፣ እንጦጦ ኪዳነ ምሕረት፣ ቁልቢ ገብርኤል፣እና የመሳሰሉት ካላቸው ታሪካዊ ቦታ፣ ከቅርሶቻቸው፣ ከሚያስተዳድሩት አገልጋዮች እና ሀብት ብዛት አንፃር የቅዱስ ሲኖዶስ ትኩረት ያስፈልጋቸዋል፡፡

• ***ረዳት ጳጳሳት፡*** ቅዱስ ፓትርያርኩን የሚያማክሩ፣ የቅዱስ ፓትርያርኩን ተልእኮ የሚያፋጥኑ አባቶች፡፡

• ***የሕጋውያን ካህናት ተወካይ ሊቀ ካህናት፡*** የቤተ ክርስቲያናችን ቅዱስ ሲኖዶስ ሊያስብባቸው ከሚገቡ ጉዳዮች አንዱ የሕጋውያን ካህናት ጉዳይ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ አብዛኛውን የሹመት ቦታ መነኮሳት ብቻ እየያዙት መምጣታቸው ሕጋዊ ካህናትን እያስከፋና፣ያለ ፍላጎታቸው ለሹመት ሲሉ የሚመነኩሱ እንዲበዙ አድርጓል፡፡ ከዚህም በላይ የሕጋውያኑ ጉዳይ በሌሉበት እንዲታይም አድርጓል፡፡

የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ጥያቄ በሦስት ደረጃ ለመመለስ ሞክራለች፡፡ የመጀመርያው የከተሞችን እና የውጭ ሀገርን አገልግሎት ለሕጋውያን ካህናት ብቻ በመስጠት፤ የአድባራት አስተዳዳሪነትን፣ የልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍሎች ኃላፊነትን በመፍቀድ፣ በሲኖዶሱ ቋሚ ኮሚቴዎች ውስጥ ተሳትፎ እንዲኖራቸው በማድረግ፤ ሦስተኛው እና ከፍተኛው ደግሞ በቅዱስ ሲኖዶስ ውስጥ አንድ ወኪል እንዲኖራቸው በማድረግ ነው፡፡

ቅዱስ ሲኖዶስም እነዚህን ነገሮች ሊያስብባቸው ይገባል፡፡ የካህናት ልጆች የአባቶቻቸውን አስተዳደራዊ በደል እና መገፋት እያዩ «ቤተ ክርስቲያንን እያሳየን» ከማለታቸው በፊት ጉዳዩ መፍትሔ ይሻል፡፡ እንደ እኔ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የተከተለችው መንገድ የተሻለ ይመስለኛል፡፡

እንግዲህ በአጠቃላይ ሲኖዶሳችን ግንቦት እና ጥቅምት በመጣ ቁጥር የሚናጥ፣ ማንም የፈለገ በሩን እየሰበረ የሚያስፈራራው፣ በሌላ ቦታ ቦታ ያጡ ሴት ወይዛዝርት ጉልበት መሞከርያ፣ የአንድ ሰው አምባገነንነት የሚንጸባረቅበት፣ በቤተ ዘመድ አሠራር የተተበተበ፣ በሀገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ምንም ድርሻ የሌለው፣ በብዙ ያልተመለሱ ሃይማኖታዊ እና ሥርዓታዊ ጉዳዮች የተከበበ እንዳይሆን ከምንጊዜውም በላይ ሊታሰብበት የሚገባው ጊዜ አሁን ነው፡፡

ቤተ ክህነታችን የአስተዳደር እና የአሠራር አርአያ እንጂ የብልሹነት፣ የሙስና፣ የዘመድ አሠራር እና ብቃት የሌላቸው ሰዎች መከማቻ መሆን የለበትም፡፡ ለዚህ ደግሞ ጳጳሳት፣ ሊቃውንት፣ካህናት፣ ምእመናን፣መንግሥት፣ ሌሎችም የዚህችን ሀገር ዕድገት የሚመኙ ሁሉ አስተዋጽዖ ማድረግ አለባቸው፡፡ ይህቺ ቤተ ክርስቲያን ሳታድግ ሀገሪቱ ልታድግ በፍጹም አትችልምና፡፡

# የአንድ ዕብድ ትንቢት

አንድ ዕብድ አራት ኪሎ ላይ ጆሊ ባር ፊት ለፊት ቆሞ «ወደፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ በስድስት ይከፈላል፣ በስድስት ይከፈላል» እያለ ቡትቶውን እየጎተተ ይጮኻል፡፡ አጠገቡ የነበሩ ጋዜጣ ሻጮች «ዝም በል፣ ዕብድ፣ ተነሣብህ ደግሞ፤ማን ይከፍለዋል ደግሞ፤ መዓት አውሪ» አሉና ሊያባርሩት እጃቸውን ወነጨፉ፡፡ እርሱም በተራው ከት ብሎ ሳቀና «የዕውቀት ማነስ ችግር አለባችሁ፡፡ ኩላሊታችሁ ችግር አለበት፡፡ የኛ ሰው መከፋፈል ልማዱኮ ነው፡፡ በዝባዥ እና ተበዝባዥ፤ አድኃሪ እና ተራማጅ፤ ፊውዳል እና ፀረ ፊውዳል፤ ኢምፔሪያሊስት እና ፀረ ኢምፔሪያሊስት፤ አብዮተኛ እና ፀረ አብዮተኛ፤ ሕዝባዊ እና ፀረ ሕዝብ፤ ልማታዊ እና ፀረ ልማት፤ ኮሚቴ ሰብሳቢ እና ኪራይ ሰብሳቢ» መልሶ ከት ብሎ ሳቀ፡፡

ቀጠለ «ወደፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ በስድስት ይከፈላል» አለና የቀኝ እጁን መዳፍ ጠቅልሎ እንደ ጡሩንባ ነፋው፡፡

«ምን ተብሎ ነው የሚከፈለው» አሉት አንድ ጋዜጣ የሚያነበቡ አዛውንት፡፡

«ጥሩ ጥያቄ ነው» አለና ጉሮሮውን በስላቅ እንደመጠራረግ ብሎ «የሚበላ፣ የሚበላ /'በ' ይጠብቃል/፣ የማይበላ፣ የሚያባላ፣ የሚያስበላ፣ የሚያብላላ ተብሎ ይከፈላል» ይህንን ሲናገር በአካባቢው የሚያልፉትን የብዙዎችን ጆሮ ለመሳብ ችሎ ነበር፡፡ አንዳንዶቹም መንገዳቸውን ገታ አድርገው ያዳምጡት ጀምረዋል፡፡

«እስኪ ተንትነው» አሉት እኒያ አዛውንት ጋዜጣቸውን አጠፍ አድርገው፡፡

«'የሚበላ' ማለት ጤፍ መቶም መቶ ሺም፣ መቶ ሚሊዮንም ቢገባ መገዛቱን እንጂ የተገዛበትን የማያውቅ፤ በጋዜጣ ካልተጻፈ፣ በሬዲዮ ካልተነገረ በቀር የኑሮ ውድነቱ የማይነካው፤ የውጭ ምንዛሪ ቢጠፋም ባይጠፋም ዶላር የማያጣ፣ ወረፋ ቢኖርም ባይኖርም ባንክ እምቢ የማይለው፣ ጨረታውን ሁሉ ለማሸነፍ የሚያስችል ድግምት ያለው፤ ተራራ ቁልቁለት መውጣትና መውረድ ሳያስፈልገው ቤቱ ቁጭ ብሎ ሚሊየኖችን የሚያፍስ፤ ሰው ሁሉ በእጁ የጠቀለለው በእርሱ ጉሮሮ የሚያልፍለት፤ ሰው ሁሉ የጎረሰው በእርሱ ሆድ የሚቀመጥለት፣ ሰው ሁሉ ሮጦ እርሱ ሜዳልያ የሚሸለም፣ ለመብላት እንጂ ለመሥራት ያልተፈጠረ ማለት ነው፡፡

«'የሚበላ' ማለት ደግሞ ጉቦ ለመስጠት፣ ኪራይ ለመክፈል፣ ግብር ለመክፈል የተፈጠረ፡፡ ምንም ሕግ አክብሮ ቢሠራ አንዳች ጉርሻ ካላጎረሰ ሥራው የማያልቅለት፤ ለመጋገር እንጂ ለመብላት ያልታደለ ማለት ነው፡፡ 'ቅቤ አንጣሪዋ እያለች ጎመን ቀንጣሿን ምች መታት' ሲባል አልሰማችሁም፡፡ የርሱም ነገር እንደዚህ ነው፡፡ ለመበላት የተፈጠረ ነውና ሕገ ወጦቹ ተቀምጠው እርሱ በሕጋዊ መንገድ እየሠራ እና እየኖረ እርሱ ነው የሚከሰሰው፤ እርሱ ነው የሚጉላላው፡፡ እዚህ አንዳንድ ሠፈር ያሉ ቀበጥ ወላጆች ለልጆቻቸው ሁለት ሁለት ሞግዚት ነው አሉ የሚቀጥሩት፡፡ አንዷ አሳዳጊ ናት፡፡ አንዷ ደግሞ ልጁ ሲያጠፋ የምትመታ ናት፡፡ ልጃቸው እንዳያመው እርሱ ባጠፋ ቁጥር እርሷ ትመታለች፣ እርሷ ታለቅሳለች፡፡ እነዚህም እንደ እርሷ ናቸው፡፡

«'የማይበላ' የሚባለው ለቁጥር የሚኖረው ነው» አለና ወደ ሕዝቡ ዞወር ብሎ «አሁን ለምሳሌ እኔ እና እናንተ ጥቅማችን ለቁጥር ነው» ሲል ብዙዎች በፈገግታ አዩት፡፡ «አዎ እኛኮ ቁጥሮች ነን፡፡ ቁጥር ደግሞ ምዝገባ እንጂ ምግብ አያስፈልገውም፡፡ የኛ ሥራ መመዝገብ ነው፤ መብላት አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲቆጠር እንካተታለን፤ ሲበላ ግን አንካተትም፤ ርዳታ ለማግኘት እናስፈልጋለን፤ እርዳታውን ለመቀበል ግን አናስፈልግም፡፡ ስለዚህ ቁጥር ነን ማለት ነው፡፡ ወደፊት እንጀራን በቴሌቭዥን ዳቦንም በፊልም ነው የምናየው፡፡ ወደፊት ምግብ ቤቶች ሁለት ዓይነት ክፍያ ያዘጋጃሉ፡፡ አንዱ ለሚበላ፣ አንዱ የሚበላውን ለሚያይ፡፡ እኔ እና እናንተ ገባ ብለን ምግብ እና አመጋገብ አይተን እንወጣለን፡፡

***እንጀራ በሰማይ እኔ በእግሬ ሆኜ***
***አልደርስበት አልኩኝ ባክኜ ባክኜ***

የተባለው በ'ፍካሬ ሕዝብ መጽሐፍ' ላይ የተጻፈው ትንቢት ይፈጸማል፡፡

«'የሚያባላ' የሚባለው ደግሞ ከሚበላው ተጠግቶ ለበይዎች እንደ 'ህፒታይዘር' የሚያገለግል ነው፡፡ አያችሁ የሚበሉት መንቀሳቀስ አይወዱም፣ ውቃቢያቸው ይጣላቸዋል፤ ስለዚህም የሚያባላቸው ይፈልጋሉ፡፡ እነዚህ የሚቀበሉ፣ የሚያቀባብሉ፣ የሚያስተላልፉ ናቸው፡፡ እንደነዚያ ጠግበው ባይበሉም ትርፍራፊ ግን አያጡም፡፡ እነዚያ ግንድ እነዚህ ሥር ናቸው፡፡ እነዚያ ሆድ እነዚህ ግን እጅ ናቸው፡፡ የነዚህ ጥቅማቸው ከምርቱ ሳይሆን ከቃርሚያው ነው፡፡ በሞያቸው፣ በልምዳቸው፣ በአፍ ቅልጥፍናቸው፣ በመመቻመች ችሎታቸው ከሚበሉት ይጠጉና 'እባክህ ጌታዬ እንዲበላ ብቻ ሳይሆን በልቶ እንዲያተርፍም አድርገው' እያሉ እየጸለዩ ይኖራሉ፡፡ እነዚያ የሚበሉት ምግብ ሲዘጋቸው የሚያባሉትን ይሰበስቡና ይጋብዟቸዋል፡፡ ታድያ እነዚህ መታ መታ እያደረጉ ሲበሉ የነዚያም የምግብ ፍላጎታቸው ይከፈትላቸዋል፡፡ ምናልባትም የሚበሉት ካልተስማማቸው የሚያባሉት ይታመሙላቸዋል፡፡

«አንድ ጊዜ አንድ ገበየሁ የሚባል ሰው በምኒሊክ ጊዜ ነበር አሉ»

«እ.............ሺ» የሚል የቀልድ ምላሽ ከከበበው ሰው አገኘ፡፡

«እና ገበየሁ በወቅቱ ለነበሩት አቡን አገልጋይ ሆነና የተጣላውን ሰው ሁሉ እያስገዘተ እጅ እግሩን አሣሠረው፡፡ ይህንን ያዩ ያገሩ ሰዎች

***ገብሽ መች ቀሰሰ ከየትስ አምጥቶ***
***ይወጋናል እንጂ ካቡን ተጠግቶ***

ብለው ገጠሙለት አሉ፡፡

«'የሚያስበላ' የሚባለው ደግሞ የተሰጠውን ሥልጣን፣ ዕውቀት እና ኃላፊነት ተጠቅሞ የሚበሉትም እንዳይራቡ የማይበሉትም እንዲጠግቡ ማድረግ ሲገባው 'ላለው ይጨመርለታል' እያለ መሬቱን ሲቸበችብ፣ ግብር ሲቀንስ፣ ያልተፈቀደ ዕቃ ሲያስገባ፣ ሕገወጥ የሆነ መመርያ ሲያስተላልፍ፣ የሚውል ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሀገር የሚያስበሉ ናቸው፡፡ ስሕተቱን፣ ጥፋቱን፣ ሕገ ወጥነቱን፣ ጉዳቱን፣ በኋላ ዘመን የሚያመጣውን መዘዝ እያወቁ እኔን ምን ቸገረኝ ብለው ለበይዎች የሚስማማውን ብቻ የሚሠሩ ናቸው፡፡ እነርሱም አይጠቀሙም፤ መጨረሻቸው ጥፋት ነው፤ ሀገራቸው ማረሚያ ቤት ነው፤ እነሆ ነገ ግዳጃቸውን ሲፈጽሙ እንደ ሸንኮራ ተመጥጠው፣ እንደ ሙዝ ልጣጭ ተልጠው ይወድቃሉ፡፡»

'የሚያብላላ' ይህ ደግሞ ለሙብላት የሚያመች ሕግ ፣መመርያ፣ አሠራር እንዲዘረጋ የሚያደርግ፣ የሚበሉት አጋጣሚዎችን ሁሉ እንዲጠቀሙ መንገድ የሚያመቻች፤ ከበሉም በኋላ በተቻለ መጠን የበሉትም ፣አበላላቸውም ሕጋዊ መልክ እንዲኖረው የሚያመቻች ነው፡፡ መንግሥት ለበጎ ብሎ የዘረጋውን አሠራር፣ ያወጣውን መመርያ እና ያዋቀረውን መዋቅር እርሱ እንዴት ለበይዎች እንደሚስማማ ያጠናል፣ ያመቻቻል፣ ያስፈጽማል፡፡ ከመመርያው እና ከአሠራሩ ጋር የሚሄድ ደረሰኝ፤ ዶክመንት፣ ማስረጃ፣ ያዘጋጃል፤ አበላሉን ያሳልጠዋል፡፡ እነዚህ የጨጓራ አሲድ ናቸው፡፡ የጨጓራ አሲድ የበላነውን እንዲዋሐደን አድርጎ ይፈጨዋል፣ያስማማዋል፡፡ እነዚህም እንደ ጨጓራ አሲድ ይፈጩታል ያስማሙታል፡፡

«አንተ ይህንን ትንቢት ከየት አመጣኸው» አሉት አንዲት እናት ገርሟቸው፡፡

«በዕብድነቴ ነዋ እናቴ፤ አዩ እዚህ ሀገር ካላበዱ በቀር ብዙ ነገር አይገለጥልዎትም፡፡ እንዲገለጥልዎት ከፈለጉ እንደ እኔ ማበድ አለብዎ፡፡ ለነገሩ እዚህ ሀገር ዕብዱ ብዙ ነው ግን ዓይነቱ ልዩ ልዩ ነው» አላቸው፡፡ «ደግሞ የዕብድ ምን ዓይነት አለው፤ ሁሉም ያው ነው» አሉት እኒያው እናት የነጠላቸውን ጫፍ ወደ ትከሻቸው እየመለሱ፡፡

«ተሳስተዋል፤ አዩ ይህም ቢሆን ካላበዱ በቀር አይታይዎትም፡፡ ብዙ ዓይነት ነው ዕብዱ፡፡ የመጀመርያው ያበደና ማበዱን እንደኔ የተረዳ ነው፡፡ ሁለተኛው አብዶ ማበዱን እያወቀ ግን ማመን የማይፈልግ ነው፣ እንደ ብዙዎቻችሁ፤ ሌላው አብዶ ግን ማበዱን ባለማወቁ የተምታታበት ነው፡፡»

«ቆይ አንተ ችግሩ ብቻ ነው የተገለጠልህ፤ መፍትሔውን አልገለጠልህም፤ ማበድህ ካልቀረ ለምን ከነ መፍትሔው አታብድም ነበር» አሉት እኒያ አረጋዊ፡፡

**«ጊዜ፣ እድሜ፣ ቦታ፣ ፈቃድ፣ ችሎታ እና ስምምነት እነዚህ ስድስቱ ከተረዳዱ ሥራ ሁሉ ይፈጸማል»**

***(አንጋረ ፈላሰፋ፥ ምዕ. 28)***

# ለጠላት አንድ ሺ፣ ለወዳጅ አንድም

የዓለም የወዳጅነት ቀን ሲከበር አንድ ወዳጄ እንዲህ የሚል ጥቅስ ላከልኝ «ጠላትህ ወዳጅህ ይሆን ዘንድ አንድ ሺ ዕድል ስጠው፤ ወዳጅህ ጠላትህ ይሆን ዘንድ ግን አንድም ዕድል አትስጠው»፡፡ እነሆ ይህ ጥቅስ ከአእምሮዬ አይጠፋም፡፡

እውነት ነው በዚህ ዓለም ላይ ወዳጅ እንደ ማፍራት የከበደ፤ ጠላት እንደማፍራትም የቀለለ ነገር የለም፡፡ እሥራኤልን ያህል ሳኦል፣ ዳዊት እና ሰሎሞን አንድ አድርገው የገዟትን እና ገናና መንግሥት የነበራትን ሀገር ለውድቀት የዳረጋት የሮብዓም ከንቱ ንግግር ነበር፡፡ አያሌ ወዳጆችን ሊያፈራበት የሚችለውን ንግግር ጠላት ማፍርያ አደረገውና የእሥራኤልን ጠላት ከእሥራኤል መካከል አሥነሣባት፡፡

በአባቱ ዘመን የነበረው ቀንበር የተጫናቸው ወገኖቹ መጥተው «አባትህ ያከበደብንን ቀንበር አቅልልን» ብለው ጠየቁት፡፡ እርሱም በአባቱ በሰሎሞን ዘመን የነበሩት አማካሪዎች የነገሩትን ትቶ ከብላቴኖች ጋር ተማከረና «ትንሿ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ትወፍራለች፤ አባቴ ቀንበር አክብዶባችሁ ነበር፤ እኔም በቀንበራችሁ ላይ እጨምራለሁ፤ አባቴ በአለንጋ ገርፏችኋል፤ እኔም በጊንጥ እገርፋችኋለሁ» ብሎ ተናገራቸው፡፡

ይህ ንግግሩ እሥራልን «ሰማርያ» እና «ይሁዳ» ብሎ ለሁለት ከፈላት፡፡ ከዚያ በኋላ የደረሰው የእሥራኤል ውድቀትም በመከፋፈሏ ምክንያት የተከሰተ ነበር፡፡

ሮብዓም የሕዝቡን ቀንበር ባያቀልል እንኳን በመልካም ንግግር በመናገር፣ ለምን ቀንበሩን እንደ ማያቀልም በማስረዳት ቢያንስ ሕዝብን ከማስቆጣት እና ጠላትን ከማፍራት ይድን ነበር፡፡ ሌላውን ወገን በማስቆጣት፣ በማበሳጨት፣ በማናደድ እና በማስቀየም ለውጥ ማምጣት አይቻልም፡፡በማስ ረዳት፣ በማግባባት እና በማሰለፍ

እንጂ፡፡ መሪዎች፣ ምሁራን፣ ባለ ሥልጣናት፣ ታዋቂ ሰዎች እና ሌሎችም የሚናገሯቸው ንግግሮች እንደ ጨው የተቀመሙ መሆን አለባቸው የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡ ንግግራቸው የሮብዓምን ውጤት ሊያመጣ ይችላልና፡፡

በተለይም መሪዎች የሚናገሯቸው ንግግሮች ፍቅርን፣ አክብሮትን፣ ትኅትናን እና ትኁትነትን የሚያንፀባርቁ፤ ለማናደድ እና ለማበሳጨት ሳይሆን ለማስረዳት እና ለማሳመን የሚቀርቡ፤ አግቦ እና ሽሙጫ፣ ትዕቢት እና ስላቅ የተሞሉ ሳይሆን ዕውቀት እና ተጠየቅ፣ የሃሳብ ልዕልና እና የመረጃ ብልጫ፣ ጨዋነት እና ብልህነት የተሞሉ መሆን አለባቸው፡፡

ዐፄ ምኒልክ በእምባቦ ጦርነት ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር ተዋግተው ባሸነፉ ጊዜ የጎጃም ጦር ተማረከ፤ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ተያዙ፡፡ ያን ጊዜ ዐፄ ምኒልክ «ጠላት አሳስቶህ ነው እንጂ አንተ በኔ ላይ አትዘምትም ነበር» እያሉ ቁስላቸውን በማጠብ እና በራሳቸው በቅሎ በመጫን ነበር ተሸንፎ ሊሸፍት የነበረውን የጎጃም ጦር በፍቅር የመለሱት፡፡ እንዲያውም በአድዋ ጦርነት ከልዩ ልዩ ጎሳዎች፣ ነገዶች፣ የመጡ ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነው እንዲዘምቱ ካደረጓቸው ምክንያቶች አንዱ የዐፄ ምኒሊክ ጠላትን ወዳጅ የማድረግ ስልት ነበር ይባላል፡፡

አንዳንዶቻችን ጠባያችንን እና አቋማችንን እኛ ሳንሆን ሌሎች እንዲወስኑ እንሰጣቸዋለን፡፡ ደግነታችን በክፉዎች፣ ለጋስነታችን በስስታሞች፣ ሰላማዊነታችን በጦረኞች፣ ሕግ አክባሪነታችን በሕገ ወጦች፣ ታማኝነታችን በአጭበርባሪዎች ይወሰናል፡፡ የአንድ ዳኛ ፍትሐዊነት የገዛ ጠላቱ በችሎቱ ሲቀርብ መለወጥ የለበትም፡፡ ፍትሐዊ ከሆነ ፍትሐዊነቱ ጠላቴ ነው ለሚለውም ሰው መሆን አለበት፡፡ የአንድ ሰው ቸርነት ንፉግ ሰው ሲገጥመው መቀየር የለበትም፡፡ እርሱ ለጋስ መሆን ያለበት ከራሱ አቋም አንፃር እንጂ ንፉግ እስኪያጋጥመው ድረስ መሆን የለበትም፡፡

እንዲያውም አንዳንዴ በሕይወት ያሉት ጠላቶች አልበቃን ብለው ከሞቱትም ወገን ጠላት ለማፍራት ስንጥር የምንገኝበት ጊዜ አለ፡፡ «እገሌ ጠላቴ ነው፣ እገሌ በወገኖቼ ላይ እንዲህ አድርጓል፤ እገሌ በዚህ ጎሳ እና ነገድ ላይ ይህንን እና ያንን አድርጓል» እያልን ከሞቱ መቶ እና አምስት መቶ ከሆናቸው ሰዎች መካከል ጠላት ለማፍራት መከራ በማየት ላይ ነን፡፡

ለመሆኑ ሰዎች ለምን ጠላቶቻችን ይሆናሉ?

በገዛ ንግግራችን ወዳጅም ጠላትም መፍጠር እንችላለን፡፡ ሌላው ቀርቶ «እባክዎ፣ እግዜር ይስጥልኝ፣ ይቅርታ፣ አዝናለሁ፣ ተሳስቻለሁ» ወዘተ የሚሉትን ቃላት ገንዘብ በማድረግ እንኳን ያለ ብዙ ወጭ ብዙ ወዳጅ ማግኘት እንችል ነበር፡፡ በተለይ በኛ ልማድ የአክብሮት ቃላት ከከተሞቻችን የተሰደዱ ይመስላሉ፡፡ ማመናጨቅ፣ አንጠልጥሎ መጥራት፣ መቆጣት፣ ከፍ ዝቅ ማድረግ፣ ቦታውን ይዘውታል፡፡ አስተናጋጆች፣ የጥበቃ ሠራተኞች፣ የየመሥሪያ ቤቱ ባለ ጉዳይ ተቀባዮች፣ ባለ ሥልጣኖች፣ ፖሊሶች፣ ዳኞች፣ የእምነት አባቶች የትኅትና እና የአክብሮት ቃላት ድርቅ መትቶናል፡፡ «እባክዎ» «በሞቴ» የሚሉት ቃላትማ «ጥፊ፣ ሂጂ፣ ብረሪ» አለኝ ብለው ሳይሸሹ አይቀሩም፡፡

የአንዳንዶቹ ጥላቻ ከመረጃ እጥረት ነው፡፡ ስለኛ ያላቸው መረጃ ከሚያስፈልጋቸው በታች ይሆንና በቀረው ቦታ አሉባልታ እና ወሬ ይሞሉበታል፡፡ ከዚያም ወዳጃቸውን መጥላት ይጀምራሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ የተሳሳተ መረጃ ከማግኘታቸው ይመነጫል፡፡ አንዳንዶቻችን የሰማነውን ሁሉ ያለ ምንም ጥርጣሬ እናምናለን፡፡ ተጨማሪ መረጃ ለማፈላለግ፣ ከሌሎች ምንጮችም ለመስማት፣ ብሎም ባለቤቱ እንዲናገር እድል ለመስጠት አንፈልግም፡፡ በዚህ የተነሣ ከተሳሳተ መረጃ ተነሥተን የተሳሳተ ውሳኔ እንወስናለን፡፡

አንዳንዶቻችን ደግሞ ልዩነትን ሁሉ ጠላትነት አድርገን ስለምንወስደው ነው፡፡ የኛን ሃሳብ የማይቀበለውን፣ በሄድንበት መንገድ የማይሄደውን፣ ያልነውን የማይደግመውን፣ ካዘዝነው ምግብ የተለየ የሚያዝዘውን፣ ከምናምነው ውጭ የሚያምነውን፣ ከለበስነው ውጭ የሚለብሰውን ሁሉ ጠላት አድርገን እንወስደዋለን፡፡ አሜሪካኖች በቀዝቃዛው ጦርነት ይከተሉት እንደነበረው አሠራር «ወይ ከኛ ወገን ወይንም ከጠላቶቻችን ወገን» ብለን እንፈርጃለን፡፡ በዚህም የተነሣ በሃሳብ ተለይተውን ነገር ግን ወዳጆቻችን ሊሆኑ የሚችሉትን አካላት ጠላቶቻችን እናደርጋቸዋለን፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ወረተኞች እና ነገን የማናስብ በመሆን ለዕለቱ ብቻ የሚሆን ነገር ስንናገር እና ስናደርግ በዘመናት ውስጥ ጠላቶችን እናፈራለን፡፡ የምናደርገው እና የምንናገረው ነገር ከመርሐችን እና ከአቋማችን የሚመነጩ መሆን አለባቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች ደግሞ ከመረጃ እና ከማስረጃ መነሣት ቢችሉ መልካም ነው፡፡ እንደዚያ ከሆነ ብንሳሳት እንኳን ስሕተታችን ተችዎችን እንጂ ጠላቶችን አያፈራም፡፡

አንድ ወቅት የሚፈጥረውን ሞቅታ እና አጋጣሚ በመጠቀም፣በወቅቱ የተነሡ መሪዎችን፣ ባዕለ ጸጎች፣ ታዋቂ ሰዎች ወይንም ዘመነኞችን ለማስደሰት ሲባል ብቻ በአእምሮ ስካር የሚነገሩ እና የሚደረጉ ነገሮች ታካዊ ጠላቶችን ያፈራሉ፡፡

በአንድ ወቅት ዐፄ ቴዎድሮስ ደጃች ካሣ እየተባሉ ከደጃች ጎሹ ጋር በጉር አምባ ጦርነት ገጥመው ነበር፡፡ ከጦርነቱ በፊት አንድ ደጃች ጎሹን ተከትሎ የሄደ አዝማሪ

***ሊያችሁት ብያ የኛን እብድ***

***አምስት ጋሞች ይዞ ጉር አምባ ሲወርድ***

***ያንጓብባል እንጂ መች ይዋጋል ካሣ***

***ወርደህ ግጠምበት በሸንብራው ማሳ***

ብሎ በደጃች ካሣ ላይ የፌዝ ዘፈን ይዘፍናል፡፡ ጦርነቱ ተከናውኖ ደጃች ጎሹ ድል ይሆናሉ፡፡ አዝማሪውም ይያዛል፡፡ ደጃች ካሣም «ለምን እንዲህ ብለህ ሰደብኸኝ» ይሉታል፡፡ እርሱም ባደረገው ነገር ተጠጥቶ

***አወይ ያምላክ ቁጣ፣ አወይ የግዜር ቁጣ***

***አፍ ወዳጁን ያማል ለካስ ሥራ ሲያጣ***

***ሽመል ይገባዋል ያዝማሪ ቀልባጣ***

ብሎ በራሱ ፈረደ ይባላል፡፡ ጦርነት የገጠሟቸውን ደጃች ጎሹን በልቅሶ ያስቀበሩት ደጃች ካሣ አዝማሪውን ግን በሽመል አስመቱት ይባላል፡፡ አሁን ምን ክፉ አናገረው? ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ ክፉ ከመናገር ስለ ደጃች ጎሹ አይናገርም?

አንዳንዴም ሳናስበው የምናደርገው እና የምንሠራው ነገር ወዳጆቻችንን ጠላቶቻችን የሚያደርግበት ዕድል አለ፡፡ ለአንዳንዶቻችን ጥሩ መናገር ማለት ብዙ መናገር ይመስለናል፡፡ ጥሩ መናገር ማለት ግን በቂ ዕውቀት፣ ሃሳብ፣ መረጃ እና ጥበብ ያለበት ንግግር እንጂ የቃላት ድሪቶ አይደለም፡፡ ንግግሮቻችን ዕውቀት፣ሃሳብ፣ መረጃ እና ጥበብ ሲጎድላቸው ወደ መለካከፍ፣ መሰዳደብ፣ መወራረድ፣ ይዘቅጣሉ፡፡ የዘር፣ የሃይማኖት፣ የባህል፣ የቡድን መሰዳደቦችን እና መቀላለዶችንም ያመነጫሉ፡፡ በዚህ መካከል የሚያመልጡ ነገሮች ብዙ ወዳጆችን ያሳጣሉ፡፡

ሌላው መንሥኤ ደግሞ ተጣጣፊነት ነው፡፡ አቋም እና ወጥነት የሌለው ጉዞ፡፡ እንደ ቦይ ውኃ የመሬቱን ሁኔታ፣ እንደ እስስት የአካባቢውን ሁኔታ፣ እንደ ሱፍ የፀሐዩን አቅጣጫ እያዩ መተጣጠፍ፡፡ ይህ ዓይነቱ ጠባይ ዛሬ ያስደሰትነውን ሰው ነገ እንድናስከ ፋው ስለሚያደርገን ጠላት እንጂ ወዳጅ አያፈራልንም፡፡ አንድን ነገር የማናደርገው እንደሆነ በምክንያት እና በዘለቄታ አናድረገው፤ የምናደርገው እንደሆነም እንዲሁ፡፡ የማንሄድ ከሆነ በምክንያት እና ዘለቄታዊ በሆነ መልኩ አንሂድ፤ ከሄድንም እንዲሁ፡፡ ምክንያቶቻችን እና አቋሞቻችን እንደየሁኔታው የሚቀያየሩ ከሆነ የትናንቱን ስለምንረሳው ከራሳችን ጋር የማይጣጣም ነገር ከመፈጸም ወደኋላ አንልም፡፡

ለአንዳንዱ ሰውኮ እንኳን ሌላ ወዳጅ ሊያፈራ የገዛ ጠባዩ፣ ምላሱ፣ ዓይኑ፣ እጁ፣ አመሉ፣ ጠላቱ የሚሆንበት ጊዜም አለ፡፡ ሳያስብ ቃል እየገባ የገዛ ቃሉ ያዳኝበታል፤ ሳያስብ እየፈጸመ፣ ዛሬ የሚፈጽ መውም ከትናንቱ ጋር እየተጋጨ፣ የገዛ ሥራው ጠላቱ ይሆናል፡፡

ሰው ዓላማ እና አቋም ያለው፣ ምክንያታዊ እና ዘለቄታዊ ሲሆን እኮ የሚወድደው እንኳን ቢያጣ የሚያደንቀው አያጣም፡፡ የሚቃወሙት እና የሚጠሉት ሰዎች እንኳን ሲያመሰግኑት፣ ሲያደንቁት እና ሲያሞግሱት ይሰማል፡፡ ዛሬ በስደት የሚኖሩት መንግሥቱ ኃይለ ማርያም «የመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ትዝታዎች» በሚለው መጽሐፍ ላይ ስለ አንድ ባለ ሥልጣናቸው ተጠይቀው ነበር፡፡ እኚህ ባለ ሥልጣን ከመጀመርያዎቹ የደርግ ባለ ሥልጣናት አንዱ ናቸው ነገር ግን ሃይማኖተኛ እና ጸሎተኛ ነበሩ፡፡ እኚህ ባለ ሥልጣን ታምመው ስለ ነበሩ በመንግሥቱ ፈቃድ ስዊዲን ተልከው በዚያው ቀርተዋል፡፡ ታድያ መንግሥቱ ስለ እኚህ ሰው «ከማንም ሾክሿኳ ኮሚኒስት ነኝ ባይ እንደ እርሳቸው ያለ ሃይማኖተኛ ይሻለኛል» ነበር ያሉት፡፡

ክርስትናቸውን ሳይቀይሩ፣ በክርስትና ሕግ መሠረት ኖረው ነገር ግን ሙስሊሞች የሚወድዷቸውና የሚያከብሯቸው ክርስቲያኖች፤ እስልምናቸውን ሳይቀይሩ እንደ እስልምና ሕግ ኖረው፣ ነገር ግን ክርስቲያኖች የሚወድዷቸውና የሚያከብሯቸው ሙስሊሞች አሉኮ፡፡ እነዚህ ሰዎች እውነተኛ እና ቀጥተኛ ሰዎች በመሆናቸው ሰዎች ከእምነት አስተምሯቸው እንኳን ባይማሩ ከጥንካሬያቸው፣ ከዓላማ ጽናታቸው፣ ከእምነት ፍቅራቸው፣ ከደግነታቸው፣ ከመንፈሳዊ ብቃታቸው፣ ከቀጥተኛነታቸው፣ ይማሩባቸዋል፤ በእነዚህም ምክንያት ያደንቋቸዋል፡፡ ያከብሯቸዋል፡፡

ሶቅራጥስ እና አፍላጦን፣ ዲዮጋን እና አርስጣጣሊስ እምነታቸው አረማዊ፣ ሀገራቸው ግሪክ፣ ቁም ነገራቸውም ፍልስፍና ነው፡፡ የኦርቶዶክስ እምነትን አያውቁትም፤ በዘመናቸውም አልነበረም፡፡ ነገር ግን የእነዚህ ሰዎች ኑሮ፣

የኑሮም ፍልስፍና፣ ሰብአዊነት እና ለሰው ልጅ ኑሮ ያደረጉት ተጋድሎ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ክብር እና ፍቅርን አትርፎላቸዋል፡፡ መጽሐፎቻቸውም ወደ ግእዝ ተተርጉመዋል፡፡ «አንጋረ ፈላስፋ» ተብሎ እንደ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ይነበባል፡፡

የማር ይስሐቅ ደራሲ ቅዱስ ይስሐቅ ሶርያዊ ኦርቶዶክሳዊ አይደለም፡፡ እንዲያውም ንስጥሮሳውያን ከሚባሉት ወገን ነው፡፡ ነገር ግን ከሊቀ ጵጵስናው መንበር በራሱ ጊዜ መንኖ በረሃ በመውረድ የኖረው የቅድስና ኑሮ ለሁሉም አርአያ የሚሆን በመሆኑ ንስጥሮስን የሚቃወሙት አብያተ ክርስቲያናት ሳይቀሩ የርሱን ትምህርት እና ሕይወት ይከተሉታል፣ ያደንቁለታል፡፡ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ከአራቱ የመጻሕፍት ጉባኤያት አንዱ የርሱ መጽሐፍ ነው፡፡

የበርለዓም መጽሐፍ የሕንድ ብርሃማኒስቶች መጽሐፍ ነው፡፡ ነገር ግን ወደ ግእዝ ቋንቋ ተተርጉሞ እንደ አንድ የሃይማኖት ማስተማርያ ሲያገለግል ዘመናትን አስቆጥሯል፡፡ የክርስትናው ሊቃውንትም የብርሃማኒስቶችን መጽሐፍ «እንዲል በርለዓም» እያሉ ይጠቅሱታል፡፡ ዘመን እና ድንበር ተሻግሮ ወዳጅ ማፍራት ማለት ይህ ነው፡፡

በንጹሕ ሥራቸው፣ በዘላቂ ዓላማቸው እና በእውነተኛ ሕይወታቸው ምክንያት እንዲህ ዘመን እና ድንበር ተሻግረው ወዳጅ የሚያፈሩ ያሉትን ያህል በተቃራኒው ዘመን እና ድንበር የማይሽረው ጠላት የሚያፈሩም አሉ፡፡

ወዳጅ ስንል በዙርያችን ያሉ የምናውቃቸውን ሰዎች ብቻ በማሰብ እንዳናጠብበው፡፡ ወዳጆች ዘመናትን ተሻግረውም ይገኛሉ፡፡ በተለይም ለእውነት የሚቆሙ ሰዎች ዘመነኛ ወዳጆች አይኖሯቸውም፡፡ እነዚህ ሰዎች ከዘመንም ስለሚቀድሙ በዚያ በዘመናቸው እንደ እብድ፣ እንደ ጅል፣ ዘመን እንደ ማይገባው እና እንደ ቅዠታም ሊታዩ ይችላሉ፡፡ በኋላ ግን እነርሱ የወጡበት ተራራ ላይ ሌላውም ሰው መውጣት ሲጀምር፤ እነርሱ ያዩትንም ማየት ሲችል የበደላቸው ይቅርታ ይጠይቃቸዋል፡፡ የጠላቸው ይወድዳቸዋል፣ ያልተረዳቸው ይረዳቸዋል፣ ያዋረዳቸው ያደንቃቸዋል፡፡ እነ ሶቅራጥስ እና እነ ጋሊሊዮ ይህንን ዕድል ካገኙት መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ነቢያቱ ኢሳይያስ እና ኤርምያስም በዘመናቸው እውነት ቢናገሩ በመጋዝ ተሰንጥቀው፣ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፡፡ ከብዙ ዘመናት በኋላ ግን «ሕዝብ ዘኢየአምረኒ ተቀነየ ሊተ» እንደሚለው የማያውቃቸው ሰው ሁሉ ወደዳቸው፡፡

አያሌ ምሁራን እና ሊቃውንት ግን በገዛ እጃቸው ሰሞነኞች እየሆኑ፣ ከአእምሮአቸው ይልቅ ሆዳቸውን እያዳመጡ፣ ከብእር ይልቅ ገንዘብ እየገዛቸው ወዳጆቻቸውን ሁሉ ጠላቶቻቸው አድርገዋቸዋል፡፡ ሌላው ቀርቶ ዘመን ሲያልፍ የገዛ ልጆቻቸው እና ዘመዶቻቸው እንኳን የእገሌ ልጅ ነን፤ የእገሌም ዘመድ ነን እንዳይሉ አድርገዋል፡፡

እናም የኑሮ መሥመራችን እና ፍልስፍናችን፣ ተግባራችን እና ንግግራችን ቢቻል ጠላቶቻችንን ወዳጆች የሚያደርግ፣ ባይቻል ወዳጆቻችንን ጠላቶቻችን የማያደርግ፤ ወይም በሌላ በጓደኛዬ አገላለጥ «ወዳጆቻችን ጠላቶች እንዲሆኑ አንድም ዕድል የማይሰጥ፤ ጠላቶቻችን ግን ወዳጆቻችን ይሆኑ ዘንድ አንድ ሺ ዕድል የሚሰጥ» ቢሆን መልካም ነው፡፡

# ቺፋን ለማ

የዛሬን አያርገውና ቻይናዎች ከ30 ዓመት በፊት ችግርን በታሪክ ብቻ ሳይሆን በአካልም ያውቁት ነበር፡፡ አለንጋውን ይዞ ገርፏቸዋል፤ ጥርሱን አውጥቶ ነክሷቸዋል፤ ጥፍሩን አርዝሞ ቧጭሯቸዋል፡፡ ሀገራቸው በታሪካዊ ቅርሶቿ እና በጥንታዊው ሥልጣኔዋ ካልሆነ በቀር ከድህነቷ ውጭ ሌላ መታወቂያ አልነበራትም፡፡

መቼም ከሠሩ የማይገኝ፣ ከለፉ የማይሰናኝ የለምና ጥረው ግረው በወዛቸው ሀገራቸውንም ስማቸውንም ቀየሩት፡፡ እነሆ ቻይናም በዓለም ሁለተኛዋ የኢኮኖሚ ኃያል ሀገር ለመሆን በቃች፡፡ ቻይና በኦሎምፒክ ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚም ወርቅ መሰብሰብ ጀመረች፡፡

ታድያ እነዚህ ቻይናዎች በድህነቱ ዘመናቸው ዋናው ችግራቸው የረሃብ ጥያቄ ነበረ፡፡ በልቶ ማደር ጠጥቶ መዋል የእያንዳንዱ ቻይናዊ የየዕለቱ ፈተና ነበረ፡፡ ያ እንደ ጉንዳን የሚርመሰመስ፣ እንደ ጎርፍ ውኃ የሚተራመስ ሕዝብ ዛሬን ቢበላ ነገን ለመድገሙ ዋስትና አልነበረውም፡፡

በዚህ የተነሣ የቻይናዎቹ ዕለታዊ ሰላምታ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ሆነ፡፡ ቻይናውያን ሲገናኙ «ቺፋን ለማ» «በልተሃልን?» ነበር የሚባባሉት፡፡ መልሱም «አልበላሁም/በልቻለሁ አንተስ እንዴት ነው በልተሃል?» የሚል

ነበር፡፡ ልጆቹ፣ ቤተሰቡ፣ አካባው ሁሉ በልቶ ማደሩን ነበር የሚጠያየቀው፡፡ በልቻለሁ የሚል መልስ ከተገኘ እሰዬው ነው፡፡ አልበላሁም ከተባለ ግን ተዛዝኖ እና መንገድ ተመለካክቶ መሰነባበት ነው፡፡

በሌላ በኩል ምዕራባውያኑ ትልቁ ፈተናቸው አካባቢያቸው ነበር፡፡ እንዲህ እንደዛሬ ሙቀት እና ቅዝቃዜውን፣ ነፋስ እና ማዕበሉን፣ በረዶ እና ውሽንፍሩን በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዐቅም መቋቋም ከመጀመራቸው በፊት፤ እንዲህ እንደዛሬው የነገውን የአየር ሁኔታ አውቀው ለመዘጋጀት፣ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ለመዘርጋት፣ ብሎም አካባቢያቸውን ለኑሮ በሚሆን መልኩ ማመቻቸት ከመጀመራቸው በፊት ዋናው ችግራቸው ዛሬን ማደር ነገንም ማግኘት ነው፡፡

በዚህ የተነሣም ሰላምታቸው ሁሉ በምኞት የተሞላ፣ ነገን ተስፋ የሚያደርግ ነው «good morning, good evening, good afternoon, good night,» መልካም ጠዋት፣ መልካም ምሽት፣ መልካም ቀን፣ መልካም ሌሊት እያሉ ይመኛሉ፡፡

ኢትዮጵያውያን ደግሞ ትልቁ ጥያቄያቸው የደኅንነት ጥያቄ ነው፡፡ ይህች ሀገር በጦርነት ስትታመስ ነው የኖረችው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንኳን ቲርሐቅ የተባለው የኢትዮጵያ ንጉሥ አንድ ሚሊዮን ጦር አስከትቶ እስከ ታኅታይ ግብጽ ድረስ ዘምቶ ነበረ፡፡

ሀገሪቱ በውጭ ወራሪ እና በርስ በርስ ጦርነት ስትታመስ፡፡ ሕዝቦቿ ከአንዱ ሥፍራ ወደ ሌላው ሥፍራ ሲዘዋወሩ፤ አሸናፊው ተሸናፊውን ሲያስገብር፤ ተሸናፊው ኃይል አግኝቶ መልሶ ሲያጠቃ ኖረውባታል፡፡ መሳፍንቱ እና መኳንንቱ፣ ነገሥታቱ እና ልዑላኑ ጎራ ለይተው ሕዝብ አሰልፈው ተጋድለዋል፡፡

በዚህ የተነሣ ይመስለኛል የኢትዮጵያውያን የሰላምታ ባህል ደኅንነትን ማረጋገጥ የሆነው፡፡ «እንዴት አደርክ? እንዴት ሰነበትክ? እንዴት ከረምክ? እንዴት ዋልክ? እንዴት አለህ?» እነዚህ ሁሉ ደኅንነትን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ችግሩ፣ መፈናቀሉ፣ መዘረፉ፣ ጦርነቱ ልጆችንም፣ ከብቶችንም፣ ቀየውንም ይመለ ከታልና ሰላምታችን ወደነዚህ ነገሮችም ተራዝሞ ቤቱ ሰላም ነው? ልጆቹ፣ ከብቶቹ ደኅና ናቸው? ቀየው ሰላም ነው? የሚሉ የደኅንነት ጥያቄዎችም ይከተላሉ፡

ይህ ሥነ ልቡና ዛሬ ላለንበት ገጽታ የራሱን አስተዋጽዖ አድርጓል፤ የራሱንም ጠባሳ ትቷል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የርስ በርስ ግንኙነታችን በጥርጣሬ የተቃኘ ነው፡፡ የሰው ዓይን ይፈራል፡፡ ልጆች እንኳን ጡት ሲጠቡ ሰው እንዳያየቸው ይሸፈናሉ፡፡ ዘመናውያን የሚባሉት ወላጆች እንኳን የልጆቻቸውን ጡጦ በካልሲ ሸፍነው ካልሆነ በቀር በአደባባይ አይወጡም፡፡

አንድ ወጣ ወጣ ያለ ሰው አንዳች መሰናከል ሲገጥመው «ምን ዓይን በላው፣ ማን በክፉ አየው» ማለት የተለመደ ነው፡፡ ሽማግሌዎቹ ጠዋት ተነሥተው ፊታቸውን እና እጃ ቸውን ሲታጠቡ «ቀኝ አውለኝ ከሸረኛ ጠብቀኝ» ይላሉ፡፡ ፍርሃት አላቸው አካባቢያቸውን ይጠራጠሩታል፡፡ በቀኝ መነሣት እና በግራ መነሣት ትልቅ ትርጉም አለው፡፡ አንድ ሰው የከፋ ነገር ከተናገረ «ምን በግራ ጎኑ የተነሣ ሰው ነው» ይባላል፡፡

ከጥርጣሬ ጋር የተያያዙ አያሌ ብሂሎች አሉን፡፡ ጠርጥር ከገንፎም ይገኛል ስንጥር እያልን ነገሮችን አለማመንን እናበረታታለን፡፡ ያልጠረጠረ ተመነጠረ ብለን ደግሞ ተጠራጣሪነት ከብዙ ነገር እንደሚያድን እንሰብካለን፡፡ በገጠሩ እንኳን የሚጠራጠርን ሰው «አይ ጠርጣራው» እየተባለ ማሞካሸት የተለመደ ነው፡፡

የእርስ በርስ አለመተማመኑ ባህል ከመሆኑ የተነሣ በመርዝ መግደል በየተረቶቻችን ውስጥ ሰፊ ቦታ ይዞ ይገኛል፡፡ ቡና ሲፈላ አፍይው ቀድሞ መጠጣት አለበት፡፡ ጠላ ሲጠጣ ቀጅው በእፍኙ አፍስሶ መቅመስ ልማድ ነው፡፡ ምግብ ሲቀርብ ቆርሶ በመጉረስ ማስረገጥ ይጠበቃል፡፡ ጥሩ ነገር ሲታይ እንኳን ዓይን ስለሚፈራ «እትፍ እትፍ» ይባላል፡፡ ሌላው ቀርቶ ይጎዳል የሚባለው ሰው እንኳን ባህሉን ተቀብሎት ማንም ሳይለው «እትፍ እትፍ» ብሎ ምራቁን በመርጨት ዓይኑን ከክፉ ይከለክላል፡፡

ሰማዩ ሲያቅላላ ጦርነት ሊመጣ ነው፣ ደመናው ሲጠቁር ክፉ ዘመን ቀረበ፣ ወፍ በጠዋት ስትጮኽ ትልቅ ሰው ሊሞት ነው፣ ከሰሉ ሲንጣጣ ነገር ሊመጣ ነው፣ እንጀራው ሊጥ ሲሆን ኑሮ ሊበላሽ ነው፣ ቡናው አተላ ሲሆን ፍቅር ሊደፈርስ ነው፣ እያለ ሰው አካባቢውን ይጠራጠራል፡፡ ሌላው ቀርቶ የደመራው መውደቂያ አቅጣጫ እንኳን ከጦርነት እና ሰላም አንፃር ነው የሚተረጎመው፡፡

ይህ ሥጋት የተሞላ የኑሮ ዘይቤ ሰዎች ራሳቸውን ችለው በድፍረት እና በመተማመን ብቅ እንዳይሉም ይከላከላል፡፡ በንግግሩም ይሁን በችሎታው ቀደም ቀደም የሚለውን፣ ልውጣ ልውጣ ብሎ የሚጣጣረውን ሰው «ወጣሁ ወጣሁ ማለት፤ አንድም ለወፍ አንድም ለወንጭፍ» እያለ ያስፈራራዋል፡፡ መቅደም መንቀዥቀዥ፣ መፍጠን እታይ እታይ ማለት፣ ሃሳብን መግለጥ እና መብትን ማስከበር ከሰው አፍ መግባት፣ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

ተደብቆ፣ ሰው ሳይሰማ፣ ነገርን ሁሉ መፈጸም ብልህነት፤ ድብቅነት ምሥጢራዊነት ነው ተባለ፡፡ ይህ ደግሞ ሐሜት ከመረጃ ይልቅ ትልቅ ቦታ እንዲኖረው አደረገ፡፡ ድምጽን አሰምቶ፣ ራስን ገልጦ መናገር ከሰው አፍ መግባት፣ ብሎም በሰው ጥቁር ምላስ ተገርፎ መውደቅን ያመጣል ስለሚባል ሐሜት በሹክሹክታ ሀገሩን ያምሳል፡፡

ለሀገራቸው አያሌ የሥነ ጽሑፍ ሀብትን ያተረፉ ጥንታውያን ደራሲዎቻችን እንኳን በገዛ ስማቸው ያልጻፉት በዚሁ የደጎንነት ጥያቄ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም፡፡ እርሱ ማነውና? ከየት አመጣው? ሰርቆ ነው እንጂ አሁን የእርሱ ነው? ደግሞ እርሱን ብሎ ጻሐፊ? የሚሉ ነገሮች ይመጡና እድሜያችን ያጥራል ብለው በመሥጋት በብእር ስም እየጻፉ አስቀምጠዋል፡፡ በዚህም የተነሣ አንድ ምሁር እንዳሉት በአባቶቻችን እንዳንኮራ ሆነናል፡፡

ከፊት ለፊት ካለው ነገር ይልቅ ከጀርባ ያለውን ነገር የመፈለጉ ልማድ የመጠራጠሩ እና ደጎንነት ያለመሰማቱ ውጤት ነው፡፡ ሰውዬው ከአንድ የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ይገባና ጥበቃውን ጠጋ ብሎ «ይህ ቤተ ክርስቲያን ለምን መድኃኔዓለም ተባለ» ብሎ ይጠይቃቸዋል፡፡ እርሳቸውም «አንዳች ነገር ቢኖረው ነው እንጂ ያለ ምክንያት መድኃኔዓለም አልተባለም፡፡ አንድ ነገር ከጀርባው ይኖረዋል፤ መቼም ያለ ምክንያት መድኃኔዓለም አላሉትም» አሉት ይባላል፡፡

አንድ ሰው አንድ ነገር ሲያደርግ ወይንም ሲናገር ያደረገውን ወይንም የተናገረውን ከመመዘን ይልቅ «አንዳች ምክንያት ቢኖረው ነው፤ ከጀርባው አንድ ነገር ቢኖር ነው፤» እያልን ከሚታየው ጀርባ የማይታይ ነገር እንጎረጉራለን፡፡ «ማጅራቱ አባቱን ይመስላል» ያሉትኮ ወደው አይደለም፡፡

ከጦርነቱ በተጨማሪ ድግምት፣ መተት እና ጥንቆላ ዋናዎቹ ማስፈራርያዎች በመሆናቸው ሰው ስሙን እንኳን እንዳይናገር ሥጋት ውስጥ ከተቱት፡፡ ሀብት አለው መባል፣ ልጆች አሉት መባል፣ ንብረት አለው መባል ለክፉ ምልኪ አሳልፎ ይሰጣል ተብሎ ታመነ፡፡ እናም ብዙው ሰው ልጆቹን ሲቆጥሩበት ይከፋዋል፡፡ ሀብቱን ሲዘረዝሩበት የተዘረፈ ያህል ያናድደዋል፡፡

ሃይማኖተኛ ይባሉ የነበሩት ነገሥታት እና መኳንንት እንኳን አንዳንድ ጠንቋይ ወይንም መተተኛ ከየጓዳቸው አያጡም ነበር፡፡ ኮከብ ቆጣሪዎች እና ድግምተኞች ዋና አማካሪዎቻቸው ነበሩ፡፡ መንግሥ ታቸው ደጎንነት አይሰማውም፤ ዙፋናቸው በጥርጣሬ የተሞላ ነበር፡፡ እናም ነገ ይህ ይሆናል የሚል ካላገኙ ዕንቅልፍ አይወስዳቸውም፡፡

ዛሬ ዛሬ በፖለቲካው መስክ፣ በምሁርነቱ ሜዳ፣ በሳይንሱ ዘርፍ፣ በሀብቱ ጎዳና፣ በሥልጣኑ ጉዞ ለምናየው የመጠፋፋት፣ ያለመተማመን እና የመበላላት አባዜ መነሻው ይህ ደጎንነት ያለመሰማት እና የመጠራጠር ልማድ ነው፡፡ ተወዳድሮ ከመሸናነፍ፣ በግልጽ ተነጋግሮ ከመግባባት እና ከመለያየት፣ ከመተማመን ይልቅ መጠራጠር የምናበዛው ከልማድ የወረስነው አዙሪት አልለቀን ብሎ ነው፡፡

በሥልጣን ላይ የሚሆኑት አካላት እንኳን ከፉውንም ደጉንም ለሕዝቡ ነግረው፣ ድክመትንም ጥንካሬንም ግልጽ አድርገው እየተግባቡ ከመጓዝ ይልቅ ደብቀው መጓዝን የሚመርጡት ይኼው አባዜ ይዟቸው ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ጥያቄያቸውን ሳንሰማ መልሳቸውን የምንሰማቸው መግለጫዎች የዚህ ውጤት ናቸው፡፡

አንዳንድ ተቋማት፣ ማኅበራት፣ ድርጅቶች እና ፓርቲዎች እየሞቱ፣ እየደከሙ፣ እየፈራረሱ፣ እርስ በርስ እየተነታረኩ በአደባባይ ሲወጡ ግን ሰላማዊ፣ ችግር ነክቷቸው የማያውቅ፣ አገር ደኅና የሚሉት ነገሩን በመ ግለጥ ደጎንነት ስለማይሰማቸው ነው፡፡ ችግሩ ተፍረጥርጦ በግልጽ ወጥቶ ከሚመጣው ፈውስ ይልቅ መጠቃቱ፣ አጀንዳ መሆኑ ይበልጥ ይሰማቸዋል፡፡ ድርጊቱ በራሱ ያላመማቸውን ድርጊቱ ሲወራ ያማቸዋል፡፡

ከመድረክ ይልቅ የተዘጋ ቤት፣ ከይፋ ይልቅ ሥውር፣ ከአደባባይ ይልቅ ጓዳ ይበልጥ ደጎንነት ይሰጠናል፡፡ በመረጃ ዘመን፤ ዓለም አንድ በምትሆንበት፤ ኑሮ ይበልጥ ይፋ በሆነበት በዚህ ጊዜ ይህ ልማድ ሳይጠፋ እንዴት ዕድገት ይኖራል?

***ዋሽንግተን፣ ዲሲ***

*ይህ ጽሑፍ በሮዝ መጽሔት ወጥቶ ነበር*

# አባ ሐና

በኢትዮጵያ ታሪክ ስማቸው የጠፋ ሁለት ገብረ ሐናዎች አሉ፡፡ አለቃ ገብረ ሐና እና አባ ገብረ ሐና ጂማ፡፡ ሕዝቡ ሁለቱንም ባለ ውለታዎች በተሳሳተ መንገድ ተረዳቸው፣ ታሪካቸውንም በተሳሳተ መንገድ አስተላለፈው፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ የሼክስፔሩን ሻይሎክ ያህል ገብጋባ ናቸው እየተባሉ የሚጠሩት አባ ሐና ጂማ ማን ናቸው? ለምንስ ገብጋባ ሰው «አባ ሐና» ተብሎ ሊጠራ ቻለ? አብራችሁ ቆዩ፡፡

እስከ 1953 ድረስ ከ30 ዓመታት በላይ የዐፄ ኃይለ ሥላሴ ግምጃ ቤት ኃላፊ ስለነበሩት ስለ አባ ሐና ጂማ በተመለከተ በቂ የሆነ የተጻፈ መረጃ የለም፡፡ በአፈ ታሪክ ግን ገብጋባ ናቸው እየተባለ ይነገራል፡፡ የዚህ ብሎግ አዘጋጅ ለማሰባሰብ የሞከረው ታሪካቸው ግን ይህን የሚያስተባብል ሆኖ አግኝቶታል፡፡

የአባ ሐናን ትውልድ እና ዘመን በተመለከተ ታኅሣሥ 26 ቀን 1953 ዓም ታትሞ የወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ «አባታቸው ፊታውራሪ ጂማ አባ ጋርጠው፣ እናታቸው ወ/ሮ እሰዩ እንደሚባሉ፤ የተወለዱትም በ1889 ዓም እንደሆነ» ይገልጣል፡፡ ትውልዳቸውንም ጎጃም እነብሴ ነው ይላል፡፡ እኔ ግን በሌላ መረጃ የፊታውራሪ ጂማ አባ ጋርጠው ትውልድ ሰሜን ሸዋ ነው የሚል አይቻለሁ፡፡ ለ30 ዓመታት አብረዋቸው በቤተ መንግሥት ከአባ ሐና ጋር የግምጃ ቤት ሹም በመሆን የሠሩት አቶ አርአያ ተገኝ እንደሚገልጡት ደግሞ ሰሜን ሸዋ ሚዳ ወረሞ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ምናልባትም የአባታቸው ስም «ጅማ» መሆኑን ስናይ ሚዳ ወረሞ የኦሮሞ ተወላጅ ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል፡፡ አባታቸው የሰሜን ሸዋ ሰው ናቸው ከሚለው ጋር ስናስተያየውም የአቶ አርአያ ገለጻ ትክክል ይመስለኛል፡፡ ትክክለኛው ስማቸው አባ ገብረ ሐና ጅማ ነው፡፡ ሕዝቡ ግን ለማሳጠር አባ ሐና እያለ ስለጠራቸው ይሄው ተለምዶ ቀረ፡፡

ጋዜጣው እንደሚተርከው አባታቸው ፊታውራሪ ጅማ ልዑል መኮንንን ተከትለው ወደ ሐረር በመውረዳቸው አባ ሐና የተወለዱት ሐረር ነው፡፡ እስከ የልጅነት ጊዜያቸውን በትምህርት ቤት አሳልፈው በ1902 ዓም በልዑል መኮንን ግቢ ማገልገል ጀመሩ፡፡ መነን መጽሔት የካቲት /መጋቢት 1953 እትም እንደሚገልጠው እስከ 1910 ዓም የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ አሽከር ሆነው ከቆዩ በኋላ ጠፍተው ደብረ ሊባኖስ በመሄድ መነኮሱ፡፡ አልጋ ወራሽ ተፈሪ ንጉሠ ነገሥት ሲሆኑም በቤተ መንግሥቱ ሥራ እንዲረዷቸው ያቀረቡላቸውን ጥያቄ ተቀብለው ወደ አዲስ አበባ መጡ፡፡

እንደ አቶ አርአያ ትረካ ግን አባ ሐና መጀመሪያ ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ገብተው በመመንኮስ ገዳማውያኑን በረድእነት ያገለግሉ ነበር፡፡ እንጨት በመስበር፣ ውኃ በመቅዳትና በየቀኑ ከ50 ያላነሰ ዳቤ በመጋገር በአገልጋይነታቸው የተመሰገኑ ነበሩ፡፡ በሚያዝያ 27 ቀን 1953 ዓ.ም የምስካየ ኅዙናን ገዳም የተምሮ ማስተማር ማኅበር ያሳተመው በራሪ ጽሑፍም «ቀድሞም በምናኔ ገዳምን አበው መነኮሳትን አሥራ ሁለት ዓመት በተልእኮ በመርዳታቸው ስመ ጥሩ እንደ ነበሩ ያሉት በቃላቸው የሞቱትም በመንፈሳቸው አስተላልፈውላቸው ይገኛል» ይላል፡፡ የቅዳሴ ትምህርት መማራቸውንና ዜማ እንደሚያውቁ አቶ አርአያ ይናገራሉ፡፡ ለዜማ የሚሆን ድምፅ ግን እጅግም አልነበራቸውም፡፡

ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣን እንደ ያዙ ወደ ደብረ ሊባኖስ ወርደው አንድን የበቁ አባት «አብያተ ክርስቲያናትን ለማሠራት አስበናል ሀብታችንን ተቆጣጥሮ ለሀገራችንም ለቤተ ክርስቲ ያናችንም በአግባቡ እንዲውል ለማድረግ ሁነኛ ሰው ያስፈልገናልና ምን እናድርግ)» ብለው አማከሯቸው፡፡ እኚያም አባት «ይህን የመሰለውን ሥራ ከአባ ሐና በቀር ማንም አይሠራውም» ሲሉ መለሱላቸው፡፡ ዐፄ ኃይለ ሥላሴና አባ ሐና የተገናኙት በዚህ መንገድ ነበር ይላሉ አቶ አርአያ፡፡ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ አባ ሐናን ከደብረ ሊባኖስ አምጥተው የግምጃ ቤቱ ኃላፊ አደረጓቸው፡፡

አቶ አርአያ አንደሚገልጡት አባ ሐና ሲበዛ መንፈሳዊ ሰው ነበሩ፡፡ ከሥጋና ከመጠጥ ተከልክለው ሽሮና ጎመን ነበር የሚበሉት፡፡ እንዲያውም በቤተ መንግሥቱ «የአባ ሐናን ሽሮ አምጡልን» እየተባለ ይጠየቅ እንደ ነበር ያስታውሱታል፡፡ ቤታቸው አንዲት ጠበባብ ክፍል፣ መኝታቸው ከደረቅ አልጋ ላይ እንደ ነበር በቅርብ የሚያውቋቸውና ብዙ ጊዜ በሥራ ምክንያት እየመሸባቸው በአባ ሐና ቤት ያድሩ የነበሩት አቶ አርአያ ይገልጣሉ፡፡

በዚያ ጊዜ ገና መሥሪያ ቤቶች ሁሉ በሚገባ ባለመደራጀታቸው አባ ሐና ብዙ ኃላፊነት ተሸክመው ነበር፡፡ ለአብያተ ክርስቲያናት መሥሪያና ለገዳማት መርጃ የሚውለውን ማደራጀት፡፡ ለጦሩ ልብስና ቀለብ ማዘጋጀት፣ የንጉሡን ትእዛዝ ለሚመለከተው ማስተላለፍ፣ ለቤተ መንግሥቱ የሚሆነውን ምግብና ቁሳቁስ ማዘጋጀት፣ ንጉሡ የሚሸልሙትን አልባሳትና ሌሎች የወግ ዕቃዎች ማደራጀት፣ወዘተ በእርሳቸው ኃላፊነት ላይ የወደቀ ነበር፡፡

በዚህ ሁሉ ኃላፊነታቸው የተነሣ እስከ ምሽቱ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ አምሽተው ይሠሩ እንደ ነበር አቶ አርአያ ያስታውሱታል፡፡ እንዲያውም አንድ ቀን ከምሽቱ ዘጠኝ ሰዓት ገብተው በአባ ሐና ቤት ምግብ ባለመኖሩ አቶ

አርአያ ጦማቸውን አደሩ፡፡ አባ ሐና ያንን ለንጉሡ በመናገራቸው 300 ብር አበል እንዲቀበሉ እንዳደረጓቸው ያስታውሳሉ፡፡

አባ ሐና ጅማ ሠራተኞችን በፍቅር ማሠራትን እንጂ በበላይነት ማዘዝን አይወዱም ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት በሥራቸው የነበሩትን አገልጋዮች ሥራ ባለበት ቦታ በጋራ የመሥራት ባሕልን አስለምደው ነበር፡፡ ሠራተኞቹ ሲያገለግሉ ውለው ተግባራቸውን ሲፈጽሙ ከአራዳ ጊዮርጊስ አካባቢ በገዛ ገንዘባቸው ሥጋ ገዝተው ማብላት ማጠጣጣት ልማዳቸው ነበር፡፡ በዚህም አገልጋዮቹ ይወዷቸው ነበር፡፡

ከአሁኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከድሮው ቤተ መንግሥት በስተ ጀርባ /በአፍንጮ በር በኩል/ ለቤተ መንግሥቱ ያቋቋሙት የአባ ሐና ወፍጮ የሚባል ነበር፡፡ እዚያ ቦታ ላይ ብዙ የአብነት ተማሪዎችን ከደመወዛቸው እያወጡ ይረዷቸው ነበር፡፡ ብዙ ወላጅ የሞቱባቸውን ሕፃናት ይረዱ እንደ ነበር ገንዘቡን በማከፋፈል በተግባር የተሳተፉት አቶ አርአያ ይገልጣሉ፡፡

አባ ሐና በጠባያቸው ቁጣና ቂም አያውቁም፡፡ ብዙ ሰዎች በክፉ ሲናገሯቸው «ዝለለው» እያሉ ያልፏቸው ስለ ነበር አባ ሐና «ዝለለው» በማለት የሚጠሯቸው ነበሩ፡፡

አባ ሐና ገብጋባ የሚለውን ስም ያተረፉት በራሳቸው ጠባይ ሳይሆን በቤተ መንግሥቱ የአሠራር ችግር የተነœ መሆኑን በዚያ ጊዜ በልጅነት አባ ሐናን የሚያውቋቸውና ቤተ መንግሥት ያገለግሉ በነበሩት አባታቸው ምክንያት ወደ ቤተ መንግሥቱ እየገቡ አባ ሐናን ለማወቅ የበቁት ሊቀ ጉባኤ አባ አበራ በቀለ ይገልጣሉ፡፡ እንዲያውም «አባ ሐና «escape goat» /በኦሪቱ ባላጠፋው ጥፋት የሕዝቡን ኃጢአት ተሸክሞ ወደ በረሃ የሚለቀቀው ፍየል/ ናቸው» ሲሉ ሊቀ ጉባኤ አስረድተዋል፡፡

በቤተ መንግሥቱ የነበረው የመጀመርያው የአሠራር ችግር ንጉሡ የግምጃ ቤቱን ዐቅም ሳያገናዝቡ ቃል መግባታቸው ነው፡፡ ይህ ንጉሡ ይገቡት የነበረው ቃል ከግምጃ ቤቱ ዐቅም በላይ ሲሆን አባ ሐና ያለውን ብቻ ለመስጠት ይገደዱ እንደ ነበርና ይህም ከተቀባዮቹ ጋር በግምጃ ቤት ሹምነታቸው ያጣላቸው እንደነበረ አቶ አርአያ ይናገራሉ፡፡ በዚህ የተነሣ ንጉሡ ቢሰጡኝም አባ ሐና ከለከሉኝ እያሉ የሚናገሩ ሰዎች ስማቸውን አጥፍተውታል፡፡

ሌላው ችግር ደግሞ በተለይም ከ1933 ዓ.ም በኋላ ግምጃ ቤቱ በጣልያን ስለ ተዘረፈ ባዶ ነበር፡፡ የእንግሊዝ መንግሥት ለጃንሆይ የሰጠው መጠነኛ ገንዘብ ብቻ ነበረ፡፡ አርበኞቹ እየመጡ ሲፎክሩ ንጉሡ ይህን ያህል ገንዘብና ልብስ ይሰጠው ብለው ያዝዛሉ አባ ሐናም ያለውን አብቃቅተው ይሰጣሉ፡፡ ይህ ተግባር በብዙ አርበኞች ዘንድ አልተወደደላቸውም፡፡ 25ኛው ዓመት ኢዮቤልዩ እስኪከበር ድረስ በቤተ መንግሥቱ የሀብት ችግር እንደ ነበር በቅርብ የሚያውቁት አቶ አርአያ ጠቁመዋል፡፡ ይህ ወቅት በተለይ አባ ሐናን በእጅጉ አሳጥቷቸዋል፡፡ አባ ሐና ግን « እኔኮ የንጉሡን ሸክም ተሸክሜ የምኖር ነኝ» እያሉ በደሉን በመሸከማቸው ይደሰቱበት ነበር፡፡ አባ ሐና ምንም መልካም ስም ባያተርፉባቸውም ብዙ ገዳማትና አድባራት እንዲረዱ፣ እንዲጠገኑና አዲስ እንዲሠሩ አድርገዋል፡፡ «ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አጠገብ ሆነው በመንፈሳዊው ረገድ ያለውን ኃላፊነት እየጠበቁ እንዲያስፈጽሙ ከተጠሩበት ጊዜ ጀምሮ ምቾቱ ሳያታልላቸው፤ ትሩፋታቸውንና ትህርምታቸውን ሳይከለክላቸው፤ ከርዳታቸው ሳይወጡ፤ ከመሥመራቸው ሳይናወጡ፤ በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለውን የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አደራ በታላቅ ትጋትና ታማኝነት ጠብቀው ትልቅ መገናኛ ድልድይ በመሆን የፈረሱት አብያተ ክርስቲያናት እንዲሠሩ፣ያረጁትም እንዲታደሱ፣ ካህናቱ በየጊዜው የሚደርስባቸው ችግር እንዲወገድላቸው ለግርማዊነታቸው እያቀረቡ ያስፈጽሙ ነበር» በማለት በምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም የተምሮ ማስተማር ማኅበር ያሳተመው የመታሰቢያ ወረቀት ያመሰግናቸዋል፡፡

አባ ሐና ፈሪሃ እግዚአብሔር የነበራቸው ሰው እንደ ነበሩ ለማስረዳት አቶ አርአያ አንድ ገጠመኛቸውን ይጠቅሳሉ፡፡ አንድ ቀን ዕቃ ለማፈላለግ ከተማዋን ሲዞሩ ውለው ከምሽቱ ሰባት ሰዓት አካባቢ ወደ ቤተ መንግሥቱ ለመመለስ ራስ መኮንን ድልድይ ሲደርሱ አባ ሐና አቶ አርአያን «እባክህ እግዚኦ ብለህ አዚም» ይሏቸዋል፡፡ በሁኔታው ግራ የተጋቡት አቶ አርአያ «በዚህ ምሽት የምን እግዚኦታ ነው?» ይላሉ፡፡ «አይ ዝም ብለህ እግዚኦ በል» ይሏቸዋል አባ ሐና፡፡ አቶ አርአያም «እግዚኦ» ብለው ያዜሙላቸዋል፡፡ ከዚያ በኋላ አባ ሐና አንድ ጥያቄ ጠየቋቸው፡፡ ለመሆኑ «እኔ የማን ነኝ? የእግዚአብሔር ነኝ እንዳልል አንድም ቀን አቡነ ዘበሰማያት ብዬ ጠይቄው አላውቅም? የሕዝቡ ነኝ እንዳልል አይ አባ ሐና ይለኛል፣ ታድያ እኔ የማን ነኝ?» ሲሉ ከባድ ጥያቄ አቀረቡላቸው፡፡ አቶ አርአያም «የማንም አይደሉም፤ የእግዚአብሔር ነዎት፡፡ ለዚህ ሥራ ያመጣዎት እግዚአብሔር ነው፡፡ ስለዚህ

በዚህ ሳይጨነቁ እርሱ ያመለከተዎትን ብቻ ይሥሩ» አሏቸው፡፡ ይህ ጉዳይ እስከ ንጉሡ ደርሶ አቶ አርአያን እንዳስመሰገናቸው ይተርካሉ፡፡

የምስካየ ኅዙናን ገዳም የመጀመሪያው አስተዳዳሪና ገዳሙ እንዲጠናከር ታላቅ አስተዋጽዖ ያደረጉት አባ ሐና ነበሩ፡፡ ገዳሙ በልማት ራሱን እንዲችል፣ ገዳማውያኑ በሥርዓት እንዲኖሩ ጥረት አድርገዋል፡፡ እንዲያውም በቤተ መንግሥቱ አንዳች ጠቃሚ ንብረት ሲያገኙ «ለምስካየ ኅዙናን ይሁን» እያሉ ንጉሡን አስፈቅደው ይወስዱ እንደ ነበር ይነገራል፡፡

የተምሮ ማስተማር ማኅበር እንዲጀመር፣ አባላቱ እንዲበዙና ከንጉሠ ነገሥቱ ጀምሮ መኳንንቱና መሳፍንቱ አባል እንዲሆኑ፣ በሀብት እንዲበለጽግ ታላቅ አስተዋጽዖ ማድረጋቸውን ገዳሙ ባረፉበት ቀን ያሳተመው ጽሑፍ ያስረዳል፡፡

አባ ሐና ሌላው የሚታወሱበት ሥራ የደብረ ሊባኖስን ቤተ ሰሊሆም የደካሞች መርጃ ገዳም እንዲመሠረት ማድረጋቸው ነው፡፡ ከዚህም በላይ ብዙ ዘመን ያገለገሉበትን ገዳም ደብረ ሊባኖስን በሚያስፈልገው ሁሉ ለመርዳት ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡

አባ ሐና ከራሳቸው ይልቅ ሌሎች እንዲሾሙ የሚፈልጉ ሰው እንደ ነበሩ ሟቹ ብጹዕ አቡነ ማቴዎስ ይናገራሉ፡፡ መንግሥቱ ንዋይን፣ አቡነ ማቴዎስን /ለታእካ ነገሥት በኣታ ለማርያም ሊቀ ሊቃውንትነት/፣አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህን፣ ወዘተ እየጠቆሙ ያስሾሟቸው እርሳቸው ነበሩ፡፡

ሌላው አባ ሐና የሚታወሱበት ነገር ለመነኮሳት የሚሆን አዲስ አለባበስ ያመጡ መሆናቸው ነው፡፡ ረዘም ያለ ካፖርትና ሱሪ መልበስን በስደት ወቅት ኢየሩሳሌም ሄደው ሳለ ተመልክተው ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያስተዋወቁት እርሳቸው ናቸው፡፡

አባ ሐናና መንግሥቱ ንዋይ ከጥንት ጀምሮ ወዳጆች ነበሩ፡፡ ብዙ ጊዜ ወደ ገዳማት ሙብፀ ለመላክ መኪና የሚጠይቁት ከእርሱ ነበር፡፡ የመፈንቅለ መንግሥቱ ዕለት አባ ሐናና አቶ አርአያ ወደ ብራዚል ለንጉሡ የሚላክ ቡና እያፈላለጉ ገበያ ነበሩ፡፡ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሲመጡ ነገሩ ሁሉ እንዳልነበር ሆኗል፡፡ ታላላቅ ባለ ሥልጣናት እየተያዙ ታሥረው ነበር፡፡ አባ ሐና ግን በመንግሥቱ ንዋይ መኪና እንዲቀመጡ ተደርገው ይዟቸው ሲዞር ነበር የዋለው፡፡

በመጨረሻ መፈንቅለ መንግሥቱ መክሸፉ ሲታወቅ የተያዙት ባለሥልጣናት እንዲገደሉ ሃሳብ ሲቀርብ መንግሥቱ ንዋይ ራስ ስዩምና አባ ሐና እንዲለቀቁ ሃሳብ ነበረው፡፡ ግርማሜ$ ንዋይ ግን በዚህ ሃሳብ አልተስማማም፡፡ ስለዚህም እርሱ ራሱ በጥይት መትቶ ረቡዕ ለኀሙስ ሌሊት ታኅሳስ 3 ቀን 1953 ዓም ገደላቸው፡፡ እሑድ ዕለትም ደብረ ሊባኖስ ተቀበሩ፡፡

ሲሞቱ ዕድሜያቸው ወደ 70 ይጠጋ እንደ ነበር አቶ አርአያ ገምተዋል፡፡ እርሳቸው ካረፉ በኋላ የሚጠሏቸው ሰዎች አንዲት ሥራ ቤት ውስጥ ታገለግል የነበረች ሴት በገንዘብ አታልለው ወደ እቴጌ መነን ላኩ፡፡ እርሷም ሁለት ልጆቿን ይዛ ቀርባ «ከአባ ሐና የወለድኳቸው ናቸውና ውርስ ይገባኛል» አለች፡፡ እቴጌ መነን ተናድደው «አባ ሐና ከአንቺ ጋር ይህን የመሰለ ነገር የሚፈጽምበት ቀርቶ እህል የሚቀምስበት ጊዜ የሌለው ሰው ነው፡፡ ይህ ስሙን ለማጥፋት ያቀዳችሁት ነው፡፡ በሉ ያዟትና እውነቱን ታውጣ፡፡» ብለው ተናገሩ፡፡ በዚህ ጊዜ ሴትዮዋ ደንግጣ በገንዘብ ተገዝታ ይህንን መፈጸሟን በግልጽ ተናገረች፡፡ ምንጭ፡ የቃል አስረጅ፡ ሊቀ ጉባኤ አባ አበራ በቀለ፣ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ የነበሩ፤አቶ አርአያ ተገኘ፣ በቤተ መንግሥት የግምጃ ቤት ሹም የነበሩ፤ ሟቹ ብጹእ አቡነ ማቴዎስ፤ የተምሮ ማስተማር ማኅበር ሚያዝያ 27 ቀን 1953 ዓ.ም ያሳተመው ወረቀት፤ ፋንታሁን እንግዳ፣ታሪካዊ መዝገበ ሰብ፣ 2000 ዓም፡፡ አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ታኅሣስ 26፣ 1953፤ መነን መጽሔት፣ የካቲት/ መጋቢት፣ 1953 ዓም

## የሴቶች አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን

የሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መጀመርያ በፖርቹጋሎች፣ በኋላም በእንግሊዝ ቅኝ ገዥዎች በደረሰባት መከራ ዐቅሟ ተዳከመ፡፡ መንበረ -ፓትርያርኩ የነበረበት ሶርያም በደረሰበት ጫና ምክንያት ሕንድን ለመርዳት አልቻለም፡፡ በ1806 እኤአ ወደ ፕሮቴስታንቶች ማሠልጠኛ እየገቡ በተማሩ አገልጋዮች ምክንያት «ቤተ ክርስቲያን በወንጌል አልተመራችም´ የሚል ንቅናቄ ተጀመረ፡፡ ቀጥሎም «ለቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ያስፈልጋል´ የሚል እንቅስቃሴ ተቀጣጠለ፡፡ የተሐድሶ ኮሚቴ የሚባልም ተቋቁሞ ምልጃ ቅዱሳን፣ በዓለ ቅዱሳን፣ ነገረ ማርያም፣ ክብረ ሥዕል፣ ቅዳሴ፣ ጾም እና መጻሕፍተ ቅዱሳን እንዲቀሩ ወሰነ፡፡

ይህንን ውሳኔ አብዛኞቹ ጳጳሳት እና ካህናት ተቃወሙት፡፡ ምእመናንም ለሁለት ተከ ፈለ፡፡ ነገር ግን በፕሮቴስታንት እምነት የተለከፉ አገልጋዮች የራሳቸውን ጳጳስ ሾመው ተሐድሶውን ገፉበት፡፡ ተሐድሶዎቹ ቤተ ክርስቲያኒቱን በፍርድ ቤት ከሰሱ፡፡ በ1879 ዓም የተጀመረውም ክስ በጁላይ 12 1889 ዓም እኤአ ተጠናቀቀ፡፡ ፍርድ ቤቱም የቤተ ክርስቲያኒቱ ሀብት እና አጥቢያዎች ለሁለት እንዲከፈሉ ወሰነ፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቱም በሕግ ለሁለት ተከፈለች፡፡ ተሐድሶዎችም «ማር ቶማ ቤተክርስቲያን´ የሚባል መሠረቱ፡፡ቤተ ክርስቲያኒቱ ሀብቷን፣ አጥቢያዎቿን እና ገዳማቷን በማጣቷ ተዳከመች፡፡ ሕዝቡም ተስፋ ቆረጠ፡፡ ካህናቱ ደመወዝ አጡ፡፡ አገልግሎቱንም መስጠት ተቸገሩ፡፡ ምእመኑንም ተሐድሶዎቹ እና ፕሮቴስታንቶቹ ይወስዱት ጀመር፡፡ በዚህ ሁኔታ ያዘኑት የሕንድ እናቶች ተሰብስበው «አንድ ሆነን ቤተ ክርስቲያናችንን እንታደግ» ብለው ወሰኑ፡፡ በሳምንቱ ቀናት ሩዝ ሲቀቅሉ አንድ እፍኝ ሩዝ በማስቀመጥ በሰንበት ይዘው ለመምጣት ተስማሙ፡፡ ያንን አጠራቅመውም አብያተ ክርስቲያናቱን አስጠገኑ፡፡ ገዳማቱን አሠሩ፡፡ ለካህናቱ ደመወዝ ከፈሉ፡፡ መንፈሳዊ ኮሌጅ ከፈቱ፡፡ መም ህራንን አሠለጠኑ፡፡ እንዳሉትም ቤተ ክርስቲያናቸውን ታደጉ፡፡ ዛሬ የሕንድ ሴቶች በቤተ ክርስቲያናቸው ክህነታዊ ባልሆነው አገልግሎት ሁሉ በመሳተፍ ዕድገት እያስመ ዘገቡ ነው፡፡ እኛስ ጋ?በቤተ ክርስቲያን የሴቶችን ተሳትፎ በተመለከተ ሁለት ዓይነት ጽንፈኛ አስተሳሰቦች አሉ፡፡ የመጀመርያው ሴቶች እስከ ክህነት ድረስ በሚደርስ አገልግሎት መሳተፍ አለባቸው የሚለውና ከቤተ ክርስቲያን አመሠራረት፣ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን እና ከተፈጥሮ ጋር የሚጣረስ አመለካከት ነው፡፡ ሐዋርያት ሁሉም ወንዶች ናቸው፡፡ በጥንቷ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የሴቶች ተሳትፎ ክህነታዊ ባልሆነው አገልግሎት ነበር፡፡ ለሴቶች ክህነት የሚሰጥ ቢሆን ኖሮ ከድንግል ማርያም በተሻለ የቀረበ እና የተገባው ባልኖረ ነበር፡፡ ሁለተኛው ደግሞ እናቶች እና እኅቶች ምግብ ከማብሰል ቢበዛም ቆሞ ከማስቀደስ ያለፈ አገልግሎት አይገባቸውም የሚለው እና ሴቶችን ፈጽሞ «የሚያገልለው´ አመለካከት ነው፡፡ ይኼኛውም አመለካከት ቢሆን ድንግል ማርያም በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የነበራትን ቦታ የዘነጋ፣ ጌታችንም ሠላሳ ስድስት ቅዱሳት አንስት መምረጡን የማያስ ታውስ አስተሳሰብ ነው፡፡ትክክለኛው መንገድ ከሁለቱም መካከለኛው ነው፡፡ ለእናቶች እና ለእኅቶች ጾታቸውን ያልረሳ፣ደረጃቸውን የጠበቀ፣በበቂ ሁኔታ ዕውቀታቸውን እና ጊዜያቸውን ሠውተው ሊያገለግሉበት የሚችሉት ተገቢ ቦታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያስፈልጋቸዋል፡፡እናቶች እና እኅቶች በብዛት የሚሳተፉባት በቤተ ክርስቲያን የታደለች ናት፡፡ ቤተ ክርስቲያናች ለሁለት ሺ ዓመታት ከውጭ ሀገር ምንም ዓይነት ንዋያተ ቅድሳትን ሳታስገባ አገልግሎቷን እንድትቀጥል ያደረጓት እናቶች ናቸው፡፡ አልባሳቱን ፈትለው፣ መጎናጸፊያውን አዘጋጅተው፣ ሞሰበ ወርቁን ፈትለው፣ መገበርያውን መርጠው አዘጋጅተው፣ ተማሪውን አብልተው አስተምረው፣ ቤተ ክርስቲያኑን ጠርገው፣ ምንጣፉን አራግፈው፣ ካህናቱን አብልተው ለዚህ ያደረሱን እናቶቻችን ናቸው፡፡ የግሪክ አልባሳት ቦታውን የያዙት ከሠላሳ ዓመታት ወዲህ ነው፡፡ሌላው ቀርቶ እንደ እነ እሙሐይ ሐይመት፣ እሙሐይ ገላነሽ የመሳሰሉት አንስት ቅኔውን ተምረው፣ በቅኔውም ተመርቀው፣ የቅኔ መምህራን በመሆን አያሌ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል፡፡ እንደነ እቴጌ እሌኒ ያሉት ደግሞ የሃይማኖት መጻሕፍትን አበርክተዋል፡፡ እንደ እነ ወለተ ጴጥሮስ ያሉት በሱስንዮስ ዘመን ሃይማኖታቸውን እየዞሩ አስተምረዋል፣ ገዳም መሥርተዋል፡፡ እንደ እነ ክርስቶስ ሠምራ ያሉት በሃይማኖት ተጋድለዋል፣ እንድ እነ መስቀል ክብራ ያሉት ከላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዱን አንጸዋል፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን በቂ እና ውጤታማ ዕድገት ሊመጡ ካልቻሉባቸው ምክንያቶች አንዱ የእናቶቻችን እና እኅቶቻችን ምግብ ከማብሰል ያለፈ አገልግሎት ባለመስጠታቸው ነው፡፡ እነርሱም ያንኑ እንደ በቂ ተቀብለውታል እኛም አናበረታታቸውም፡፡ በቤተ ክህነቱም ከተላላኪነት፣ ከገንዘብ ያዥነት፣ ከታይፒስትነት እና መዝገብ ቤትነት ያለፈ ድርሻ ያላቸው እኅቶችን አይቼ አላውቅም፡፡ እናቶቻችን እና እኅቶቻችን ግን ከዚህም የበለጠ ኃላፊነት በቤተ ክርስቲያን ሊኖራቸው ይገባል፡፡ እንደምናውቀው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁለት ዓይነት አገልግሎቶች አሉ፡፡ የክህነት እና የክህነት ያልሆኑ፡፡ እናቶቻችን እና እኅቶቻችን ክህነታዊ ባልሆኑት አገልግሎቶች ከወንዶች የተሻለ ውጤታማ ናቸው ብዬ አስባለሁ፡፡ ክህነታዊ ያልሆኑ አገልግሎቶች የምንላቸው በአስተዳደር፣ በፋይናንስ፣ በትምህርት፣ በማኅበራዊ አገልግሎት፣ በማስታረቅ አገልግሎት፣ በኅትመት፣ በንዋያተ ቅድሳት ዝግጅት፣ እና በመሳሰሉት ነው፡፡በእነዚህ አገልግሎቶች ክርስትናው የገባቸው፣ ደረጃቸውን የሚያውቁ፣ በሃይማኖት ትምህርት የበሰሉ እናቶችን እና እኅቶችን ክህነታዊ ባልሆነው አገልግሎት ማሳተፉ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎቶች ቀልጣፋ እና ውጤታማ ያደርጋቸዋል፡፡ለምን?· እናቶች እና እኅቶች ከወንዶች ይልቅ በአንድ ነገር ላይ ተረጋግተው መሥራት ይችላሉ፡፡ በየጊዜው ስሜታቸውን እና መንገዳቸውን በመቀያየር ሥራዎችን አያባክኑም፡፡· በፖለቲካዊ እና ጎሳዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የወንዶችን ያህል

ጥልቅ ስለማይሉ ዘር እና ፖለቲካን ከእምነት ጋር የመቀላቀሉ በሽታ እምብዛም አይታይባቸውም፡፡· በቤተ ክርስቲያን ሰው ለሚያጫርሰው የደብር አስተዳዳሪነት፣ ወረዳ ሊቀ ካህንነት፣ የጳጳስነት እና ሌላውም ዓይነት ሹመት ስለማይመለከታቸው ከሥልጣን ፆር የራቀ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡፡· እነርሱ የቤተ ክርስቲያንን ነገር በሚገባ ካወቁ ልጆቻቸውን ለቤተ ክርስቲያን የሚመቹ አድርገው ማሳደግ ይችላሉ፡፡· «ሴት የላከው ጅብ አይፈራም´ ይባላልና ወንዶቹን በትክክለኛው መንገድ እንዲጓዙ መንገዱን ማመላከት እና መግፋትም ይችላሉ፡፡· የርኅራኄ እና የኀዘኔታ ልብ ስላላቸው ባለጉዳዮችን በሚገባ ለማስተናገድ፣ ገዳማት እና ለአድባራት፣ ገጠርም አብያተ ክርስቲያናት፣ ተጎዱ ምእመናንም ያዝናሉ፡፡· ሕፃናትን በሰንበት ት/ቤቶች ለማስተማር እኅቶች የተሻለ ትእግሥት እና ችሎታ አላቸው· በሕክምና አገልግሎት፣ ድኾችን በመርዳት፣ ማኅበረሰብ ተኮር አገልግሎት በመስጠት ሴቶች የተሻለ ውጤታማ ናቸውበእነዚህ እና በሌሎችም ምክንያቶች እናቶቻችን እና እኅቶቻችን በቤተ ክርስቲያን ተገቢያቸው የሆነውን አገልግሎት እንዲያገለግሉ መበረታታት አለባቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ በአበው መካከል ልዩነት እና ግጭት ሲፈጠር ከወንዶቹ ይልቅ አልቅሰውም ይሁን ብልሃት ፈጥረው እንዲታረቁ እና እንዲስማሙ ለማድረግ እናቶቻችን እና እኅቶቻችን ይሻላሉ፡፡

በዚህ አገልግሎት የሚሳተፉት እኅቶች እና እናቶች ግን ለራሳቸውም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን የመከራ ምንጭ እንዳይሆኑ መመዘኛዎች ያስፈልጋሉ፡፡ እነዚህ መመዘ ኛዎች ታድያ ወንዶቹንም የሚመለከቱ ናቸው፡፡1.የሃይማኖት ትምህርት በሚገባ የተማሩ2.የንስሐ አባት ያላቸው እና በሥጋ ወደሙ የጸኑ3.በአንድ ባል የጸኑ ወይንም መነኮሳዪያት የሆኑ4.በማኅበረሰቡ ዘንድ በሥነ ምግባር የተመሰከረላቸው5.ፈሪሃ እግዚአብሔርን እና ትኅትናን ገንዘብ ያደረጉመሆን አለባቸው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገባቸው እናቶች አና እኅቶች በተገቢው ቦታ እንዲያገለግሉ ካላደረግን በገንዘባቸው የሚመኩ፣ ሥነ ምግባር የሌላቸው፣ ሴትነ ታቸውን ለክፉ ሥራ የሚጠቀሙበት፣ ደረጃቸውን የማያውቁ፣ እነርሱ ተሰድበው ቤተ ክርስቲያንን የሚያሰድቡ፣ ለአባቶች የስሕተት ምንጭ የሚሆኑ ሴቶች ቦታውን ይዘው መከራ ያመጡብናል፡፡

# <u>ግመሎቹም ይሄዳሉ ውሾቹም ይጮኻሉ</u>

ሚቹ የ «እንደ ቸርነትህ´ መዝሙር ደራሲ ዶክተር ኢሳይያስ ዓለሜ እንዲህ ይላሉ፡-

አንድ አባት አህያውን እየነዳ ከልጁ ጋር መንገድ ጀመረ፡፡ እልፍ እንዳለ ሰዎች ተመለከቱትና «ምን ዓይነት ሞኞች ናቸው፤ እንዴት አህያ እያለ በእግራቸው ይሄዳሉ´ በማለት ተቿቸው፡፡ አባትም ትችቱን ሲሰማ ሀሳቡን ቀየረ፡፡ ሁለቱም አህያዋ ላይ ወጡና መንገዳቸውን ቀጠሉ፡፡ ጥቂት እንደሄዱ ሌሎች ሰዎች አዩዋቸውና «እንዴት ያሉ ጨካኞች ናቸው፤ እንዴት አንድ አህያ ለሁለት ይጋልባሉ´ ብለው ራሳቸውን ነቅንቀውባቸው ጥለዋቸው ሄዱ፡፡

አባትዬውም ከአህያዋ ላይ ወረደ፡፡ እርሱ ከኋላ አህያዋን እየነዳ ልጁን በአህያዋ ጭኖ ጉዞውን ተያያዘው፡፡ የተወሰነ መንገድ ከተጓዘ በኋላም ሌሎች መንገደኞችን አገኘ፡፡ እነዚያም መንገደኞች አባት እና ልጁን አዩና «አይ ስምንተኛው ሺ፤ አያሳየን የለ፤ ልጁ በአህያ ተቀምጦ ሽማግሌ አባቱን በእግሩ ያስኬደዋል፡፡ አበስኩ ገበርኩ´ ሲሉ ሰማ፡፡

ወዲያው ልጁን ከአህያዋ አውርዶ እርሱ ተጫነና ጉዞው ተጀመረ፡፡ መንገዳቸውን እንዳጋመሱም ከገበያ የመጡ ሰዎችን አገኟቸው፡፡ እነዚያም መንገደኞች ጉዟቸውን ገትተው «እንዴት ምኑንም የማያውቅ ልጁን በእግሩ እያስደገደገ እርሱ በአህያ ይሄዳል፤ ወይ ጭካኔ፣ወይ ጭካኔ´ ብለው ደረታቸውን ደቅተው ሄዱ፡፡

በዚህ ጊዜ አባትዬው ከአህያዋ ወረደና ለልጁ እንዲህ አለው፡፡ «አየህ ልጄ በዚህ ዓለም ምንም ነገር ብትሠራ ሰውን ሁሉ ማስደሰት አይቻልም፡፡ ሰዎች እንዲህ ይሉኛል እያልክ የምትፈራ ከሆነ ምንም ነገር ማድረግ አትችልም፡፡ ሰዎች ምንም ብታደርግ የሚሉት አያጡምና፡፡ አንተ ሰውን ሳይሆን ስሕተትን ፍራ፡፡ ትችትን ሳይሆን ኃጢአትን ፍራ፡፡

ሰዎች ስላሉት ብቻ የምትቀበል ከሆነ ሃሳብህን መቶ ጊዜ ትቀያይራለህ፡፡ መቀበል ያለብህ የሚሉት ነገር ትክክል ከሆነ ብቻ ነው፡፡´ አለው፡፡ ከዚያም አባት እና ልጅ እየተጨዋወቱ መንገዳቸውን ቀጠሉ፡፡

ሰዎች ቢያመሰግኑን አይጠላም፡፡ እንዲያመሰግኑን ብለን መሥራት ግን የለብንም፡፡ ለምዶብን አንዳንዶቻችን የብርጭቆውን ውኃ ስናይ ግማሽ ጎዶሎ መሆኑን እንጂ ግማሽ ሙሉ መሆኑን አናይም፡፡

የሰዎችን ሃሳብ ስንሰማ ቢያንስ ሦስት ነገሮችን መመዘን አለብን፡፡

ይህ ሰው ይህንን አስተያየት ለመስጠት ብቁ ነውን? በሞያው፣ በዕድሜው፣ በውሎው፣ በትምህርቱ፣ በልምዱ፣ ይህንን አስተያየት ለመስጠት ሚዛን የሚደፋ ከሆነ ግምት ውስጥ አስገብተን እንመርምረው፡፡

ይህ ሰው ይህንን አስተያየት አስተያየት ሲሰጥ ከልቡ ነውን? አስቦበት፣ አመዛዝኖ፣ በመሠረተ ሃሳብ አስደግፎ ነው ወይስ እንዲሁ ስለመጣለት በስሜት ተነሣሥቶ?

ይህ ሰው ከሚያነሣው ነገር ጋር የጥቅም ግጭት የለውምን? ክብሩን፣ ሥልጣኑን፣ ገንዘቡን ስለሚነካበት ያንን ለማስጠበቅ ነውን? ተመቅኝቶ፣ ቀንቶ ወይንም ግላዊነት አጥቅቶት ነውን?

ጉዳዩን ያለዚያ ቀን ሰምቶት የማያውቅ፣ በዚያ ነገር በትምህርት፣ በዕድሜ፣ በንባብ ወይንም በልምድ የተገኘ ዕውቀት የሌለው፤ እንዴው አፌ ተባልኝ፣ ንግግሬ ተደመጠልኝ፣ ጨዋታዬ ደራልኝ ያለ ሁሉ የሚናገረውን ሰምተን ሃሳባችን መቀየር፣ መጠራጠር ወይንም ደግሞ ራሳችንን እንደ ስሕተተኛ መቁጠር የለብንም፡፡ አንዳንዱኮ «ይህ ነገር አላማረብህም´ ሲል የሠራውን አርፍተ ነገር ትርጉም እንኳን በቅጡ አያውቀውም፡፡ አንዳንዱም ሰው ሁሉ ሲናገር ከሚቀርብኝ ብሎ ሃሳብ የሚሰጥም አለ፡፡

እንደመጣለት የሚናገረውስ ቢሆን፡፡ ሊቃውንት «አንድ ጊዜ ከመናገር በፊት ሁለት ጊዜ ማሰብ ይገባል´ ይላሉ፡፡ እንኳን ሁለት ጊዜ አንድ ጊዜ እንኳን ሳያስብበት እንደመጣለት የሚናገረውን ሰው እየሰማን እኛ ለምን እንዳደዳለን? ለምንስ መንገዳችንን እንስታለን፡፡ ምናልባትኮ አንዳንዱ የተናገረው ለርሱ ቀልድ ይሆናል? በጆሮው የሰማውን በአንደበቱ ለማውጣት ምንም ዓይነት ሂደት በአእምሮው የማያከናውን ሰው ሞልቷል፡፡ የመንገድ ላይ ቱቦ ያስገባውን ሁሉ እንደሚያወጣ ያየውን እና የሰማውን ሁሉ ሳያጣራ፣ ሳያበጥር፣ ሳይመረምር፣ ይዋል ይደር ሳይል እንዳለ የሚለቅም አለኮ፡፡

«ይህን ነገር ማድረግሽ ስሕተት ነው´ ሲል «ማድረግ የነበረብኝ እኔ ነበርኩ´ እያለ መሆኑን ልንረዳለት የሚገባን ሰውኮ አለ፡፡ «ሰዎች እንዲህ ይላሉ´ ከሚለው ወገናችን በዛ ያለው ራሱ የሚለውን «ሰዎች´ በሚል ባለቤት አልባ ባለቤት በኩል እየነገረን መሆኑንም መጠርጠር ይገባል፡፡

ታድያ የሚያዋጣው ምንድን ነው? መሥራት፡፡ መጀመርያ ነገር ለምናደርገው ሁሉ ለራሳችን አሳማኝ ምክንያት ይኑረን፡፡ ርግጠኞች እንሁን፡፡ ከምንመራበት መሠረተ ሃሳብ፣ ከእውነት እና ከታወቁ እውነታዎች ጋር መዝነነው ትክክል መሆኑን እንመንበት፡፡ ሰዎች በማስረጃ ወይንም በመረጃ የሚያቀርቡልንን ሃሳብ ሁሉ ለመቀበል ለራሳችን ዝግጁ እንሁን፡፡

ከዚያ በኋላ ያለ የሌለ ጉልበታችንን ሥራችን ላይ እናውል፡፡ ምን ተባለ ም?ን አሉ? ምን መልስ ልስጥ? በምን ላሳምናቸው? እያልን ስንብሰከሰክ ወርቃማውን የሥራ ጊዜ እናሳልፈው፡፡ «ወፎች ከጭንቅላታችን በላይ እንዳይበርሩ ማድረግ አይቻልም፤ በጭንቅላታችን ላይ ጎጆ እንዳይሠሩ ማድረግ ግን ይቻላል» የሚል አባባል አለ፡፡ ሰዎች ስለ እኛ ሥራ አንሥተው እንዳያሙ፤ እንዳይተቹ፣ እንዳያጣጥሉ፣ እንዳያንቋሽሹ ማድረግ አንችልም፡፡ የእነርሱ ትችት እና ሐሜት በጆሯችን ገብቶ ኅሊናችንን እንዳይረበሽን ማድረግ ግን እንችላለን፡፡ የተነገረውን ሁሉ ማስማት የተጮኸውን ሁሉ ማዳመጥ የለብንምና፡፡

ደግሞም ሁሉንም ሰዎች ማስደሰት አይቻልም፡፡ እኛ ሃሳብ እና አእምሮ ያላቸውን፣ በምላሳቸው ሳይሆን በጭንቅላታቸው የሚያስቡትን፡፡ አንደበታቸው ከልባቸው፣ ስሜታቸው ከኅሊናቸው ያልቀደመባቸውን ሰዎች፣ ያውም ከእነርሱም መካከል ነገራችን ሊገባቸው የሚችሉትን ካረካን እድለኞች ነን፡፡

ብዙ የሚለፈልፉ ሰዎችን አንፍረድባቸው፡፡ ሠርተው የሚያሳዩት ነገር የላቸውምና፡፡ ብዙ የሚሠሩ ሰዎች ግን ምንም መናገር አያስፈልጋቸውም፡፡ ከንግግር በላይ ተግባር መልስ ነውና፡፡ ሰዎች ለምን እንዲህ ይሉኛል? ለምን የኔ ሥራ አይገባቸውም? ለምን አይረዱኝም? እያሉ በመጨነቅ አእምሮን በማይጠቅሙ ቫይረሶች ከመሙላት የሚችሉትን ሠርቶ ሰዎች በራሳቸው ጊዜ እንዲረዱት መተው ነው፡፡

በዓለም ላይኮ መሬት ክብ ናት በማለታቸው ሞት የተፈረደባቸው ሰዎች ነበሩ፡፡ ነገር ግን ሰዎች ስለተቿቸውና በዘመኑ ስላልተቀበሉት ብለው አልተውትም፡፡ በመጨረሻ ያሸነፉት እነርሱ ናቸው፡፡ በወቅቱ ዓለም ያላየውን እነርሱ አዩ፡፡ ዓለም ግን ዘግይቶ እነርሱ ያዩትን አየ፡፡ ያን ጊዜ ዓለም ይቅርታ ጠየቀ፡፡

የምንሠራው ሥራ ዛሬ ሰዎች ላይገባቸው ይችላል፤ ላይፈልጉትም ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ቀን አለው፡፡ ሰው ሁሉ በአንድ ቀን አልተፈጠረምና በአንድ ቀን እኩል አይረዳም፡፡ ቀልድ ተነግሮት እንኳን ሲጀመር የሚስቅ አለ፤ በመካከል መሳቅ የሚጀምር አለ፤ ሲያልቅ ገብቶት የሚስቅ አለ፤ አድሮ የሚያስቀው አለ፤ ከርሞ የሚያስቀው አለ፤ ጭራሽ የማያስቀውም አለ፡፡ አሁን ቀልዱ ቀልድ መሆኑን በምንድን ነው ማወቅ የሚቻለው?

ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ ስልብ ነበሩ ይባላል፡፡ ታድያ ዐፄ ምኒሊክ ጎራ ሸለሟቸውና ሰው ሁሉ አደነቀላቸው፡፡ ወዳጆቻቸውም «ይህንን ነገር የማያደንቅ ገብረ ሐና ብቻ ነው» ይሏቸዋል፡፡ ያስጠሯቸውና ለአለቃ ገብረ ሐና ያሳዩዋቸዋል፡፡ አለቃም ጎራዴውን እያገላበጡ «አይ ጎራዴ፣ አይ ጎራዴ፣ ጎራዴ፣ ጥሩ ጎራዴ» ብለው ያደንቁላቸዋል፡፡ ባልቻም ደስ ብሏቸው ይለያያሉ፡፡

ወዳጆቻቸውም «ገብረ ሐና ምናለ?» ብለው ይጠይቋቸዋል፡፡ ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶም «በደንብ ነው ያደነቀው» ብለው ይመልሳሉ፡፡ «እስኪ ምናለ?» ይላሉ ወግ ፈላጊዎቹ፡፡ «አይ ጎራዴ፣ አይ ጎራዴ ብሎ አደነቀ» ይሏቸዋል፡፡ ያ ሁሉ ሰው በሳቅ ያወካና «እንዴ ደጃዝማች ባልቻ ከዚህ በላይ ገብረ ሐና ምን ሊልዎት ነው» ብለው ያስረዷቸዋል፡፡ ያን ጊዜ ጀግናው ባልቻ እገላለሁ ብለው ያዙኝ ልቀቁኝ አሉ ይባላል፡፡

ዐረቦች «ግመሎችም ይሄዳሉ፣ ውሾቹም ይጮኻሉ» የሚል አባባል አላቸው፡፡ የዐረብ ነጋዴዎች ግመሎቻቸውን ጭነው በመንደሮቹ መካከል ሲያልፉ ውሾቹ እየጮኹ አያሳልፏቸውም፡፡ ነገር ግን በእነርሱ ምክንያት መንገዳቸውን አያቆሙም፡፡ ግመሎቹም መሄዳቸው፣ ውኾቹም መጮኻቸው የማይቀር ነገር ነውና፡፡

ሰው በሚያገባውም በማያገባውም መተቸቱ የማይቀር ነው፡፡ ዋናው መርጦ መውሰዱ ላይ ነው፡፡ ነጭ ሲደረግ ለምን ጥቁር አልሆነም፣ ጥቁር ሲደረግ ለምን ሰማያዊ? ሰማያዊ ሲሆን ለምን ግራጫ? ግራጫ ሲሆን ለምን ቢጫ? ይቀጥላል፡፡ ሰው ይህንን ሁሉ እየሰማ ቀለም ሲቀያይር የሚኖር ከሆነ የሚሠራው ቤት ቀለም ማስተማርያ መሆኑ ነው፡፡

እኛም የምንናገር ሰዎችም ብንሆን የምንናገረው ነገር የዕውቀታችን ማስመስከርያ ሞን የለበትም፡፡ ሊሆን ሊደረግ የሚችል መሆኑን እና አለመሆኑን መለየት አለብንኮ፡፡ ሴትዮዋ ወንበር ገዝታ ከመጣች በኋላ «አይ እዚህ ሱቅኮ በርካሽ የሚሸጥ ነበረልሽ´ ብሎ ማስፀፀት ጥቅሙ ምንድን ነው? እየደጋገመ ሴት የወለደን ሰው «የአሁኗ እንኳን ወንድ ብትሆን ጥሩ ነበር» እያሉ መመጻደቅ ምንድን ነው? ሰውዬው ወስኖ አልወለዳት፡፡ ሰውዬው ከሞተ በኋላ ቋሚውን «እንዲህ ቢያደርግ ኖሮኮ አይሞትም ነበር» እያሉ ለማይመለስ ነገር ቆሽት ማሳረር ምን የሚሉት ሞያ ነው?

ሰው የሚለውን ሁሉ አልቀበልም ማለትም በሽታ ነው፡፡ ሰው የሚለውን ሁሉ መቀበልም ጦስ ነው፡፡ ሰው ለሚለው ሁሉ ዝም ማለትም በሽታ ነው፡፡ ሰው ለሚለው ሁሉ መልስ መስጠትም ጦስ ነው፡፡ ሰው በተቸ ቁጥር ሃሳብን መቀየር ጅልነት ነው፡፡ ሰው የፈለገውን ቢል ሃሳቤን አልቀይርም ማለትም ግትርነት ነው፡፡ ሰው በተናገረ ቁጥር መናደድ እና ማረርም ቂልነት ነው፡፡ በሰው ንግግር ሁሉ መቀለድም ቂላቂልነት ነው፡፡

ልብ ያለው የሚባለውን ነገር ጆሮው በር ላይ አስቀምጦ ይመዝነዋል፡፡ የሚረባ ከሆነ ያስገባዋል፤ የማይረባ ከሆነ ተቀባይ እንዳጣ ፖስታ ይመልሰዋል፡፡ እንዲህ ያለው ሰው በልቡናው ውስጥ የማይጠቅሙ ሃሳቦች ማጠራቀሚያ ቅርጫት የለውም፡፡

# ባርባራ እና ስቴፈን

አንዳንድ ጊዜ በሕይወታችን የዕለት ተዕለት ተግባራት የሚያጋጥሙንን ነገሮች ካስተዋልናቸው በትምህርት ቤት የማናገኛቸውን ዕውቀቶች እንገበይባቸዋለን፡፡ መደበኛውን ሥራችንን እንኳን ቢሆን በማዳመጥ እና በፍቅር ከሠራነው ለዕድሜ ልክ የሚሆኑ ዕውቀቶችን እግረ መንገዳችንን እናገኛለን፡፡ አንዲት አሜሪካዊት ነርስን ያጋጠማት ነገርም እንደዋዛ ነበር ሕይወቷን የቀየረው፡፡

አንድ ቀን አንድ ሽማግሌ ታካሚ ሰው ከነርሷ ፊት ለፊት ተቀምጠው አሁንም አሁንም ይቁነጠነጡ ነበር፡፡ አሁንም አሁንም ደጋግመው ሰዓታቸውን ያያሉ፡፡ ነርሷ ገረማትና ረጋ ብለው ሕክምናቸውን እንዲከታተሉ ነገረቻቸው፡፡ ሃሳቧን ተቀብለው ለጥቂት ሰኮንዶች ረጋ ቢሉም አሁንም የቀደመ ነገራቸው ተመለሰ፡፡

«ለምንድን ነው ይህንን ያህል ያልተረጋጉት? ያጋጠመዎ ችግር አለ?» አለቻቸው፡፡

«ፈጽሞ፤ ምንም ዓይነት ችግር አላጋጠመኝም»

«ታድያ ለምን ይቁነጠነጣሉ፤ መረጋጋትኮ አልቻሉም» አለቻቸው፡፡

«ይቅርታ» አሉና አንገታቸውን ደፋ አደረጉ፡፡ ነገር ግን ወዲያውኑ ሰዓታቸውን ደግመው ተመለከቱት፡፡

«ሐኪሙን ለማግኘት የቸኮሉበት ምክንያት አለ?» አለቻቸው ነርሷ የሰውዬው ሁኔታ እንግዳ ሆኖባት፡፡

«አዎ፤ በቶሎ እርሳቸው ጋር ቀርቤ ብጨርስ ጥሩ ነው» አሏት፡፡

«ሌላ ሐኪም ጋር ቀጠሮ ይዘዋል» አለቻቸው፡፡

«ፈጽሞ፤ ሌላ ሐኪም ጋርስ ቀጠሮ የለኝም» አሉ ታካሚው፡፡

«ታድያ ወዴት ለመሄድ ነው ይህንን ያህል የቸኮሉት፡፡»

«ከባለቤቴ ጋር አምስት ሰዓት ላይ ቀጠሮ አለኝ» አሉ ታካሚው፡፡

«ኦ፤ ከባለቤትዎ ጋር ከሆነማ ነገሩ ቀላል ነው፤ ማስረዳትም ይችላሉ፤ ባለቤትዎም ቢሆኑኮ የርስዎን ታክመው መዳን ይፈልጉታል፡፡ እናም እባክዎ አሁን በቂ ጊዜ ስለ ሌለዎ ይደውሉላቸውና አንድ አሥራ አምስት ደቂቃ እንደሚያረፍዱ ይንገሯቸው» አለች ነፍሷ እፎይታ እየተሰማት፡፡

«ባለቤቴ ጋር መደወል አልችልም፡፡ እርሷ ብደውልላትም መደወሌን አታውቅም፤ መደወሌንም አታስታውስም» አሉ በኀዘን ስሜት፡፡

«እንዴ ለምን?» አለች ነርሷ አሁን እንደገና ግራ እየተጋባች፡፡

«እርሷ ታምማለች፡፡ ያለችውም በአረጋውያን መጦርያ ነው፡፡ ሁሉንም ነገር አታስታውሰውም፡፡ አልዛይመር የተባለው በሽታ በጣም አጥቅቷታል፡፡» አሉና ታካሚው ሰዓታቸውን ተመለከቱ፡፡

«ታድያ በዚህ ዓይነት እርስዎንስ ያስታውሱዎታል እንዴ?» አለች ነርሷ በተሰበረ ልብ፡፡

«የኔ ልጅ እርሷኮ እኔንም አታስታውሰኝም፡፡ ፈጽማ ረስታኛለች» አሉ ታካሚው፡፡

«ማንነትዎን አያስታውሱዎትም፤ አያውቁዎትም ማለት ነው?»

«አዎ አታውቀኝም፡፡ የምታስታውሰው ነገርም የላትም፤ ፈጽማ ረስታኛለች፤ የምገዛላትን፤ የማደርግላትን ነገር ሁሉ ረስታዋለች፡፡ እኔ አሁን ማን እንደሆንኩ አታውቅም»

«ታድያ እንደዚህ የማያስታውሱዎ ከሆነ ለምን ቸኮሉ?» ለእርሳቸውኮ አምስት ሰዓትም ሆነ ሰባት ሰዓት ያው ነው፡፡ በሉ ቀስ ብለው ሕክምናዎን ጨርሰው ይሂዱ» አለች ነርሷ ነገሩን በማቅለል፡፡

«የለም የኔ ልጅ፤ እንደዚያ አይደለም፡፡ እኔ እርሷጋ ዘወትር እሑድ በአምስት ሰዓት መሄድን አስለምጃለሁ፡፡ ከርሷ ጋር በዚህ ሰዓት ቀጠሮ አለኝ፡፡ ብታውቀውም ባታውቀውም፤ ብታስታውሰውም ባታስታውሰውም ቀጠሮዬ ግን አይቀርም፡፡ ዋናው ነገር የርሷ ማስታወስ አይደለም ልጄ፤ የኔ ማክበር ነው፡፡ ይህ ለእኔ እና ለእርሷ ፍቅር ከሚከፈሉት መሥዋዕትነቶች አንዱ ነው፡፡ እርሷ አታውቀኝም፤ እኔ ግን አውቃታለሁ፡፡ ትናንት እንደዚህ አልነበረችም፡፡ እኔ የትናንትናዋን ሚስቴን ነው የማስታውሰው፡፡ ስለዚህ በሰዓቱ መሄድ አለብኝ፡፡

«ያኔ አታዬኝም፤ አትሰማብኝም ብዬ ምንም ነገር ተደብቄያት አድርጌ አላውቅም ነበር፡፡ ዛሬም አታውቅም ብዬ ምንም ነገር ላደርግ አልፈልግም፡፡ በሰው አለማወቅ መጠቀም ይበልጥ አላዋቂነት ነው ልጄ፡፡»

«ለመሆኑ ካላስታወሱዎት አሁን ሄደው ምን ያደርጋሉ?» አለች ነርሷ የኒህን አስገራሚ ሰው የኑሮ ምሥጢር ለማወቅ ጓጉታ፡፡

«ልብሷን እቀይርላታለሁ፤ የቤቷን አበባ እቀይራለሁ፡፡ ወደ ውጭ አወጣትና ብታስታውሰውም ባታስታውሰውም ዝም ብዬ በዚህ ሳምንት የሆነውን ነገር አወራታለሁ፤ ያለፈውን ትዝታ እያነሣሁ አጫውታታለሁ፡፡ ብትስቅም፣ ባትስቅም አንዳንድ ጊዜ ቀልድ እነግራታለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አጫጭር ታሪኮችን አነብላታለሁ፡፡ ይህ ሁሉ ድሮ ደኅና እያለች የማደርግላት ነው፡፡ አንዳችም አላጓድልባትም፡፡ አየሽ ልጄ፣ እኔ ያኔ ስንጋባ ቃል የገባሁት ለሚስቴ እንዲህ እና እንዲያ አደርግላታለሁ ብዬ እንጂ እርሷ እንዲህ እና እንዲያ ታደርግልኛለች ብዬ አይደለም፡፡ ይህንን ቃል የገባችው እርሷ ናት፡፡ እርሷ ደግሞ እስከ ምትችል ድረስ ይህንን ነገር አክብራ ፈጽማለች፡፡ አሁን ግን አትችልም፡፡ እኔ ግን ቃል የገባሁትን መፈጸም እችላለሁ፡፡ ስለዚህ ለምን አስቀርባታለሁ፡፡ አንቺ ለምን የራስሽን አታደርጊም? ያንቺን ጥሩነት እና መጥፎነት ለምን ሰዎች ይወስኑልሻል? አንቺ ራስሽ መወሰን አትችይም?»

«አምስት ደቂቃዎን ብቻ ልውሰድብዎት፤ ይህንን ሁሉ እንደሚያደርጉላቸው ውለታዎን የማያስቡልዎ ከሆነ፤ ከርሳቸውም አንዳች ምላሽ የማያገኙ ከሆነ፤ ምን ይሁነኝ ብለው ይደክማሉ?» አለች ነርሷ አገጪን በመዳፏ ደግፋ፡፡

«እኔ ለሚስቴ አንዳች ነገር የማደርገው ውለታ ፍለጋ ብዬ አይደለም፡፡ የኔ ደስታ ሳደርግ እንጂ ሲደረግልኝ የሚገኝ አይደለም፤ በመስጠት እንጂ በመቀበል አይገኝም፤ በመሞት እንጂ በመግደል አይገኝም፤ እኛ አብረን ለመኖር

ተስማማን፤ ቃል ገባን እንጂ፤ በደኅንነታችን ጊዜ ብቻ አብረን ለመሥራት ኮንትራት አልተፈራረምንም፡፡ ለኔ በደጉ ጊዜም ሚስቴ፣ ናት በክፉው ጊዜም ሚስቴ ናት፡፡ ሳትታመምም ሚስቴ ናት፤ ታምማም ሚስቴ ናት፡፡ ሌላው ቀርቶ ስትሞትም ሚስቴ ናት፡፡ እርሷ ብታልፍም እኔ ግን ትዝታዋን አግብቼው እቀጥላለሁ፡፡ ከዚያም ደግሞ በሞት እከተላታለሁ፡፡ ስለሚቀጥለው ዓለም አላውቅም፡፡ ከቻልኩ ግን እዚያም ብትሆን ሚስቴ ናት፡፡ እኔ ባልዋ ስሆን ለርሷ የባልነት ግዴታዬን ለማድረግ እንጂ ከርሷ ለመቀበል አይደለም፡፡ እርሷም የርሷን ለማድረግ እንጂ ከኔ ለመቀበል አይደለም፡፡ ልጇ ከሰጡሽ ተቀበይ እንጂ ለመቀበል ግን ስትይ ግን አትስጭ፡፡ አሁን ይብቃኝና እባክሽን ሐኪሙ ጋር ቶሎ አገናኚኝና ልሂድ፡፡» አሉ ታካሚው አሁንም ሰዓታቸውን እያዩ፡፡ ነርሷ ተገረመች፡፡

«ካላስቸገርኩዎ እባክዎን የባለቤትዎን ስም ይንገሩኝ» አለች ነርሷ በሶፍት ዓይኖቿን እየጠረገች፡፡

«ባለቤቴ ባርባራ ትባላለች፤ የኔ ከመዝገቡ ላይ አለልሽ» አሏት፡፡

«አዎ ሚስተር ስቴፈን» አለችና ማወቋን ገለጠችላቸው፡፡

ቀዳሚው ታካሚ ከሐኪሙ ጋ ለመውጣት ሲዘገዩ እኒህኛው ታካሚ ተነሡና ሄዱ፡፡ «እባክዎን ቆዩ» ለማለት ነርሷ ልብ አልቀረላትም፡፡

ነርሷ ፈቃድ ወሰደችና ለአሥራ አምስት ቀናት ያህል ቤቷ ተቀመጠች፡፡ እኒያ አረጋዊ ታካሚ የነገሯትን ነገር ደግማ ደጋግማ አምሰለሰለችው፡፡ በእርሳቸው ሕይወት ውስጥ ያለውን መመርያ መረመረችው፡፡ ከራስዋም ጋር ለማዛመድ ሞከረች፡፡ በአሥራ አምስተኛው ቀን አንድ ሃሳብ መጣላት፡፡ ሰዎች በራሳቸው ተነሣሽነት ከማንም ዋጋ እና ውለታ ሳይጠብቁ በጎ ነገርን እንዲያደርጉ የሚያበረታታ፤ የሚያስተባብር እና የሚያስተምር ተቋም መመሥረት፡፡

እጅግ ብዙ ሰዎችን በዚህ ዓላማ ያሰለፈ አንድ ትልቅ ተቋም መሠረተች «ባርባራ እና ስቴፈን» ይባላል፡፡

ይህንን ታሪክ ሳነብብ ብዙ ነገሮች ታወሱኝ፡፡ አንተ እንዲህ የማታደርግ ከሆነ እኔም እንዲህ አደርጋለሁ ብለው በእልህ ዥዋዥዌ የሚጫወቱ ባል እና ሚስት፡፡ ከእገሌት ጋር ስለሄደ ከእገሌ ጋር ሄጄ ልኩን እሰጠዋለሁ ብለው የሚጠዛጠዙ ፍቅረኞች፡፡ ሌላው ሰው ቀጠሮ ስለማያከብር የኛ ቀጠሮ ማክበር ምን ዋጋ አለው ብለው አርፋጅ የሆኑ ሰዎች፡፡ የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ እንደሚባለው ሌላው ሰው እየዘረፈ የኔ ሐቀኛ መሆን ምን ዋጋ አለው ብለው ራሳቸውን በሌሎች ምክንያት ያበላሹ ሰዎች፡፡

ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ትኩረት ካልሰጡት እኔ ምን አግብቶኝ እጨነቃለሁ ብለው የተማሪዎቻቸው ቸልተኛነት የተጋባባቸው መምህራን፡፡ የሠፈሩ ሰው ቆሻሻ የትም እየጣለ እኔ ብቻዬን ብጠነቀቅ ምን ዋጋ አለው ብለው እነርሱም ከበራቸው ላይ ቆሻሻ መከመር የጀመሩ ሰዎች፡፡

እገሌ ከኔ ሠርግ አልመጣም ብለው ከሰው ሠርግ የቀሩ፤ እገሌ ልቅሶ ሳይደርሰኝ ቀረ ብለው ከሰው ልቅሶ የቀሩ፡፡ እገሌ ታምሜ አልጠየቀኝም ብለው ሲታመም በመቅረት ብድር የሚመልሱ ሰዎች፤ እገሌ ሰላም አላለኝምና ሰላም አልለውም ብለው ሰላምታ ያቆሙ ሰዎች፤ ሌሎቹም ሌሎቹም፡፡

እገሌ አስቀይሞኛልና ከዕድር ከማኅበር ተለይቻለሁ፤ እገሌ እንደምጠብቀው አልሆነልኝምና ከዛሬ ጀምሮ አልመጣም፡፡ ከመንግሥት ጋር ተጣልቻለሁና ከንግዱህ ለሀገሬ አንዳች በጎ ነገር አልሠራም፡፡ ፓትርያርኩ ሊሰሙ አልቻሉምና ከንግዲህ ስደተኛ፣ ገለልተኛ፣ ቁሪተኛ፣ ስሞተኛ ሆኛለሁ፡፡ እነ እገሌ ለምሠራው ሥራ፣ለምሰጠው አገልግሎት፣ለማደርገው አስተዋጽዖ ግምት አልሰጡትምና ትቼዋለሁ፤ የምንለውን ሰዎች ሚስተር ስቴፋን ቢሰሙ ምን ይሉ ይሆን?

እኒያ ታካሚ ሽማግሌ እንዳሉት ለምን ይሆን ግን የኛን ማንነት ሰዎች የሚወስኑት? ፀሐይ ትወጣለች፤ ነገር ግን እኛ እንድንሞቃት አስባ አይደለም፡፡ እርሷ ግን ምንጊዜም ትወጣለች፡፡ ነፋሱም ይነፍሳል፤ እኛ እህል ብናበራይበትም ባናበራይበትም ይነፍሳል፡፡ መሬት በፀሐይ ዙርያ ትዞራለች፤ በብርሃኑ እና በጨለማው ጊዜ ሰዎች ቢጠቀሙም ባይጠቀሙም ትዞራለች፡፡ እነዚህ ሁሉ የእነርሱን ድርሻ ይወጣሉ እንጂ የኛን ምላሽ አስበው አይለወጡም፡፡

ታድያ እኛ ምነዋ!

# ችግር ነን መፍትሔ ?

ሁለት መኪኖችን ብቻ አጨናንቃ የምታሳልፍ መንገድ ነበረች፡፡ ሁለቱ መኪኖች ሲተላለፉ ጎንና ጎናቸው ሊነካካ ለጥቂት ብቻ ነው የሚያመልጡት፡፡ ነገር ግን ሾፌሮቹ ሁሉ ለምደውታልና በቀላሉ ፈገግ እያሉ ይተላለፋሉ፡፡

አንድ ቀን አንድ ለምድር ለሰማይ የከበደ ወፍራም የትራፊክ ፖሊስ መሐል መንገድ ላይ ቆሞ በግራ እና በቀኝ የሚተላለፉትን ተሽከርካሪዎች «እለፉ እለፉ» ይላል፡፡ መኪኖቹ መተላለፍ ስላልቻሉ ከሚሄደው የሚቆመው በዛ፡፡ በተለይማ ትልልቆቹ የጭነት መኪኖች መተላለፍ አልቻሉም፡፡ የትራፊክ ፖሊሱ ግራ ገባው፡፡ ከዚያ በፊት ምንም እንኳን መንገዱ ጠባብ ቢሆንም እንደዚያ ቀን ያለ መጨናነቅ ግን ታይቶ አይታወቅም፡፡ መኪኖቹ ቀስ ይሉ ይሆናል እንጂ አይቆሙም፡፡

«ዛሬ ምን ተፈጠረ፣ ምን ዓይነት ሾፌሮች ናቸው ደግሞ ዛሬ የመጡት፣ ምን ዓይነት የተረገመ ቀን ነው» እያለ ያማርራል፡፡ በሾፌሮቹ እና በመኪኖቹም ላይ ይቆጣል፡፡ አልቻለም እንጂ እየሳበ ሊያሳልፋቸውም ይፈልጋል፡፡ «የኔ አባት በአንድ እጁ ሙቶ መኪና ያቆማል» ብላ አንዲት ሕፃን ልጅ ለጓደኞቿ ነገረቻቸው አሉ፡፡ «እንዴ ምን ዓይነት ስፖርተኛ ቢሆን ነው?» ብለው ቢጠይቋት «አይ ስፖርተኛ አይደለም የትራፊክ ፖሊስ ነው» አለች እየተባለ የሚነገረው ለርሱ ነው እያሉ ይሳሳቃሉ፡፡

የትራፊክ ፖሊሱ የትራፊክ መጨናነቁ የመጣበት ምክንያት አልተገለጠለትም፡፡ ምንም እንኳን መንገዱ አስቸጋሪ፣ መሠራት ሲገባው ሳይሠራ የኖረ፣ እንኳን ሁለት መኪኖችን አንድን መኪና በደንብ የማያሳልፍ ቢሆንም የዛሬው መጨናነቅ ግን ለየት ያለበት ምክንያት ግን አልተገለጠለትም፡፡

እየቆየ መናደድ እና ከፉ ቃል መናገር ጀመረ፡፡ ሾፌሮቹን ጮኸባቸው «ዛሬ ምንድን ነው የኾናችሁት?» እያለ አፈጠጠባቸው፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ ሾፌር በመስኮቱ ብቅ ብሎ «ወንድሜ አንዱ ችግርኮ አንተው ነህ» አለው፡፡ የትራፊክ ፖሊሱ ከጠዋት ጀምሮ የለፋው ድካሙ ትዝ አለውና «እንዴት ይህንን ሁሉ ስደክም እያየህ ችግሩ አንተም ነህ ትለኛለህ?» አለው፡፡ ሾፌሩም፡፡ «በዚህ በጠባብ መንገድ ተራራ የምታህል ሰውዬ ስትጨመርበት በምን እንለፍ፡፡ አንተኮ መፍትሔ የሰጠህ መስሎሃል እንጂ ችግር እያበባስክ ነው፡፡ እስኪ ከመንገዱ ወጣ በልና የሚሆነውን እየው» አለው፡፡

የትራፊክ ፖሊሱ ለተወሰነ ጊዜ ሲያቅማማ ከቆየ በኋላ ከመንገዱ መሐል ወጣ፡፡ ያን ጊዜ ሲጨናነቁ የነበሩት መኪኖች እንደ ቀድሟቸው መተላለፍ ጀመሩ፡፡ ምንም እንኳን የመንገዱ ችግር እንዳለ ቢሆንም የቆሙት መኪኖች ግን መንቀሳቀስ ቻሉ፡፡

ዛሬ በቤተ ክርስቲያን መንገድ ላይ የቆምን ሰዎችም ይህንን ጥያቄ መጠየቅ አለብን፡፡ እኛ ለቤተ ክርስቲያን ችግሮች መፍትሔ አመጣን ወይስ እኛው ራሳችን ችግሮች ሆንን?

ኢትዮጵያውያን አበው ጵጵስና አይሾሙ በሚል በኋላ የመጣ ሕግ ምክንያት 117 ጳጳሳትን ከግብጽ አመጣን፡፡ ቋንቋችንን አያውቁም፣ ከሀገሪቱ ስፋት አንፃርም በቂ አይደሉም፣ ደግሞስ ኢትዮጵያ ከማን አንሳ ነው ሰዎቿ ብቁ አይደለም የሚባሉት? ብለን ከግብጻውያን ጋር ተከራከረን ጵጵናን አመጣን ፡፡

ይህንን ለማየት ብዙ አበው ወደዱ ግን አላዩም፣ የኛ ዓይኖች ግን ንዑዳን ክቡራን ናቸው፤ ኢትዮጵያን አበው ኢትዮጵያውያንን ሲሾሙ፤ ሕዝቡም በየአካባቢው ጳጳሳትን ሲያገኝ ተመልክተዋልና፡፡

ግን ግብፃውያን ይሾሙበት ከነበረው ዘመን ምን ያህል ለውጥ አመጣን? ምን ያህል ስብከተ ወንጌልን አስፋፋን? ምን ያህል በየገጠሩ ደረስን? ምን ያህል አዳዲስ ሕዝቦችን ለወንጌል ጠራን? ምን ያህሉ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ተምረው፣ አምነው፣ ተጠምቀው፣ ተክነው፣ ጸጽሰው ለማየት በቃን?

የክህነት እና የምንኩስና አሰጣጡ ከግብፃውያን ዘመን ይልቅ የተሻለ ሆነ? የራሳችን ሲኖዶስ በስንት የቀኖና ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ወሰነ? ስንት ያረፉ ቅዱሳን በሲኖዶሳችን «ቅዱስ» ተብለው ተወሰነላቸው፡፡ መጻሕፍት ተቆጥረው ተሰፍረው በሲኖዶሱ ጸደቁ ዛሬ የራሳችን ሲኖዶስ እያለን «ዓሣ ይበላል አይበላም? ስቅለት በማርያም ዕለት ሲውል ይሰገዳል አይሰገድም» የሚሉት እንኳን ውሳኔ አጥተው እያጨቃጨቁን አይደለም»

የቤተ ክህነቱ አሠራር የሀገር ልጆች ሲይዙት ምን ያህል ተቀላጠፈ» ግብጽ ድረስ ከመሄድ አዲስ አበባ ድረስ መምጣት ቀላል ሆነ» ለግብጻውያን ይገበር የነበረው ወርቅ እና ብር ቀርቶልናልን» የጵጵስናው መዓርግስ ከግብጻውያኑ ዘመን ይልቅ ዛሬ ይበልጥ በሕዝቡ ዘንድ ተከበረን»

## የጵጵስና ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ችግር ሆነ ወይስ መፍትሔ»

ወንጌል በሚገባ አልተሰበከም፣ የጥንቱ አካሄድ አያስኬድም፣ በአዲስ ጉልበት እና በአዲስ መንገድ ሕዝቡን ማስተማር አለብን ብለን አያሌ «ሰባክያን» ተነሣን፡፡ ነጠላም፣ ጋቢም፣ ቀሚስም፣ ወይባም፣ ካፖርትም ደርበን በየመድረኩ ቆምን፡፡ ከመሐል ከተማ እስከ ዳር ሀገር፣ ከሀገር ውስጥ እስከ ባሕር ማዶ ዞርን፡፡ ሕዝቡም እሰይ ሰባክያን አገኘን፣ ቃለ እግዚአብሔርን ተማርን፣ ሃይማኖታችንንም ዐወቅን ብሎ ደስ አለው፡፡

ለመሆኑ ከዚህ ሁሉ በኋላ ሕዝቡ ቁራቢ ሆነ? በመናፍቃን መወሰዱ ቀረ? ባዕድ አምልኮ ቀረ? ገባው ወይስ ተደናገረ? ቲፎዞ ነው ወይስ ደቀ መዝሙር ያፈራነው? ለመሆኑ በኛ ዘመን ስንቶቹ ዐፄ ካሌቦች ሥልጣናቸውን ትተው መነኑ? ስንቶቹ አቡነ ሳሙኤሎች ተነሥተው በአንበሳ እየሄዱ አስተማሩ? ስንቶቹ ክፍለ ዮሐንሶች በዕውቀት ከበሰሉ በኋላ መነኑ? ስንቶቹ ላሊበላዎች አዲስ ተአምር ሠሩ? ስንት እግዚእ ኃረያ እና ጸጋ ዘአብ ተገኙ? ምንድን ነው ያፈራነው ፍሬ?

እኛ ባልነበርን ጊዜ ዘንዶ ይረግጡ፣ አንበሳ ይረግጡ፣ በደመና ይወጡ የነበሩት ቅዱሳን በስብከተ ወንጌሉ ዘመን የት ሄዱ?

ሕዝቡ ጥቅስ ዐወቀ፤ ዐውቆ ግን ምን አደረገ? ማይክራፎኑ አደገ፣ የስብከቱ መድረክ ጨመረ፣ የሰባኪው ቀሚስ ተለወጠ፣ የሰባኪው የኑሮ ሁኔታ ተለወጠ፣ ትምህርቱ ከብራና ወደ ዲቪዲ ተሻሻለ፣ ከዶግማ ትምህርት ወደ ቀልዳ ቀልድ ተቀየረ፣ ሰውን ከማዳን ሰውን ወደ ማስደሰት ተሸጋገረ፣ የተማሩ ሊቃውንት ያልተማረውን ሰው ማስተ ማራቸው ቀርቶ ያልተማርን ሰባክያን ያልተማረውን ሰው ማስተማር ጀመርን፡፡

የማይጾም የሚጾመውን፣ የማይጸልይ የሚጸልየውን፣ የማያስቀድስ የሚያስቀድሰውን ወደ ሚያስተምርበት ዘመን ደረስን፤ ሕዝቡን ከቤተ ክርስቲያን ወደ አዳራሽ፣ ገድል እና ተአምር ከመስማት ቀልድ እና ጨዋታ ወደመስማት አሸጋገርነው፡፡ እኛ ባልነበርንበት ዘመን ምንም ያልሆነ ሕዝብ ሰባክያን በዙ በሚባልበት ዘመን በአሥር ዓመት ውስጥ 10% ቀነሰ፡፡ የክርስቶስ ተከታዮች አናፈራለን ብለን የእገሌ ተከታይ አፍርተን አረፍነው፤ ከቤተ ክርስቲያኑ ቁጥር ይልቅ በኛ ዘመን ጫት ቤቱ በለጠ፡፡

## ታድያ እኛ አሁን ለቤተ ክርስቲያን ተጨማሪ ችግር ነን ወይስ መፍትሔ?

«ነይ ነይ እምዬ ማርያም» እየተባለ የተዘመረው መዝሙር አይበቃም ብለን ተነሣን፡፡ መናፍቃን ሕዝቡን በመዝሙር ከሚወስዱት በመዝሙር እናስቀረው ተባለ፡፡ ዘማርያን መጡ፣ የብስ ረገጡ፡፡ መዝሙር አወጡ፡፡ ካሴት አስቀረጡ፡፡ በየሦስት ቀኑ አንድ የመዝሙር ካሴት እስከመውጣት ደረሰ፡፡ መዝሙር ከጠፋበት ዘመን ተነሥተን መዝሙር የበዛበት ዘመን ላይ ደረስን፡፡ ቤቱ፣ ሻሂ ቤቱ፣ ታክሲው፣ የቤት መኪናው፣ ጫት ቤቱ ሁሉ መዝሙር በመዝሙር ሆነ፡፡

ሕዝቡም በቋንቋችን፣ የሚገባን መዝሙር አገኘን ብሎ ደስ አለው፡፡ ዘማርያኑም «በምስጋና ምድራቱን ከደንናት» ብለው ተኩራሩ፡፡

ለመሆኑ የያሬድ ዜማ ይበልጥ ታወቀ ወይስ ጠፋ? በመዝሙር በኩል መናፍቃንን ተከላከልን ወይስ አስገባን? ድምፃዊው በዛ ወይስ ዘማሪው? መዝሙር አገልግሎት ሆነ ወይስ ሥራ? ዝማሬ ጽደቅ ሆነ ወይስ ሞያ? ሕዝቡን ከዘፈን አመጣነው ወይስ ከቅዳሴ አስወጣነው? የዘማርያኑ ኑሮ ነው ወይስ የሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት ነው የተለወጠው? ሕዝቡ መንፈሳዊ መዝሙር ነው የሚገዛው ወይስ በእናቱ ዘፈን በአባቱ መዝሙር የሆነ? ሕዝቡን ወደ ጸጥታ ወደብ ወሰድነው ወይስ አጨቃጨቅነው? አስማማነው ወይስ አለያየነው? የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት አስፋፋን ወይስ የራሳችንን አመለካከት? ታድያ እኛ ለቤተ ክርስቲያን ተጨማሪ ችግር ነን ወይስ መፍትሔ?

ነዳያንን ለማብላት፣ ገዳማትን ለመጎብኘት፣ ገዳማትን ለመርዳት፣ጽዋ ለመጠጣት፣ ስብከተ ወንጌል ለማስፋት፣ የሞያ እገዛ ለማድረግ፣ ወዘተ ተብሎ ማኅበራት እንደ እንጉዳይ ወጡ፡፡ ሕፃኑ፣ ወጣቱ፣ ሽማግሌው፣ ወንዱ፣ ሴቱ ማኅበርተኛ ሆነ፡፡ አንድ አልበቃ ብሎ አንድ ሰው ሁለት ሦስት ማኅበር ገባ፡፡

ቤተ ክህነቱ በሚገባ አልሠራም፣ ገዳማት አድባራቱ ተጎድተዋል፣ መዘምራን ተለያይተዋል፣ ሰባክያን ተራርቀዋል፣ እየተባለ የማኅበር ዓይነት መጣ፡፡ ሌላው ቀርቶ በየበኣታቸው ይጸልያሉ የሚባሉት ባሕታውያንም ማኅበር አቋቁመናል አሉ፡፡ በሰማይ የሚበሩ፣ በምድር የሚሽከረከሩ፣ በባሕር የሚኖሩ ሁሉ ማኅበር መሠረቱ፡፡ የተማሩ፣ ያልተማሩ፣ ለመማር ያላሰቡ ማኅበር ኖራቸው፡፡

ቤተ ክህነቱ ተረሳ፡፡ ሁሉም በየራሱ መሮጥ ጀመረ፡፡ ዋናው ሞተር እንዲሠራ እናደርጋለን ብለው የተቋቋሙ ማኅበራት ለራሳቸው ሞተር ሆኑ፡፡ ቤተ ክህነትም ሳያውቃቸው፣ ቤተ ክህነቱንም ሳያውቁት ቀጠሉ፡፡ የቤተ ክርስቲያን ዋናው ችግር አይመለከተንም ብለው ማሉ፡፡ ዕንቅርቱን ትተው ንቅሳቱ ላይ አተኮሩ፡፡ ገብተው ከመሥራት ይልቅ ወጥተው መተቸትን መረጡ፡፡

እንደ ዘመነ መሳፍንት ሁሉም በየራሳቸው ነው የሚጓዙት፡፡ ለመተባበር፣ ለመነጋገር፣ አይፈልጉም፤ አያስቡምም፡፡ በአንድ መንገድ እየተጓዙ ይገፋፋሉ፡፡ አንድ ቦታ እየሠሩ፣ ይነጣጠቃሉ፡፡ ብዙዎቹ ማኅተም እንጂ ራእይ የላቸውም፡፡ አባል እንጂ ዓላማ ይጎድላቸዋል፡፡ የትኛውን ገዳም እንደሚረዱ እንጂ የትኛውን ችግር እንደሚፈቱ አያውቁም፡፡

ሕዝቡ እነርሱን ተስፋ አድርጎ እንዲቀመጥ አደረጉት፡፡ ለጥያቄዎች መልስ፣ ለችግሮች መፍትሔ፣ ለጨለማው ብርሃን ከእነርሱ ይጠብቃል፡፡ እነርሱ ደግሞ «ሀ- ራስክን አድን» ብለው በራሳቸው አጀንዳ ተጠምደዋል፡፡ «ቤተ ክርስቲያናችን» ማለት ትተው «ማኅበራችን» ማለት ጀምረዋል፡፡ «የቤተ ክርስ ቲያናችን ልጅ» መባሉ ቀርቶ «የማኅበራችን ልጅ» ሆኗል ቋንቋቸው፡፡

ቤተ ክህነቱን ያስተካክላሉ ሲባሉ እነርሱ ራሳቸው እንግሊዝኛ ተናጋሪ ቤተ ክህነቶች ሆነዋል፡፡ አሠራርን ያስተካክላሉ ሲባሉ እነርሱ ራሳቸው በተወሳሰበ፣ ግልጽነት በጎደለው እና ኋላ ቀር በሆነ አሠራር ተተብትበዋል፡፡ የገንዘብ አያያዛቸው፣ የርዳታ አሰጣጣቸው፣ የአባላት አመዘጋገባቸው፣ የሪፖርት አቀራረባቸው፣ የፋይል አያያዛቸው፣ የዶክመንት አደረጃጀታቸው፣ የስብሰባ አካሄዳቸው ከቤተ ክህነቱ የባሰ ሆነዋል፡፡ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተገላገሉትን ቢሮክራሲ እነርሱ ወሰዱት፡፡ ለጉባኤ እና ለድግስ ብሎም ሞቅታ ላለበት ተግባር እንጂ ለአገልግሎት የሰነፉ አባላት መናኸርያ እየሆኑ ነው፡፡

የቤተ ክርስቲያን ፈተና ማኅበራት ካልነበሩበት ዘመን ይልቅ በበዙበት ዘመን ብሷል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን ቦታ የያዙት በማኅበራት ዘመን ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን መድረክ ሐውልት መቆም የጀመረው፣ የፎቶ ፖስተር በዐውደ ምሕረት የተሰቀለው፤ የቤተ ክርስቲያን ያልሆነ ትምህርት በዐውደ ምሕረት መሰጠት የጀመረው፤ ቅዱስ ሲኖዶስ ተዳክሞ ግለሰቦች ቦታውን መያዝ የጀመሩት በማኅበራት ዘመን ነው፡፡

አንጀቴ ተቆርጦ ከሆዴ ከወጣ

ከንግዲህ ሐኪሙ ምን ሊቀጥል መጣ

አንድ ሰው የችግሩም የመፍትሔውም አካል መሆን አይችልም፡፡ መጀመርያ የችግሩ አካል ከመሆን መላቀቅ መቻል አለበት፡፡ አንድ ሐኪም ለአንድ በሽተኛ መድኃኒት የሚያዝዘው እንዲያድነው ወይንም እንዲያሽለው እንጂ እንዲገድለው መሆን የለበትም፡፡ ቀዶ ጥገና ያደረገ ሐኪም ቀጥሎ ኢንፌክሽን እንዳይከተል መከላከልም አለበት፡፡

በደርግ ዘመን ኮሚቴ በዝቷል ይቀነስ ሲባል ኮሚቴ የሚቀንስ ሌላ ኮሚቴ እንዲቋቋም ተወሰነ እየተባለ የሚተረተው ቀልድ ቀልድ ብቻ አይደለም፡፡ የተሰጠው መፍትሔ ችግሩን የሚጨምር እንጂ የሚፈታ አለመሆኑን የሚያሳይም ነው፡፡

አሁንም የቤተ ክርስቲያንን ችግሮች ለመፍታት ተብለው የመጡ መፍትሔዎች እና የተቋቋሙ አካላት በራሳቸው መታየት አለባቸው፡፡ በርግጥ እነዚህ መንገዶች እና አካላት ችግር ጨምረዋል ወይስ መፍትሔ አምጥተዋል? እነርሱ ራሳቸውም ራሳቸውን ማየት አለባቸው፡፡ ምንድን ነው ያመጣነው ለውጥ? ካለመ ኖራችን መኖራችን ምን ይጠቅማል? የቆምነው በትክክለኛው መንገድ ላይ ነውን? ብለን መጠየቅ አለ ብን፡፡ እስኪ 2003 ዓም ከመምጣቱ ወይንም ከማለፉ በፊት ከላይ የተጠቀስነው አካላት ራሳችንን እንመርምር፤ በተለይም አመራሮቹ ወይምን ዋና ዋናዎቹ አሁን የምንሄድበትን መንገድ ከወቅቱ ችግሮች እና ተግዳሮቶች አንፃር እንመዝነው፤ ከዚያም ችግር ሳይሆን መፍትሔ የሚያደርገንን አቅጣጫ እንተልም፡፡ ያለበለዚያ ግን ምንን ምን ቢመራው ሁለቱም ወደ ገደል ይሄዳሉ የተባለው ይፈጸምብናል፡፡

# የሆስፒታል ቫይረስ

በሕክምና እና በሕክምና ባለሞያዎች ዘንድ ካሉት ሥጋቶች መካከል አንደኛው በሆስፒታል ውስጥ ሆስፒታሉን ለምደው እና ወድደው፤ የሚኖሩት ቫይረሶች ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ቫይረሶች በተለያዩ ሕመምተኞች አማካኝነት ወደ ሆስፒታሉ ይመጡና እዚያ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በመላመድ፣ የሚረጩትን መድኃኒቶች፣ ኬሚካሎች እና የማጽጃ ነገሮች ሁሉ ቀስ በቀስ በመቋቋም ኑሯቸውን በሕክምና ተቋሙ ውስጥ ያደርጋሉ፡፡ በዚህም የተነሣ የሕክምና ባለሞያዎችን እንዲሁም ታካሚዎችን ያጠቃሉ፡፡

እንደዚህ ዓይነቶቹ ቫይረሶች መከላከያዎችንም ሆነ መድኃኒቶቹን ስለተለማማዷቸው እነርሱን በማከም ማሸነፍም ሆነ ማድከም አስቸጋሪ ነው፡፡ ሕክምናው ባለበት በዚያው በሆፒታሉ ውስጥ ስለሚኖሩም ራሳቸውን እያባዙ እና እንደነርሱው ሕክምናውን የሚቋቋሙ መሰሎቻቸውን እያበራከቱ በመሄድ፣ የሕክምና ማዕከል ተብሎ የተቋቋመውን አካል የማይድኑ በሽታዎች ማምረቻ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡

እንዲህ ዓይነቶቹ ቫይረሶች ለረዥም ጊዜ ከቆዩና በቶሎ ካልተነቃባቸው፣ የሕክምና ማዕከሉን ይቆጣጠሩታል፡፡ መፍትሔውንም ውስብስብና ከዐቅም በላይ ያደርጉታል፡፡ ሆስፒታሉን እስከማስቀየር፤ እስከማቃጠል፣ እስከማፍረስ እና እስከማዘጋት ይደርሳሉ፡፡

በመንፈሳዊ እና በፖለቲካ ተቋሞቻችን ውስጥ ከምናያቸው አልፈቱ ካሉን ችግሮች መካከል አንደኛው የሆስፒታል ቫይረስ ችግር ነው፡፡

ደግነት፣ ቅንነት፣ ትኅትና፣ ፍቅር፣ ሰላም፣ መከባበር፣ ይቅርታ፣ ለጋስነት፣ ራስን መግዛት፣ ይነግሥባቸዋል ተብለው በሚጠበቁት መንፈሳዊ ተቋሞቻችን ውስጥ ትዕቢት፣ጠማማነት፣እኔን ብቻ ይድላኝ ማ|ት፣ብጥብጥ፣ መናናቅ፣ ቂም

በቀል፣ ስስት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣ ነግሦባቸው እናያለን፡፡ ለሌሎች አርአያ ይሆናሉ፤ ማኅበረሰቡን በሞራል ሕጎች እና በሥነ ምግባር ይታደጋሉ ተብለው ተስፋ ሲደረግባቸው እነርሱ ራሳቸው የሥነ ምግባር ብልሹነት መገለጫ ቦታዎች ይሆናሉ፡፡

ለሀገሪቱ ዕድገት እና ብልጽግና፣ መሻሻል እና ብርታት፣ አርአያዎች እና ሞተሮች፣ ብቁ እና ታታሪ፣ በሥነ ምግባር የታነፀ እና ሕግ አክባሪ ዜጋ ፈጣሪዎች ሲባሉ የሙስና እና የብልሹ አሠራሮች፣ የኋላ ቀር ቢሮክራሲ እና የአምባገነንነት ምሳሌዎች፣ የሀገሪቱንም እድገት ጎታቾች ሆነው ይታያሉ፡፡ ለምን?

የሆስፒታል ቫይረስ አለ ማለት ነው፡፡ ሰይጣን መንኩሶ፣ ቀስሶ፣ ደቁኖ፣ ሰባኪ ሆኖ፣ ቅኔ ተምሮ፣ ጸጉሩን አስረዝሞ፣ ሼህ እና ቃዲ፣ ዑለማ ሆኖ፤ ፓስተር እና ወንጌላዊ፣ ዘማሪ እና ነቢይ፣ አገልጋይ እና አስመላኪ፣ ሆኖ ራሱ በቦታው ተቀምጧል ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ሌሎችን ያድናል ተብሎ ተስፋ የተሰጠው ተቋም ራሱ የበሽታዎቹ መነሻ/ የቫይረሶቹ መኖርያ ሆኗል ማለት ነው፡፡

ሌላ ቦታ ያለው ቫይረስ መድኃኒት የሚፈራ፣ በመድኃኒትም የሚጠቃ፣ በመድኃኒትም የሚድን ነው፡፡ ሆስፒታል ውስጥ የሚኖር ቫይረስ ግን ምንም አይፈራም፡፡ ተለማምዶታላ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ምእመናን ምንም ያህል ቢያጠፉ እና ቢበድሉ፣ ቢሳሳቱ እና ኃጢአት ቢሠሩም መገሠጽ፣ ማስተማር፣ ማስፈራራት፣ የፈጣሪን ስም ጠርቶ መመለስ፣ ቃለ መጽሐፍ ጠቅሶ ልባቸውን መስበር ቀላል ነው፡፡ እነርሱ ጋር ያለው ቫይረስ በመድኃኒት ሊታከም፣ ሊድን ወይንም ሊዳከም የሚችል ነው፡፡

አሁን የቸገረን ሆስፒታል ውስጥ ያለው ቫይረስ ነው፡፡ ትምህርት፣ ጸሎት፣ መቅሰፍት፣ ተግሣጽ፣ ድርሳን እና ተአምር፣ ትንቢት እና መገለጥ፣ ቁርዐን እና ዱአ፣ ባህታዊ እና ልሣን ተናጋሪ፣ ሊፈራ የማይችል፡፡ ጠበል የለመደ ሆኖብን ነው የተቸገርነው፡፡ እግዚአብሔርን የማያውቁ የእግዚአብሔር ሰዎች በዝተው ነው የተሰቃየነው፡፡ ለቤተ እምነት ቅርብ ለፈጣሪ ግን ሩቅ የሆኑ አካላት ናቸው ሊድኑ ያልቻሉት፡፡

አትስረቅ የሚለው አካል ከሰረቀ፣ አታመንዝር ያለውም ካመነዘረ፤ ተፋቀሩ ያሉት ከተጣሉ፣ አንድ ሁኑ የሚሉት ከተከፋፈሉ፤ ሁላችን የአንድ የፈጣሪ ልጆች ነን የሚሉት በዘር እና በጎሣ ከተባሉ፤ የመነኑትን የሥልጣን ጥም ከያዛቸው፤ ሞተዋል የተባሉት የየራሳቸውን ቪላ ከገነቡ፤ የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ የያዙት የቢሮውን ቁልፍ ከዘጉ፤ ሌላ ልሳን እንናገራለን እያሉ የሕዝቡን ልሣን ካላዳመጡ፤ የነገው ትንቢት ተገለጠልን እያሉ የዛሬው ችግር ከጠፋቸው፤ በሽተኞችን እንፈውሳለን እያሉ እነርሱ ራሳቸው የማይፈወሱ በሽተኞች ከሆኑ፤ እንግዲህ «ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጡታል፣ ውኃ ቢያንቅ በምን ይውጡታል» የተባለው ደርሷል ማለት ነው፡፡

ፖለቲካችንም ተመሳሳይ ቫይረስ እያጠቃው ነው፡፡

ሕዝቡን በርእዮተ ዓለም አንቅተው ያሰልፋሉ ሲባሉ እነርሱ ራሳቸው ርእዮተ ዓለም ከሌላቸው፤ ሕዝቡን አደራጅተው እና መንገድ አሳይተው ወደ ዕድገት እና ብልጽግና ያደርሱታል ሲባሉ እነርሱ ራሳቸው መደራጀት እና መንቃት አቅቷቸው መንገድ ከጠፋባቸው፤ ሕዝብን የሥልጣን ባለቤት ያደርጉታል ተብለው ተስፋ ሲጣልባቸው እነርሱ ለራሳቸው ሥልጣን ብቻ የሚያስቡ ከሆኑ፤ ለሌላው ያስረዳሉ፣ ያሳውቃሉ፣ ሲባሉ እነርሱ ራሳቸው የድርጅታቸውን ፕሮግራም፣ ሕግ እና መመርያ ማወቅ እና መተግበር ሲሳናቸው፤ የተወዳደሩበት ዓላማ እና የሚሠሩት ሥራ ሲለያይ፤ የሆስፒታሉ ቫይረስ አለ ማለት ነው፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ዘመናዊው የፖለቲካ አካሄድ ከተጀመረ ጀምሮ ሥርዓታት ቢለዋወጡ እንኳን ያልጠፉ ችግሮች ግን አሉ፡፡ የደጋፊውም ሆነ የተቃዋሚው፣ ያለፈውም ሆነ የመጣው፣ የሚጋሯቸው ተመሳሳይ በሽታዎች አሉ፡፡ ከአዲሱ ትውልድ ይልቅ በነባሮቹ ማመን፤ የተወሰኑትን ብቻ የፖለቲካ ተዋንያን ማድረግ፣ በየጊዜው መለያየት እና መሰነጣጠቅ፤ ለችግሮች ምንጊዜም የውጭ ተጠያቂን መፈለግ፤ የማይጨበጥ እና የማይዳሰስ ጠላት መፍጠር፤ ከተሳትፎ ይልቅ ቲፎዞነትን መምረጥ፣ ከአመክንዮ ይልቅ ስሜትን ማዳመጥ፣ ከመሠረተ ሃሳቦች ይልቅ ግለሰቦችን መከተል፤ የፖለቲካ አካሄዶችን ከግላዊ ጥቅም አንፃር መመዘን፤ ስሕተትን መቀበል እንደ ውርደት ማየት፤ ራስን ብቻ ማዳመጥ፡፡

እነዚህ እና ሌሎች መሰሎቻቸው የፖለቲካውን ሆስፒታል ተላምደውት እየኖሩ ያሉ ቫይረሶች ናቸው፡፡ ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተላምደው፣ መሰሎቻቸውንም ተክተው ተቀምጠዋል፡፡ የሚመጡ መከላከ ያዎችም ሆኑ

መድኃኒቶች ሊያጠፏቸው አልቻሉም፡፡ ሆስፒታሉ ውስጥ ከመኖራቸው የተነሣ እነርሱ ራሳቸው የሆስፒታሉ አካላት ሆነዋልና፡፡ እዚህም እዚያም ቢኬድ፣ ይህኛውንም ሆነ ያኛውን አካል ብናይ ይቃወማቸዋል፣ እዋጋቸዋለሁ ይላል፣ ይምላል፣ ይገዘታልÝÝ ነገር ግን ራሱ የችግሩ እንጂ የመፍትሔው አካል ስላልሆነ አያከማቸውም፡፡

እዚህኛው ፓርቲ ውስጥ እንዲህ እና እንዲያ አለ፣ ይህኛው አካሄድ በዚህ እና በዚያ ምክንያት አያስኬድም ብሎ የተሻለ ነገር ሊፈጥር፣ ሌላ አካሄድ ሊያሳይ እንደ አዲስ ይደራጅና ሳያስበው ያንኑ ስሕተት ይወርሰዋል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ችግሮች እንደ ሆስፒታሉ ቫይረስ ቋንቋችንን፣ አሠራራችንን፣ባህላችንን፣ ሕጎቻችንን፣ መመርያዎቻችንን፣ ውሳኔዎቻችንን ተለማምደዋቸዋል፡፡

ባለፈው ሥርዓት ሕዝብ ሁሉ የሚያውቀው አንድ አባባል ነበር፡፡ በሀገሪቱ ውስጥ ኮሚቴዎች በዙ ተብሎ ምክክር ተደረገ፡፡ በመጨረሻም ተመካካሪዎች በአንድ ሃሳብ ላይ ተስማማሙ ይባላል፡፡ ኮሚቴዎችን አጥንቶ የሚቀንስ ሌላ ኮሚቴ ይቋቋም፡፡ እነዚህ ሰዎች ኮሚቴን እንቀንሳለን ብለው ሌላ ተጨማሪ ኮሚቴ እንዲያቋቁሙ ያደረጋቸው ቫይረሱ ነው፡፡ ይህ ችግር ዛሬም እንኳን አልለቀን ስላለ በየመሥሪያ ቤቱ፣ድርጅቱ፣ ማኅበራቱ፣ ወዘተ አንዳች ችግር ተፈጠረ፣ ሕዝብ ተማረረ፣ አሠራር ተበላሸ፣ ተብሎ ሲጠየቅ እንደ መጀመርያ እና ዋና መፍትሔ ተደርጎ የሚቆጠረው ኮሚቴ ማቋቋም ነው፡፡ ያለ ኮሚቴ ማሰብ እና መሥራት የሚቻል አይመስለንም፡፡ ለምን? የሆስፒታሉ ቫይረስ መፍትሔውን ስለለመደው ችግሩን መፍትሔ እያደረገው ይኖራል፡፡

እዚህ ሲያትል ያሉ ሰዎች የነገሩኝን ላውጋችሁ፡፡ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ተዳከመ፡፡ አዳዲሱ ትውልድ ራቀው፣ ነባሮቹ አመራሮች መሥራት አልቻሉም ተባለ፡፡ አመራሩን በአዲስ ለመተካት፤ በተለይም አዲሱን ትውልድ ቦታ ለመስጠት፤ ወጣቶች ገብተው እንዲይዙት ለማድረግ በየቦታው፣ በየሬዲዮው፣ በየጋዜጣው ተደሰኮረና ስብሰባ ተጠራ፡፡ ይሄው ሃሳብም በስብሰባው ቦታ ይበልጥ ተንፀባረቀ፡፡ በመጨረሻ ምርጫ ተደረገ፡፡ የሚገርመው ግን የተመረጡት በሙሉ ሽማግሌዎች፣ ደጃዝማች፣ ባሻ፣ ሻለቃ፣ የተሰኙ½ ብለው ብለው ያልተሳካላቸው ሰዎች ሆኑ፡፡ የተባለው እና የሆነው ነገር ሊገጣጠም አልቻለም፡፡ ይሄ የሆስፒታል ቫይረስ መች በፉከራ ብቻ ይጠፋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎቻችን በርእዮተ ዓለም የተለያየን ነን ይሉና በአደረጃጀት ግን ተመሳሳይ ናቸው፤ በድብቅነት፣ በአመራረጥ፣ ከውጭ ለመጣ ነገር በሚሰጡት ልዩ ቦታ፣ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ትናንት ያልተሳካላቸው ሰዎች ለአሥራ ሁለተኛ እና አሥራ ሦስተኛ ጊዜ መሪነትን የሚሞክሩበት፤ ያጠፉ ሰዎች የሚሸለሙበት ፖለቲካዊ አካሄድ የሁሉም ጠባይ ነው፡፡ ሃሳባቸውን ከመናገር አልፈው ለመጻፍ የማይ ወድዱ፤ ራሳቸውን በራሳቸው ለመተቸት የማይደፍሩ፤ አጠቃላይ ፖለቲካዊ አካሄዱን፣ አስተሳሰቡን፣ ለመለወጥ ከመሥራት ይልቅ ለምርጫ ብቻ የሚሠሩ ፓርቲዎችን መመሥረት ተመሳሳዩ ጠባይ ነው፡፡ በትክክል ቢታይ፣ ፕሮግራማቸው ቢመረመር፣ ዘጠና ስድስቱ የሀገራችን ፓርቲዎች ከአራት እና አምስት አይበልጡም ነበር፡፡ ዘጠና ስድስት ያደረጓቸው ርእዮታቸውና ፕሮግራማቸው ሳይሆን መሪዎቻቸው እና ቲፎዞዎቻቸው ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ መድኃኒት የማያስለቅቀው የሆስፒታል ቫይረስ ነው፡፡

የሆስፒታልን ቫይረስ በተለመደው የሕክምና መንገድ እና አሠራር ማጥፋት፣ ማዳከም እና ማላቀቅ አይቻልም፡፡ ሆስፒታሉን ከመድኃኒቶቹ በላይ ያውቀዋልና፡፡ እርሱኮ በሕክምና በለሞያዎቹ፣ በመድኃኒት መሣርያዎቹ፣ በአልጋዎቹ እና ግድግዳዎቹ፣ በፋርማሲዎቹ እና ላቦራቶሪዎቹ ውስጥ ነው ያለው፡፡ ስለዚህም ሆስፒታሉ ሙሉ በሙሉ በእነዚህ ቫይረሶች ተወርሮ ሥራ ከማቆሙ በፊት ከተለመዱት የተለየ፤ አዲስ እና መሠረታዊ የሆነ መፍትሔ መምጣት አለበት፡፡ ሕክምናው ሐኪሞቹን፣ መሣርያዎቹን፣ አልጋዎቹን፣ ቤቱን ከማከም መጀመር አለበት፡፡

# ኳሱን አትንኩብን

***በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ላይ የጀመርነውን ውይይት ለማሰቢያ ጊዜ እናገኝ ዘንድ ለጊዜው ዐረፍ እንበልና ማክሰኞ ደግሞ የሌሎቻችሁን አስተያየት በመጨመር እንመለሳለን፡፡ ለዛሬው ለማረፊያ እነሆ፡፡***

«ወጣቱ በአውሮፓ እግር ኳስ ነፍሱ ሊወጣ ነው። የሀገሩን እግር ኳስ እና የሀገሩን ጉዳዮች ከመከታተል ይልቅ በእን ግሊዝ፣ በጣልያን እና በስፔይን የእግር ኳስ ተጨዋቾች ልቡ ተነድፏል። ሚዲያዎችም ቢሆኑ እንዴው ለአመል ያህል የሀገራችንን ኳስ ነካ ነካ ያደርጉና እጥፍጥፍ ብለው ወደ አውሮፓ ይሻገራሉ» እያላችሁ ታሙናላችሁ አሉ።

ወገኞች ናችሁ እንዴው። የጨዋታውን ዓይነት፣ የግቡን ልዩነት፣ የታክቲክ እና የቴክኒኩን ነገር ተውት ይቅር ግዴለም። የተጨዋቾቹን ዝና እና ታዋቂነት፣ የሚያሳዩትን ምትሐት ተውት አይነሣ ግዴለም። አሁን እኛ ሀገር በእግር የሚመታ ኳስ እንጂ እግር ኳስ አለ ይባላል? እንኳን የአፍሪካ እግር ኳስ ፌዴሬሽንን ከመሠረቱት ሦስት ሀገሮች አንዱ ልንመስል እግር ኳስ ከአውሮፐላን ተወርውሮ የነጠረባት ሀገር እንመስላለን? ለመሆኑ እኛ ሀገር ስለ ተጨዋቹ እና ስለ ጨዋታው ከሚነገረው በላይ ስለ ቡድኖቹ ሽኩቻ እና ስለ ፌዴሬሽኑ ውዝግብ የሚነገረው አይበልጥም?

«ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከንቢያው ቁጢጥ» ሲባል አልሰማችሁም። ኳሱ መከራ እያየ፣ እኛ ማን ሥልጣን ላይ ይውጣ የሚለው ነው የሚያወዛግበን። መጀመርያ ኳሱ ሲኖር እኮ ነው ፌዴሬሽን እና የፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት የሚያስፈልገው። «ጥርስ የላት ትወቀር አማራት» አሉ። የኢትዮጵያን እግር ኳስ አሁን ካለበት ደረጃ ለማድረስ እኮ ግዴለሽነት እና ከፋት እንጂ ፌዴሬሽን አያስፈልግም ነበር።

ስንት ዋንጫ እየሳሙ፣ስንት ውጤት እያመጡ፣ ስንት ታሪክ እየሠሩ ዓለምን የሚያናውጡ ቡድኖች ያሏቸው ፌዴሬሽኖች ሳይወዛገቡ እኛ ፊፋ ድረስ ሄደን እንካሰሳለን። «ቅቤ አንጓሪዋ ተቀምጣ ጎመን ቀንጣሿን ምች መታት» አሉ ወይዘሮ ዘርፌ። ፊፋስ ቢሆን «ማስረጃችሁን አምጡ፣ የፊፋ ሕግ አልተከበረም፣ መተዳደርያው ተጥሷል» እያለ ያለ ደረጃችን ደረጃ ከሚሰጠን መጀመርያ እስኪ ስታዲዮም ገብቼ ስትጫወቱ ልያችሁ፣ እስኪ ቡድኖቻችሁ እንዴት እንደተደራጁ አሳዩኝ፣ እስኪ ስንት ስታዲዮም ገነባችሁ፣ እስኪ ቢሮአችሁ እንዴት እንደ ተደራጀ ልይ» ቢል ኖሮ ውዝግቡ ይህንን ያህል ዘመን መች ይፈጅ ነበር። በሌለ ነገር እኮ ነው መከራ የምናየው።

«ሥጋ ቁጠር ቢሉት ጣፊያ አንድ አለ» የተባለው ደረሰና ለምንድን ነው ኳሳችሁ የማያድገው? ተብለው ሲጠየቁ «ሕዝቡ የአውሮፓ እግር ኳስ ስለሚያይ ከስታዲዮም ስለ ጠፋ ነው። ስለዚህም የአውሮፓ ጨዋታ የማይታይበትን መንገድ እንፈልጋለን» አሉ አሉ። ለሠራነው ስሕተት ራሳችንን ተጠያቂ የምናደርግበት፣ ይህ ነገር ሊከሰት የቻለው ምን ስሕተት ስለሠራሁ ነው? ብለን የምንጠይቅበት ዘመን መቼ ይሆን የሚመጣው። እንዴው እድሜ ልካችንን ለችግራችን ሁሉ ውጫዊ ምክንያት እንደፈለግን ልንኖር ነው?

የጤፍ ነጋዴ ፓስታ በብዛት ስለተመረተ ገበያ ጠፋብኝ ብሎ ያውቃል? የቢራ ፋብሪካ እዚህም እዚያም ቢከፈት የሀገሬ ጠጅ ቤቶች መች ንቅንቅ አሉ። እነ ገደል ግቡ፣ እነ ውስኪ ለምኔ፣ ጠጅ ቤት ይሄው ጢም እንዳሉ ናቸው። ሌላውን ተውት የሀገሬ ሰው በፊልሞቹ ላይ የሚሰጠውን ያንን ሁሉ ትችት እየሰማ እንኳን፣ «ሰው በዐቅሙ ነው የሚጸድቀው» ብሎ ከውጭ ሀገር ፊልሞች እኩል እንዲያውም በላይ፣ የሀገሩን ፊልም እያየ አይደለም እንዴ?

ለመሆኑ ሕዝቡ የአውሮፓ እግር ኳስን ለምን እንደሚወድደው ያውቁታል። የጨዋታውን ጣዕም እና የቡድኖቹን የብቃት ደረጃ አላነሣውም። እንዳላስጎመጇቸው ብዬ። ኧረ ሌላ ሌላውን። ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለ አንድ ቡድን፣ ተጨዋች፣ የቡድን አሰላለፍ፣ የአሠልጣኞች ሁኔታ፣ የክለብ ባለቤቶች እንቅስቃሴ፣ የገቢ እና ወጭ ጉዳይ ለማውራት መረጃ ይገኛል? የተጠናከረ ዌብ ሳይት ያለው ቡድን አለ? የተደራጀ ሙዝየም ያለው ቡድን አለ? የአንድ ተጨዋች ታሪክ፣ ያገባቸው ግቦች፣ መቼ እንዳገባ፣ የት ላይ እንዳገባ? በመዝገብ ይያዛል? በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ በዛሬው ዕለት የዛሬ ሠላሳ ዓመት ምን ተደርጓል? ተብሎ ቢጠየቅ መልስ ያለው ክለብ እና ፌዴሬሽን አለን?

በሐሜት ከሚነገረው በዘለለ የተጠናቀረ፣ሁሉም ሊያውቀው የሚችል እና የሰሚውን ልቡና ሊያረካ የሚችል መረጃ አለ? ስለ አውሮፓ ቡድኖች፣ ፌዴሬሽኖች፣ ተጨዋቾች፣ አሠልጣኞች እኮ ከሚፈለገው በላይ የመረጃ ጎረፍ ይፈስሳል። ምን በሉ፣ ምን ጠጡ፣ የት ዋሉ፣ የጫማ ቁጥራቸው ስንት ነው፣ የቤተሰባቸው ሁኔታ እንዴት ነው ተብሎ ቢጠየቅ፣ በደቂቃ መረጃ ማግኘት ይቻላል። «የማያውቁት ሀገር አይናፍቅም» ሲባል አልሰማችሁም፣ ታድያ የማናውቀውን እግር ኳሳችንን እንዴት እንውደደው።

አንዳንድ ባለሥልጣናት እኮ መረጃ መስጠት የሚመስላቸው ጋዜጠኛ ጠርተው የሚያስቡትን እና የሚፈልጉትን መናገር ነው፡፡ ይሄኮ ሃሳብን መግለጥ እንጂ መረጃ መስጠት አይደለም፡፡ መረጃ መስጠት ማለትማ መረጃ መሰብሰብ፣ ሊገኝ በሚችልበት ቦታ እና መንገድ ማስቀመጥ፣ በልዩ ልዩ የመረጃ ማስተላለፊያ መንገዶች ወደ ተጠቃሚዎቹ ማድረስ ነው፡፡ ደግሞምኮ እኛ የምንፈልገውን እና የምንወደውን ብቻ እንዲታወቅ የምናደርግ ከሆነ መረጃ መስጠት ሳይሆን ዕንቁልልጮሽ ነው የሚሆነው፡፡

ደግሞስ መረጃ ቢኖርስ ነጻነቱ የት ይገኛል፡፡ የአውሮፓ እግር ኳስን እኮ ብንፈልግ ስለ ተጨዋቹ ፣ብንፈልግ ስለ አሠልጣኙ፣ ብንፈልግ ስለ ክለቡ ባለቤት፣ ብንፈልግ ስለ ቡድኑ ገቢ እና ወጭ፣ ብንፈልግ ስለ ፌዴሬሽኑ የዕለት ውሎ ስንተች፣ ስንተነትን፣ ስንከራከር ብንወል ማን ተቆጭ አለን፡፡ ጋዜጠኞቹ እንኳን ዘና ብለው መዘገብ የሚችሉት የሀገሪቱን ዘገባ ጨርሰው ሜዲትራንያንን ሲሻገሩ ነው፡፡ የሚቆጣቸው ፌዴሬሽን፣ የሚያስፈራራቸው ባለሀብት፣ የሚሰድባቸው ደጋፊ፣ የሚዝትባቸው ክለብ የለ፡፡ እኛ ሀገርኮ ኳሱ ለትንታኔ አይመች፣ የኳሱም ሰዎች ለትንታኔ አይመቹ፡፡

ስለ ጊዮርጊስ ከተቸህ «ፀረ ጊዮርጊስ» ትባልና መቆሚያ መቀመጫ ታጣለህ፡፡ ስለ ቡና ከተናገርክ «ፀረ ቡና» ትባልና ምስህ ዱላ ይሆናል፡፡ እንኳንስ ስትተቸው ስታመሰግነው እንኳን «ሦስት ጊዜ ምስጋና አንዱ ለነገር ነው»ብሎ በሚጠራጠርህ ሰው መካከል ሆነህ እንዴት ነው ስለ ሀገራችን ክለቦች የምትጨነቀውና የምትደግፈው፡፡ «ድጋፍ ተቃውሞን ካልፈቀደ፣ እንጀራ እርሾን ካልወሰደ» ምን ያደርጉልናል፡፡

ሁለት የአውሮፓ ኃያላን ቡድኖች ከመጋጠማቸው በፊት እዚህ አዲስ አበባ ሆነን አሰላለፋቸውን እናውቀዋለን፡፡ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ማን ለማን እንደተሰለፈ በግልጽ ይታወቃል? በዛሬ ጨዋታ ለአርሴናል የተሰለፈው በቀጣዩ ጨዋታ አሠልጣኙ እንኳን ሳይሰማ ለማንቸስተር እየተሰለፈ መከራ አየንኮ፡፡ እዚህ አዲስ አበባ ሆነን የተጨዋቾች የዝውውር መስኮት ሲከፈት ማን ወደ የትኛው ቡድን ሊሄድ እንደሚችል በግምትም፣ በፍንጭም፣ በመረጃም እንናገራለን፡፡ መሄድ አለበት፣ የለበትም እያልን እንከራከራለን፡፡

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም መስክ ማን ወደ የትኛው ቡድን ለመቀላቀል እንዳሰበ፣ እነማን ማንን እንዳስፈረሙ፣ ማን ከነማን ጋር ለመፈራረም ውስጥ ውስጡን እየመከረ እንደሆነ ማወቅ፣ ካወቁስ በኋላ ሃሳብ መስጠት ይቻላል? ይኼው ስንቶቹ መቼ እንደ ተነጋገሩና፣ መቼ ሃሳባቸውን እንደቀየሩ ሳናውቀው ለሌላ ቡድን ሲጫወቱ አገኘናቸው አይደል እንዴ፡፡ አንዳንዶቹም ጭራሽ የነበሩበትን ቡድን ለቅቀው፣ እንዲያውም አብረዋቸው ከተጫወቱት ጋር ተጋጭተው፣ የሌላ ቡድን አሠልጣኝ ሲሆኑ ያየናቸው በድንገት ነው፡፡ የአውሮፓ ኳስ ቢሆን ኖሮ ቢያንስ ለመገመት በቻልን፣ ከተቻለም ፍንጭ ባገኘን ነበር፡

ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ማንንም ሳይፈሩና ሳይሰቀቁ እንደ ልብ ሊያወሩበት እና ሊከራከሩበት የሚችሉት ጉዳይ የአውሮፓ ኳስ መሆኑን ታውቃላችሁ፡፡ ብንደግፍ፣ ብንቃወም፣ የደገፍነውን ቡድን ዓርማ ብናውለበልብ፣ ማልያውን ብንለብስ፤ ስለ እያንዳንዱ ነገር እያነሳን ብንፈልጥ ብንቆርጥ ማን ተቆጭ አለን፡፡ እና እንደዚህ በነጻነት የሚወራ ጉዳይ ከየት ይገኛል ጃል፡፡ አቦ ተውና፡፡

ደጋፊም ተቃዋሚም መሆን እዚህ ሀገር ዕዳ ነው፡፡ የመንግሥት ደጋፊ ነኝ ካልክ ገልማጭህ ብዙ ነው፡፡ ተቃዋሚም ነኝ ካልክ የሚያጉረጠርጥብህ በዚያው ልክ ነው፡፡ የአንዱን ማልያ መልበስ ቀርቶ ልትገዛ ስታገላብጥ ከታየህ መከራ ነው፡፡ እንኳንስ ስለ ተጨዋቾቹ አንሥቶ ለመነጋገር እና ለመተቸት ይቅር እና በቴሌቭዥን ሲቀርቡ እንኳን እነርሱን ትኩር ብለህ ካየህ አንዱ «ምን ታፈጣለህ?» ይልሃል ሌላው ደግሞ «ምነው ሙድ ያዝኸሳ» ብሎ ይተርብሃል፡፡ በአውሮፓ ኳስ ግን፣ ብትደግፉ ተለጣፊ፣ ብትቃወሙ አደናቃፊ የሚላችሁ የለም፡፡

ደግሞስ ደጋፊ እና ተቃዋሚ በአንድ አዳራሽ የሚሰበሰብበት ይህንን የመሰለ ነገር ከየት ይገኛል፡፡ ከመተራረብ፣ ከመተቻቸት ያለፈ ሌላ ነገር የለ፡፡ ርግጥ ነው እግር ኳሱን በፖለቲካው መንገድ ለማስኬድ የሚፈልጉት አንዳንዶች ብጥብጥ እያነሡ ተቸግረን ነበር፡፡ አሁን ግን ጋብ ብለዋል፡፡ በኳስኮ በዚህኛው ጨዋታ ካሸነፋችሁ እየጨፈራችሁ ቤታችሁ ትገባላችሁ፣ አንድ ሳምንት ትተነትናላችሁ፣ ከዚያ በኋላ ለቀጣዩ ጨዋታ መዘጋጀት ነው፡፡ ትናንት አሸነፋችሁ ማለት ነገም ታሸንፋላችሁ ማለት አይደለም፡፡ ብትሸነፉም ለጊዜው ትናደዱና እንደ ገና ለማሸነፍ መሥራት ነው፡፡ ቴክኒክ እና ታክቲክ መቀየር፣ ሥልጠናውን ማጠናከር ብቻ ነው፡፡ ትናንት ለምን እንዲህ ሆነ ብሎ ሙዝዝ ማለት የለም፡፡ ሌላ ሌላውንማ ሲያሸንፍና ሲሸነፍ ምን እንደሚመስል አየነውኮ፡፡

ኧረ ለመሆኑ የአውሮፓ ኳስ ባይኖር ስለ ምን እናወራ ነበር፡፡ ሰው ቋንቋ ኖሮት እንዴት ሳያወራ ይኖራል? ምሳ ሲበላ፣ ሻሂ ሲጠጣ፣ ቡና ሲፈላ፣ በታክሲ እና በአውቶቡስ ሲኬድ ታድያ ምን ይወራ? ሁሉም ነገር ፖለቲካ በሆነበት ጊዜ ታድያ ምን እናውራ፡፡ ጤፍ ተወደደ ፖለቲካ ነው፣ጤፍ ረከሰም ፖለቲካ ነው፡፡ ሀገራችን አደገች ማለት ፖለቲካ ነው፣ ሀገራችን ወደ ኋላ ቀረች ማለትም ፖለቲካ ነው፡፡ እገሌ ተሳስቷል ማለት ፖለቲካ ነው፣ልክ ነው ብሎ መናገርም ፖለቲካ ነው፡፡ ታድያ ምን እንበል?

ምን እባል ይሆን? ማን ሰምቶኝ ይሆን? ተብሎ በሚወራበት በዚህ ጊዜ እንደ ልብ የሚወራ ነገር ማግኘት ቀላል ይመቻል እንዴ! እኛ ተመልካቾች በሂደት አንድ የጥናት ውጤት አግኝተናል፡፡ ቢያንስ ስለ አውሮፓ እግር ኳስ ስታወራ የትኛውም የፓርቲ አባል እንደማይቆጣ፡፡ አውሮፓውያን ኢትዮጵያውያን ቢሆኑ ኖሮኮ በስፔን ቡድን ላይ ትችት ስትሰነዝር የስፔን ኤምባሲ፣ በእንግሊዝ ቡድን ላይ ስትወርድበት የእንግሊዝ ኤምባሲ፣ የጣልያንን ቡድን ስታነሣ ጣልያን ኤምባሲ አያስቀምጡንም ነበር፡፡ አቦ እንኳን ኢትዮጵያውያን አልሆናችሁ፤ ተመችታችሁናል፡፡

## ግመሎቹም ይሄዳሉ ውሾቹም ይጮኻሉ

ሚቼ የ «እንደ ቸርነትህ´ መዝሙር ደራሲ ዶክተር ኢሳይያስ ዓለሜ እንዲህ ይላሉ፡-

አንድ አባት አህያውን እየነዳ ከልጁ ጋር መንገድ ጀመረ፡፡ እልፍ እንዳለ ሰዎች ተመለከቱትና «ምን ዓይነት ሞኞች ናቸው፤ እንዴት አህያ እያለ በእግራቸው ይሄዳሉ´ በማለት ተቿቸው፡፡ አባትም ትችቱን ሲሰማ ሀሳቡን ቀየረ፡፡ ሁለቱም አህያዋ ላይ ወጡና መንገዳቸውን ቀጠሉ፡፡ ጥቂት እንደሄዱ ሌሎች ሰዎች አዩዋቸውና «እንዴት ያሉ ጨካኞች ናቸው፤ እንዴት አንድ አህያ ለሁለት ይጋልባሉ´ ብለው ራሳቸውን ነቅንቀውባቸው ጥለዋቸው ሄዱ፡፡

አባትዬውም ከአህያዋ ላይ ወረደ፡፡ እርሱ ከኋላ አህያዋን እየነዳ ልጁን በአህያዋ ጭኖ ጉዞውን ተያያዘው፡፡ የተወሰነ መንገድ ከተጓዘ በኋላም ሌሎች መንገደኞችን አገኘ፡፡ እነዚያም መንገደኞች አባት እና ልጁን አዩና «አይ ስምንተኛው ሺ፤ አያሳየን የለ፤ ልጁ በአህያ ተቀምጦ ሽማግሌ አባቱን በእግሩ ያስኬደዋል፡፡ አበስኩ ገበርኩ´ ሲሉ ሰማ፡፡

ወዲያው ልጁን ከአህያዋ አውርዶ እርሱ ተጫነና ጉዞው ተጀመረ፡፡ መንገዳቸውን እንዳጋመሱም ከገበያ የመጡ ሰዎችን አገኟቸው፡፡ እነዚያም መንገደኞች ጉዟቸውን ገትተው «እንዴት ምኑንም የማያውቅ ልጁን በእግሩ እያስደገደገ እርሱ በአህያ ይሄዳል፤ ወይ ጭካኔ፣ወይ ጭካኔ´ ብለው ደረታቸውን ደቅተው ሄዱ፡፡

በዚህ ጊዜ አባትዬው ከአህያዋ ወረደና ለልጁ እንዲህ አለው፡፡ «አየህ ልጄ በዚህ ዓለም ምንም ነገር ብትሠራ ሰውን ሁሉ ማስደሰት አይቻልም፡፡ ሰዎች እንዲህ ይሉኛል እያልክ የምትፈራ ከሆነ ምንም ነገር ማድረግ አትችልም፡፡ ሰዎች ምንም ብታደርግ የሚሉት አያጡምና፡፡ አንተ ሰውን ሳይሆን ስሕተትን ፍራ፡፡ ትችትን ሳይሆን ኃጢአትን ፍራ፡፡ ሰዎች ስላሉት ብቻ የምትቀበል ከሆነ ሃሳብህን መቶ ጊዜ ትቀያይራለህ፡፡ መቀበል ያለብህ የሚሉት ነገር ትክክል ከሆነ ብቻ ነው፡፡´ አለው፡፡ ከዚያም አባት እና ልጅ እየተጨዋወቱ መንገዳቸውን ቀጠሉ፡፡

ሰዎች ቢያመሰግኑን አይጠላም፡፡ እንዲያመሰግኑን ብለን መሥራት ግን የለብንም፡፡ ለምዶብን አንዳንዶቻችን የብርጭቆውን ውኃ ስናይ ግማሽ ጎዶሎ መሆኑን እንጂ ግማሽ ሙሉ መሆኑን አናይም፡፡

የሰዎችን ሃሳብ ስንሰማ ቢያንስ ሦስት ነገሮችን መመዘን አለብን፡፡

ይህ ሰው ይህንን አስተያየት ለመስጠት ብቁ ነውን? በሞያው፣ በዕድሜው፣ በውሎው፣ በትምህርቱ፣ በልምዱ፣ ይህንን አስተያየት ለመስጠት ሚዛን የሚደፋ ከሆነ ግምት ውስጥ አስገብተን እንመርምረው፡፡

ይህ ሰው ይህንን አስተያየት አስተያየት ሲሰጥ ከልቡ ነውን? አስቦበት፣ አመዛዝኖ፣ በመሠረተ ሃሳብ አስደግፎ ነው ወይስ እንዲሁ ስለመጣለት በስሜት ተነሣሥቶ?

ይህ ሰው ከሚያነሣው ነገር ጋር የጥቅም ግጭት የለውምን? ክብሩን፣ ሥልጣኑን፣ ገንዘቡን ስለሚነካበት ያንን ለማስጠበቅ ነውን? ተመቅኝቶ፣ ቀንቶ ወይንም ግላዊነት አጥቅቶት ነውን?

ጉዳዩን ያለዚያ ቀን ሰምቶት የማያውቅ፣ በዚያ ነገር በትምህርት፣ በዕድሜ፣ በንባብ ወይንም በልምድ የተገኘ ዕውቀት የሌለው፤ እንዴው አፌ ተባልኝ፣ ንግግሬ ተደመጠልኝ፣ ጨዋታዬ ደራልኝ ያለ ሁሉ የሚናገረውን ሰምተን ሃሳባችን መቀየር፣ መጠራጠር ወይንም ደግሞ ራሳችንን እንደ ስሕተተኛ መቁጠር የለብንም፡፡ አንዳንዱኮ «ይህ ነገር አላማረብህም´ ሲል የሠራውን አርፍተ ነገር ትርጉም እንኳን በቅጡ አያውቀውም፡፡ አንዳንዱም ሰው ሁሉ ሲናገር ከሚቀርብኝ ብሎ ሃሳብ የሚሰጥም አለ፡፡

እንደመጣለት የሚናገረውስ ቢሆን፡፡ ሊቃውንት «አንድ ጊዜ ከመናገር በፊት ሁለት ጊዜ ማሰብ ይገባል´ ይላሉ፡፡ እንኳን ሁለት ጊዜ አንድ ጊዜ እንኳን ሳያስብበት እንደመጣለት የሚናገረውን ሰው እየሰማን እኛ ለምን እንዳደዳለን? ለምንስ መንገዳችንን እንስታለን፡፡ ምናልባትኮ አንዳንዱ የተናገረው ለርሱ ቀልድ ይሆናል? በጆሮው የሰማውን በአንደበቱ ለማውጣት ምንም ዓይነት ሂደት በአእምሮው የማያከናውን ሰው ሞልቷል፡፡ የመንገድ ላይ ቱቦ ያስገባውን ሁሉ እንደሚያወጣ ያየውን እና የሰማውን ሁሉ ሳያጣራ፣ ሳያበጥር፣ ሳይመረምር፣ ይዋል ይደር ሳይል እንዳለ የሚለቅም አለኮ፡፡

«ይህን ነገር ማድረግሽ ስሕተት ነው´ ሲል «ማድረግ የነበረብኝ እኔ ነበርኩ´ እያለ መሆኑን ልንረዳለት የሚገባን ሰውኮ አለ፡፡ «ሰዎች እንዲህ ይላሉ´ ከሚለው ወገናችን በዛ ያለው ራሱ የሚለውን «ሰዎች´ በሚል ባለቤት አልባ ባለቤት በኩል እየነገረን መሆኑንም መጠርጠር ይገባል፡፡

ታድያ የሚያዋጣው ምንድን ነው? መሥራት፡፡ መጀመርያ ነገር ለምናደርገው ሁሉ ለራሳችን አሳማኝ ምክንያት ይኑረን፡፡ ርግጠኞች እንሁን፡፡ ከምንመራበት መሠረተ ሃሳብ፣ ከእውነት እና ከታወቁ እውነታዎች ጋር መዝነነው ትክክል መሆኑን እንመንበት፡፡ ሰዎች በማስረጃ ወይንም በመረጃ የሚያቀርቡልንን ሃሳብ ሁሉ ለመቀበል ለራሳችን ዝግጁ እንሁን፡፡

ከዚያ በኋላ ያለ የሌለ ጉልበታችንን ሥራችን ላይ እናውል፡፡ ምን ተባለ ም?ን አሉ? ምን መልስ ልስጥ? በምን ላሳምናቸው? እያልን ስንብሰከሰክ ወርቃማውን የሥራ ጊዜ አናሳልፈው፡፡ «ወፎች ከጭንቅላታችን በላይ እንዳይበርሩ

ማድረግ አይቻልም፤ በጭንቅላታችን ላይ ጎጆ እንዳይሠሩ ማድረግ ግን ይቻላል» የሚል አባባል አለ፡፡ ሰዎች ስለ እኛ ሥራ አንሥተው እንዳያሙ፤ እንዳይተቹ፣ እንዳያጣጥሉ፣ እንዳያንቋሽሹ ማድረግ አንችልም፡፡ የእነርሱ ትችት እና ሐሜት በጆሯችን ገብቶ ኅሊናችንን እንዳይረብሸን ማድረግ ግን እንችላለን፡፡ የተነገረውን ሁሉ ማስማት የተጮኸውን ሁሉ ማዳመጥ የለብንምና፡፡

ደግሞም ሁሉንም ሰዎች ማስደሰት አይቻልም፡፡ እኛ ሃሳብ እና አእምሮ ያላቸውን፣ በምላሳቸው ሳይሆን በጭንቅላታቸው የሚያስቡትን፡፡ አንደበታቸው ከልባቸው፣ ስሜታቸው ከኅሊናቸው ያልቀደመባቸውን ሰዎች፣ ያውም ከእነርሱም መካከል ነገራችን ሊገባቸው የሚችሉትን ካረካን እድለኞች ነን፡፡

ብዙ የሚለፈልፉ ሰዎችን አንፍረድባቸው፡፡ ሠርተው የሚያሳዩት ነገር የላቸውምና፡፡ ብዙ የሚሠሩ ሰዎች ግን ምንም መናገር አያስፈልጋቸውም፡፡ ከንግግር በላይ ተግባር መልስ ነውና፡፡ ሰዎች ለምን እንዲህ ይሉኛል? ለምን የኔ ሥራ አይገባቸውም? ለምን አይረዱኝም? እያሉ በመጨነቅ አእምሮን በማይጠቅሙ ቫይረሶች ከመሙላት የሚችሉትን ሠርቶ ሰዎች በራሳቸው ጊዜ እንዲረዱት መተው ነው፡፡

በዓለም ላይኮ መሬት ክብ ናት በማለታቸው ሞት የተፈረደባቸው ሰዎች ነበሩ፡፡ ነገር ግን ሰዎች ስለተቿቸውና በዘመኑ ስላልተቀበሉት ብለው አልተውትም፡፡ በመጨረሻ ያሸነፉት እነርሱ ናቸው፡፡ በወቅቱ ዓለም ያላየውን እነርሱ አዩ፡፡ ዓለም ግን ዘግይቶ እነርሱ ያዩትን አየ፡፡ ያን ጊዜ ዓለም ይቅርታ ጠየቀ፡፡

የምንሠራው ሥራ ዛሬ ሰዎች ላይገባቸው ይችላል፤ ላይፈልጉትም ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ቀን አለው፡፡ ሰው ሁሉ በአንድ ቀን አልተፈጠረምና በአንድ ቀን እኩል አይረዳም፡፡ ቀልድ ተነግሮት እንኳን ሲጀመር የሚስቅ አለ፤ በመካከል መሳቅ የሚጀምር አለ፤ ሲያልቅ ገብቶት የሚስቅ አለ፤ አድሮ የሚያስቀው አለ፤ ከርሞ የሚያስቀው አለ፤ ጭራሽ የማያስቀውም አለ፡፡ አሁን ቀልዱ ቀልድ መሆኑን በምንድን ነው ማወቅ የሚቻለው?

ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ ስልብ ነበሩ ይባላል፡፡ ታድያ ዐፄ ምኒሊክ ጎራ ሸለሟቸውና ሰው ሁሉ አደነቀላቸው፡፡ ወዳጆቻቸውም «ይህንን ነገር የማያደንቅ ገብረ ሐና ብቻ ነው» ይሏቸዋል፡፡ ያስጠሯቸውና ለአለቃ ገብረ ሐና ያሳዩዋቸዋል፡፡ አለቃም ጎራዴውን እያገላበጡ «አይ ጎራዴ፣ አይ ጎራዴ፣ ጎራዴ፣ ጥሩ ጎራዴ» ብለው ያደንቁላቸዋል፡፡ ባልቻም ደስ ብሏቸው ይለያያሉ፡፡

ወዳጆቻቸውም «ገብረ ሐና ምናለ?» ብለው ይጠይቋቸዋል፡፡ ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶም «በደንብ ነው ያደነቀው» ብለው ይመልሳሉ፡፡ «እስኪ ምናለ?» ይላሉ ወግ ፈላጊዎቹ፡፡ «አይ ጎራዴ፣ አይ ጎራዴ ብሎ አደነቀ» ይሏቸዋል፡፡ ያ ሁሉ ሰው በሳቅ ያወካና «እንዴ ደጃዝማች ባልቻ ከዚህ በላይ ገብረ ሐና ምን ሊልዎት ነው» ብለው ያስረዷቸዋል፡፡ ያን ጊዜ ጀግናው ባልቻ እገላለሁ ብለው ያዙኝ ልቀቁኝ አሉ ይባላል፡፡

ዐረቦች «ግመሎችም ይሄዳሉ፣ ውሾቹም ይጮኻሉ» የሚል አባባል አላቸው፡፡ የዐረብ ነጋዴዎች ግመሎቻቸውን ጭነው በመንደሮቹ መካከል ሲያልፉ ውሾቹ እየጮኹ አያሳልፏቸውም፡፡ ነገር ግን በእነርሱ ምክንያት መንገዳቸውን አያቆሙም፡፡ ግመሎቹም መሄዳቸው፣ ውኾቹም መጮኻቸው የማይቀር ነገር ነውና፡፡

ሰው በሚያገባውም በማያገባውም መተቸቱ የማይቀር ነው፡፡ ዋናው መርጦ መውሰዱ ላይ ነው፡፡ ነጭ ሲደረግ ለምን ጥቁር አልሆነም፣ ጥቁር ሲደረግ ለምን ሰማያዊ? ሰማያዊ ሲሆን ለምን ግራጫ? ግራጫ ሲሆን ለምን ቢጫ? ይቀጥላል፡፡ ሰው ይህንን ሁሉ እየሰማ ቀለም ሲቀያይር የሚኖር ከሆነ የሚሠራው ቤት ቀለም ማስተማርያ መሆኑ ነው፡፡

እኛም የምንናገር ሰዎችም ብንሆን የምንናገረው ነገር የዕውቀታችን ማስመስከርያ ሞን የለበትም፡፡ ሊሆን ሊደረግ የሚችል መሆኑን እና አለመሆኑን መለየት አለብንኮ፡፡ ሴትዮዋ ወንበር ገዝታ ከመጣች በኋላ «አይ እዚህ ሱቅኮ በርካሽ የሚሸጥ ነበረልሽ´ ብሎ ማስፀፀት ጥቅሙ ምንድን ነው? እየደጋገመ ሴት የወለደን ሰው «የአሁኗ እንኳን ወንድ ብትሆን ጥሩ ነበር» እያሉ መመጻደቅ ምንድን ነው? ሰውዬው ወስኖ አልወለዳት፡፡ ሰውዬው ከሞተ በኋላ ቋሚውን «እንዲህ ቢያደርግ ኖሮኮ አይሞትም ነበር» እያሉ ለማይመለስ ነገር ቆሽት ማሳረር ምን የሚሉት ሞያ ነው?

ሰው የሚለውን ሁሉ አልቀበልም ማለትም በሽታ ነው፡፡ ሰው የሚለውን ሁሉ መቀበልም ጦስ ነው፡፡ ሰው ለሚለው ሁሉ ዝም ማለትም በሽታ ነው፡፡ ሰው ለሚለው ሁሉ መልስ መስጠትም ጦስ ነው፡፡ ሰው በተቸ ቁጥር ሃሳብን መቀየር ጅልነት ነው፡፡ ሰው የፈለገውን ቢል ሃሳቤን አልቀይርም ማለትም ግትርነት ነው፡፡ ሰው በተናገረ ቁጥር መናደድ እና ማረርም ቂልነት ነው፡፡ በሰው ንግግር ሁሉ መቀለድም ቂላቂልነት ነው፡፡

ልብ ያለው የሚባለውን ነገር ጆሮው በር ላይ አስቀምጦ ይመዝነዋል፡፡ የሚረባ ከሆነ ያስገባዋል፤ የማይረባ ከሆነ ተቀባይ እንዳጣ ፖስታ ይመልሰዋል፡፡ እንዲህ ያለው ሰው በልቡናው ውስጥ የማይጠቅሙ ሃሳቦች ማጠራቀሚያ ቅርጫት የለውም፡፡

## ኳሱን አትንኩብን

*በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ላይ የጀመርነውን ውይይት ለማሰቢያ ጊዜ እናገኝ ዘንድ ለጊዜው ዐረፍ እንበልና ማክሰኞ ደግሞ የሌሎቻችሁን አስተያየት በመጨመር እንመለሳለን፡፡ ለዛሬው ለማረፊያ እነሆ፡፡*

«ወጣቱ በአውሮፓ እግር ኳስ ነፍሱ ሊወጣ ነው፡፡ የሀገሩን እግር ኳስ እና የሀገሩን ጉዳዮች ከመከታተል ይልቅ በእን ግሊዝ፣ በጣልያን እና በስፔይን የእግር ኳስ ተጨዋቾች ልቡ ተነድፏል፡፡ ሚዲያዎችም ቢሆኑ እንዴው ለአመል ያህል የሀገራችንን ኳስ ነካ ነካ ያደርጉና እጥፍጥፍ ብለው ወደ አውሮፓ ይሻገራሉ» እያላችሁ ታሙናላችሁ አሉ፡፡

ወገኞች ናችሁ እንዴው፡፡ የጨዋታውን ዓይነት፣ የግቡን ልዩነት፣ የታክቲክ እና የቴክኒኩን ነገር ተውት ይቅር ግዴለም፡፡ የተጨዋቾቹን ዝና እና ታዋቂነት፣ የሚያሳዩትን ምትሐት ተውት አይነሣ ግዴለም፡፡ አሁን እኛ ሀገር በእግር የሚመታ ኳስ እንጂ እግር ኳስ አለ ይባላል? እንኳን የአፍሪካ እግር ኳስ ፌዴሬሽንን ከመሠረቱት ሦስት ሀገሮች አንዱ ልንመስል

እግር ኳስ ከአውሮፕላን ተወርውሮ የነጠረባት ሀገር እንመስላለን? ለመሆኑ እኛ ሀገር ስለ ተጨዋቹ እና ስለ ጨዋታው ከሚነገረው በላይ ስለ ቡድኖቹ ሽኩቻ እና ስለ ፌዴሬሽኑ ውዝግብ የሚነገረው አይበልጥም?

«ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከንቢያው ቁጢጥ» ሲባል አልሰማችሁም፡፡ ኳሱ መከራ እያየ፣ እኛ ማን ሥልጣን ላይ ይውጣ የሚለው ነው የሚያወዛግበን፡፡ መጀመርያ ኳሱ ሲኖር እኮ ነው ፌዴሬሽን እና የፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት የሚያስፈልገው፡፡ «ጥርስ የላት ትወቀር አማራት» አሉ፡፡ የኢትዮጵያን እግር ኳስ አሁን ካለበት ደረጃ ለማድረስ እኮ ግዴለሽነት እና ክፋት እንጂ ፌዴሬሽን አያስፈልግም ነበር፡፡

ስንት ዋንጫ እየሳሙ፣ስንት ውጤት እያመጡ፣ ስንት ታሪክ እየሠሩ ዓለምን የሚያናውጡ ቡድኖች ያሏቸው ፌዴሬሽኖች ሳይወዛገቡ እኛ ፊፋ ድረስ ሄደን እንካሰሳለን፡፡ «ቅቤ አንጣሪዋ ተቀምጣ ጎመን ቀንጣሿን ምች መታት» አሉ ወይዘሮ ዘርፌ፡፡ ፊፋስ ቢሆን «ማስረጃችሁን አምጡ፣ የፊፋ ሕግ አልተከበረም፣ መተዳደርያው ተጥሷል» እያለ ያለ ደረጃችን ደረጃ ከሚሰጠን መጀመርያ እስኪ ስታዲዮም ገብቼ ስትጫወቱ ልያችሁ፣ እስኪ ቡድኖቻችሁ እንዴት እንደተደራጁ አሳዩኝ፣ እስኪ ስንት ስታዲዮም ገነባችሁ፣ እስኪ ቢሮአችሁ እንዴት እንደ ተደራጀ ልይ» ቢል ኖሮ ውዝግቡ ይህንን ያህል ዘመን መች ይፈጅ ነበር፡፡ በሌለ ነገር እኮ ነው መከራ የምናየው፡፡

«ሥጋ ቁጠር ቢሉት ጣፊያ አንድ አለ» የተባለው ደረሰና ለምንድን ነው ኳሳችሁ የማያድገው? ተብለው ሲጠየቁ «ሕዝቡ የአውሮፓ እግር ኳስ ስለሚያይ ከስታዲዮም ስለ ጠፋ ነው፡፡ ስለዚህም የአውሮፓ ጨዋታ የማይታይበትን መንገድ እንፈልጋለን» አሉ አሉ፡፡ ለሠራነው ስሕተት ራሳችንን ተጠያቂ የምናደርግበት፣ ይህ ነገር ሊከሰት የቻለው ምን ስሕተት ስለሠራሁ ነው? ብለን የምንጠይቅበት ዘመን መቼ ይሆን የሚመጣው፡፡ እንዴው እድሜ ልካችንን ለችግራችን ሁሉ ውጫዊ ምክንያት እንደፈለግን ልንኖር ነው?

የጤፍ ነጋዴ ፓስታ በብዛት ስለተመረተ ገበያ ጠፋብኝ ብሎ ያውቃል? የቢራ ፋብሪካ እዚህም እዚያም ቢከፈት የሀገሬ ጠጅ ቤቶች መች ንቅንቅ አሉ፡፡ እነ ገደል ግቡ፣ እነ ውስኪ ለምኔ፣ ጠጅ ቤት ይሄው ጢም እንዳሉ ናቸው፡፡ ሌላውን ተውት የሀገሬ ሰው በፊልሞቹ ላይ የሚሰጠውን ያንን ሁሉ ትችት እየሰማ እንኳን፣ «ሰው በዐቅሙ ነው የሚጸድቀው» ብሎ ከውጭ ሀገር ፊልሞች እኩል እንዲያውም በላይ፣ የሀገሩን ፊልም እያየ አይደለም እንዴ?

ለመሆኑ ሕዝቡ የአውሮፓ እግር ኳስን ለምን እንደሚወድደው ያውቁታል፡፡ የጨዋታውን ጣዕም እና የቡድኖቹን የብቃት ደረጃ አላነሣውም፡፡ እንዳላስጎመጃቸው ብዬ፡፡ ኸረ ሌላ ሌላውን፡፡ ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለ አንድ ቡድን፣ ተጨዋቾች፣ የቡድን አሰላለፍ፣ የአሠልጣኞች ሁኔታ፣ የክለብ ባለቤቶች እንቅስቃሴ፣ የገቢ እና ወጭ ጉዳይ ለማውራት መረጃ ይገኛል? የተጠናከረ ዌብ ሳይት ያለው ቡድን አለ? የተደራጀ ሙዝየም ያለው ቡድን አለ? የአንድ ተጨዋች ታሪክ፣ ያገባቸው ግቦች፣ መቼ እንዳገባ፣ የት ላይ እንዳገባ? በመዝገብ ይያዛል? በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ በዛሬው ዕለት የዛሬ ሠላሳ ዓመት ምን ተደርጓል? ተብሎ ቢጠየቅ መልስ ያለው ክለብ እና ፌዴሬሽን አለን?

በሐሜት ከሚነገረው በዘለለ የተጠናቀረ፣ሁሉም ሊያውቀው የሚችል እና የሰሚውን ልቡና ሊያረካ የሚችል መረጃ አለ? ስለ አውሮፓ ቡድኖች፣ ፌዴሬሽኖች፣ ተጨዋቾች፣ አሠልጣኞች እኮ ከሚፈለገው በላይ የመረጃ ጎረፍ ይፈስሳል፡፡ ምን በሉ፣ ምን ጠጡ፣ የት ዋሉ፣ የጫማ ቁጥራቸው ስንት ነው፣ የቤተሰባቸው ሁኔታ እንዴት ነው ተብሎ ቢጠየቅ፣

በደቂቃ መረጃ ማግኘት ይቻላል፡፡ «የማያውቁት ሀገር አይናፍቅም» ሲባል አልሰማችሁም፣ ታድያ የማናውቀውን እግር ኳሳችንን እንዴት እንውደደው፡፡

አንዳንድ ባለሥልጣናት እኮ መረጃ መስጠት የሚመስላቸው ጋዜጠኛ ጠርተው የሚያስቡትን እና የሚፈልጉትን መናገር ነው፡፡ ይሄኮ ሃሳብን መግለጥ እንጂ መረጃ መስጠት አይደለም፡፡ መረጃ መስጠት ማለትማ መረጃ መሰብሰብ፣ ሊገኝ በሚችልበት ቦታ እና መንገድ ማስቀመጥ፣ በልዩ ልዩ የመረጃ ማስተላለፊያ መንገዶች ወደ ተጠቃሚዎቹ ማድረስ ነው፡፡ ደግሞምኮ እኛ የምንፈልገውን እና የምንወደውን ብቻ እንዲታወቅ የምናደርግ ከሆነ መረጃ መስጠት ሳይሆን ዕንቁልልጮሽ ነው የሚሆነው፡፡

ደግሞስ መረጃ ቢኖርስ ነጻነቱ የት ይገኛል፡፡ የአውሮፓ እግር ኳስን እኮ ብንፈልግ ስለ ተጨዋቹ ፣ብንፈልግ ስለ አሠልጣኙ፣ ብንፈልግ ስለ ክለቡ ባለቤት፣ ብንፈልግ ስለ ቡድኑ ገቢ እና ወጭ፣ ብንፈልግ ስለ ፌዴሬሽኑ የዕለት ውሎ ስንተች፣ ስንተነትን፣ ስንከራከር ብንወል ማን ተቆጭ አለን፡፡ ጋዜጠኞቹ እንኳን ዘና ብለው መዘገብ የሚችሉት የሀገሪቱን ዘገባ ጨርሰው ሜዲትራንያንን ሲሻገሩ ነው፡፡ የሚቆጣቸው ፌዴሬሽን፣ የሚያስፈራራቸው ባለሀብት፣ የሚሰድባቸው ደጋፊ፣ የሚዝትባቸው ክለብ የለ፡፡ እኛ ሀገርኮ ኳሱ ለትንታኔ አይመች፣ የኳሱም ሰዎች ለትንታኔ አይመቹ፡፡

ስለ ጊዮርጊስ ከተቸህ «ፀረ ጊዮርጊስ» ትባልና መቆሚያ መቀመጫ ታጣለህ፡፡ ስለ ቡና ከተናገርክ «ፀረ ቡና» ትባልና ምስህ ዱላ ይሆናል፡፡ እንኳንስ ስትተቸው ስታመሰግነው እንኳን «ሦስት ጊዜ ምስጋና አንዱ ለነገር ነው»ብሎ በሚጠራጠርህ ሰው መካከል ሆነህ እንዴት ነው ስለ ሀገራችን ክለቦች የምትጨነቀውና የምትደግፈው፡፡ «ድጋፍ ተቃውሞን ካልፈቀደ፣ እንጀራ እርሾን ካልወሰደ» ምን ያደርጉልናል፡፡

ሁለት የአውሮፓ ኃያላን ቡድኖች ከመጋጠማቸው በፊት እዚህ አዲስ አበባ ሆነን አሰላለፋቸውን እናውቀዋለን፡፡ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ማን ለማን እንደተሰለፈ በግልጽ ይታወቃል? በዛሬ ጨዋታ ለአርሴናል የተሰለፈው በቀጣዩ ጨዋታ አሠልጣኙ እንኳን ሳይሰማ ለማንቸስተር እየተሰለፈ መከራ አየንኮ፡፡ እዚህ አዲስ አበባ ሆነን የተጨዋቾች የዝውውር መስኮት ሲከፈት ማን ወደ የትኛው ቡድን ሊሄድ እንደሚችል በግምትም፣ በፍንጭም፣ በመረጃም እንናገራለን፡፡ መሄድ አለበት፣ የለበትም እያልን እንከራከራለን፡፡

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም መስክ ማን ወደ የትኛው ቡድን ለመቀላቀል እንዳሰበ፣ እነማን ማንን እንዳስፈረሙ፣ ማን ከነማን ጋር ለመፈራረም ውስጥ ውስጡን እየመከረ እንደሆነ ማወቅ፣ ካወቁስ በኋላ ሃሳብ መስጠት ይቻላል? ይኼው ስንቶቹ መቼ እንደ ተነጋገሩና፣ መቼ ሃሳባቸውን እንደቀየሩ ሳናውቀው ለሌላ ቡድን ሲጫወቱ አገኘናቸው አይደል እንዴ፡፡ አንዳንዶቹም ጭራሽ የነበሩበትን ቡድን ለቅቀው፣ እንዲያውም አብረዋቸው ከተጫወቱት ጋር ተጋጭተው፣ የሌላ ቡድን አሠልጣኝ ሲሆኑ ያየናቸው በድንገት ነው፡፡ የአውሮፓ ኳስ ቢሆን ኖሮ ቢያንስ ለመገመት በቻልን፣ ከተቻለም ፍንጭ ባገኘን ነበር፡

ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ማንንም ሳይፈሩና ሳይሰቀቁ እንደ ልብ ሊያወሩበት እና ሊከራከሩበት የሚችሉት ጉዳይ የአውሮፓ ኳስ መሆኑን ታውቃላችሁ፡፡ ብንደግፍ፣ ብንቃወም፣ የደገፍነውን ቡድን ዓርማ ብናውለበልብ፣ ማልያውን

ብንለብስ፤ ስለ እያንዳንዱ ነገር እያነሳን ብንፈልጥ ብንቆርጥ ማን ተቆጭ አለን፡፡ እና እንደዚህ በነጻነት የሚወራ ጉዳይ ከየት ይገኛል ጃል፡፡ አቦ ተውና፡፡

*ደጋፊም ተቃዋሚም መሆን እዚህ ሀገር ዕዳ ነው፡፡ የመንግሥት ደጋፊ ነኝ ካልክ ገልማጭህ ብዙ ነው፡፡ ተቃዋሚም ነኝ ካልክ የሚያጉረጠርጥብህ በዚያው ልክ ነው፡፡ የአንዱን ማልያ መልበስ ቀርቶ ልትገዛ ስታገላብጥ ከታየህ መከራ ነው፡፡ እንኳንስ ስለ ተጨዋቾቹ አንሥቶ ለመነጋገር እና ለመተቸት ይቅር እና በቴሌቭዥን ሲቀርቡ እንኳን እነርሱን ትኩር ብለህ ካየህ አንዱ «ምን ታፈጣለህ?» ይልሃል ሌላው ደግሞ «ምነው ሙድ ያዝኸሳ» ብሎ ይተርብሃል፡፡ በአውሮፓ ኳስ ግን፣ ብትደግፉ ተለጣፊ፣ ብትቃወሙ አደናቃፊ የሚላችሁ የለም፡፡*

*ደግሞስ ደጋፊ እና ተቃዋሚ በአንድ አዳራሽ የሚሰበሰብበት ይህንን የመሰለ ነገር ከየት ይገኛል፡፡ ከመተራረብ፣ ከመተቻቸት ያለፈ ሌላ ነገር የለ፡፡ ርግጥ ነው እግር ኳሱን በፖለቲካው መንገድ ለማስኬድ የሚፈልጉት አንዳንዶች ብጥብጥ እያነሡ ተቸግረን ነበር፡፡ አሁን ግን ጋብ ብለዋል፡፡ በኳስኮ በዚህኛው ጨዋታ ካሸነፋችሁ እየጨፈራችሁ ቤታችሁ ትገባላችሁ፣ አንድ ሳምንት ትተነትናላችሁ፣ ከዚያ በኋላ ለቀጣዩ ጨዋታ መዘጋጀት ነው፡፡ ትናንት አሸነፋችሁ ማለት ነገም ታሸንፋላችሁ ማለት አይደለም፡፡ ብትሸነፉም ለጊዜው ትናደዱና እንደ ገና ለማሸነፍ መሥራት ነው፡፡ ቴክኒክ እና ታክቲክ መቀየር፣ ሥልጠናውን ማጠናከር ብቻ ነው፡፡ ትናንት ለምን እንዲህ ሆነ ብሎ ሙዝዝ ማለት የለም፡፡ ሌላ ሌላውንማ ሲያሸንፍና ሲሸነፍ ምን እንደሚመስል አየነውኮ፡፡*

*ኧረ ለመሆኑ የአውሮፓ ኳስ ባይኖር ስለ ምን እናወራ ነበር፡፡ ሰው ቋንቋ ኖሮት እንዴት ሳያወራ ይኖራል? ምሳ ሲበላ፣ ሻሂ ሲጠጣ፣ ቡና ሲፈላ፣ በታክሲ እና በአውቶቡስ ሲኬድ ታድያ ምን ይወራ? ሁሉም ነገር ፖለቲካ በሆነበት ጊዜ ታድያ ምን እናውራ፡፡ ጤፍ ተወደደ ፖለቲካ ነው፣ጤፍ ረከሰም ፖለቲካ ነው፡፡ ሀገራችን አደገች ማለት ፖለቲካ ነው፣ ሀገራችን ወደ ኋላ ቀረች ማለትም ፖለቲካ ነው፡፡ እገሌ ተሳስቷል ማለት ፖለቲካ ነው፣ልክ ነው ብሎ መናገርም ፖለቲካ ነው፡፡ ታድያ ምን እንበል?*

*ምን እባል ይሆን? ማን ሰምቶኝ ይሆን? ተብሎ በሚወራበት በዚህ ጊዜ እንደ ልብ የሚወራ ነገር ማግኘት ቀላል ይመቻል እንዴ! እኛ ተመልካቾች በሂደት አንድ የጥናት ውጤት አግኝተናል፡፡ ቢያንስ ስለ አውሮፓ እግር ኳስ ስታወራ የትኛውም የፓርቲ አባል እንደማይቆጣ፡፡ አውሮፓውያን ኢትዮጵያውያን ቢሆኑ ኖሮኮ በስፔን ቡድን ላይ ትችት ስትሰነዝር የስፔን ኤምባሲ፣ በእንግሊዝ ቡድን ላይ ስትወርድበት የእንግሊዝ ኤምባሲ፣ የጣልያንን ቡድን ስታነሣ ጣልያን ኤምባሲ አያስቀምጡንም ነበር፡፡ አቦ እንኳን ኢትዮጵያውያን አልሆናችሁ፤ ተመችታችሁናል፡፡*

## [የመፍትሔ ሃሳቦች ክፍል 2]

**8 እኔም አጥፍቻለሁ ብሎ መጀመር**

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለደረሰባት ፈተና ተጠያቂ የማይሆን የቤተ ክርስቲያን ልጅ የለም፡፡ ምናልባት የጥፋቱ ደረጃ ይለያይ ካልሆነ በቀር፡፡ አንዳንዶቹ በቀጥታ ሌሎቹ በተዘዋዋሪ፤ አንዳንዶቹ ስሕተት በመፈጸም ሌሎቹ ስሕተት ሲፈጸም ዝም በማለት፤ አንዳንዶቹ እኔ የለሁበትም በማለት፣ ሌሎቹ እኔን ካልነካኝ ብለን፤ አንዳንዶቹ ለዕለት ጥቅም፣ ሌሎቹ ለወገንተኛነት፤ ሲባል ለፈጸምናቸው ስሕተቶች መጸጸት አለብን፡፡ ስሕተት መሥራትም ሆነ ሲሠራ በቸልታ ማየት ሁለቱም ያስጠይቃል፡፡ በሉቃስ 10 በተጻፈው የሩኅሩኁ ሳምራዊ ታሪክ ላይ ካህኑ እና ሌዋዊው የተወቀሱት «አይተው ገለል ብለው በማለፋቸው» ነው፡፡

አሁን እንደሚታየው ነገሮችን በጥቂት ሰዎች ላይ ብቻ በመጠቆም እጅን ከደሙ ለመታጠብ መሞከር መፍትሔ ሳይሆን ችግር ይወልዳል፡፡ አንዳንዶቻችንም በአጋጣሚ ከሥልጣኑ ቦታ ዘወር በማለታችን የተነሣ የማንጠየቅ ይመስለናል፡፡ ዘወር ብሎ ሲታይ ግን እኛም በቦታው ሳለን እንዲሁ ነበርን፡፡ ልዩነቱ የአንዳንዶች ተሰምቷል የአንዳንዶች አልተሰማም፡፡ የአንዳንዶች ብሏል፣ የአንዳንዶች አልባሰም፡፡ እናም በመጀመርያ ራሳችንን ነጻ እናውጣ፡፡ በንስሐ፣ በመጸጸት፣ ለተሻለም ተግባር በመነሣት፡፡

ዛሬ በቤተ ክህነቱ ለሚታየው ነገር በቤተ ክህነቱ ውስጥ በአንድም በሌላም ያለፉት ሁሉ ይጠየቁበታል፡፡ በዕንቁላሉ ጊዜ ቀጥተውት ቢሆን ኖሮ ይህ ሁሉ ባልመጣ ነበር፡፡ ምእመናንም ጠለቅ ብለን ቤተ ክርስቲ ያናችንን ከማየት ይልቅ ተሳልሞ በመሄድ ብቻ ስለተውናት ዛሬ ተጠያቂነት የሌለበት አሠራር እንዲሰፍን አደረግን፡፡ ታቦቱንም የሀገሬ ታቦት፣ ጳጳሱንም የሀገሬ ጳጳስ፣ ቄሱንም የሀገሬ ቄስ፣ እያልን ወንዛ ወንዙን ከመሄድ አልፈን «የሃይማኖቴ፣ የቤተ ክርስቲያኔ» ስለማንል ይህ ሁሉ ነገር መጣ፡፡ ቤተ ክህነቱን ርቀነው «እንደ ፍጥርጥሩ ይሁን» ብለን ስለተውነው የሚገባቸው ቀሩና የማይገባቸው ገቡበት፡፡ እናም ከተጠያቂነት አናመልጥም፡፡

ሰባክያን እና መዘምራንም ብንሆን ለዕለት እንጀራችን እና ክብራችን እንጂ ለቤተ ክርስቲያናችን ተቆረቁረን የድርሻችንን ስላልተወጣን፤ ዓይተን እንዳላየን፣ ሰምተን እንዳልሰማን በማለፋችን ይህ ሁሉ መጣ፡፡

አሁን «እኔም አለሁበት» ብለን መነሣት አለብን፡፡ ችግሩን ለመቅረፍ ከራሳችን እንጀምር፡፡

**9 ማኅበራት የሚጠበቅባቸውን ይሥሩ**

በቤተ ክርስቲያን ሥር ነን ብለው የተቋቋሙ ልዩ ልዩ ማኅበራት አሉ፡፡ ለጉዞ፣ ነዳያንን ለማብላት፣ ገዳማትን ለመርዳት፣ ለጽዋ፣ ለስብከተ ወንጌል ወዘተ እየተባለ አያሌ ማኅበራት ተቋቁመዋል፡፡ እነዚህ ማኅበራት ድምፃቸውን ማሰማት ያለባቸው ጊዜ አሁን ነው፡፡ ሥርዓት ሲጠፋ፣ በቤተ ክርስቲያን መድረክ ኑፋቄ ሲሰበክ፣ የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ያልሆነ ነገር በቤተ ክርስቲያን ሲሠራ፣ የጥፋት ርኩሰት በተቀደሰው ሥፍራ ሲቆም፣ የሲኖዶሱን ሥልጣን መበለቶች ሲረከቡት ዝም ካሉ መቼ ሊናገሩ ነው፡፡

መጽሔቶቻቸው እና ጋዜጦቻቸው «አቡነ እገሌ ዐረፉ፣ ይህ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ፣ ኢየሱስ ከናዝሬት ወደ ገሊላ ሄደ» ለማለት ከሆነ የተቋቋሙት ይህንን የሚሠራ ስላለ ቢያስረክቡት መልካም ነው፡፡ እኔ ጉዞ ካደረግኩ፣ ነዳያንን ካበላሁ፣ ዝክር ከዘከርኩ ሌላው አያገባኝም የሚሉ ማኅበራትም ካሉ ሁሉም የሚኖረው ይህች ቤተ ክርስቲያን ስትኖር መሆኑን ማወቅ አለባቸው፡፡

በተለይም ለቤተ ክህነቱ ቅርብ የሆኑ፣ ብዙ የሰው ኃይል ያላቸው፣ ቅዱስ ሲኖዶስም ኃላፊነት የሰጣቸው ማኅበራት በዝምታቸው ቤተ ክርስቲያንን መጉዳት የለባቸውም፡፡ ችግሩን ለመቅረፍ መንግሥት ምን ማድረግ እንዳለበት፣ አባቶች ምን ማድረግ እንዳለባቸው፣ የቤተ ክህነቱ አገልጋዮች ምን ማድረግ እንዳ ለባቸው፣ ምእመናን ምን ማድረግ እንዳለባቸው አቅጣጫ መስጠት ይገባቸዋል፡፡ አሁን ሰዓቱ ስለ ቤተ ክርስቲያን ህልውና እንጂ ስለራሳቸው ህልውና የሚያስቡበት ጊዜ አይደለም፡፡

**10 ሰባክያን እና መዘምራን የድርሻቸውን መወጣት አለባቸው**

ሕዝቡ ወንጌል ያስተምራሉ፣ወንጌል ይዘምራሉ ብሎ ቦታ የሰጠን አገልጋዮች ለካሴት ሽያጭ እና ለመድረክ ታይታ መሯሯጣችንን ትተን ለቤተ ክርስቲያን መቆም አለብን፡፡ ሆዴ ይሙላ ደረቴ ይቅላ ብለን ነገረ ቤተ ክርስቲያንን ትተን

ለራሳችን ብንሯሯጥ ታሪክም ፈጣሪም ይጠይቀናል፡፡ ስምም፣ ክብርም፣ ገንዘብም ያገኘነው በዚህች ቤተ ክርስቲያን መሆኑን መርሳት የለብንም፡፡

በመጀመርያ ራሳችንን ከችግሩ ነጻ እናድርግ፡፡ ከችግር ፈጣሪዎቹ ጋር መሰለፋችንን እናቁም፡፡ ቀጥሎ ደግሞ የሚጠበቅብንን እናድርግ፡፡ አንዳንዶቻችን የአስተሳሰብ ችሎታችን፣ የችግር አረዳድ ዐቅማችን እና የኃላፊነት ስሜታችን የስማችንን ያህል አይደለም፡፡ ስማችን እንደ 12ኛ ክፍል፣ ተግባራችን እንደ ሦስተኛ ክፍል ነው፡፡ የማንበብ፣ የመረዳት፣ የመገምገም፣ የማጥናትና ወስኖ የመነሣት ችግሮች አሉብን፡፡
የሚጮኽ ሞንታርቦ፣ የደመቀ ጉባኤ፣ እልልታ የበዛበት መዝሙር የአገልግሎታችን መጨረሻ ሆኗል፡፡ የቤተ ክርስቲያንን የትናንት እና የዛሬ ሁኔታ ሰከን ብለን አንገመግምም፡፡
በየጊዜው በኢትዮጵያም ሆነ በአሜሪካ «የአገልጋይ ኅብረት» እየተባለ ሰዎች ይሰባሰባሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከመተማማት፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ አብሮ ከመብላት በቀር ያስገኘነው ውጤት ግን የለም፡፡ እንዴው ለመሆኑ ግን ተጠራቀምን ወይስ ተሰባሰብን? መሰባሰብኮ የሃሳብ፣ የእምነት እና የግብ አንድነትን ይፈልጋል፡፡ መጠራቀም ግን እንደ ነዳይ ቋጠሮ ከየቦታው መጥቶ በአንድ ቦታ መቀመጥን ብቻ ይፈልጋል፡፡
አጀንዳችንስ ምንድን ነው? በመዝሙር ስለመረዳዳት፣ በመድረክ ስለመረዳዳት፣ አንዱ ሌላውን ስለማጀብ፣ ከዚህ አያልፍም፡፡ ስለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ በጥናት በተመረኮዘ ሁኔታ ተነጋግረን እናውቃለን? ወስነንስ እናውቃለን? ለውሳኔያችንስ ተገዝተን እናውቃለን?

ሕዝቡ እየበሰለ እኛ ባለንበት እየረገጥን ከሆነ ቀድሞን ይሄዳል፡፡ ተቀምጦ ስለሰማን የቀደምነው እንዳይ መስለን፡፡ ስለ ክብረ ወንጌል፣ ስለ ክብረ ቤተ ክርስቲያን ብሎ እንጂ ከምናውቀው በላይ ያውቃል፣ ከምንነግረው በላይም ይሰማል፤ ደግሞም ይታዘባል፡፡

ስለዚህም በእውነት የቤተ ክርስቲያን ልጆች ከሆንን የልጅነት ስሜታችንን ትተን ለቤተ ክርስቲያን እንነሣ፤ ለቤተ ክርስቲያን ጠበቃ Apologists የምንሆንበት ዘመን ዛሬ ነው፡፡
ሰዎቹ ለራሳቸው ሐውልት መሥራታቸው ሳያንስ «ሐውልት በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የተደገፈ ነው» ብለው ሲያስተምሩ፣ በየጋዜጣው ሲጽፉ እና መጽሐፍ ሲበትኑ ዝም ነው ያልነው፡፡ ጥብቅናችን የት ላይ ነው፡፡ ተሐድሶዎች ገድላቱን እና ቅዳሴያቱን ሲያብጠለጥሉ ዝም አልን፣ የጥፋት ርኩሰት በተቀደሰው ሥፍራ ስናይ ዝም አልን፤ ታድያ ድርሻችን ምንድን ነው፡፡ ናቡከደነፆር ሕልም አይቶ ሲጠፋው መተተኞቹን፣ አስማተኞቹን እና ኮከብ ቆጣሪዎቹን ሰብስቦ «ሕልሙንም ትርጉሙንም አምጡ» አላቸው፡፡ እነርሱ ግን አልቻሉም፡፡ በዚህ ጊዜ ያላቸውን መተርጉማን ሲነግሩን «ፈረስ አይደላችሁ አልጋልባችሁ፣ በሬ አይደላችሁ አላርስባችሁ፣ ለዚህ ጊዜ ካልሆናችሁኝ ምን ታደርጉልኛላችሁ» ብሎ አስወጣቸው ይላሉ፡፡ የኛም ዕጣ ፈንታ ይኼው እንዳይሆን፡፡

**11 ችግሩን ከውስጥ መፍታት**
አንዳንዶች የተወሰኑ ሰዎች ተጋድለው ችግሩን እንዲፈቱ ይፈልጋሉ፡፡ እነርሱ ግን ችግሩ ከተፈታ በኋላ ተጠርተው ቦታውን መያዝ ያምራቸዋል፡፡ አንዳንድ ከቤተ ክርስቲያን መሥመር ያፈነገጡ ሰዎች «ችግሩ ሲስተካከል እንመለሳለን» ይላሉ፡፡ ጥያቄው ማን ሲያስተካክለው? የሚል ነው፡፡ ችግሩ ሲስተካከልማ እንኳን ክርስቲያኖች ሙስሊሞችስ ይመጡ የለም ወይ? አሁን ቤተ ክርስቲያን ተጫውቶ ዋንጫ የሚያመጣ እንጂ ዙርያ ከብቦ የሚያጨበጭብ ተመልካች አትፈልግም፡፡
አሁን በቤተ ክህነቱ የምናየው ችግር እንዲፈታ ከፈለግን የሥጋ ዖራችን ያመጣብንን ልዩነት ትተን አንድ ሆነን እንሰለፍ፡፡ ከውጭ ሳይሆን ከውስጥ እንጋደል፡፡ መጀመርያ ቤተኛ እንሁንና የልጅነት መብታችንን እንጠይቅ፡፡ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በውስጧ ያልነበሩ፣ አጋጣሚዎችን ተጠቅመው ብቅ የሚሉ ሰዎች ጤና ሰጥተዋት አያውቁም፡፡
ለቤተ ክርስቲያን የምንቆረቆር ከሆነ «ገለልተኛ» «ስደተኛ» «መጻተኛ» እያልን የምናዜመውን አራተኛ እና አምስተኛ ዜማ ትተን፣ ያገባናል ብለን ቤታችንን እንረከብ፡፡ ከውጭ ሆነን ችግሩ እንዲፈታ ከምንመኝ ይልቅ ወደ ውስጥ ገብተን ከሚጋደሉት ጋር አብረን ሆነን እንጋደል፡፡
**12 ሊቃውንት ድምፃቸው ይሰማ**
ትምህርተ ሃይማኖትን፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን፣ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን እና ሥነ ምግባርን የሚመለከቱ ጉዳዮች እየመጡ ነው፡፡ ችግሮቹ ዓይን አውጥተው ራሳቸው እየተናገሩ ነው፡፡ እንዲህ ባለ ጊዜ የሃይማኖት ጦር ሰብቀው፣

የዕውቀት ዘገር ነቅንቀው፣ የጥብዐት ዝናር ታጥቀው ብቅ የሚሉ ሊቃውንት ያስፈልጋሉ፡፡ አሁን ጥያቄው «እውነት ወይንም ውሸት በል» የሚል ነው፡፡ ምእመናን መልሱን ይፈልጋሉ፡፡ ሊቃውንት ደግሞ መልሱን መናገር አለባቸው፡፡ በተለይም ከአቡነ ቴዎፍሎስ እስከ አሁን ያለው ታሪክ ግልጽ መልስ ይጠይቃል፡፡ አቡነ ቴዎፍሎስ እንዴት ተገደሉ? በዚያ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? ቅዱስ ሲኖዶስ በወቅቱ ምን አለ? አቡነ መርቆሬዎስ እንዴት ወረዱ? ቅዱስ ሲኖዶስ እንዴት ወሰነ? ምክንያቱ ምን ነበር? አቡነ ጳውሎስ እንዴት ተሾሙ? አመራረጡ እንዴት ነበር? መልስ የሚፈልጉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እዚህም እዚያም ከሚረጩ ነገሮች ያለፈ ግልጽ እና እውነት ነገር የመነገሪያ ጊዜው አሁን ነው፡፡ በተለይም ሁለቱ ፓትር ያርኮች በሕይወት እያሉ፣ ራሳቸው መልስ ለመስጠት በሚችሉበት ጊዜ ሊቃውንቱ መናገር፣ መጻፍ አለባቸው፡፡ በሞት ከተቀደምን ሐሜት ይሆንብናል፡፡

በሌላም በኩል በምንኩስና፣ በክህነት፣ በጵጵስና አሰጣጥ፣ በቅዱስ ሲኖዶስ አሠራር፣ በቤተ ክህነቱ መንፈሳዊ ጉዞ ወዘተ የሚታዩትን ነገሮች ከቅዱሳት መጻሕፍት አንፃር አስተያይቶ መናገር፣ ማሳየት እና ማረም ከእናንተ ይጠበቃል፡፡

**13 የሰበካ ጉባኤ አመራሮች የድርሻቸውን ይወጡ**

የየአጥቢያው ገንዘብ ሲመዘበር፣ ተገቢ ላልሆነ ነገር ሲውል፣ ምስኪን ካህናት ደመወዝ አልበቃ ብሏቸው ልጆቻቸውን የሚያበሉት እና የሚያስተምሩበት ሲያጡ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጥይት የማይበሳው መኪና ለመግዛት ሚሊዮኖች ከየአጥቢያው ሲዋጣ የአጥቢያ ሰበካ ጉባኤ አባላት ዝም ማለት የለባቸውም፡፡

ቢያንስ ሦስት ነገሮች ማድረግ አለባቸው፡፡

የመጀመርያው ለምን ብለው መጠየቅ አለባቸው፡፡ በስብሰባቸው ያልወሰኑት ነገር ሲፈጸም ምንም ማድረግ አንችልም ብለው መተው የለባቸውም፡፡ ሁለተኛም መረጃ መያዝ አለባቸው ነገ በምርመራ ሊጣራ ይችላልና ተገቢውን ዶክመንት መያዝ ያስፈልጋል፡፡ እየባሰ ሲመጣ ደግሞ ለምእመናኑ፣ ለፀረ ሙስና ኮሚሽን እና ለሚመለከታቸው አካላት መግለጽ አለባቸው፡፡

እስኪ የሙዳየ ምጽዋቱን ሳጥን ይቁጠሩት? ስንት ሙዳየ ምጽዋት የደብሩ ስንትስ የግለሰቦች አለ? እስኪ የሕንፃውን አከረያየት እና የኪራይ መጠን ይጠይቁ? እስኪ የንዋያተ ቅድሳቱን መጠን እና አድራሻ ይመርምሩ? የቻሉትን ያስተካክሉ ያልቻሉትን ግን አቤት ይበሉ፡፡ ዝም ብሎ መቀመጥ ግን በስሕተቱ መስማማት ነው፡፡

**14 ብጹአን አበው ራሳቸውን ቢያዩ**

አባግዐ ቤተ ክርስቶስን እንዲያሰማሩ የተሾሙት አበው ምን ያህል የተሠማሩበትን እንደፈጸሙ ራሳቸውን ቢያዩት፡፡ ጥፋቱን ሁሉ በአንድ ሰው ላይ አላክኮ መቀመጥ ራስን ብቻ ነው የሚያሳምነው፡፡ ለመሆኑ የየራሱን ሐውልት በልዩ ልዩ ቅርጽ ያላቆመ አለ? ችግሩን መፍታት ለምን ከራስ አይጀመርም፡፡ ቀኖና ያላፈረሰ አለ? የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ሆነው አሜሪካ ሲኖዶስ የማያውቃት፣ ሲኖዶስንም የማታውቅ የየራሳቸው የግል ቤተ ክርስቲያን ያላቸው ጳጳሳት የሉም? በሰው ሀገረ ስብከት ገብተው ክህነት የሚሰጡ አባቶች የሉም? በሰው ሀገረ ስብከት ገብተው ቤተ ክርስቲያን የሚባርኩ አባቶች የሉም? የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ንብረት ነው እየተባለ የሚታወቀው ሁሉ በርግጥ የቤተ ክርስቲያንዋ ነው? የመኳንንት እና የመበለቶች እጅ የለበትም? ታድያ ማን ማንን ያማል? ማንስ ማንን ይወቅሳል? ማንስ በማን ይፈርዳል?

የዘመድ አሠራር በየሀገረ ስብከቱ የለም? ለመሆኑ ከወንዛችን ሰው ውጭ እናምናለን? እስኪ ሾፌሮቻችን ይታዩ? በየሀገረ ስብከቱ ብክነት የለም? በየሠፈሩ የቤት ሐውልት አላቆምንም? ከጥቂት አበው በስተቀር ከዚህ ነጻ የሚሆን ይገኛል? ታድያ ራሳችንን ሳናጸዳ እንዴት ሰውን ለመውቀስ ሞራል ይኖረናል? ለዝምታችንም አንዱ ምክንያት ይኼው ነው፡፡

እስኪ ጽዳቱን ከቤታችን እንጀምረው፡፡ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ልናየው የምንፈልገውን ዓይነት አሠራር በሀገረ ስብከታችን፣ በኮሌጆቻችን እና በመምሪያዎቻችን እንጀምረው፡፡ ለመሆኑ በየሀገረ ስብከቱ ይሂዱልን የሚባሉ አበው ለምን እየበከቱ መጡ? ዘመኑስ ይምጡልን ከሚለው ይሂዱልን ወደሚለው ለምን ተቀየረ?

ምንም እንኳን እናንተን ለመውቀስ ሥልጣን ባይኖረንም፣ ይቅር በሉኝና ለቤተ ክርስቲያን ሲባል መጀመርያ በየቤቱ ያለው ችግር ይፈታ፡፡ እያንዳንዱ አካባቢውን ቢያጸዳ ከተማዋ ትጸዳለች ይባል የለ፡፡ ከዚያ በአንድነት ሆኖ የዋናውን ቤት ችግር መፍታት ይቻላል፡፡

**15 የመዝሙር ቤቶች የድርሻቸውን ይወጡ**

ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ ከሙዚቃ ቤቶች ይልቅ የመዝሙር ቤቶች በዝተዋል፡፡ ታክሲዎችን እና ካፍቴርያዎችን ያጨናነቁት ዘፈኖች ቀንሰዋል፡፡ በአንድ በኩል መልካም ውጤት ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ መሥመሩን ከሳተ

አደገኛ ነው፡፡ መዝሙሮቹን እና ስብከቶቹን መርምሮ ማሳለፍ እና ማረም የቤተ ክህነቱ ድርሻ ነበር፡፡ ነገር ግን ከቁም ነገር አልጣፈውም፡፡ እኛም የተከፈተ ቤት አገኘንና እንደ ልብ ተዘልለን ተቀመጥን፡፡ የሚገባንን ሳይሆን የምንፈልገውን እየሠራን፡፡ የሚያጸድቀንን ሳይሆን የሚያዋጣንን ብቻ እያሳታምን፡፡ ሃይማኖት ያለውን ትተን ገበያ ያለውን እያሠራጨን፡፡ ሥርዓት መር መሆን ሲገባን ገበያ መር ሆነን፡፡

ለምን ግን ቤተ ክርስቲያንን አብረን እንጎዳታለን? እንዴት ከጉዳቷ እናተርፋለን? ለኢንሹራንስ ሲሉ ወላጆቻቸውን እንደሚገድሉ ክፉ ልጆች እንዴት ለገንዘብ ስንል ከሚጥሏት ጋር እንተባበራለን?
ለምን እኛ የምንችለውን አናደርግም? በምዕራቡ ዓለም የሙያ ማኅበራት ደረጃ ያወጣሉ፣ ሥርዓት ያስይዛሉ፣ ባለሞያ ፈትነው ፈቃድ ይሰጣሉ፣ ሞያውን ይቆጣጠራሉ፡፡ እኛስ ታድያ አንድነት ፈጥረን፣ ሊቃውንቱን መድበን፣ ደመወዛቸውን ሰጥተን የምናወጣቸውን ብናስመረምር እና ብናሳርም ምን አለ? ለማንም ብለን አይደለም፤ ለነፍሳችንና ለቤተ ክርስቲያናችን ስንል፡፡

ቤተ ክህነቱ ኃላፊነቱን አልተወጣም ብለን እንዴት እኛም ኃላፊነት የጎደለው ሥራ እንሠራለን? ቤተ ክርስቲያን እኮ አደረጃጀት እንጂ ሊቃውንት አላጣችም፡፡ ቤተ ክርስቲያን እስኪሠራ በመቃኞ እንደ ሚቀደሰው ሁሉ ዋናው ቤተ ክህነት እስኪሠራ እኛ ለመቃኞ የሚሆን አሠራር ብንዘረጋ ምናለበት? ማን ያውቃል እግዚአብሔር በጎ ኅሊና ችንን፣ለሥርዓት ተገዥነታችንን፣ ለእውነት ያለንን ትጋት አይቶ መፍትሔውን ይሰጠን ይሆናል፡፡

## 16 ሁሉም ወደ የበኣቱ ይመለስ

የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ያገባኛል የሚል ሰው ሁሉ በቤተ ክርስቲያናዊ በኣት ብቻ መገናኘት አለበት፡፡ ምንም እንኳን በሃይማኖት ምክንያት፣ በሀገር ፍቅር ስሜት፣ ለታሪክ ባላቸው ክብር እና ፍቅር፣ ለበጎ ነገር ባላቸው ቅንዐት፣ ወዘተ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን ለመርዳት ቢመጡ፣ በኣታቸው ግን ክርስትና መሆን አለበት፡፡

በዘር፣ በፖለቲካ፣ በጥቅም፣ በሥልጣን እና በፍቅረ ሲመት ተነሣሥተው የራሳቸውን አጀንዳ በቤተ ክርስቲያን ላይ ለመጫን እና የቤተ ክርስቲያንን ችግር ለአጀንዳቸው ማቀጣጠያ ለማድረግ የሚነሡትን ኃይሎች ግን «ወደየበኣታችሁ ተመለሱ» ማለት ያስፈልጋል፡፡

አንዳንዶች የቤተ ክህነቱን ችግር የፖለቲካ አጀንዳቸው ማንፀባረቂያ፣ ሌሎች የዘር አጀንዳቸውን ማቅረቢያ፣ ሌሎችም የሹመት ፍላጎታቸውን ማንገሻ ሊያደርጉት አሰፍስፈዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ በጥብርያዶስ ባሕር እንደ ተገኙት አምስት ገበያ ሕዝብ ናቸው፡፡ እነዚያ መልኩን ለማየት፣ ምግብ ለመብላት፣ ለመፈወስ፣ ተአምር ለማየት፣ ወሬ ለመቃረም፣ ሮማውያንን ገልብጦ ለመንገሥ፣ ሥልጣን ለማግኘት ወዘተ ተሰብስበው ነበር፡፡ በትክክለኛው ዓላማ የተሰባሰቡት ከ120 አይበልጡም ነበር፡፡

ጌታችን በአይሁድ እጅ ሲያዝ ግን የበሉበትን ወጭት ሰብረው፣ ያገኙትን ፈውስ ረስተው፣ ያዩትን ተአምራት ዘንግተው፣ የተማሩትን ትምህርት ትተው «ስቅሎ፣ ስቅሎ» እያሉ ነው የጮኹት፡፡ ሁሉም የየራሳቸው አጀንዳ አልሳካ ሲላቸው መልሰው በጠላትነት ተሰለፉ፡፡
አሁንም ለየራሳቸው ዓላማ ሲሉ ችግሩን የሚያቀጣጥሉ፣ የሚያራግቡ እና ባለቤት መስለው የሚታዩትን «ወደ በኣታችሁ ተመለሱ» እንበላቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን አጀንዳ ከመጋራት ይልቅ፣ ቤተ ክርስቲያን የእነርሱን አጀንዳ እንድትጋራ የሚፈልጉ ናቸው፡፡ ለቤተ ክርስቲያን አይሠሩም፤ ቤተ ክርስቲያን ግን ለእነርሱ እንድትሠራ ይፈልጋሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያንን አይጠቅሟትም፤ ቤተ ክርስቲያንን ግን መጠቀሚያ ማድረግ ይፈልጋሉ፡፡ እናም እባካችሁ «ወደየበኣታችሁ ተመለሱ»፡፡

## 17 የሚሠሩትን ማገዝ

የቤተ ክርስቲያንን ጉዳት ዝም ብለው ማየት አቅቷቸው፣ ክርስትናቸውም አስገድዷቸው የሚችሉትን የሚያደርጉ አካላት አሉ፡፡ በግለሰብም ሆነ በማኅበር ደረጃ ተነሥተው ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት፣ ለአብነት ት/ቤቶች መጠናከር፣ ለገጠር አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎት መቀጠል፣ የሚተጉ ወገኖች አሉ፡፡ እነዚህን አካላት ማገዝ ያስፈልጋል፡፡ እንደ ጽርሐ ጽዮን ዘተዋሕዶ ማኅበር ያሉትን፣ የመኖርያ ቤታቸውን ቀንሰው ለገጠር አብያተ ክርስቲያናት የሰባኪያን ማሠልጠኛ የገነቡትን፤ እንደ ደጆችሽ አይዘጉ ያሉትን፣ የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናትን አገልግሎት ለማስቀጠል የሚደክሙትን፤ እንደ ደቡብ ኦሞ አብያተ ክርስቲያናት መርጃ ማኅበር ያሉትን፣ ወደ ክርስትና ያልመጡ ወገኖችን ለማገልገል የተነሡትን፤ እንደ ማኅበረ ቅዱሳን ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት፣ገዳማት እና አድባራትን ለመርዳት እንዲሁም ቅርስ እና ታሪክን ለመጠበቅ የተነሡትን፤እንደ ማኅበረ ሰላም፣ የመዝሙርን

አገልግሎት ሥርዓትን በጠበቀ መንገድ ለማስፋፋት የሚተጉትን፤ሌሎችንም በስም ያልተጠቀሱትን በማገዝ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዳይዳከም ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ዛሬ ዛሬ የሰንበት ት/ቤቶች በኮሌጅ ደረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ኮርሶችን እየሰጡ ነው፡፡ እንደ ዓምደ ሃይማኖት ሰሰንበት ት/ቤት ያሉት ደግሞ በተልዕኮ ትምህርት እያስተማሩ ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ጅምሮች ማደግ አለባቸው፡፡ ትናንትና ሁለት ኮምፒውተር ይዘው የጀመሩ ማዕከላት ኮሌጅ ሲባሉ አራት እና አምስት መቶ ደቀ መዝሙር የሚያሠለጥኑት፣ የመማርያ መጻሕፍትን የሚያዘጋጁት ሰንበት ት/ቤቶቻችን ወደ ኮሌጅ ደረጃ የማያድጉት ለምንድን ነው?

ቀዳማይ፣ ካልኣይ፣ ሣልሳይ፣ ራብኣይ የሚለው ኮርስ አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ፣ አራተኛ ዓመት ተብሎ ለምን አይሰጥም? በውኑ የቀጣዩ ትውልድ ልጆች አሁን እኛ በተማርንበት መንገድ ይማራሉ? ታድያ ሰንበት ት/ቤቶቻችንን ካሁኑ ለምን አናዘጋጃቸውም?

በአንድ በኩል ሊቃውንቱ ተተኪውን ትውልድ የሚያስተምሩበት ዕድል ያገኛሉ፤ በሌላም በኩል በተልዕኮ ትምህርት በውጭ ያሉትን ምእመናን ማዳረስ ይቻላል፤ እንደ ገናም ደግሞ አንድ የሰንበት ተማሪ እድሜ ልኩን ሥላሴ ስንት ናቸው? እየተባለ ሲማር ከሚኖር ዕድገት ያለው ትምህርት ለማግኘት ይረዳዋል፡፡ እናም እስኪ በየዐቅማችን እንጀምረው፡፡ ነገን ዛሬ እንትከል፡፡

## 18 ለትልቁ ስንል ትንንሾችን መተው

በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን፣ በዶግማ እና በትውፊት ላይ ካልሆነ በቀር በአሠራር፣ በይትበሃል፣ በጊዜያዊ ጠብ፣ በልጅነት ስሜት እና ባለ መረዳዳት የተፈጠሩትን ልዩነቶች ለቤተ ክርስቲያን ሲባል ማስማማት እና ይቅር መባባል ያስፈልጋል፡፡

አንድ ዓይነት ዓላማ፣ እምነት እና ራእይ እያላቸው እርስ በርሳቸው የማይስማሙ አገልጋዮች፣ ማኅበራት እና ቡድኖች አሉ፡፡ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ እያሉ የሚፎካከሩ፤ አንዱ አንዱን ከመርዳት ይልቅ መገፋፋትን የሚወድዱ፤ ተባብሮ ከመሥራት ይልቅ በየፊናቸው መሮጥን የሚመርጡ አሉ፡፡ ይህ ግን ማብቂያው አሁን ነው፡፡ የማይስማሙት ተስማምተው ቤተ ክርስቲያንን ሲያጠቁ መስማማት የሚገባን እንዴት እንለያየን፡፡ አሠራር ልዩ ልዩ ነው፤ ሃይማኖት ግን አንድ ነው፡፡ ሁላችንም የግድ አንድ ዓይነት ሰዎች የአንድ ማኅበርም አባላት መሆን አይጠበቅብንም፤ ነገር ግን ተግባብተን መሥራት ይጠበቅብናል፡፡ ትንንሽ ልዩነቶችን ሳንፈታ ትልቁን ችግር መፍታት አንችለም፡፡

ለመነጋገር፣ ለመግባባት እና ተባብሮ ለመሥራት እንነሣ፡፡ አባላቱም ብንሆን ዝም ብለን በአመራሮቹ አንመራ፡፡ ከእነ እገሌ ጋር ለምን አብረን አንሠራም? ለምን አንረዳዳም? ለምን ሥራ አንካፈልም? ለምን ልምድ አንለዋወጥም? ለምን እንተማማለን? ለምን እንራራቃለን? ብለን እንጠይቅ፡፡ በእውነት ቤተ ክርስቲያናችንን የምንወድድ ከሆነ ተዋድደን በአንድነት እንቁመላት፡፡

## 19 እንወያይ

ሐሜቱን እናቁም፤ አሁን እንወያይ፡፡ ምንተ ንግበር? እንበል፡፡ ጊዜው የተግባር ነው፡፡ በየአለንበት ሃሳብ እንለዋወጥ፡፡ አንዱ ሌላውን ይቀስቅስ፡፡ የተኛ እንዳይኖር አስተውሉ፡፡ በየጉባኤያቱ መብል እና መጠጥ ይቀነስ፣መዝሙር አይብዛ፤ እንመካከር፡፡ እንወያይ፡፡ የተግባር ዕቅድ እናውጣ፡፡ እየተነጋገርን እንርሳ፡፡ ቀስቃሽም እንፈልግ፡፡

ለመሆኑ ስለ ቤተ ክርስቲያን ለማሰብ እና ለመወያየት አንዳች አስደንጋጭ ዜና መስማት አለብን? እስከ ዛሬ የሰማነው አይበቃንም? ሰንበት ት/ቤቶች ከሰንበት ት/ቤቶች፤ ማኅበራት ከማኅበራት፤ አገልጋዮች ከአገልጋዮች፣ አባቶች ከአባቶች እንነጋገር፤ አጀንዳችን ቤተ ክርስቲያን ትሁን፡፡ ለማማት አይደለም፤ ለተግባር፡፡ ለአፍ ጅምናስቲክ አይደለም፤ ለተጋድሎ፡፡ ወሬ ለማሟሟቅ አይደለም፤ ለቁጭት፡፡ የራስዋ እያረረባት የሰው ታማስላለች እንደሚባለው አሁን ሌሎች ነገሮችን ለጊዜው ጋብ አድርገን ወደ ራሳችን እንመለስ፡፡

## 20 ትውልድ ይዳን በኛ ይብቃ

በኢትዮጵያ ኤች አይ ቪ /ኤድስን ለመግታት ከተነሡት አካላት መካከል ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩት ወገኖች ግንባር ቀደሙን ቦታ ይይዛሉ፡፡ ይዘውት የተነሡት መሪ ቃልም «ትውልድ ይዳን በኛ ይብቃ» የሚለው ነው፡፡ እኛም ይህ የምንሰማው ችግር ሁሉ ለልጆቻችን መተላለፍ የለበትም፡፡ ይህንን ከታሪክ መጻሕፍት ብቻ ያንብቡት፡፡ «ትውልድ ይዳን በኛ ይብቃ» ብለን እንነሣ፡፡ ሁላችንም ለራሳችን ቃል እንግባ፡፡

«ይህ ችግር ወደ ትውልድ እንዳይሸጋገር በእግዚአብሔር ኢጋዥነት የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ፡፡ ትውልድ ይዳን

በኔ ይብቃ፡፡»
እግዚአብሔር ቤተ ክስቲያናችንን ይጠብቅ፡፡ አሜን፡፡

***እነሆ በቀጣዮቹ ቀናት ይህ ብሎግ የእናንተን የመፍትሔ ሃሳቦች ያስተናግዳል፡፡ በተሰጡት ላይ መጨመር፣ ማሻሻል፤ መቃወምም ሆነ የድጋፍ ሃሳብ መስጠት ይቻላል፡፡ በተቻለ መጠን ሃሳቦቻችን ከግለሰቦች ይልቅ ጉዳዮች ላይ ያተኩሩ፤ ከምስጋናና ጥላቻ ይልቅም ሃሳብ ላይ ያነጣጥሩ፡፡***

## ንጉሡ ራቁታቸውን ናቸው

ሁለት እራት አግባ ብልሃተኞች ወደ አንድ ንጉሥ ግቢ ያመሩና ደጅ ይመታሉ፡፡ የግቢው ጠባቂም አቤት ይላል፡፡ እነዚያ ብልሃተኞችም «ለንጉሡ ኃጢአተኛ ሰው የማያየው አዲስ ልብስ ልንሠራ መጥተናል» ይላሉ፡፡ ግቢ ጠባቂውም ሲሮጥ ሄዶ ለንጉሡ ጉዳዩን ያቀርባል፡፡ ንጉሡ ይፈቅዱና ሰዎቹ ገብተው እጅ ነሡ፡፡ «ምን ዓይነት ልብስ ነው የምትሠሩት» አሉ ንጉሡ፡፡ ብልሃተኞቹም «ኃጢአት የሠራ ቀርቶ ያሰበም ሰው ሊያየው የማይችል አዲስ ዓይነት ልብስ ነው» ሲሉ ማብራርያ ሰጡ፡፡ ንጉሡም በነገሩ ተደስተው የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ መድበው ልብሱን እንዲሠሩላቸው አዘዙ፡፡

በወርቅ እና በብር የተንቆጠቆጡት፣ ልዩ ድርጎ እና ቤት የተሰጣቸው እነዚያ ብልሃተኞች ቤቱን ዘግተው ሥራ ጀመሩ፡፡ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ንጉሡ አንዱን ባለሟላቸውን ሥራው የት እንደ ደረሰ እንዲያይላቸውት ላኩት፡፡ ብልሃተኞቹም ተቀብለው አስተናገዱት፡፡ ባለሟሉ ወደ ቤታቸው ሲገባ የሚያየው ነገር አልነበረም፡፡ ባዶ የልብስ መሥሪያ ማሽን፣ ባዶ ጠረጴዛ እና ባዶ አዳራሽ፡፡ ግራ ተጋባ፡፡ ከብልሃተኞቹ አንዱ ወደ ጠረጴዛው አመራና «አዩ ጌታው፤ እጀ ጠባቡ እያለቀ ነው» አለው ባዶውን ጠረጴዛ እያሳየ፡፡ ባለሟሉ ግን እንኳን እጀ ጠባብ ብጫቂም ጨርቅ በጠረጴዛው ላይ ለማየት አልቻለም፡፡ ነገር ግን «ኃጢአት የሠራ ሰው ልብሱን ማየት አይችልም» ተብሏልና «አላየሁም» ቢል ኃጢአት ስለ ሠራህ ነው የሚለው እንጂ የሚያምነው ስለሌለ «በጣም የሚገርም እጀ ጠባብ ነው፡፡ መቼም ንጉሣችን ሲያዩት ይደሰታሉ» ብሎ ራሱን እየነቀነቀ አደነቀ፡፡ በልቡ ግን ግራ እንደተጋባ ነበር፡፡

«ንጉሥ የሚያምረውን እንጂ የሚያምርበትን፣ ንጉሥ የሚፈልገውን እንጂ የሚያስፈልገውን አይነግሩትም» ይባላልና ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመልሶ ለንጉሡ «እጅግ የሚገርም፣ ዓይን ያላየው ጆሮም ያልሰማው ልዩ የሆነ እጀ ጠባብ ተሠርቷል፡፡» ሲል ሪፖርቱን አቀረበ፡፡ አሁንም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ንጉሡ ሌላ ባለሟላቸውን ላኩት፡፡ ያም ባለሟል ወደ ብልሃተኞቹ ቤት ገብቶ አካባቢውን ሲያይ ደነገጠ፡፡ እንኳን የተሰፋ ልብስ የተዘረጋ ክር የለም፡፡ ነገር ግን የቀድሞው ባለሟል አየሁ ብሎ ይሄኛው አላየሁም ቢል ከኳደኛው ማነሱ ነው፡፡ ብልሃተኞቹም ወደ ጠረጴዛው ወስደው «እጀ ጠባቡ ይህንን ይመስላል፤ ሱሪው ደግሞ በመሰፋት ላይ ነው፡፡ የሚቀረን ጫማው ነው» እያሉ ማስጎብኘት ቀጠሉ፡፡

ባለሟሉ እንኳንስ አዲስ የተሠራ እጀ ጠባብና የተሰፋ ሱሪ ቀርቶ አሮጌ ልብስ እንኳን እንኳን ለማየት አልታደለም፡፡ ነገር ግን ኃጢአተኛ ከሚባል «እንደ ዘመኑ ይኖሩ እንደ ንጉሡ ይናገሩ» ነውና «ይህንን ነገር ለማየት በመታደሌ

ፈጣሪዬን አመሰግነዋለሁ፡፡ ይህንን ነገር ለማየት ፈልገው ያላዩ ስንት አሉ፡፡ በሥራችሁ ንጉሡ እንደሚደሰቱ ርግጠኛ ነኝ» ብሎ አመስግኗቸው ወጣ፡፡ በልቡ ግን «እነዚህ ሰዎች ያሾፋሉ እንዴ፤ ምን ዓይነት ነገር ነው እየሠሩ ያሉት» እያለ ያጉተመትም ነበር፡፡ ለንጉሡም ድንቅ ነገር ማየቱን ከዚያኛው አስበልጦ አንቆለጳጵሶ አቀረበ፡፡

በመጨረሻ ራሳቸው ንጉሡ የሥራውን ማለቅ ለማየት ከባለሚሎቻቸው ጋር መጡ፡፡ እነዚያም ብልሃተኞች እንደተለመደው ወገባቸውን አሥረው ማስጎብኘት ጀመሩ፡፡ «ይሄ እጀ ጠባቡ፣ ይሄ ሱሪው፣ ይሄ ካባው፣ ይሄ ጫማው ነው» እያሉ ያሳያሉ፡፡ ንጉሡ ምንም ነገር ለማየት አልቻሉም፡፡ ነገር ግን የእርሳቸው ባለሚሎች አየን ብለው እያወሩ እርሳቸው አላየሁም ቢሉ ራሳቸውን ማስገመት ነው፡፡ ሕዝቡስ ምን ይላል? ደግሞም ዋናው ነገር እርሳቸው አየሁ ማለታቸው እንጂ ማየታቸው አይደለም፡፡ ይህንን ሁሉ አስበው «በሕይወቴ ላየው የምፈልገውን ነገር ነው ያየሁት፡፡ በነገሥታት ታሪክ እንደዚህ ያለ ልብስ መልበሱ የተነገረለት ንጉሥ የለም፡፡ ልዩ የሆነ ሽልማት ይዘጋጅላችኋል» ብለው አድናቆታቸውን ገለጡ፡፡ አጅበዋቸው የመጡትም ምንም ነገር ለማየት ባይችሉም ኃጢአተኛ እንዳይባሉ ሲሉ አደነቁ፤ አመሰገኑ፡፡

«ንጉሥ ሆይ» አለ አንደኛው ብልሃተኛ «ሕዝቡ ሁሉ በዐዋጅ ተጠርቶ ይህንን ልብስ ለብሰው ማየት አለበት»፡፡ የንጉሡም ባለሚሎች «እውነት ነው፤ ይህንን መሰሉ ልብስማ የቤት ልብስ አይሆንም» ብለው እያዳነቁ ሃሳቡን ደገፉት፡፡ ንጉሡም ተስማሙ፡፡

ዐዋጅ ታወጀ፡፡ «ንጉሡ ኃጢአት የሠራ ሰው ሊያየው የማይችል ልብስ ስላሠሩ እንዲህ ባለ ቀን፣ እንዲህ ባለ ቦታ፣ በዚህ ሰዓት ወጥታችሁ እንድታዩ» ተባለ፡፡ በተባለውም ቀን ሕዝቡ ጉድ ለማየት ግልብጥ ብሎ ወጣ፡፡ ንጉሡም ወደ ብልሃተኞቹ ዘንድ መጡ፡፡ ሁለቱ ጓደኞች እየተረዳዱ ንጉሡን ማልበስ ቀጠሉ፡፡ እነዚያ ብልሃተኞች ንጉሡ የለበሱትን ልብስ ሙልጭ አድርገው አውልቀው «አሁን ሱሪውን፣ አሁን እጀ ጠባቡን፣ አሁን ካባውን» እያሉ አለበሷቸው፡፡ ንጉሡም እየሳቁ፣ፈገግ እያሉ፤ በዙርያቸው የተሰለፉትም ራሳቸውን እየነቀነቁ ልብሱን ለበሱ ተባለ፡፡ ንጉሡም በልባቸው «ራቁቴን ሊያስኬዱኝ ነው እንዴ?» ይላሉ፡፡ ግን አይናገሩትም፡፡ ተከታዮቻቸውም «እኒህ ሰውዬ ሊያብዱ ነው እንዴ፤ ራቁታቸውን ናቸውኮ» ይላሉ ግን አይናገሩትም፡፡ አፍ እና ልብ እንደ ተለያዩ ንጉሡ ለብሰው ጨረሱ ተባለ፡፡

ከዚያም ሠረገላው ቀረበና ንጉሡ በትረ መንግሥት ጨብጠው ቆሙ፡፡ ባለሚሎቻቸውም ሰግደው አጨበጨቡ፡፡ ከዚያም ሠረገላ ነጅው እንደ ዛሬ ንጉሡን ራቁታቸውን አይቷቸው ስለማያውቅ ሳቅ እያፈነው ሠረገላውን መንዳት ጀመረ፡፡ ወደ አደባባዩም ወጡ፡፡ ሕዝቡ ሁሉ አጨበጨበ፡፡ አንዱ ለጓደኛው «ግሩምኮ ነው፤ ከየት አገኙት ባክህ» ይላል፡፡ ኃጢአተኛ እንዳይባል፡፡ በልቡ ግን «በቃ ስምንተኛው ሺ ማለት ይሄ አይደለም እንዴ፡፡ ንጉሥ ራቁቱን ሲሄድ ከማየት በላይ ምን ምልክት አለ» ይላል፡፡ ሌላው ደግሞ «ተመልከት፣ ተመልከት እጀ ጠባቡ ሲያብረቀርቅ፣ ንጹሕ ሐር እኮ ነው» ይልና በውስጡ ግን «አብደዋል፣ አብደዋል እንጂ፤ ደኅና ዘመድ አጥተዋል» ብሎ ያማል፡፡ ሁሉም ራሱን ላለማዋረድ እና ኃጢአተኛ ላለመባል ሲል ያላየውን እንዳየ እያደረገ ይጨዋወታል፡፡ በልቡ ግን ግማሹ ይስቃል፣ግማሹ ያፍራል፣ ግማሹ ይራገማል፣ ቀሪውም ያማል፡፡

ንጉሡም ከሕዝቡ የሚቀርብላቸውን ልክ የሌለው ሙገሳ እየሰሙ፤ የባለሟሎቻቸውን ውዳሴ እያዳመጡ ሰውነታቸው በሙሉ ጥርስ በጥርስ ሆነ፡፡ በውስጣቸው ግን ብርዱ አላስቆም አላቸው፡፡ ነፋሱ ይቀጠቅጣቸው ጀመር፡፡ «ምን ዓይነት ሞኝ ብሆን ነው የነዚያን አጭበርባሪዎች ምክር የሰማሁት፤ አሁን የውስጤን ብናገር ማን ያምነኛል» ይሉ ነበር፡፡

በዚህ መካከል እናቱን ተከትሎ የመጣ አንድ ሕፃን ልጅ «እማዬ፣ እማዬ እይ፣ ንጉሡኮ ራቁታቸውን ናቸው» አለና ጮኸ፡፡ በዙርያው የነበሩ ሁሉ «ዝም በል፤ ይሄ ገና ከልጅነቱ ኃጢአት የወረሰው፡፡ ምን የዛሬ ዘመን ልጆች እንዲህ ያለው ግሩም ነገር አይታያችሁ፡፡ ዝም በል፤ የተረገመ» እያሉ ተረባረቡበት፡፡ እናቱም አፈሩ፡፡ በዚህ ሰዓት ካፊያ እየጣለ ነበር፡፡ ንጉሡ ግን ፈገግታቸው እየጨመረ፣ ስቃያቸውም እያየለ ሄደ፡፡ ያ ሕፃን ልጅ ከእናቱ እጅ አፈትልኮ ወጣና ሠረገላውን እየተከተለ «ኧረ ንጉሡ ራቁታ ቸውን፤ ኧረ ንጉሡ ራቁታቸውን» እያለ መጮኹ ቀጠለ፡፡ ሕዝቡም በኃጢአተኛነቱ እያዘነበት፣ ርግማኑንም እያዥጎ ደጎደበት፣ ዝናሙም እያየለ፣ ንጉሡም እንደቆሙ ትእይንቱ ቀጠለ፡፡

ሕዝቡ ያጨበጭባል፣ ባለሟሎችም እንጀራቸው ነውና ሕዝቡ እንዲያጨበጭብ ያስተባብራሉ፡፡ ቀራቢዎቻቸው እጅ ያውለበልባሉ፤ ንጉሡም የሚቀርብላቸውን ሁሉ በደስታ ይቀበላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡም ያማል፡፡ በዚህ ዘመን መፈጠሩን ይረግማል፡፡ በንጉሡ እብደት ይናደዳል፣ ይዝታል፡፡ ባለሟሎቻቸውም በውስጣቸው አፍረዋል፡፡ በነዚያ ሁለት ብልሃተኞች ድርጊት ተበሳጭተዋል፡፡ እንዲህ ባለው ዘመን ባለሟል በመሆናቸው ራሳቸውን ይረግማሉ፤ ዘመኑንም ይረግማሉ፣ በውስጣቸውም ያማሉ፡፡ ግን ምኑንም አይናገሩትም፡፡ እንዲያውም በተቃራኒው ሥራቸው ነውና ሳያጨበጭብ ቆሞ የሚያዩትን ሰው «አጨብጭብ፣ ኃጢአተኛ!´ እያሉ ይቆጣሉ፡፡

ብርዱ እየከፋ፣ ዝናሙ እየጨመረ መጣ፡፡ ንጉሡም ጥርሳቸውን እያፋጩ፣ ሰውነታቸው በብርድ እየተርገፈገፈ፣ ብርዱ አጥንታቸው ድረስ እየሠረሠራቸውም ቢሆን ከመሳቅና፣ ፈገግ ከማለት፣በደስታ እጃቸውን ለሕዝቡ ከማንሣትና ራሳቸውን ከመነቅነቅ አልተቆጠቡም፡፡ ያ ሕፃን ልጅ ብቻ ከኋላ ከኋላ እየተከተለ «ኧረ ንጉሡ ራቁታቸውን ናቸው፣ ኧረ ንጉሡ ራቁታቸውን ናቸው» እያለ ይጮኻል፡፡ በርሱ ላይ የሚደርሰው ርግማኑና ቁጣውም አሁንም እንደ ቀጠለ ነው፡፡

በመጨረሻ ግን ንጉሡ አልቻሉም፡፡ ብርዱ እና ዝናቡ ከዐቅማቸው በላይ ሆነ፡፡ ሰውነታቸው መርገፍገፍ፣ ጥርሳቸውም እንደ ገጠር ወፍጮ መፋጨት ጀመረ፡፡ ውጫዊ ማስመሰያ ውስጥን ሸፍኖ መቆየት የሚችለው ጥቂት ጊዜ ነውና ንጉሡም የውስጣቸው ሕመም እንደልብ ፈገግ ለማለት እና ደስተኛ ለመምሰል አላስቻላቸውም፡፡ የሆነውን ሳይሆን እንዲሆን የሚፈልጉትን ተቀብሎ መዝለቅ አይቻልም፡፡ ሽል ከሆነ ይገፋል፣ ቂጣ ከሆነ ይጠፋል፡፡

በድንገት ንጉሡ ሠረገላ ነጅውን «አቁም!» ብለው በቁጣ ተናገሩት፡፡ እርሱም ሳቁ ወደ ድንጋጤ ተለወጠበትና አቆመ፡፡ «ያ ሕፃን ልጅ ብቻ ነው እውነተኛ፡፡ አዎን እውነት ነው እኔ ራቁቴን ነኝ፡፡ ሁላችሁም ውሸታችሁን ነው፡፡ እኔም ውሸቴን ነው» አሉና ተቀመጡ፡፡ ባለሟሎቻቸውም የቀድሞ ካባቸውን ሰጧቸው፡፡

አንዳንዶቹ ባለሟሎች «እኛ ምን እናድርግ ራሳቸው ናቸው ለዚህ የበቁት» አሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ «ጥፋተኞቹ እኛ ሳንሆን ያኔ ተልከው ያላዩትን እንዳዩ አድርገው የተናገሩት ናቸው» ብለው ወቀሱ፡፡ የቀሩትም «ሰሚ አጥተን ነው እንጂ

ኧረ እኛስ ተናግረን ነበር» ብለዋል፡፡ ከሕዝቡም አንዳንዶቹ «አላልኳችሁም፣ እኔ ቀድሞም ተናግሬ ነበር» ያሉ አሉ፡፡ «ድሮም ነገሩ አላማረኝም ነበር» ያሉም ነበሩ፡፡

አንደኛው ሰውዬ ደግሞ ሁሉንም ያስደነቀ ነገር ተናገረ፡፡

«ለዚያ ሕፃን ልጅ ንጉሡ ራቁታቸውን መሆናቸውን የነገርኩትኮ እኔ ነኝ» ሲል፡፡

እነዚያ ሁለት ብልሃተኞች ግን ብራቸውን ይዘው የት እንደ ደረሱ እስካሁን አልታወቀም፡፡

## የመፍትሔ ሃሳቦች

ባለፈው ሳምንት የቤተ ክህነታችንን ተግዳሮት አንሥተን ተወያይተን ነበር፡፡ በስተ መጨረሻም አጠቃላይ መፍትሔዎችን ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡ በዚህኛው ጽሑፍ ደግሞ ዝርዝር የመፍትሔ ሃሳቦችን እናያለን፡፡ እነዚህ መፍትሔዎች በአዘጋጁ የታዩ ናቸው፡፡ አንባብያን ደግሞ የመፍትሔ ሃሳቦችን መሰንዘር አለባቸው፡፡

# ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች

ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋት ምን ዓይነት መፍትሔ ነው?

በአሁኑ ጊዜ የቤተ ክህነቱ አሠራር ሥርዓትን እየለቀቀ የመጣበት ጊዜ ነው፡፡ እንደ ያዝያን ለምጽም ግንባር ላይ ወጥቷል፡፡ ንጉሡ ያዝያን በእግዚአብሔር ላይ በሠራው የድፍረት ኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር በለምጽ መታው፡ መጀመርያ ለምጹ በሰውነቱ ላይ ብቻ ስለነበረ በቀሚስ እና ካባ፣ በወርቀ ዘቦ እና በብር ዝርግፍ ሸፈነው፡፡ ኃጢአቱ እየባሰ ሲመጣ ግን ለምጹ ግንባሩ ላይ ወጣ፡፡ እርሱም ኃጢአቱን በንስሐ ከማስወገድ ይልቅ ለምጹን በሻሽ ለመሸፈን ሞከረ፡፡ ለተወሰነ ጊዜም ተሳካለት፡፡ በደሉ እና ግፉ እየባሰ በመምጣቱ ግን ለምጹ ሻሹ ላይ ወጣ፡፡ ከዚህ በኋላ ለመሸፈን አልቻለም፡፡

አሁን አሁን ነገራችን እንደ ያዝያን ለምጽ ሊሸፈንበት ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ራሱ ችግሩም «አለሁ፣አለሁ» ብሏል፡፡ የለህም ብንለውም ራሱን በራሱ ያስመሰክራል፡፡

በዚህም ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ላይ ይመለከተኛል የሚሉ ሁሉ በመነጋገር ላይ ናቸው፡፡ መፍትሔም ይሰነዝራሉ፡፡ የመፍትሔ አቅጣጫዎቻቸውን ስናይ ሁለት መልክ አላቸው፡፡ ተሐድሶ/reform/ ትንሣኤ /renaissance/ ፡፡

### ተሐድሶ

ይህንን መንገድ የሚመርጡት አካላት በቤተ ክርስቲያን ላይ ሥር ነቀል አብዮት መምጣት አለበት ይላሉ፡፡ ይህ አብዮት ዶግማዋን፣ ቀኖናዋን፣ትውፊቷን፣ ቅዳሴዋን፣ ጸሎቷን፣ ገዳማዊ ሕይወቷን፣ ወዘተ የሚመለከት ነው ባይ ናቸው፡፡ እነርሱ የሚያቀነቅኑት መንገድ ከ500 ዓመታት ጀምሮ ምዕራብ አውሮፓውያን እና አሜሪካውያን በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያቀነቀኑት መንገድ ነው፡፡ በወቅቱ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በአስተዳደርዋ ላይ ይታይ

በነበረው የሞራል ውድቀት፣ብኩንነት፣ አምባገነንነት፣ ሥርዓት አልበኝነት እና ዓለማዊነት ምክንያት ሕዝቡ ተማረረ። የወሰደው መፍትሔ ግን ችግርን በችግር የሚተካ ሆነ። የካቶሊክን ማንኛውንም አስተምሕሮ በመቃወምና በማፍረስ ሌላ ዓይነት አስተምህሮ ተካ። ከዚያም አልፎ ክርስትናን ርግፍ አድርጎ እስከ መተው ደረሰ።

ተሐድሶ ውጤቱ ይሄው ነው። ምክንያቱም ነባርዋን ቤተ ክርስቲያን አፍርሶ በለዘብተኛነት በኩል ወደ ጽንፈኛ ዓለማዊነት ያደርሳታልና። ተሐድሶ መነኮሳት አጠፉ ብሎ ምንኩስና ሕይወትን ለማጥፋት ይነሣል፤ ጳጳሳት አጠፉ ብሎ ጵጵስናን ለማስቀረት ይጥራል፤ በአንዳንድ ቀሳውስት ችግር ቅዳሴን ያስቀራል፤ በሰባክያን ጥፋት ስብከት ይቅር ይላል፤ በተንዛዛ ድግስ ምክንያት ዝክር አያስፈልግም ይላል፤ በአጠቃላይ የሥነ ምግባር ችግሮችን ከመሠረተ እምነት ጋር ይቀላቅላቸውና ቤተ ክርስቲያንን ከመሠረቷ ይንዳታል።

«*መነሣት*»

*ይህ የመፍትሔ አቅጣጫ የሚነሣው በክርስትና ሕይወት መዳከም፣ መዛል እና ዓላማን መሳት ሊያጋጥም ይችላል። ከበጎች ጋር ተኩላዎች፣ ከስንዴ ጋር እንክርዳድ ሊቀላቀል ይችላል ከሚለው ነው። በመሆኑም የደከመውን ማጽናት፣ የላሉትን ማጠንከር፣ የተቀላቀሉትን መለየት፣ የተረሱትን ማስታወስ፣ የተበላሹትን ማስተካከል ይገባል ነው። በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ጥንት ክብርዋ መመለስ ማለት ነው።*

*ይህንን ለማድረግ ደግሞ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች አሉ።*

*የመጀመርያው አብርሖት ነው። ሕዝቡ በትምህርት መንገዱ እንዲበራለት ማድረግ። የቤተ ክርስቲያኑን ማንነት፣ መሠረተ እምነቷን፣ ታሪኳን፣ ሥርዓቷን ያጋጠማትንም ፈተና ዐውቆ፤ ራሱንም የቤተ ክርስቲያን አካል ማድረግ አለበት። ቤተ ክርስቲያን ተፈተነች ስንል ራሳችን ተፈተንን ማለታችን ነው። መከራ ገጠማት ስንል መከራ ገጠመን ማለታችን ነው። እየተነጋገርን ያለነው ከኛ ውጭ ስለሆነ አካል አይደለም ብሎ ማመን አለበት። ያላወቀ፣ ያላመነ እና ያልቆረጠን ሕዝብ ለትንሣኤ ማዘጋጀት ከባድ ነው። አስቀድሞ ሕማማትን ለማለፍ የሚያስችል ብቃት ይጠይቃልና።*

*ሁለተኛው መዋቅራዊ ሽግግር* /structural transformation/ *ነው። መዋቅራዊ ሽግግር ማለት ቤተ ክርስቲያኒቱን ወደ ጥንት ክብርዋ የሚመልስ ደረጃውን የጠበቀ እና ዘመኑን የሚዋጅ አሠራር፣ መዋቅር፣ አስተሳሰብ መመሥረት ማለት ነው። ይህም ማለት ክህነቱ ሳይሆን አሰጣጡ እና አኗኗሩ፤ ጵጵስናው ሳይሆን አሰጣጡ እና አሠራሩ፤ ምንኩስናው ሳይሆን አሰጣጡ፣ አነዋወሩ፤ ብሕትውናው ሳይሆን አነዋወሩ፤ ቅዱሳት መጻሕፍቱ ሳይሆኑ አገባባቸው፤ የቤተ ክርስቲያን ናቸው ተብሎ የሚመዘኑበት መመዘኛ፣ አተረጓጎማቸው፣ ለምን ለምን ጥቅም እንደሚውሉ፤ በዓላቱ ሳይሆኑ፣ ብዛታቸው፣ አከባበራቸው፣ ድንጋጌያቸው፤ ሲኖዶሱ ሳይሆን አሠራሩ፣አወቃቀሩ፤ ወዘተ ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል ማለት ነው።*

*መዋቅራዊ ሽግግር ሆ ተብሎ በአብዮት አይመጣም። አስቀድሞ ችግሩን በመረዳት፣ ከዚያም የችግሩን አንኳር* /center of gravity/ *በመለየት፣ ከዚያም ደረጃ በደረጃ በመፍታት የሚመጣ ነው። መግባባትን፣ለአንድ ዓላማ መነሣትን እና ሁሉ ዐቀፍነትን ይጠይቃል።*

*ለቤተ ክርስቲያን ትንሣኤዋን እንጂ መለወጧን ለማምጣት የምንሠራ ከሆነ በክርስቶስ መሠረት ላይ ሳይሆን በኛ ፍላጎት ላይ የተመሠረተች ሌላ ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት እየሞከርን ነው ማለት ነው።*

*እናም እኔ የመፍትሔ ሃሳቦችን የምሰነዝረው ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋት ተሐድሶ ሳይሆን ትንሣኤ ነው። በምእመናኑ ሕይወት እና ጉዞ፣ በአባቶች ሕይወት እና ጉዞ፣ በገዳማት ሕይወት እና ዐቅም፣ በአብያተ ክርስቲያናት አስተዳደር እና ዐቅም፣ በቤተ ክህነቱ አስተዳደር፣መንፈሳዊ ሕይወት እና አሠራር ላይ ዝለት አለ፤ ድክመት አለ፤ የዓላማ መሳት አለ። ስለዚህም መነሣሣት፣ ወደ ጥንቱ መመለስ እና እንደገና ቀና ማለት ያስፈልጋል በሚለው እምነት ነው።*

**1 ጉዳዬ ብሎ መጸለይ**

ብዙ ጊዜ ስለ ቤተ ክርስቲያን ፈተና ሲነገር ብዙዎቻችን እንጸልይ እንላለን፡፡ ልክ ነው፡፡ ያለ ጸሎት እና ጾም ሰይጣን አይወጣም፡፡ እኛ ግን ይህንን የምንለው አንድም ለማምለጫ፣ አንድም ለምዶብን፣ አንድም መቼም ማንም አያየንም ብለን ነው፡፡ እስኪ ስንቶቻችን ደረታችንን እየደቃን እንደ ራሔል እናለቅሳለን? እስኪ ስንቶ ቻችን ከልባችን እንደ ዳዊት ተዋርደን እግዚአብሔርን ጠየቅነው? የምንጸልየውም ጸሎት የፎርማሊቲ ጸሎት ነው፡፡ ቀድሞ ከምንጸልይበት መንገድ የጨመርነው አንዳች ነገር የለም፡፡

በእውነት የቤተ ክርስቲያንን ትንሣኤ ማየት ከፈለግን ግን ቀልዳችንን አቁመን ለጸሎት እንነሣ፡፡ ለራሳችን ሱባኤ እንግባ፣ ራሳችንን በምንችለው መንገድ እናዋርድ፤ ይህንን ጉዳይ ሳንረሳ እናስበው፡፡

በየገዳማቱ ለሚገኙት አበውም ችግሩን ከማስረዳት ጋር ጸልዩ እንበላቸው፡፡ ባለ ማቋረጥ መባ እየላክን እግዚአብሔርን እንዲማልዱ እናድርግ፡፡ እናቶቻችንንም እንንገራቸው፡፡ ይህች ቤተ ክርስቲያን እና ሀገር ተጠብቃ የምትኖረው በየዋሐን እናቶች ጸሎት ነው፡፡ የእናቶች ጸሎት እንደ ራሔል በቶሎ ይሰማልና ለጉዳዩ እንዲያስቡበት፣ እንዲያዝኑ በትና እንዲያለቅሱበት እናድርግ፡፡

ብጹአን አበውም በውይይት እና በስብሰባ ችግሩን ለመፍታት ካልቻላችሁ ሌላውን ነገር ትታችሁ ወደ ጸሎቱ ፊታችሁን አዙሩ፡፡

**2 ከቲፎዞነት መውጣት**

በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ጥብቅና ልንቆም የሚገባው ወገንተኛም ልሆን የሚገባው ለቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ይህም ማለት ለዶግማዋ፣ለሥርዓቷ እና ለትውፊቷ ማለት ነው፡፡ ስለ ሰዎች የምንነጋገረው ከእነዚህ ነገሮች አንፃር መሆን አለበት፡፡ እኛ ሰዎችን በቤተ ክርስቲያን በኩል አገኘናቸው እንጂ ቤተ ክርስቲያንን በሰዎች በኩል አላገኘናትም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርኮችን፣ ጳጳሳትን፣ ቀሳውስትን፣ ዲያቆናትን፣ ሊቃውንትን፣ ሰባኪያንን፣ መዘምራንን አፈራች እንጂ እነርሱ አላስገኟትም፡፡ በመሆኑም የሰዎች እና የቡድኖች ቲፎዞ በመሆን ዶግማዋን ፣ሥርዓቷን እና ትውፊቷን ከማፍረስ መቆጠብ አለብን፡፡

ሰውን መውደድ፣ ማድነቅ እና ማክበር መልካም እና ክርስቲያናዊ ምግባርም ነው፡፡ ያ ማለት ግን ከፉ ሥራውን መውደድ፣ማድነቅ እና ማክበር ማለት አይደለም፡፡ ቅዱስ ቁርሎስ ለንስጥሮስ በጻፈው ደብዳቤ «ንስጥሮስ ሆይ አንተን እወድድሃለሁ፤ ኑፋቄህን ግን እጠላለሁ» ያለውን መርሳት የለብንም፡፡ እገሌ የሀገሬ ልጅ ነው፣ ውለታው አለብኝ፤ የኔን ፖለቲካ ያራምዳል፣ ይወደኛል፣ ይጠቅመኛል፣ አብሮ አደጌ ነው ወዘተ እያልን ጥፋታቸውን በዝምታ ያለፍናቸው ሰዎች ተቀምጠን የሰቀልነውን ቆመን ማውረድ እንዳንችል አድርገውናል፡፡

ታላቁ አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ለኢያሱ ወልደ ነዌ በአንፃረ ኢያሪኮ በተገለጠ ጊዜ ኢያሱ «ከኛ ወገን ነህ ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን?» ሲል ጠይቆት ነበር፡፡ ቅዱስ ሚካኤል ግን የወገንተኛነትን ጥያቄ አልመለሰም፡፡ «እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ነኝ» ነበር ያለው፡፡ «የእግዚአብሔር ከሆነው ጋር ነኝ» ማለቱ ነበር፡፡ በመሆኑም መመዘኛችን ከእግዚአብሔር ጋር የሆነ ማን ነው? የሚለው እንጂ የኔ ወገን ማን ነው? የሚለው መሆን የለበትም፡፡

በሌላም በኩል እኛ የክርስቶስ ነን ማለትን መልመድ አለብን፡፡ የአቡነ እገሌ፣ የቄስ እገሌ፣ የአባ እገሌ፣ የባሕታዊ እገሌ፣ የሰባኪ እገሌ፣የዘማሪ እገሌ፣ የማኅበረ እገሌ፣አይደለንም፡፡ የጎንደር፣ የጎጃም፣ የትግሬ፣ የወሎ፣ የሸዋ፣ የወለጋ፣ የሲዳሞ፣ የከፋ፣ የሐረር፣ የባሌ፣ የጉሙዝ፣ የአፋር አይደለንም፡፡ እኛ የክርስቶስ ነን፡፡ የክርስቶስ ከሆኑት ጋርም አብረን እንቆማለን፡፡ የሚያገናኘን ሃይማኖት እንጂ ዘር፣ፖለቲካ፣ ወንዝ፣ ተራራ፣ አብሮ አደግነት፣ ጉርብትና፣ አይደለም ብለን ለራሳችን ማሳመን እና መቁረጥ አለብን፡፡

ቲፎዞነት ጭፍን ድጋፍ እና ተቃውሞን ያመጣል፡፡ ነገሮችን በሰከነ መንፈስ፣ በሕግ እና በሥርዓት አንፃር፣ከታሪክ እና ከቅዱሳት መጻሕፍት አንፃር፣ ከተጠየቅ እና ከማስረጃ አንፃር ከመገምገምና አቋም ከመያዝ ይልቅ እነማን አሉበት? እነማን ተናገሩ? ወገኖቼ ናቸው አይደሉም? በሚል መመዘኛ ብቻ ወደ መቃወምና መደገፍ ይወስደናል፡፡ ተፍጻሜት

ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ የመከረውን ትቶ አኪላስ አርዮስን ለመሾም የበቃው አብረው የተማሩ የትምህርት ቤት ጓደኞች በመሆናቸው ከሕጉ ዝምድናው በልጦበት ነበር፡፡ ነገር ግን አኪላስም በመንበሩ አልሰነበተም፣ ለቤተ ክርስቲያንም ነቀርሳ አተረፈላት፡፡ ቲፎዞነትም ውጤቱ ይኼው ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የዳዊትን እና የዮናታንን ወዳጅነት እናስብ፡፡ ዮናታን የንጉሡ የሳኦል ልጅ ነው፡፡ አባቱ ቢሞት ወራሽ ነው፡፡ ዳዊት ደግሞ መንበሩን ይወርሳል የተባለ ሰው ነው፡፡ ዮናታን የአባቱ ቲፎዞ ሆኖ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ከመጋጨት ይልቅ እግዚአብሔር አብሮት ከሆነው ከዳዊት ጋር መሆንን መረጠ፡፡ በሥጋ፣ በዝምድና እና በጥቅም ሳኦል ይሻለው ነበር፡፡ ዳዊት የአባቱን መንበር እንደሚወስድ እያወቀ እንኳን ሥልጣን ሳያጓጓው ለእውነት መቆምን መረጠ፡፡

ግሪኮች ዲዮስቆሮስ ያለ ሕግ ሲባረር እና ሃይማኖት በኬልቄዶን ስትፈርስ የሮም ቲፎዞ ሆነው አጨበጨቡ፡፡ ከአምስት መቶ ዓመታት በኋላ ግን እነርሱ ራሳቸው ከሮም ተለዩ፡፡ መጀመርያውኑ ከቲፎዞነት ይልቅ ለሃይማኖት ቢያደሉ ኖሮ ይህ ሁሉ ባልደረሰ ነበር፡፡

## 3 መንገር

ብዙ ምእመናን በቤተ ክርስቲያን ላይ በደረሰው ፈተና ያዝናሉ፡፡ የቤተ ክህነቱን መመሰቃቀል እያዩ ይናደዳሉ፡፡ ሚዲያው እና ወሬው ሁሉ ስለሚወድዷት ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ዘመኑን ይኮንናሉ፡፡ አሁን ግን ይህ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ኃላፊነት ላለባቸው አካላት መንገር ያስፈልጋል፡፡ ፓትርያርኩን፣ ጳጳሳቱን፣ መነኮሳቱን፣ ቀሳውስቱን፣ የሚቀርቡ ምእመናን አሉ፡፡ እነዚህ ምእመናን ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የሚያውቁትን እና የሚሰሙትን መንገር ይገባቸዋል፡፡

ወደ አባቶች ዘንድ መባውን እና ፍትፍቱን ብቻ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያንንም ነገር መውሰድ አለባቸው፡፡ ምእመናኑ ምን ያህል ምሬት ላይ እንደ ደረሱ፤ ሁኔታው ካልታረመና በዚሁ ከቀጠለ መጨረሻው ምን ሊሆን እንደሚችል ማስረዳት አለባቸው፡፡ አባቶችን ማማት መፍትሔ አያመጣም፡፡ እነርሱ በሌሉበት ማውገዝ እነርሱ ባሉበት አቦ አቦ ማለት ውጤት አላመጣም፡፡ የምንወዳቸው ከሆነ እንንገራቸው፡፡ እናሳስባቸው፡፡ መስተዋት እንሁናቸው፡፡

ለኛ ለልጆቻችሁ ፈተና ሆናችሁን፤ ስለ እናንተ ክፉ መስማት ሰለቸን፤ ልጆቻችን እየጠየቁን ነው፤ ለምን ዝም ትላላችሁ እያልን ለመፍትሔ እንዲነሡ መቀስቀስ ይገባናል፡፡ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን በአቡነ ሺኖዳ እና በአንድ ሌላ ጳጳስ መካከል ልዩነት ተፈጠረና ቤተ ክርስቲያኒቱ አደጋ ላይ ወደቀች፡፡ ሁለቱ አበው በየራሳቸው መንገድ እየሄዱ መሥመሩ ተበላሸ፡፡ በዚህ ጊዜ ምእመናኑ መከረው ተነሡ፡፡

አንድ ቀን ሁለቱ አበው በየራሳቸው ወደ ቅዳሴ ሲገቡ ምእመናኑ በር ላይ ጠበቋቸው፡፡ እርስ በርሳችሁ ተጣልታችሁ አትቀድሱም፤ እኛም አናስቀድስም፤ መጀመርያ ታረቁ፤ አሉ፡፡ ሁለቱም ለጊዜው እምቢ አሉ፡፡ ምእመናኑን ካልታረቃችሁ ብለው መሬት ላይ ወደቁ፡፡ በመጨረሻም ሁለቱም አባቶች ቀርበው ይቅር ተባባሉ፡፡ ከዚያም አብረው ቀደሱ፡፡

ከቅዱስ ፓትርያርኩ ጀምሮ ያሉትን አበው የሚቀርቡ እናቶች እና ሽማግሌዎች፣ ባለ ሀብቶች እና ባለሞያዎች አሉ፡፡ እነዚህ አካላት አባቶቻችን የቤተ ክርስቲያንን ችግር እንዲፈቱ መጠየቅ አለባቸው፡፡ እናንተ የሰላም እና የፍቅር አርአያ ካልሆናችሁ፣ ችግር በመፍታት እና ስሕተትን በማረም አርአያ ካልሆናችሁ፤ የእድገት እና የብልጽግና አርአያ ካልሆናችሁ፣ ተወያይቶ የመስማማት እና የመግባባት አርአያ ካልሆናችሁ፣ ግብረ ሰላሙን ለምን እናመጣለን? ማለት አለባቸው፡፡

## 4 ከዚህ በኋላ ሹመት ቢቆም

የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ለ10 ሚሊዮን ክርስቲያኖች ከ50 በላይ ጳጳሳት ሲኖሯት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግን ከ45 ሚሊዮን ለሆነው ሕዝቧ ጳጳሳቷ ከአርባ አይበልጡም፡፡ እናም ገና አባት ያላገኘ ሕዝብ መኖሩ የማይካድ ነው፡፡

በቤተ ክርስቲያናችን አስቸኳይ መፍትሔ ከሚያሻቸው ነገሮች አንዱ የሢመት አሰጣጥ ጉዳይ ነው፡፡ ከሢመተ ዲቁና እስከ ጵጵስና ከሕገ ቤተ ክርስቲያንን አንፃር ችግሮች መኖራቸውን በየጊዜው የተካሄዱ የአጠቃላይ የሰበካ ጉባኤያት የአቋም መግለጫዎች ሁሉ ይናገራሉ፡፡ በሲኖዶስም በተደጋጋሚ ተነሥቷል፡፡ ነገር ግን እርምት አልተሰጠውም፡፡

ቤተ ክርስቲያን ዲያቆናትን፣ካህናትን እና መነኮሳትን ሠፍራ ቆጥራ አታውቃቸውም፡፡ እያንዳንዱ አባት ክህነት የሚሰጠው በተለያየ መመዘኛ ነው፡፡ የክህነቱ መታወቂያ በቀላሉ ፎርጅድ ሊሠራ የሚችል ነው፡፡ አበው ክህነት የሰጡትን ሰው ስለማይመዘግቡት ለማን ምን እንደሰጡት አያስታውሱትም፡፡ አንዳንዶች ፈትነው ይሰጣሉ፤ አንዳንዶች በዕውቂያ ያደርጉታል፡፡ አንዳንዶች በአደባባይ አንዳንዶች በድብቅ፡፡ አንዳ ንዶቹ በሀገረ ስብከታቸው፤ አንዳንዶቹ ከቀኖና ውጭ ያለ ሀገረ ስብከታቸው፡፡

የምንኩስናውም እንደዚሁ ነው፡፡ ዋልድባ የመነኮሰውን መርካቶ ከመነኮሰው መለየት አልተቻለም፡፡ ገዳማቱ የታወቀ መዝገብ የላቸውም፡፡ በቤተ ክርስቲያኒቱ ዳታ ቤዝ የለም፡፡ የምንኩስናው መታወቂያ በቀላሉ ፎርጅድ ሊሠራ ይችላል፡፡ እነማን የማመንኮስ ሥልጣን እንዳላቸው በትክክል ተለይቶ አይታወቅም፡፡

በመሆኑም እነዚህን መሰል ችግሮችን በአስቸኳይ መቅረፍ ካልተቻለ ያለ ሕግ የመነኮሱ፣ ያለ ሥርዓት የተካኑ ሰዎች ወደ ትልቁ መዓርግ ወደ ጵጵስና መድረሳቸው የማይቀር ነው፡፡ ይህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን ክብር የሚነካና የማይሽር ቁስል ጥሎ የሚያልፍ ነው፡፡ በመሆኑም ሲኖዶሱ ይህንን ችግር እስኪፈታ ድረስ ሲመተ ጵጵስና ለጊዜው መቆም አለበት፡፡

አሁን አሁን ለሲመተ ጵጵስና ከሃይማኖት እና ምግባር፣ ከዕውቀት እና ችሎታም ሌላ ሌሎች መተያያዎች እየመጡ ነው፡፡ የወርቁ ቁልፍ ሁሉንም በር እየከፈተው ነው፡፡ እናም ቤተ ክርስቲያን ያሏት ችግሮች ይበቋታል፡፡ ሌላ ችግር መጨመር የለባትም፡፡ መጀመርያ አሁን ያለው ችግር ይፈታ፡፡

አራት ኪሎ ቆሞ ለሚያይ ወደዚህ ትልቅ መዓርግ ለመምጣት በእጅ እና በእግራቸው የሚፋጠኑትን ሰዎች መታዘብ ይችላል፡፡ አንዳንዶቹ እንደ ተመራቂ ተማሪ «ልሾም ነው» እያሉ ያስወራሉ፡፡ ሌሎቹም ልብሱን ገዝተው ቀናቸውን ይጠብቃሉ፡፡ እንዴው አሁን ይሄ የጤና ነው?

### 5 ***መንግሥት ተገቢውን ሥራ መሥራት አለበት***

ልዩ ልዩ መዋቅሮችን በማስተካከል፤ ቢ ፒ አርን በመተግበር፤ በሥልጠና እና በሞያ ማሻሻያ፤ አያሌ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተሻሽለዋል፡፡ ቀበሌ እንኳን ተሻሽሎ ወረፋ እና ቢሮክራሲ ብርቅ ሆኗል፡፡ እስካሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ምንም ዓይነት አስተዳደራዊ መሻሻል ያልነካው ቤተ ክህነትን ነው፡፡

ቤተ ክህነቱ አሁን ያለበት ደረጃ ለሀገሪቱ ደረጃ የሚመጥን አይደለም፡፡ ሲሆን እንደ ጥንቱ ከሀገሪቱ እድገት ቀድሞ መምራት ነበረበት፡፡ ካልሆነ ደግሞ በእኩል መሄድ፡፡ ለዚህ ደግሞ ሀገሪቱን የሚመራው መንግሥት ኃላፊነት አለበት፡፡

በመጀመርያ ቤተ ክርስቲያኒቱ የሀገሪቱ አካል በመሆንዋ፤ እንደገናም የሀገሪቱ አንዱ መገለጫ በመሆንዋ፤ ከዚህም በተጨማሪ በሀገሪቱ ታሪክም ሆነ ሥሪት ውስጥ የማይተካ ሚና ስላላት ለመንግሥት የቤተ ክርስቲያን ነገር ሊገድደው ይገባል፡፡ በርግጥ መግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገባ ሕግ ያግደዋል፡፡ በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ መግባት ማለት ግን ትክክለኛ ትርጉም ያስፈልገዋል፡፡

ገንዘብ ሲመዘበር፣ የአገልጋዮች መብት ሲነካ፣ ሕግ እና አስተዳደር ሲጠፋ፣ የሀገሪቱን መልካም ገጽታ የሚያበላሽ ተግባር ሲፈጸም ዝም ብሎ ማየት ጣልቃ አለመግባት አይመስለኝም፡፡

ቤተ ክርስቲያኒቱ ደረጃውን የጠበቀ የሠራተኛ አስተዳደር እንዲኖራት፤ ደረጃውን የጠበቀ የሂሳብ አሠራር እንዲኖራት፤ ደረጃውን የጠበቀ የፍትሕ አሰጣጥ ሥርዓት እንዲኖራት፤ ደረጃውን የጠበቀ መዋቅር እንዲኖራት ማስገደድም፤ ማበረታታትም፣ መርዳትም ይገባዋል፡፡ ይህች ቤተ ክርስቲያን በተፈለገው መጠን ካልተራመደች ከግማሽ በላይ የሆነችው ኢትዮጵያ እንዳልተራመደች ይቆጠራል፡፡

ለምሳሌ የእምነት ተቋማት ከቀረጥ ነጻ ቢሆኑም በውጭ ኦዲተር የተመሰከረለትና ደረጃውን የጠበቀ የሂሳብ ሪፖርት ከማቅረብ ግን ነጻ መሆን የለባቸውም፡፡ ገንዘቡ የሕዝብ ገንዘብ ነው፡፡ ይህ ገንዘብ ደግሞ ለትክክለኛው ተግባር እንጂ ሀገርን እና ሕዝብን ለሚጎዳ ተግባር መዋል የለበትም፡፡ ይህም የሚረጋገጠው በአሠራር ነው፡፡ በአብዛኛው

የዐለም ሀገሮች የእምነት ተቋማት ከቀረጥ እና ግብር ነጻ ናቸው፡፡ ነገር ግን የሂሳብ ሪፖርት የማስገባት ግዴታ አለባቸው፡፡ ይህ ደግሞ ሕዝቡ ነጻ የሆነ እና የታመነ ሪፖርት የማግኘት መብቱን ያረጋግጥለታል፡፡

**6 አለመተባበር**

*ምስጉን ነው በክፉዎች መንገድ ያልሄደ*

*በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ*

*በኃጥአንም መንገድ ያልሄደ /መዝ1፤1/*

አንድ ሰው ችግሩን መፍታት ካቃተው ቢያንስ የችግሩ አካል ከመሆን መራቅ አለበት፡፡ ዛፎቹ ተሰብስበው መጥረቢያ ጨረሰን ብለው ተመካከሩ ይባላል፡፡ ብዙዎቹ ዛፎች መጥረቢያ ይቃጠል፣ ገደል ይጨመር፣ ይታሠር ወዘተ እያሉ ሃሳብ ሰጡ፡፡ አንድ ሽማግሌ ዛፍ ግን «ለመጥረቢያ እጀታ ሆነን ራሳችንን ያስጨረስን እኛ ነን አሉ ይባላል፡፡ አሁንም ለችግሩ መባባስ የምእመናንም አስተዋጽዖ አለበት፡፡

መነኮሳቱ በገዳም እንዳይጸኑ ከተማ እናመጣቸዋለን፤ አጉራ ዘለል ባሕታውያንን ተከትለን መሥመር እናስወጣቸዋለን፤ ገንዘባችንን ጥቅም ላይ በማይውልበት ቦታ እናፈስሳለን፡፡ በየአጥቢያችን የሰበካ ጉባኤያቱ ሲፈርሱ እና ሲዳከሙ ዝም እንላለን፡፡ ሪርት ቢቀርብ ባይቀርብ ግድ የለንም፡፡ የልማት ሕንፃ መሠራቱን እንጂ እንዴት ጨረታ ወጣ? እንዴት ኮንትራክተሩ ተመረጠ? እንዴት ሕንፃው ተከራየ? አንጠይቅም፡፡ ግን በየቤቱ እናማለን፡፡

ገንዘብ መስጠታችንን እንጂ በትክክል መስጠታችንን በተግባርም መዋሉን አንጠይቅም፡፡ ደረሰኝ አለመቀበል ትኅትና የሚመስለን፤ ሽጉጥ አድርጎ መስጠት ከከንቱ ውዳሴ መራቅ የሚመስለን ብዙዎች ነን፡፡ ነግር ግን በቤተ ክርስቲያን ጥፋት እየተባበርን ነው፡፡

በአንዳንድ አጥቢያዎች ጧፍ እና ሻማ የአይጥ መዋያ ነው፤ ሌሎቹ ደግሞ በጉሎ ዘይት ይቀድሳሉ፤ በአንዳንድ አጥቢያዎች ልብሰ ተከህኖውን ቤት ጠብቦታል፣ ሌሎቹ ደግሞ በሴት ቀሚስ ይቀድሳሉ፤ በአንዳንድ አጥቢያ ብሩ ሞልቶ ተርፎ ለመኪና ይዋጣል፤ ሌሎቹ ለካህናት ደመወዝ የሚከፍሉት አጥተዋል፤ እኛ ደግሞ ላለው ይጨመርለታል ብለን በብኩንነት ላይ እንጨምራለን፡፡

በአሁኑ ጊዜ የአዲስ አበባ አድባራት ከመጠን በላይ በሰው ኃይል ተጨናንቀዋል፡፡ በአንድ ደብር ትንሹ የሰው ኃይል ሰማንያ ሲሆን ከፍተኛው 300 ነው፡፡ አንዳንድ የአዲስ አበባ አድባራት አገልጋዮች ሰሞነኛነት ሳይደርሳቸው ዓመት ይሞላቸዋል፡፡ ሌላ ቦታ እየሠሩ ለደመወዝ ብቻ የሚመጡም አሉ፡፡ በእነዚህም ላይ ደጀ ጠኚ እየተባለ በየጊዜው ይመደብባቸዋል፡፡ ለምን? ነው ጥያቄው፡፡

በአዲስ አበባ የተከማቸ ገንዘብ አለ፡፡ ስለዚህም ሥጋ ባለበት አሞሮች ይሰባሰባሉ በተባለው መሠረት ሁሉም ወደ አዲስ አበባ ይጎርፋል፡፡ አምስቱ አእማደ ምሥጢር፣ ሰባቱን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን እና አሥሩን ትእዛዛት እየተጠየቀ ይገባል፡፡ ከዚህም ከፍ ካለ ባለ ሠላሳ፣ ባለ ስድሳ እና ባለ መቶ ፍሬ መሆኑን አይተው ያስገቡታል፡፡

መንግሥት በፌዴሬሽን ምክር ቤት አማካይነት በሚያወጣው ቀመር መሠረት የሀገሪቱን ሀብት ያመጣጥናል፡፡ ቤተ ክህነት ግን ይህንን ማድረግ አልቻለችም፡፡ በርግጥ አንዳንድ ሀገረ ስብከቶች የበጀት ድጎማ ያገኛሉ፡፡ ያ ግን ሊያመጣጥነው አለቻለም፡፡ አንድ የገጠር ካህን አሥር ብር ሲከፈለው፤ አንድ የአዲስ አበባ ካህን አማካይ ደመወዝ ግን አንድ ሺ ብር ነው፡፡ በመካከል ያለው ክፍተት ከሰማይ እና ከምድርም ይሰፋል፡፡

ቤተ ክህነቱ ይህንን እስኪያመጣጥን ድረስ እኛ ማመጣጠን አለብን፡፡ ለምንድን ነው ገንዘባችንን ለገጠር አብያተ ክርስቲያናት፣ ለተጎዱ ገዳማት እና አድባራት፣ እንዲሁም ለተረሱት የአብነት ት/ቤቶች የማና ውለው? ለምንድን ነው ውጤት በሚያመጣበት ቦታ የማናፈስሰው? ተቀብለው አቡነ ዘበሰማያት ለሚደ ግሙ ምስኪን ካህናት ለምን አንሰጥም?

ይቀጥላል




Lord, it's too heavy...
Please cut it down a little...






Lord, please cut it down a little more...
I'll be able to carry it better...


Lord, thank you so much...


Huh?


Let's use this as a bridge and cross over...
Ahh! it's too short I can't cross...



No Pain No Gain… Accept the
Pain, Future will be Fruitful…

Don't feel the work you are doing is pain, because there will be always a reason for that pain or work.

So face the pain, for the pain you face, there will be definitely happiness ahead.